የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

በኢትዮጵያ ሰብአዊ
መብቶች ኮሚሽን የተዘጋጀ

# የኢትዮጵያ
# ሰብአዊ መብቶች ሁኔታ
# ዓመታዊ ሪፖርት




www.ehrc.org

## ለኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
## የተላከ

ከሰኔ 2016 ዓ.ም. እስከ ሰኔ 2017 ዓ.ም.

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# የኢትዮጵያ ዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት

**ከሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. እስከ ሰኔ ወር 2017 ዓ.ም.**

የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

# ማውጫ


ምኅጻረ ቃላት ........ v

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) የከተማ ጽሕፈት ቤቶች (ካርታ) ........ vii

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ኮሚሽነሮች ........ viii

የኢሰመኮ ዋና ኮሚሽነር መልዕክት ........ ix

ክፍል አንድ ........ 1

አንኳር ጉዳዮች ........ 2

- በሕይወት የመኖር መብት ........ 2
- የነጻነት መብት ........ 3
- በጥበቃ ሥር ያሉ (የታሰሩ) ሰዎች ሰብአዊ መብቶች አያያዝ ........ 4
- የመደራጀት መብት እና የሲቪክ ተሳትፎ ምኅዳር ........ 5
- ሌሎች የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ........ 6
- ለኢሰመኮ የቀረቡ አቤቱታዎች ........ 7
- ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ........ 7
- የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች ........ 9
- የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን መብቶች ........ 10
- የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶች ........ 11
- ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎች ከመወጣት አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ ........ 13
- የሀገራዊ ምክክር ሂደት ........ 14
- የሽግግር ፍትሕ ........ 14
- ምክረ ሐሳቦች ........ 15

ክፍል ሁለት ........ 17

አጠቃላይ መግቢያ ........ 17

ክፍል ሦስት ........ 22

ቁልፍ እመርታዎች እና አሳሳቢ ጉዳዮች ........ 22

- የቁልፍ እመርታዎች አጠቃላይ ምልከታ ........ 22
- የቁልፍ አሳሳቢ ጉዳዮች አጠቃላይ ምልከታ ........ 24

ዝርዝር የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ........ 29

ሀ) በሕይወት የመኖር መብት.......... 29

ለ) የነጻነት መብት .......... 47

ሐ) በጥበቃ ሥር ያሉ (የታሰሩ) ሰዎች ሰብአዊ መብቶች አያያዝ .......... 55

መ) የመደራጀት መብት እና የሲቪክ ተሳትፎ ምኅዳር.......... 65

ሠ) ሌሎች የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች.......... 68

ረ) ለኢሰመኮ የቀረቡ አቤቱታዎች .......... 73

ሰ) ማኀበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች .......... 76

ሸ) የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች .......... 83

ቀ) የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን መብቶች.......... 92

በ) የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶች .......... 98

ተ) ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎች ከመወጣት አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ .......... 110

ክፍል አራት.......... 130

የሀገራዊ ምክክር እና የሽግግር ፍትሕ ሂደት .......... 130

የሀገራዊ ምክክር ሂደት .......... 130

የሽግግር ፍትሕ ሂደት .......... 133

ክፍል አምስት .......... 138

ምክረ ሐሳቦች እና ቀጣይ አቅጣጫዎች.......... 138


የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

# ምኅጻረ ቃላት

| | |
|---|---|
| ዓ.ም. | ዓመተ ምሕረት |
| ጽ/ቤት | ጽሕፈት ቤት |
| ቅ/ጽ/ቤት | ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት |
| ፍ/ቤት | ፍርድ ቤት |
| ም/ቤት | ምክር ቤት |
| ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. | የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ |
| ኢሰመኮ | የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን |
| ተ.መ.ድ. | የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት |
| እ.ኤ.አ. | እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር |
| ሕወሓት | ሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ |
| ኦነግ | የኦሮሞ ነጻነት ግንባር |
| ብ/ብ/ሕ | ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች |
| ፖ/ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ |
| SDG | Sustainable Development Goal (ዘላቂ የልማት ግቦች) |
| CCPR-OP1-IC | Optional Protocol to the International Covenant on Civil and Political Rights (የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን አማራጭ ፕሮቶኮል) |

| | |
|---|---|
| CEDAW | Convention on the Elimination of All forms of Discrimination against Women (በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውም አድሎአዊ ልዩነት ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት) |
| CRC | Convention on the Rights of the Child (የሕፃናት መብቶች ስምምነት) |
| ICCPR | International Covenant on Civil and Political Rights (የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን |
| ICESCR | International Covenant on Economic, Social and Cultural Rights (የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ እና የባህል መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን) |
| CAT | Convention against Torture (የፀረ ኢሰብአዊ አያያዝ ስምምነት) |
| CERD | Convention on the Elimination of Racial Discrimination (አድሎአዊ የዘር ልዩነቶች ለማስቀረት የተቋቋመ ስምምነት) |
| CRPD | Convention on the Rights of Persons with Disabilities (ዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት) |
| UPR | Universal Periodic Review) በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሁሉ-አቀፍ የግምገማ መድረክ |

# የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) የከተማ ጽሕፈት ቤቶች (ካርታ)



# የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ኮሚሽነሮች



**ብርሃኑ አዴሎ**
ዋና ኮሚሽነር



**ራኬብ መሰለ**
ምክትል ዋና ኮሚሽነር



**ዶ/ር አብዲ ጅብሪል**
ሲቪል፣ ፖለቲካዊ እና ማሕበራዊ-ኢኮኖሚያዊ መብቶች ኮሚሽነር



**ርግበ ገብረሐዋሪያ**
የሴቶች፣ የሕፃናት፣ የአረጋውያን እና የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮሚሽነር

# የኢሰመኮ ዋና ኮሚሽነር መልዕክት

*ይህ 4ተኛው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ዓመታዊ ሪፖርት በ2017 በጀት ዓመት ያለውን ሀገራዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ የሚሸፍን ሲሆን በበጀት ዓመቱ የታዩ መልካም እመርታዎችን፣ አሳሳቢነታቸው የቀጠሉ ጉዳዮችን ከምክረ ሐሳቦች ጋር ያመላክታል።*

*በሀገራዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታው ላይ የየራሳቸው ውስንነቶች ያሉባቸው ቢሆንም የሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሥራዎች መጀመር፣ የሀገራዊ ምክክር ሂደት ተጠናክሮ መቀጠል እንዲሁም ለኢሰመኮ የውትወታ ሥራዎች አዎንታዊ ምላሽ የሚሰጡ እርምጃዎች መወሰዳቸውን ኢሰመኮ በበጎ የሚመለከተው ነው።*



**ብርሃኑ አዴሎ**
**ዋና ኮሚሽነር**

*በሀገሪቱ የቀጠሉ ግጭቶች እና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በዘላቂነት ለማስቆም በሰብአዊ መብቶች ላይ የተመሠረተ እና ተጎጂዎችን ማእከል ያደረገ የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ወደ ትግበራ ምእራፍ መሸጋገሩ፤ እንዲሁም በሂደት ላይ ያለው ሀገራዊ ምክክሩም በሀገሪቷ ለሚነሱ ግጭቶችና ቅራኔዎች መነሻ በሆኑ ጉዳዮች በውይይት ላይ የተመሠረተ መፍትሔ በመስጠት የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እንዳይፈጸሙ በማድረግ ረገድ ትልቅ ሚና አላቸው። በመሆኑም ከግጭት ለመውጣትና በግጭት ውስጥ ለሚደርሱ መጠነ ሰፊ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት እነዚህን የተጀመሩ የሰላም ማምጫ መንገዶች አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል።*

*ኢሰመኮ ላለፉት 3 ዓመታት ይፋ ባደረጋቸው ሪፖርቶች ላይ እንደገለጸው፤ በ2017 በጀት ዓመትም የትጥቅ ግጭቶች እንዲሁም የጸጥታ ችግሮች ጉዳይ በአጠቃላይ በሀገራዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳደር ረገድ ቀዳሚውን ስፍራ ይዞ ቀጥሏል። በዚህም ምክንያት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በየዘርፉ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተመዝግበዋል። በግጭቶች ዐውድ ውስጥ እና ውጪ የሚፈጸሙ ጥቃቶች በተለይም በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደኅንነት፣ የነጻነት እና ሌሎች የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ላይ ካደረሱት ጉዳት በተጨማሪ በማኅበራዊ መሠረተ ልማቶች ላይ ውድመት የደረሰባቸው በመሆኑ በማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ዘርፍም ጥሰቶች ተመዝግበዋል። በተለይም በግጭት ዐውድ ውስጥ በሚፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ዋነኛ ተጎጂ የሆኑት ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መሆናቸው ችግሩን ይበልጥ አሳሳቢ ያደርገዋል። ኢሰመኮ በበጀት ዓመቱ በመንግሥት እና በታጣቂ ቡድኖች መካከል የሚካሄዱ ግጭቶች በውይይት እንዲፈቱ ተደጋጋሚ ጥሪ ሲያቀርብ ቆይቷል። በዚህ ረገድ በበጀት ዓመቱ በኦሮሚያ ክልል መንግሥት እና “ጃል ሰኚ ነጋሳ” በተባለ ግለሰብ በሚመራ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) ቡድን አባላት መካከል ስምምነት መደረጉ እንደ መልካም ጅማሮ የሚወሰድ ነው። ይህ ዐይነት የሠላም አማራጮች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ እና ግጭቶች በውይይት፣ በስምምነት እና ሰብአዊ መብቶችን ባከበረ ሂደት እልባት እንዲያገኙ በድጋሚ ጥሪ አቀርባለው።*

ከዚህ ባለፈ ድርቅ፣ ጎርፍ እና የመሬት መንቀጥቀጥን የመሳሰሉ የተፈጥሮ አደጋዎች በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ለሰዎች ሞት፣ የአካል ጉዳት፣ መፈናቀል እንዲሁም የንብረት ውድመት ምክንያት መሆናቸው፤ እንዲሁም የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦቶች በሚፈለገው መጠን አለመቅረብ፣ መሠረታዊ የሆኑ የምግብ ፍጆታዎችን ጨምሮ የሸቀጦች ዋጋ መናር እና የኑሮ ውድነት የሰብአዊ መብቶች ሁኔታው እንዲባባስ ምክንያት ሆነዋል።

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር በመሆን በጥር ወር 2017 ዓ.ም. በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከተሾምኩበት ጊዜ ጀምሮ ቀደም ብለው የተጀመሩ የሰብአዊ መብቶች ሥራዎችን አጠናክሮ በማስቀጠል ረገድ ኢሰመኮ በ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅዱ (2014 ዓ.ም. እስከ 2018 ዓ.ም.) መሠረት በሀገር አቀፍ ደረጃ የሰብአዊ መብቶች ትምህርትን ለማስፋፋት፤ የሰብአዊ መብቶች ክትትልና ምርመራ ሥራን በማጠናከር እንዲሁም ከተለያዩ መንግሥታዊ እና የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶችን ጨምሮ መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋራ ያለን አጋርነት ለማጠናከር በልዩ ትኩረት በመሥራት ላይ ይገኛል። ኮሚሽኑ የሰብአዊ መብቶች ትምሕርትን ማስፋፋት እንዲሁም የሴቶችና ሕፃናት፣ የአካል ጉዳተኞች፣ የአረጋውያን፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ የፍልሰተኞች እና የስደተኞች ሰብአዊ መብቶችን በማስጠበቅ ረገድ በአንክሮ መሥራቱን ይቀጥላል።

ኢሰመኮ ወቅታዊ ለሆኑ ሀገራዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታዎችና ጉዳዮች ተመጣጣኝ የሆነ ምላሽ መስጠት እንዲችል ተደራሽነቱን እና የሰብአዊ መብቶች ሥራውን ማስፋፋትና ማጠናከር ይኖርበታል። በግጭት ዐውድ ውስጥ ባሉ እና የጸጥታ ችግር ባሉባቸው አካባቢዎች የሰብአዊ መብቶች ሥራዎችን ማከናወን አዳጋች መሆኑ እንደተጠበቀ፤ ኢሰመኮ በሕግ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችለውን በቂ የሰው ኃይል እና ፋይናንስ በማሟላት ረገድ ውስንነቶች መቀጠላቸው በምርመራና ክትትል ሥራዎቹ ላይ ተጽዕኖን ፈጥሯል። በመሆኑም ነጻና ገለልተኛ እንዲሁም ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን የሚያሟላ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ሆኖ ለመቀጠል፣ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈጸም እና ተደራሽነቱን ለማስፋት የሚችል በቂ በጀት መመደብ እንዲሁም በክልሎች ተጨማሪ ጽሕፈት ቤቶችን መክፈት አስፈላጊ ሆኗል።

ኢሰመኮ ነጻነቱን እና ገለልተኛነቱን በመጠበቅ በሀገሪቱ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን ለማሻሻል የሚረዱ ተግባራትን የሚያከናውን መሆኑን እየገለጽኩ፤ በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች የሚካሄዱ የትጥቅ ግጭቶች እንዲሁም የጸጥታ መደፍረስ ሁኔታዎች አሁንም ዋነኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች መንስኤ በመሆናቸው መንግሥትን ጨምሮ ሁሉም በትጥቅ ግጭት ውስጥ የሚሳተፉ ተፋላሚ ኃይሎች እንዲሁም ግጭቶች ሊያገረሹ የሚችሉባቸውን ፖለቲካዊ አለመግባባቶችን በውይይት እንዲፈቱ፤ በተለይም በሂደት ላይ ያሉትን የብሔራዊ ምክክር እና የሽግግር ፍትሕ ሂደቶች እንዲሁም የፕሪቶሪያ ስምምነት ዘላቂ፣ ሰላማዊ እና ሰፊ ተቀባይነት ያላቸው ውጤቶችን ለማስገኘት በሚችሉበት አግባብ እንዲተገበሩ እመክራለሁ። በሌላ በኩል የሕግ፣ የፖሊሲ እና የአሠራር ለውጦች የሚዲያና የሲቪክ ምኅዳር እንዲሁም ሐሳብን በነጻነት የመግለጽና የመደራጀት መብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳያሳድሩ በጥንቃቄ እንዲታዩ፤ በተጨማሪም እየተቃረበ በመጣውና በ2018 ዓ.ም. እንደሚካሄድ የሚጠበቀው ሀገር አቀፍ ጠቅላላ ምርጫ ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊ እና ሰብአዊ መብቶችን የሚያከብር ሂደት እንዲሆን ሁሉም ባለድርሻ አካላት የየበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ጥሪ አቀርባለሁ።

WWW.EHRC.ORG



# ክፍል ፩

# አንኳር ጉዳዮች

1. የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ለ4ኛ ተከታታይ ዓመት በዚህ መልኩ አዘጋጅቶ ያቀረበው ይህ ዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት ከሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. እስከ ሰኔ ወር 2017 ዓ.ም. ያለውን ሀገራዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ጠቅለል ባለ መልኩ የሚያሳይ ነው፡፡ ሪፖርቱ የተዘጋጀው ኢሰመኮ ዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ እና ብሔራዊ ሕጎችን፣ ደንቦችን እንዲሁም መርሖችን መሠረት በማድረግ በበጀት ዓመቱ በተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ዘርፎች ባከናወናቸው ክትትሎችና ምርመራዎች መነሻነት ነው፡፡
2. ኢሰመኮ በሪፖርቱ የተካተቱ ጉዳዮችን አስመልክቶ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ለማሰባሰብ ቃለ መጠይቆችን፣ የቡድን ውይይቶችን፣ የአካል ምልከታዎችን፣ የሰነዶች ማሰባሰብና ምርመራ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ በዚህ ሪፖርት የተካተቱ የክትትልና ምርመራ ግኝቶች በብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት እና በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ምርመራዎችና ክትትሎች እንዲሁም በዓለም አቀፍ አጣሪ ኮሚሽኖች ወይም እውነት አፈላላጊ አካላት ጥቅም ላይ የሚውሉ የማስረጃ ምዘና መስፈርቶችን መሠረት ያደረጉ ሲሆኑ፤ ኢሰመኮ ለምርመራ ሥራዎቹ "ምክንያታዊ አሳማኝነት" (reasonable grounds to believe) እንዲሁም ለክትትል ሥራዎች "ምክንያታዊ ጥርጣሬ" (reasonable suspicion) በመባል የሚታወቁትን የማስረጃ ምዘና ደረጃዎች ይከተላል፡፡
3. ይህ ዓመታዊ ሪፖርት የቁልፍ እመርታዎችንና አሳሳቢ ጉዳዮችን አጠቃላይ ምልከታ እንዲሁም በዚህ አንኳር ጉዳዮች (executive summary) ከዚህ በታች ተጠቃለው በተቀመጡት የሰብአዊ መብቶች ዘርፎች የተስተዋሉ ዝርዝር አዎንታዊ እና አሳሳቢ ጉዳዮችን ከምክረ ሐሳቦች ጋር አካትቷል፡፡ በኢትዮጵያ የተጀመሩት የሽግግር ፍትሕ እና የሀገራዊ ምክክር ሂደቶች ለሰብአዊ መብቶች መከበርና ጥበቃ አስተዋጽዖ ያላቸው ሲሆኑ፤ ኢሰመኮ እንደ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም በእነዚህ ሂደቶች ላይ ባደረጋቸው ክትትሎች የለያቸው መልካም እመርታዎች እና አሳሳቢ ጉዳዮች እንዲሁም ምክረ ሐሳቦች በዓመታዊ ሪፖርቱ ራሳቸውን ችለው እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

## በሕይወት የመኖር መብት

4. በኢትዮጵያ በተለያዩ ክልሎች የቀጠሉ የትጥቅ ግጭቶች እንዲሁም በተደጋጋሚ የሚያገረሹ የጸጥታ ችግሮች ከሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. እስከ ሰኔ ወር 2017 ዓ.ም. ባለው የሪፖርት ጊዜ በሰዎች በሕይወት የመኖርና የአካል ደኅንነት እንዲሁም ሌሎች መሠረታዊ መብቶች ላይ ጉዳት አስከትለዋል፡፡ የመንግሥት ኃይሎች በአማራ ክልል ከሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ቡድኖች (በተለምዶ "ፋኖ") እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ከኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") ታጣቂዎች ጋር በሚያካሂዱት የትጥቅ ግጭት፣ በትጥቅ ግጭት ዐውድ ውስጥ በሚፈጸሙ ጥቃቶች ሰዎች ተገድለዋል፤ እንዲሁም የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡
5. ለምሳሌ በአማራ ክልል በመንግሥት ኃይሎች እና በታጣቂ ቡድኖች (በተለምዶ "ፋኖ") መካከል በተደረጉ የተኩስ ልውውጦች የግጭቱ አካል ያልነበሩ ሰላማዊ ሰዎች ለሞት እና ለአካል ጉዳት መዳረጋቸው በሪፖርቱ በዝርዝር ማሳያዎች ተመላክቷል፡፡ በተመሳሳይ በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በመንግሥት ኃይሎች እና በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") መካከል ከሚደረገው የትጥቅ ግጭት ጋር

በተያያዘም በሰዎች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች የቀጠሉ ሲሆን በክልሉ በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ ግጭቶች በሰዎች ላይ የሞት፣ የአካል እና የንብረት ጉዳት ደርሷል። የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") ታጣቂዎች ከተለያዩ ከተሞች ወደ አዲስ አበባ ከተማ የሚጓዙ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶብሶችን በማስቆም የሚፈጽሟቸው እገታዎች በበጀት ዓመቱ የቀጠሉ ሲሆን፤ አጋቾች ከፍተኛ የማስለቀቂያ ገንዘብ ክፍያ በመጠየቅ፤ ገንዘብ ለመክፈል ባልቻሉ ታጋቾች ላይ ግድያን ጨምሮ በርካታ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን ፈጽመዋል።

6. የትጥቅ ግጭት ከሚካሄድባቸው የአማራ እና የኦሮሚያ ክልሎች በተጨማሪ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ግጭቶችና የጸጥታ ችግሮች በሚያገረሹባቸው የማእከላዊ ኢትዮጵያ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ ክልል የተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች በሰዎች ሕይወትና አካል ላይ ጉዳት ያደረሱ ጥቃቶች በመንግሥት አካላት፣ በታጣቂዎች፣ በተደራጁ ቡድኖች እንዲሁም ማንነታቸው በውል ባልታወቀ አካላት መፈጸማቸውን ሪፖርቱ አካትቷል።

7. ድርቅ፣ ጎርፍ እና የመሬት መንቀጥቀጥን የመሳሰሉ የተፈጥሮ አደጋዎች በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ለሰዎች ሞት፣ የአካል ጉዳትና መፈናቀል ምክንያት መሆናቸው እንዲሁም በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በስፋት የተከሰቱ የወባ፣ ኮሌራ እና ኩፍኝ በሽታዎች የበርካታ ሰዎች ሕይወት ማለፉንና በተለይም በግጭቶች ምክንያት የጤና አገልግሎት ተቋማት፣ መሠረተ ልማቶች እና እንደ አንቡላንስ ያሉ አስፈላጊ መገልገያዎች የተሟላ አገልግሎት በማይሰጡባቸው አካባቢዎች ሁኔታው የከፋ መሆኑ በሪፖርቱ በማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ክፍል በዝርዝር ተመላክቷል።

## የነጻነት መብት

8. የትጥቅ ግጭቶች በሚካሄዱባቸው የአማራ እና ኦሮሚያ ክልሎች የተለያዩ አካባቢዎች፣ እንዲሁም የጸጥታ ችግሮች በሚያገረሹባቸው የማእከላዊ ኢትዮጵያ እና ደቡብ ኢትዮጵያ የተወሰኑ ዞኖች በ"ኮማንድ ፖስት" እና በ"ወቅታዊ ጉዳዮች" በሚል የሚፈጸሙ እስሮች እና ተያያዥ የነጻነት መብት ጥሰቶች መቀጠላቸውን ሪፖርቱ ያሳያል። በ2016 በጀት ዓመት ታውጆ የነበረው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከግንቦት 28 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈጻሚነቱ ያበቃ ቢሆንም፣ በአማራ ክልል የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ያለ በሚመስል መልኩ በሁሉም አካባቢዎች የዘፈቀደ፣ የጅምላና የተራዘመ እስር በተስፋፋ ሁኔታ እንደሚካሄድ፤ ለምሳሌ ከመስከረም 18 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች የዘፈቀደ እና የጅምላ እስራቶች የተፈጸመባቸው በርካታ ሰዎች በዳንግላ፣ ጭልጋ (ሰራባ ወታደራዊ ካምፕ)፣ ኮንቦልቻ እና ሸዋ ሮቢት ከተሞች በሚገኙ ኢመደበኛ ማቆያ ሥፍራዎች ለወራት እንዲቆዩ ተደርገው አብዛኞቹ የ"ተሐድሶ ስልጠና ወስደው" መለቀቃቸው፤ ከተጠቀሱት ማቆያ ማእከላት በተጨማሪ በተለያዩ ማረሚያ ቤቶችና ፖሊስ ጣቢያዎች እንዲሁም ወታደራዊ ካምፖች ሰዎች "የኮማንድ ፖስት እስረኛ" እየተባሉ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ለረጅም ጊዜ ታስረው እንደሚገኙ ኢሰመኮ አረጋግጧል። በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች ካለው የትጥቅ ግጭት ጋር ተያይዞም "ወቅታዊ ጉዳይ" በሚል በዘፈቀደና ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ተይዘው በየፖሊስ ጣቢያዎች የሚገኙ ሰዎች ያሉ ሲሆን፤ ከፍርድ ቤት ትእዛዝ ውጪ ሰዎች በፖሊስ ጣቢያዎች መታሰራቸው እንዲሁም ከአንድ ፖሊስ ጣቢያ ወደ ሌላ ፖሊስ ጣቢያ ተዛውረው ታስረው እንዲቆዩ መደረጋቸው አሳሳቢ ነው።

9. በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ሳይታወጅ ሰብአዊ መብቶች የሚታገዱበት አሠራር በብሔራዊም ሆነ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ማዕቀፎች መሠረት ተቀባይነት የሌለው ቢሆንም፣ በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፣ ጉራጌ ዞን፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ ካለው የጸጥታ ችግር ጋር ተያይዞ ወልቂጤ ከተማ እና ዙሪያው "በኮማንድ ፖስት" እንዲተዳደሩ በመደረጉ የነጻነት መብትን ጨምሮ በሌሎችም መብቶች ላይ ጥሰቶች የሚፈጸሙበትን በር ከፍቷል፡፡ በተመሳሳይ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የተለያዩ ዞኖች "በኮማንድ ፖስቱ የተጠረጠራችሁ ናችሁ" በሚል ሰዎች ለተራዘመ እስር እየተዳረጉ መሆኑን እና አካልን ነጻ የማውጣት አቤቱታ የቀረበላቸው ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ባልታወጀበት ስለ አስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ የሚደነግገውን የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 93 በመጥቀስ አቤቱታዎችን ውድቅ ማድረጋቸውን ሪፖርቱ ያመለክታል፡፡
10. በመንግሥት ከሚፈጸሙ ሕገ ወጥ እና የዘፈቀደ እስር ጎን ለጎን በታጣቂ ቡድኖች፣ ለዝርፊያ በተደራጁ ቡድኖች የሚፈጸሙ እገታዎች በነጻነት እና ሌሎች መሠረታዊ መብቶች ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን ቀጥለዋል፡፡ አጋቾች ሰላማዊ ሰዎችን አግተው ወዳልታወቀ ቦታ በመውሰድ ከፍተኛ የማስለቀቂያ ገንዘብ ክፍያ እንደሚጠይቁ፤ ገንዘብ መክፈል ያልቻሉ በርካታ ታጋቾች ግድያን ጨምሮ በርካታ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እንደሚፈጸምባቸው፤ በተለይም በአማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ እና ኦሮሚያ ክልሎች በደረሱ ጉዳቶች ማሳያነት ያመላከተ ሲሆን፤ በተለይም ታጋች ሴቶች ለአስገድዶ መደፈር እና ለተለያዩ ጾታዊ ጥቃቶች እንደሚዳረጉ ያሳያል፡፡

## በጥበቃ ሥር ያሉ (የታሰሩ) ሰዎች ሰብአዊ መብቶች አያያዝ

11. ኢሰመኮ በሕግ ከተሰጡት ሥልጣንና ኃላፊነቶች አንዱ ፖሊስ ጣቢያዎችን፣ ጊዜያዊ ማቆያ ቦታዎችን እና ማረሚያ ቤቶችን በመደበኛነት በመጎብኘት የታራሚዎችን እና የተጠርጣሪዎችን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታ መከታተል ሲሆን፣ በ2017 በጀት ዓመት በሀገር አቀፍ ደረጃ በአጠቃላይ በ66 ማረሚያ ቤቶች፣ 473 ፖሊስ ጣቢያዎች እና 9 መደበኛ ያልሆኑ የማቆያ ስፍራዎች የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ክትትል አድርጓል፡፡
12. ኢሰመኮ ከዚህ ቀደም ባደረጋቸው ክትትሎች ያቀረባቸውን ምክረ ሐሳቦች ተግባራዊ በማድረግ የተጠርጣሪዎችና ታራሚዎችን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ በማሻሻል ረገድ በተለያዩ ክልሎች ፖሊስ ጣቢያዎችና ማረሚያ ቤቶች የተወሰኑ መሻሻሎች ታይተዋል፡፡ ለምሳሌ ክትትል በተደረገባቸው የአፋር፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና ሲዳማ ክልል ፖሊስ ጣቢያዎች በተጠርጣሪዎች ላይ የሚፈጸሙ ኢሰብአዊ አያያዞች ቀንሰዋል፡፡ በአማራ፣ ኦሮሚያ እና ትግራይ ክልሎች ሕጋዊ ምክንያቶችንና ሥርዓቶችን ባልተከተለ መንገድ በፖሊስ ጣቢያዎች፣ ማረሚያ ቤቶችና ኢመደበኛ ማቆያዎች ውስጥ ታስረው የነበሩ ሰዎችን የመልቀቅ እንዲሁም ፍርድ ቤት የማቅረብ ጅምር መኖሩ፤ በአፋር፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ሲዳማ እና ሶማሊ ክልሎች ማረሚያ ቤቶች የምግብ በጀት ማሻሻያ መደረጉ፤ በተወሰኑ ክልሎች ተጠርጣሪዎችና ታራሚዎች በተጨናነቁ እና ንጽሕናቸው ባልተጠበቀ ክፍሎች ውስጥ የሚያዙበትን ሁኔታ ለማስተካከል የማስፋፊያ ግንባታዎችና የመሠረት ልማት ማሟላት ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸው በሪፖርቱ ተጠቅሷል፡፡
13. ሆኖም በተለያዩ ክልሎች በተጠርጣሪዎችና ታራሚዎች ሰብአዊ መብቶች አያያዝ ረገድ በርካታ ተግዳሮቶች ባሉበት ቀጥለዋል ወይም ተባብሰዋል፡፡ የታራሚዎችና

ተጠርጣሪዎች ሰብአዊ መብቶች መከበርን ለማረጋገጥ ቁልፍ የሆነውን የኢሰመኮ ክትትልና ጉብኝት ከማድረግ አንጻር የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች ትኩረት የሚሹ ሲሆን፤ ለምሳሌ በግጭቶችና በጸጥታ ችግሮች ሳቢያ እንዲሁም ክትትል ለማድረግ ጥያቄ ቀርቦ ባለመፈቀዱ ምክንያት በአማራ ክልል በበጀት ዓመቱ ከ5 ማረሚያ ቤቶች በስተቀር በሌሎች ማረሚያ ቤቶች፣ ፖሊስ ጣቢያዎች እና ኢመደበኛ ማቆያ ሥፍራዎች ክትትል ለማድረግ አልተቻለም፡፡

14. ኢሰመኮ ክትትል ባደረገባቸው ፖሊስ ጣቢያዎችና ማረሚያ ቤቶች በተጠርጣሪዎች እና ታራሚዎች መብቶች ላይ በስፋት ከተስተዋሉ ችግሮች መካከል በበርካታ ፖሊስ ጣቢያዎች ለተጠርጣሪዎች ምግብ የማይቀርብ መሆኑ እና በማረሚያ ቤቶች ምንም እንኳን የምግብ በጀት ማስተካከያ የተደረገ ቢሆንም ለታራሚዎችና ተጠርጣሪዎች በቂ፣ የተመጣጠነ እና ጥራቱን የጠበቀ ምግብ በማቅረብ ረገድ ክፍተት መኖሩ፤ ድብደባ እና ኢ-ሰብአዊ አያያዝ የሚፈጸምባቸው ፖሊስ ጣቢያዎች መኖራቸው እና ተጠርጣሪዎች ቅሬታ የሚያቀርቡበት ሥርዓት አለመዘርጋቱ፤ በፖሊስ ጣቢያዎችም ሆነ በማረሚያ ቤቶች በወንጀል ነክ ነገር ውስጥ ገብተው የተገኙ/የተጠረጠሩ ሕፃናትን ለአካለ መጠን ከደረሱ ሰዎች ጋር በአንድ ክፍል የመያዝ ሁኔታ መቀጠሉ፤ እና በሌሎችም ዘርፎች ለያይቶ የመያዝ መርሕን ተፈጻሚነት በማረጋገጥ ረገድ ክፍተቶች መኖራቸው፤ ምንም እንኳን በተወሰኑ ፖሊስ ጣቢያዎችና ማረሚያ ቤቶች ግንባታዎችን በማስፋፋት ጭምር ማሻሻያዎችን ለማድረግ በሂደት ላይ ያሉ ጥረቶች ቢኖሩም፣ በበርካታ ክልሎች ተጠርጣሪዎችና ታራሚዎች በቂ ስፋት በሌላቸው፣ አስፈላጊው ቁሳቁስ ባልተሟላላቸው እንዲሁም ንጽሕናቸው ባልተጠበቀ ክፍሎች ውስጥ በተጨናነቀ ሁኔታ ተይዘው የሚገኙ መሆናቸው፤ ፍራሽ፣ አልባሳት እና የንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን በማሟላት ረገድ ክፍተት መኖሩ እና ለምሳሌ ምንጣፍም ሆነ ፍራሽ ባለመኖሩ ምክንያት ተጠርጣሪዎች ወለል ላይ ለመተኛት የሚገደዱባቸው ፖሊስ ጣቢያዎች መኖራቸው፤ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተጠርጣሪዎችና ታራሚዎች ፍላጎታቸውን መሠረት ያደረገ አገልግሎት በማቅረብ ረገድ ክፍተቶች መቀጠላቸው፤ እንዲሁም በበርካታ ማረሚያ ቤቶች የትምህርት እና የጤና አገልግሎቶችን ተደራሽ በማድረግና ጥራታቸውን በማስጠበቅ ረገድ ክፍተቶች ያሉ መሆኑ ይገኙበታል፡፡

## የመደራጀት መብት እና የሲቪክ ተሳትፎ ምኅዳር

15. በሰኔ ወር 2017 ዓ.ም. ለውይይት የቀረበው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ማሻሻያ ረቂቅ ሕግን በተመለከተ የሚደረገው ማሻሻያ በተለይም እንደ ሽግግር ፍትሕ፣ ሀገራዊ ምክክር እና በ2018 ዓ.ም. እንደሚካሄድ በሚጠበቀው ሀገር አቀፍ ጠቅላላ ምርጫን የመሳሰሉ ለስኬታማ አተገባበራቸው ጠንካራ የሲቪል ማሕበረሰብ ድርጅቶችን ተሳትፎ እና ሚና የሚጠይቁ ሀገራዊ ጉዳዮች እየተካሄዱ ባለበት ሁኔታ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ላይ የሚደረግ ማሻሻያ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳያሳድር እንዲሁም የሲቪክ ምኅዳሩን እና በማኅበር የመደራጀት መብትን ተፈጻሚነት የሚያጣብብ እንዳይሆን በጥናት ላይ የተመሠረተ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ትርጉም ያለው ተሳትፎ ባረጋገጠ እንዲሁም የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎችን ያከበረ ሊሆን እንደሚገባ በሪፖርቱ ተመላክቷል፡፡

16. በበጀት ዓመቱ በተለይም በሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ አተኩረው በሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ላይ ተጥሎ የነበረው እገዳ ምንም እንኳን ኢሰመኮ ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን እንዲሁም እገዳ ከተጣለባቸው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጋር ባደረጋቸው ውይይቶች እገዳው መነሳቱ አበረታች ቢሆንም፤ በበጀት ዓመቱ ከተስተዋሉ እና በሪፖርቱ በዝርዝር የተመላከቱ ሌሎች ተግዳሮቶች በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እንቅስቃሴ እና በሰብአዊ መብቶች ዘርፉ ላይ ጫና የፈጠሩ ናቸው።

## ሌሎች የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች

17. መረጃ የማግኘት መብትን ጨምሮ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ እና አቤቱታ የማቅረብ መብት፣ ፍትሕ የማግኘት መብት እንዲሁም የዳኝነት ነጻነት የሚገኙበትን አሳሳቢ ሁኔታ የሚያመላክቱ ማሳያ ጉዳዮች በሪፖርቱ በዝርዝር ቀርበዋል።
18. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ 10 ቀን 2017 ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ የመገናኛ ብዙኃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 ማሻሻያ አዋጅን አጽድቋል። ኢሰመኮ በማሻሻያ አዋጁ ድንጋጌዎች ላይ በተለይም የቦርድ አደረጃጀት አመራረጥ አሿሿም እና ስብጥር ላይ እንዲሁም ፈቃድ የመስጠትና የመሰረዝ ሥልጣንን በተመለከተ ማሻሻያ የተደረገባቸው ድንጋጌዎች ላይ ዝርዝር አስተያየትና ምክረ ሐሳብ የሰጠ ሲሆን ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ትርጉም ያለው ጥበቃ የሚያገኘው የመገናኛ ብዙኃን በዴሞክራቲክ ማሕበረሰብ ያላቸው ሚና በአግባቡ መወጣት ሲችሉ መሆኑን ለዴሞክራሲ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ሐሳቦችና አመለካከቶች በነጻ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ የመገናኛ ብዙኃን ተቆጣጣሪ አካል ነጻነትና ገለልተኝነትን በሕግ ማረጋገጥ ተቀዳሚ ተግባር እንደሆነና ይህም የሚረጋገጠው የመገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን አባላት ምልመላ እና ሹመት/ምደባ አሳታፊ፣ የተለያዩ የማሕበረሰብ ክፍሎች ውክልና ያለው መሆኑ በሕግ በግልጽ ሲቀመጥ፤ የመገናኛ ብዙኃንን የሚቆጣጠሩ አካላት ገለልተኛ እና ከማንኛውም አካል ጣልቃ ገብነት በተለይም ከፖለቲካ እና ኢኮኖሚያዊ ጣልቃ ገብነት ሲጠበቁ መሆኑን በመግለጽ የሚደረጉ ማሻሻያዎች እና አፈጻጸማቸው የባለሥልጣኑን አደረጃጀት፣ ተቋማዊና የአሠራር ነጻነቱን እንዲሁም ፈቃድና ቁጥጥርን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትንና የመገናኛ ብዙኃን ነጻነት መብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖን እንዳያስከትሉ ጥብቅ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርቱ ተመላክቷል።
19. የዳኝነት ነጻነትን እንዲሁም የሰዎችን ፍትሕ የማግኘት መብትን የሚያጣብቡ ሁኔታዎች በበርካታ የሀገሪቱ ክፍሎች ተስተውለዋል። በአማራ ክልል በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ዳኞች ላይ የሚፈጸሙ የመብት ጥሰቶች፣ ዳኞች ከዳኝነት ሥራቸው ጋር በተያያዘ በሚሰጡት ውሳኔና ትእዛዝ ሳቢያ በመንግሥት አስፈጻሚ አካላት ሕገ ወጥ እስራት፣ ማስፈራራት እና ጣልቃ ገብነት እንደሚፈጸምባቸው፤ በኦሮሚያ ክልል እንዲሁ በዳኞች እና በዐቃብያነ ሕግ ላይ ለተጠርጣሪዎች ዋስትና “ፈቅዳችኋል” ወይም “እንዲፈቀድ ተባብራችኋል” በሚል ማዋከብ እንደሚፈጸም፤ ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ማእከላዊ ኢትዮጵያ፣ ሲዳማን እንዲሁም የሲቪል አስተዳደር ያልተቋቋመባቸው እና የፍትሕ አካላት የተሟላ አገልግሎት የማይሰጡባቸው አካባቢዎች ያሉበትን ትግራይ ክልልን ጨምሮ በሀገሪቱ የተለያዩ ክልሎች የፍርድ

ቤቶችን ነጻነት እና የሰዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚያጣብቡ አሳሳቢ ጉዳዮች በሪፖርቱ ተዳሰዋል።

## ለኢሰመኮ የቀረቡ አቤቱታዎች

20. ኢሰመኮ እንደ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም በራሱ አነሳሽነት ከሚያከናውነው የሰብአዊ መብቶች ምርመራ በተጨማሪ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በተመለከተ አቤቱታዎችን የመቀበልና የመመርመር እንዲሁም መፍትሔ የመስጠት ሥልጣን እና ኃላፊነት አለው። ይህ ሥልጣንና ኃላፊነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በክልል ወይም በፌዴሬሽን ምክር ቤቶች፣ አልያም በማንኛውም ፍርድ ቤት በየትኛውም ደረጃ በመታየት ላይ ካሉ ጉዳዮች በስተቀር የሰብአዊ መብቶች መጣስን አስመልክቶ በማንኛውም ሰው ወይም ተቋም ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ሁሉ ያካትታል።
21. ኢሰመኮ በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ 1524 ሰዎች በቡድንና በተናጠል ያቀረቧቸውን 1258 አቤቱታዎች ተቀብሎ አስተናግዷል። ኢሰመኮ ዋና መሥሪያ ቤቱ በሚገኝበት አዲስ አበባ ከተማ 416 አቤቱታዎችን የተቀበለ ሲሆን፣ የጅማ (273)፣ ሃዋሳ (168) እና ባሕር ዳር (121) በበጀት ዓመቱ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው አቤቱታዎች የተስተናገዱባቸው ከተማ ጽሕፈት ቤቶች ናቸው። የአቤቱታ አቅራቢዎችን ምጣኔ በተመለከተ 77.2% ወንድ እንዲሁም 22.8% አቤቱታ አቅራቢዎች ሴቶች ሲሆኑ፤ በቁጥር 79 የሚሆኑት አቤቱታ አቅራቢዎች አካል ጉዳተኞች ናቸው። አቤቱታ ከቀረበባቸው የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች አብዛኞቹ (55.3%) የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ናቸው። ከእነዚህም መካከል በእስር ላይ የሚገኙ ሰዎች መብቶች ጥሰቶች፣ የነጻነት መነፈግ፣ የተፋጠነ ፍትሕ እጦት እና በሕይወት የመኖር መብት ጥሰትን የሚመለከቱት ከፍተኛውን ቁጥር ይይዛሉ። ኢሰመኮ ተቀብሎ ካስተናገዳቸው 1258 ጉዳዮች መካከል 968ቱ መፍትሔ ያገኙ ሲሆን፣ 39 ጉዳዮች በሌሎች ተቋማት መፍትሔ እንዲሰጥባቸው ተመርተዋል።

## ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች

22. በማኅበራዊ እና በኢኮኖሚያዊ መብቶች ዘርፍ በበጀት ዓመቱ ከታዩ ቁልፍ እመርታዎች መካከል በሀገር አቀፍ ደረጃ ከቅድመ 1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ያሉ 6.3 ሚሊዮን ተማሪዎች የምገባ ሥርዓት ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ መደረጋቸው፤ አዳዲስ ትምህርት ቤቶችን ከመገንባት እንዲሁም ለነባሮቹ እድሳት ከማከናወን በተጨማሪ በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ከተጎዱ ትምህርት ቤቶች መካከል በአማራ ክልል 45 እና በአፋር ክልል 4 ትምህርት ቤቶች ተገንብተው መጠናቀቃቸው፤ እንዲሁም ግጭቶችን ጨምሮ በተለያዩ ምክንያቶች የወደሙ ትምህርት ቤቶችን መልሶ ለመገንባት እና ከትምህርት ገበታ ውጪ የሆኑ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ለመመለስ የፌዴራል እና የክልል ትምህርት ቢሮዎች እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻዎች መግባባት ላይ የደረሱበት ምክክር መካሄዱ ይገኙበታል። በበጀት ዓመቱ የተከናወኑ የተወሰኑ የሕግ ማሻሻያዎች የማኅበራዊ እና የኢኮኖሚያዊ መብቶችን በማረጋገጥ ረገድ አበረታች እርምጃዎች የታዩባቸው ሲሆኑ፣ ለምሳሌ የጤና አገልግሎት አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1362/2017 እንዲሁም የአጠቃላይ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1368/2017 የሰብአዊ መብቶች መርሖችን ያገናዘበ የጤና እና ትምህርት አገልግሎትን ለማረጋገጥ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ድንጋጌዎችን ይዘዋል።

23. በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች እየተካሄዱ ያሉ የትጥቅ ግጭቶች እና የጸጥታ መደፍረስ ሁኔታዎች፣ ተያይዘው የሚከሰቱ የንብረትና መሠረተ ልማት ውድመቶች፣ የእንቅስቃሴ ገደብና የምርት ሥራ መቀዛቀዝ ሁኔታዎች፣ የዋጋ ንረት እንዲሁም ድርቅና ጎርፍን ጨምሮ የተፈጥሮ አደጋዎች በማኅበራዊ እና በኢኮኖሚያዊ መብቶች ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደራቸውን ቀጥለዋል። በአሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ ከሚገኙ የማኅበራዊ እና የኢኮኖሚያዊ መብቶች መካከል በቂ ምግብ የማግኘት መብት፣ የትምህርት መብት፣ የጤና መብት እንዲሁም የሥራና ተያያዥ መብቶችን የተመለከቱ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች በሪፖርቱ ተካተዋል።
24. የምግብ ዋስትና እና የተመጣጠነ ምግብ እጥረት በኢትዮጵያ በ2017 በጀት ዓመት አሳሳቢ ሆኖ የቀጠለ ሲሆን በተለይም ከ5 ዓመት በታች በሆኑ ሕፃናት ላይ ከፍተኛ ጉዳትና ሥጋት አስከትሏል። ተፈናቃዮችን እና ተመላሾችን ጨምሮ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ምግብን ጨምሮ ሌሎችም ሰብአዊ ድጋፎችን የሚያቀርቡ ድርጅቶች አገልግሎት መቋረጥ ወይም መስተጓጎል ችግሩን አባብሶታል።
25. በ2017 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን በመላ ሀገሪቱ ከ7.8 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታ ውጪ ሲሆኑ፤ በአማራ ክልል ብቻ ከ3700 በላይ ትምህርት ቤቶች በክልሉ በሚካሄደው ግጭት ሳቢያ አገልግሎት አይሰጡም። በኢትዮጵያ በተለያዩ ክልሎች አካባቢዎች የመምህራን ደመወዝ በወቅቱ እና በአግባቡ ካለመከፈሉ፣ በሰው ሠራሽ እና የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት የተፈናቀሉ ሰዎች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ከመዘጋታቸው እንዲሁም ከሌሎች ተዛማጅ ምክንያቶች ጋር ተያይዞ በትምህርት መብት አፈጻጸም ላይ ያሉ ክፍተቶች የቀጠሉ ሲሆን፤ ከትምህርት ገበታ ውጪ የሚሆኑ ሕፃናት በተለይም ሴት ሕፃናት ያለ ዕድሜ ጋብቻን ጨምሮ ለሌሎች ዘርፈ ብዙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እና ጥቃቶች ተጋላጭ እንደሚሆኑ፣ ከገጠር ወደ ከተማ እንደሚፈልሱ እና ለጉልበት ብዝበዛ፣ ለተለያዩ ሱሶች እንዲሁም ሥነ-ልቦናዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች እንደሚጋለጡ የኢሰመኮ ክትትሎች ያመላክታሉ።
26. በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የወባ፣ ኮሌራ እና ኩፍኝ በሽታዎች በስፋት ተከስተዋል። የኢትዮጵያ የጤና ክላስተር የሚያዝያ ወር 2017 ዓ.ም. ሪፖርት እንደሚያመላክተው ከጥር ወር እስከ ሚያዝያ ወር ባለው ጊዜ ብቻ በሀገሪቱ 1,978,505 የወባ፣ 4,056 የኮሌራ፣ 3,908 የኩፍኝ ክስተቶች የተመዘገቡ ሲሆን፣ በወባ 77፣ በኮሌራ 42 እንዲሁም በኩፍኝ 22 ሰዎች መሞታቸው ተገልጿል። በግጭቶች ምክንያት የጤና አገልግሎት ተቋማት፣ መሠረተ ልማቶች እና እንደ አንቡላንስ ያሉ አስፈላጊ መገልገያዎች በከፊል ወይም በሙሉ አገልግሎት ማቆማቸው፣ የእንቅስቃሴ ገደቦች መኖራቸው እንዲሁም የመድኃኒትና የሕክምና ቁሳቁሶች አቅርቦት እጥረት የጤና መብት ሁኔታ እንዲባባስ አድርጓል። ከጤና ባለሙያዎች የደመወዝ፣ ጥቅማጥቅም፣ የሙያ ዕድገት ዕድሎች እንዲሁም ምቹ የሥራ ቦታ እና ነጻነት ጥያቄዎች በወቅቱ አለመመለስ ጋር ተያይዞ በበጀት ዓመቱ የተከሰተው የጤና ባለሙያዎች የሥራ ማቆም አድማ በጤና መብት ዘርፍ ላይ ጉዳት ማስከተሉ በሪፖርቱ ተገልጿል።
27. የሥራ እና ተያያዥ መብቶችን ተፈጻሚነት በማረጋገጥ ረገድ ችግሮች የቀጠሉ ሲሆን፣ ለምሳሌ በአማራ ክልል የተወሰኑ አካባቢዎች፣ ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ማእከላዊ ኢትዮጵያ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ሲዳማ እና ትግራይ ክልሎች የመምህራንና የጤና ባለሙያዎችን ጨምሮ የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ ወቅቱን ጠብቆ በአግባቡ ባለመከፈሉ ሠራተኞች ለዘርፈ ብዙ ችግሮች መጋለጣቸው በሪፖርቱ ተመላክቷል። የኢትዮጵያ አሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል

እንዲወሰን የሕግ መሠረት ያስቀመጠ ቢሆንም በዚህ በጀት ዓመትም ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል ሳይወሰን ቀጥሏል፡፡

## የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች

28. የፍትሕ ሚኒስቴር በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ አተገባበር ሂደት ሴቶች እና ሕፃናትን ጨምሮ የተጎጂዎችና ተጋላጭ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተሳትፎ ስትራቴጂን ያረቀቀ መሆኑ፤ የአፋር ክልል ረቂቅ የቤተሰብ ሕግ ኢሰመኮ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ባቀረቧቸው ምክረ ሐሳቦች መሠረት አስፈላጊ ማሻሻያዎች ተደርጎበት ወደ ማጽደቅ ሂደት ለመግባት ዝግጅት መጠናቀቁ፤ ኢሰመኮ በአፋር እና በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች የሚፈጸመውን የሴት ልጅ ግርዛት አስመልክቶ ያካሄደውን ግልጽ የአቤቱታ መቀበያ መድረክ ጨምሮ በሴቶች እና በሕፃናት ላይ ከፍተኛ አካላዊ እና ሥነልቦናዊ ጉዳት የሚያደርሱ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስቀረት የውትወታ ተግባራት መከናወናቸው እና የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠናዎች መሰጠታቸው፤ ኢሰመኮ ቀደም ሲል በሰጠው ምክረ ሐሳብ መሠረት በኦሮሚያ ክልል በተወሰኑ የእርሻ ልማት ሥራዎች ላይ ሕፃናትን በቡና ለቀማ ላይ የማሰማራት ተግባር እና የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ መቆሙ በ2017 በጀት ዓመት በሴቶችና በሕፃናት መብቶች ዘርፍ ከታዩ ቁልፍ እመርታዎች መካከል ናቸው፡፡
29. ከሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. እስከ ሰኔ ወር 2017 ዓ.ም. በተለይም ግጭቶች በቀጠሉባቸው አካባቢዎች፣ አስፈላጊው የመልሶ ግንባታ ባልተከናወነባቸው በድኅረ ግጭት ሁኔታ ውስጥ በሚገኙ የሀገሪቱ ክፍሎች፣ እንዲሁም ድርቅ እና ጎርፍን ጨምሮ በተለያዩ የተፈጥሮ አደጋዎች ሳቢያ ጉዳት በደረሰባቸው እና ነዋሪዎች መፈናቀልን ጨምሮ ለተለያዩ ችግሮች በተጋለጡባቸው አካባቢዎች ያለው የሴቶችና ሕፃናት የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ አሳሳቢነት ቀጥሏል፡፡
30. በሪፖርቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች እንደተመላከተው በትጥቅ ግጭት እንዲሁም በጸጥታ መደፍረስ ሁኔታ ውስጥ በተለያዩ አካላት በሚፈጸሙ ጥቃቶች ሴቶችና ሕፃናት ተገድለዋል፤ በተለይም በሴቶች ላይ የሚፈጸም አስገድዶ መድፈርን ጨምሮ አካላዊ እና ሥነ ልቦናዊ ጥቃቶች ደርሶባቸዋል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች በጤና፣ ትምህርት እና ሌሎችም አገልግሎቶች ላይ የሚያጋጥሙ ከፊል እና ሙሉ የአገልግሎት መቋረጥ ሁኔታዎች በበጀት ዓመቱ አሳሳቢ ሆነው ከቀጠሉ እንደ ኩፍኝ፣ ወባ እና ኮሌራ ያሉ በሽታዎች በስፋት መሰራጨት እና ምግብን ጨምሮ ሌሎችም ሰብአዊ ድጋፎችን የሚያቀርቡ ድርጅቶች አገልግሎት መቋረጥ ወይም መስተጓጎል ጋር ተዳምሮ በሴቶች እና ሕፃናት በሕይወት የመኖር፣ የትምህርት፣ የጤና እንዲሁም ምግብን ጨምሮ በቂ የኑሮ ደረጃ የማግኘት መብቶች ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡
31. ኢሰመኮ ዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ እና ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ማዕቀፎችን መሠረት በማድረግ በኢንዱስትሪ ፓርኮች እና ፋብሪካዎች ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ ሴቶችን መብቶች አያያዝን፣ በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት መብቶች አያያዝን፣ በማሳደጊያ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት መብቶች አያያዝን፣ በወንጀል ነክ ነገር ውስጥ ገብተው በተሐድሶ ተቋም ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት መብቶችን እንዲሁም የሕፃናት የትምህርት መብት ሁኔታን በሚመለከት ያደረጋቸው ክትትሎች ትኩረት የሚሹ በርካታ አሳሳቢ ጉዳዮች የታዩባቸው መሆኑን ሪፖርቱ ያመላክታል፡፡ በተለይም ኢሰመኮ በአፋር እና በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች የሚፈጸመውን የሴት ልጅ ግርዛት አስመልክቶ በአዲስ አበባ ከተማ ሰኔ 18 እና 19 ቀን 2017 ዓ.ም. ግልጽ

የአቤቱታ መቀበያ መድረክ በመጠቀም ያከናወነው ስልታዊ ምርመራ በሴት ልጅ ግርዛት ምክንያት በሴቶችና ሴት ሕፃናት በሕይወት የመኖር፣ የጤና፣ የአካል እና የአእምሮ ደኅንነት እንዲሁም ሌሎች መሠረታዊ መብቶች ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን በዝርዝር ያመላከተ ነው፡፡

## የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን መብቶች

**32.** በ2017 በጀት ዓመት በአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን መብቶች ዘርፍ ከታዩ አበረታች እርምጃዎች መካከል ኢትዮጵያ ፊርማ ያጸደቀችው የአፍሪካ አረጋውያን መብቶች ፕሮቶኮል ወደ ሥራ ለመግባት የሚያስፈልገውን የፈራሚ ሀገራት ቁጥር ማግኘቱ፤ የአረጋውያን አዋጅ መረቀቁ፤ የአካል ጉዳተኞች ፖሊሲ የመጀመሪያ ረቂቅ መዘጋጀቱ፤ የአካል ጉዳተኞች የ10 ዓመት የድርጊት መርኃ ግብር መረቀቁ፤ የአፍሪካ የአረጋውያን መብቶች ፕሮቶኮል በሚደነግገው መሠረት አረጋውያን በቂ እንክብካቤና የሕመም ማስታገሻ ሕክምና ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የሚረዳው ብሔራዊ የጤና እንክብካቤ (palliative care) መምሪያ በቀደመው በጀት ዓመት መገባደጃ በጤና ሚኒስቴር መዘጋጀቱ እንዲሁም የአካል ጉዳተኝነትን ወቅታዊ እና አስተማማኝ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ወጥነት ባለው መልኩ ለማሰባሰብ የሚረዳ ረቂቅ መምሪያ በኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት መዘጋጀቱ ይገኙበታል፡፡ ሕግ አርቃቂ አካላት ኢሰመኮን ጨምሮ በተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሚሰጡ ምክረ ሐሳቦችን ለማካተት የተሻለ ቁርጠኝነት ማሳየታቸው እና አዳዲስ ሕጎች ከነባር ሕጎች በተሻለ የአረጋውያን እና አካል ጉዳተኞችን መብቶች አካተው በመረቀቅ ላይ መሆናቸው አበረታች ሲሆን ከእነዚህም መካከል በበጀት ዓመቱ የጸደቀው የአጠቃላይ ትምህርት አዋጅ አንዱ ነው፡፡

**33.** በሌላ በኩል የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ያዘጋጀው የአካል ጉዳተኞች ረቂቅ አዋጅ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አለመቅረቡ እንዲሁም ሀገራት የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን ትክክለኛ ቁጥራዊ መረጃ በመያዝ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ምላሽ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ቢሆንም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ብዛት በትክክል አለመታወቅ ሰብአዊ መብቶቻቸውን ከማስከበር እና ከማስጠበቅ አኳያ ተግዳሮት ሆኖ መቀጠሉ በሪፖርቱ ተመላክቷል፡፡ ኢሰመኮ ክትትል ባደረገባቸው በኢትዮጵያ በተለያዩ ከተሞች የሚገኙ የልዩ አዳሪ እና አካቶ ትምህርት ቤቶች የተስተዋሉ የከባቢያዊ፣ ተቋማዊና የመረጃ ተደራሽነት ችግሮች እንዲሁም የአካል ጉዳተኞችን ፍላጎት መሠረት ባደረገ መልኩ መጻሕፍትንና ሌሎች የትምህርት ቁሳቁሶችን እንዲሁም ተገቢው ሙያና ስልጠና ያላቸው መምህራንን በማሟላት ረገድ ተግዳሮቶች መኖራቸው፤ በተለይም ለሴት አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተደራራቢ ተጋላጭነታቸውን መሠረት ያደረገ ድጋፍ የማይቀርብ መሆኑ እና በተወሰኑ ልዩ አዳሪ እና አካቶ ትምህርት ቤቶች ሴት አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ጾታን መሠረት ላደረገ ጥቃት ጭምር የሚያጋልጡ ሁኔታዎች መኖራቸው በሪፖርቱ ተመላክቷል፡፡

**34.** ግጭቶች እና የጸጥታ ችግሮች ባሉባቸው አካባቢዎች በአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች አሳሳቢነት በ2017 በጀት ዓመትም የቀጠለ ሲሆን፤ በእነዚህ አካባቢዎች የሚገኙ የአረጋውያን መንከባከቢያ ማእከላት በግጭቶች እና ተያይዘው በሚከሰቱ ችግሮች ሳቢያ ዐቅማቸው እየተዳከመ በመምጣቱ ለአረጋውያን በሚያቀርቡት አገልግሎት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ተፈጥሯል፡፡

# የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶች

## የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች

35. በኢትዮጵያ በትጥቅ ግጭቶች፣ በጸጥታ ችግሮች እንዲሁም ጎርፍ እና የመሬት መንቀጥቀጥን ጨምሮ በተለያዩ አካባቢዎች በተከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎች ሳቢያ ከመኖሪያ ቀያቸው የተፈናቀሉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በበርካታ ክልሎች በመጠለያዎች፣ በጊዜያዊ የሰፈራ ቦታዎች ወይም ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር ተቀላቅለው ይገኛሉ።

36. በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት ብሔራዊ ስትራቴጂ መዘጋጀቱ እና ተፈናቃዮች ተጠልለው በሚገኙበት አካባቢ ብሔራዊ መታወቂያ የሚያገኙበት ሁኔታ መመቻቸቱ በ2017 በጀት ዓመት የታዩ መልካም እመርታዎች ናቸው። በአፋር ክልል በበጀት ዓመቱ በተደጋጋሚ እያጋጠመ ከሚገኘው የመሬት መንቀጥቀጥ ጋር ተያይዞ ጉዳት በደረሰባቸውና ሥጋት ባለባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ የመፈናቀል ሥጋት ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን ወደ ሌሎች አካባቢዎች የማስፈር እና ሰብአዊ ድጋፍ የማቅረብ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ መሆናቸው፤ በአማራ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች ለሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት እንዲቻል በክልሉ አደጋ መከላከል እና ምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ኮሚሽን እና በተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት (UNDP) አማካኝነት የዘላቂ መፍትሔ ስትራቴጂ መዘጋጀቱ፤ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ለሚገኙ የተሟላ ዘላቂ መፍትሔ አግኝተው ራሳቸውን ማስተዳደር ላልጀመሩ ተፈናቃዮች ክልሉ የሚያደርገውን የድጋፍ እና ጥበቃ ተግባር መቀጠሉ በሪፖርቱ የተካተቱ ተጨማሪ ቁልፍ እመርታዎች ናቸው። በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ያጸደቀችው በአፍሪካ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጥበቃ እና ድጋፍን አስመልክቶ የተደረገው የአፍሪካ ኅብረት ስምምነት (የካምፓላ ስምምነት) ማስፈጸሚያ ብሔራዊ ረቂቅ ሕግ ጸድቆ በሥራ ላይ አለመዋሉ ከሕግ እና ተቋማዊ ማዕቀፍ ጉድለቶች ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ የተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ክፍተቶች ተባብሰው እንዲቀጥሉ አስተዋጽዖ አድርጓል።

37. አፋር፣ አማራ፣ ማእከላዊ ኢትዮጵያ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና ትግራይን ጨምሮ ኢሰመኮ ክትትል ባደረገባቸው የተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች በመጠለያ ጣቢያዎችና ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር ተቀላቅለው የሚገኙ ተፈናቃዮች እንዲሁም ተመላሾች በቂ፣ ወቅቱን የጠበቀ፣ ተደራሽ እና ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተፈናቃዮች ያማከለ ሰብአዊ ድጋፍ እንዲሁም ትምህርትና ጤናን ጨምሮ የተሟላ ማኅበራዊ አገልግሎት የማይቀርብላቸው በመሆኑ በከፍተኛ ችግር ውስጥ ይገኛሉ። የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔ ሳያገኙ ፍላጎታቸውን በበቂ ሁኔታ በማያሟላ ሰብአዊ ድጋፍ ላይ ጥገኛ ሆነው በተራዘመ የመፈናቀል ሁኔታ ውስጥ መገኘታቸው አሳሳቢ ሲሆን፤ ለምሳሌ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ ደቡብ ኦሞ ዞን፣ ዳሰነች ወረዳ በኦሞ ወንዝ መሙላት ምክንያት ከ2012 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈናቅለው በ12 የተፈናቃዮች ጣቢያዎች ውስጥ የሚገኙ ከ79 ሺህ በላይ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች አሉ። በተወሰኑ ክልሎች ተግባራዊ የተደረጉ ተፈናቃዮችን ወደ ቀድሞ ቀያቸው የመመለስ የዘላቂ መፍትሔ አማራጮች የተመላሾችን ደኅንነት በማረጋገጥ፣ ለመፈናቀል መንስኤ የሆነውን ችግር መፍትሔ በመስጠት፣ እንዲሁም ተፈናቃዮችና ተመላሾች በዘላቂነት ተቋቁመው ወደ መደበኛ ኑሯቸው መመለስ እስኪችሉ ድረስ ሰብአዊ ድጋፍና መሠረታዊ አገልግሎቶችን በማቅረብ ረገድ ክፍተት የታየባቸው ናቸው።

## ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች

38. በኢትዮጵያ በከተማ እና በተለያዩ ክልሎች በሚገኙ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎች የሚኖሩ በርካታ ቁጥር ያላቸው የኤርትራ፣ የየመን፣ የሶማሊያ፣ የደቡብ ሱዳን፣ የሶሪያ፣ የኮንጎ እና የሌሎችም ሀገራት ስደተኞች ይገኛሉ። የኢትዮጵያ መንግሥት ስደተኞችን በተለይም በሱዳን የሚካሄደውን ግጭት ሸሽተው ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ስደተኞችን መቀበል እና ማስተናገድ መቀጠሉ፤ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ስደተኞች የብሔራዊ መታወቂያ፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎቶችን የሚያገኙበት ሁኔታ መመቻቸቱ፤ በኢትዮጵያ የሚገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎችን በኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ አገልግሎቶች አካታች ማድረግን ታሳቢ ያደረጉ ፕሮግራሞች መቀረጻቸው እንዲሁም ስደተኞች በተለያዩ ሥራዎች ላይ በመሰማራት ራሳቸውን እና ቤተሰቦቻቸውን በኢኮኖሚ የሚደግፉበት ሁኔታ እንዲኖር የሚያስችል የሕግ ማሻሻያ በተለይ የስደተኞችን እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የሥራ መብት የሚደነግግ መመሪያ መጽደቁ በስደተኞች መብቶች ዘርፍ በበጀት ዓመቱ ከታዩ ቁልፍ እመርታዎች መካከል ናቸው። በአማራ ክልል ምዕራብ ጎንደር ዞን ይገኙ የነበሩ የሱዳን ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎችን እንዲሁም በጋምቤላ ክልል ኦኩጉ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ ውስጥ የነበሩ የሙርሌ ጎሳ አባላት የሆኑ ደቡብ ሱዳናዊያን ስደተኞች የደኅንነት ሥጋት የነበረባቸው ሲሆን ወደ ሌሎች ቦታዎች እንዲዛወሩ በማድረግ ሥጋታቸውን መቀነስ መቻሉ በሪፖርቱ በመልካም እርምጃነት ተመላክቷል።
39. ጥገኝነት ጠያቂዎች የምዝገባ አገልግሎት ለማግኘት የሚቸገሩ መሆናቸው፤ ለምሳሌ በርካታ ስደተኞች በሚገኙበት አፋር ክልል ምንም ዐይነት የጥገኝነት ምዝገባ የማይከናወን እና ከዚህ ቀደም በክልሉ የነበሩት በርካታ የስደተኞች መቀበያ ጣቢያዎችም የተዘጉ መሆናቸው፤ በሀገሪቱ በሚካሄዱ ግጭቶችና የጸጥታ ችግሮች በስደተኞች ደኅንነት ላይ ተጽዕኖ መፍጠራቸው፤ ለምሳሌ በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር ዞን ዳባት ወረዳ ዓለም ዋጭ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ስደተኞች የታጠቁ ኃይሎች ወደ መጠለያ ጣቢያው በመግባት በሚያደርሱባቸው ጥቃት የሕይወት እና የአካል ጉዳትን ጨምሮ የተለያዩ የመብት ጥሰቶች እንደደረሰባቸው፤ ስደተኞች የስደተኝነት ሁኔታ አወሳሰን ሳይከናወንላቸው በጥገኝነት ጠያቂነት በመጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ያለ በቂ መሠረታዊ አገልግሎት ለረጅም ዓመታት የሚቆዩ መሆናቸው፤ እንዲሁም ስደተኞች በቂ ሰብአዊ ድጋፍ እና ማኅበራዊ አገልግሎት የማያገኙ መሆናቸው በሪፖርቱ ከተመላከቱ ተጨማሪ አሳሳቢ ጉዳዮች መካከል ናቸው።

## ፍልሰተኞች

40. የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት መዳረሻ ሀገራትን የማስፋት ጥረቶች መጀመራቸው በተለይም ኢትዮጵያ የሁለትዮሽ የሥራ ስምሪት ስምምነት ከተፈራረመቻቸው ነባር መዳረሻ ሀገራት ጋር የተፈረሙ ስምምነቶችን የማሻሻል ጥረቶች መኖራቸው፤ ከአዳዲስ መዳረሻ ሀገራት እና ቀጣሪ ድርጅቶች ጋር የሁለትዮሽ ስምምነቶች መመሥረታቸው፤ እንዲሁም የተሻሻለ የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪትን የሚመለከት አዋጅ መቀረጹ በበጀት ዓመቱ የታዩ አዎንታዊ እርምጃዎች ሲሆኑ ደኅንነቱ የተጠበቀ፣ በሥርዓት የሚመራ እና መደበኛ የሆነ ፍልሰትን ለማረጋገጥ አስተዋጽዖ ሊያደርጉ የሚችሉ ናቸው።
41. በአፋር ክልል ከዚህ ቀደም ለተጎጂ እና ተጋላጭ ፍልሰተኞች በዓለም አቀፍ የፍልሰተኞች ድርጅት (IOM) ይሰጥ የነበረው የጥበቃ (protection) አገልግሎት እና በክልሉ የነበረው የፍልሰተኞች ምላሽ መስጫ ጣቢያ (MRC) በመዘጋቱ ከፍልሰት

ተመላሾች እና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተጎጂ ፍልሰተኞች ለተለያዩ ተደራራቢ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተጋላጭ መሆናቸውን የኢሰመኮ ክትትል ያረጋገጠ ሲሆን፤ በዓለም አቀፍ የፍልሰተኞች ድርጅት (IOM) በሶማሊ ክልል የፍልሰተኞች ምላሽ መስጫ ጣቢያ የሚሰጡ የጥበቃና ድጋፍ አገልግሎቶችን ለመንግሥት ለማስረከብ መታቀዱ እና በመንግሥት አካላት በኩል ጣቢያውን ተረክቦ አገልግሎቱን ለማስቀጠል ምንም ዐይነት ዝግጅት እየተደረገ አለመሆኑ በዘርፉ ከተለዩ አሳሳቢ ጉዳዮች መካከል ናቸው፡፡

## ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎች ከመወጣት አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ

**42.** በዚህ የሪፖርት ዓመት ኢትዮጵያ አዲስ የፈረመችውና ያጸደቀችው አህጉራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነት የለም፡፡ በመሆኑም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስምምነቶች ከሆኑት ዋነኞቹ 9 የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች መካከል ሁሉንም ሰዎች ከአስገድዶ መሰወር ለመጠበቅ የተደረገው ስምምነት እና የፍልሰተኛ ሠራተኞችን እና የቤተሰቦቻቸውን መብቶች ለመጠበቅ የተደረገው ዓለም አቀፍ ስምምነት በዘንድሮ በጀት ዓመትም አልተፈረሙም/አልጸደቁም፡፡ በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ኅብረት 12 መሠረታዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች መካከል፣ የአፍሪካ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ፕሮቶኮልን ተቀብላ አላጸደቀችም፡፡

**43.** በዚህ የሪፖርት ዓመት ኢትዮጵያ አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶችን ስምምነቶችን በተመለከተ ለአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር እንዲሁም የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል (ማፑቶ ፕሮቶኮል) አፈጻጸምን አስመልክቶ በጥቅምት ወር 2017 ዓ.ም. በተካሄደው የአፍሪካ ኮሚሽን 81ኛ መደበኛ ጉባኤ ወቅት ማቅረብ የነበረባትን ሪፖርት ሳታቀርብ አልፋለች፡፡ ይህን ተከትሎ በግንቦት ወር 2017 ዓ.ም. በተካሄደው የኮሚሽኑ 83ኛ መደበኛ ጉባኤ ላይ የስምምነቶቹን አፈጻጸም በተመለከተና በማፑቶ ፕሮቶኮል ላይ የመጀመሪያ ሪፖርት (initial report) ለኮሚሽኑ አቅርባለች፡፡ በዚህም ኢሰመኮ እንደ አንድ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ማሟያ ሪፖርት አቅርቧል፡፡

**44.** በዓለም አቀፍ ደረጃ በዚህ የሪፖርት ዓመት ከኅዳር 3 እስከ 6 ቀን 2017 ዓ.ም. በጄኔቫ ስዊዘርላንድ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት በተካሄደው የኢትዮጵያ 4ተኛ ዙር ሁሉን አቀፍ ወቅታዊ ግምገማ መድረክ ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም በምክር ቤቱ በግንቦት 6 ቀን 2011 ዓ.ም. በሁሉን አቀፍ ወቅታዊ ግምገማ 3ተኛ ዙር በተገመገመችበት ወቅት የተቀበለቻቸው ምክረ ሐሳቦች ያሉበትን የአፈጻጸም ደረጃ አስመልክቶ ሀገራዊ ሪፖርት አቅርባለች፡፡ ኢሰመኮ እንደ አንድ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም የማሟያ ሪፖርት አቅርቧል፡፡ በመድረኩ የተሳተፉ 114 የተ.መ.ድ. አባል ሀገራት በኢትዮጵያ በሰብአዊ መብቶች አያያዝ ረገድ ባለፉት 5 ዓመታት የታዩ እመርታዎችን እና አሳሳቢ ጉዳዮችን በማንሳት በአጠቃላይ 316 ምክረ ሐሳቦችን የሰጡ ሲሆን፤ 252 የሚሆኑት ተቀባይነት ሲያገኙ (supported) 12 ምክረሐሳቦች በከፊል ተቀባይነት ያገኙ (supported/ noted) ሲሆኑ 52 ምክረ ሐሳቦች ደግሞ ከግምት ውስጥ የገቡ (noted) ናቸው፡፡

## የሀገራዊ ምክክር ሂደት

45. ሀገራዊ ምክክር ለሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ጨምሮ በርካታ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላትን በማሳተፍ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ አለመግባባቶችን እንዲሁም ልዩነቶችን በመፍታት በምክክር ላይ የተመሠረተ ሰላማዊ ግንኙነትን ለመፍጠር የሚረዳ በመሆኑ በሂደቱም ሆነ በውጤቱ ለሰብአዊ መብቶች መከበር አዎንታዊ ሚና የሚጫወት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከግንቦት 2016 ዓ.ም. እስከ ግንቦት ወር 2017 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ በ11 ክልሎች እና በ2 ከተማ አስተዳደሮች ሕዝባዊ ውይይት በማድረግ ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች አጀንዳ አሰባስቧል፡፡ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እንዲሁም ሌሎች በርካታ የማኅበረሰብ ክፍሎች በሂደቶቹ ላይ መሳተፋቸው ለተጋላጭ የማኅበረሰብ ክፍሎች በሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ የመሳተፍ መብትን ለማረጋገጥ ዕድል መስጠቱ መልካም እርምጃ ነው፡፡ በሂደቱ የቡድን ሰብሳቢዎች በውይይቶች ጊዜ ያለምንም አድሎአዊ ልዩነት ለሁሉም ተሳታፊዎች አጀንዳ የሚያቀርቡበትን እኩል ዕድል መስጠታቸው እና ምንም እንኳን በሂደቱ የተሳተፉ ሴቶች ቁጥር አጠቃላይ ተሳትፎ ከ50 በመቶ የሚያንስ ቢሆንም በውይይት ወቅት የተሻለ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያበረታቱ እርምጃዎች መወሰዳቸው ኢሰመኮ በክትትሉ የለያቸው መልካም እርምጃዎች ናቸው፡፡

46. ሆኖም በሀገራዊ ምክክር ታጣቂዎችንና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ጨምሮ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚጠበቁ ባለድርሻዎች ከሂደቱ ራሳቸውን በማግለላቸው በሂደቱ አካታችነት ላይ ተግዳሮት መፈጠሩ፤ እንዲሁም በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደቶች ላይ የሚሳተፉ ሰዎችን ግላዊነት (privacy)፣ ደኅንነት እና ነጻነት በማረጋገጥ ረገድ ክፍተቶች መኖራቸው ኢሰመኮ በክትትሉ ካረጋገጣቸው አሳሳቢ ጉዳዮች መካከል መሆናቸው በሪፖርቱ ተመላክቷል፡፡

## የሽግግር ፍትሕ

47. በሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. የጸደቀው የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ትግበራ ፍኖተ ካርታ በሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. ይፋ የተደረገ ሲሆን፤ በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው የተመላከቱትን ዋና ዋና ተቋማት ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጆች መቀረጻቸው፤ ፖሊሲውን ለማስፈጸም ቁልፍ የሆነው የዓለም አቀፍ ወንጀሎች ሕግ ከሽግግር ፍትሕ ሂደት መጠናቀቅ በኋላም በዘላቂነት ተግባራዊ ሊደረግ በሚችልበት አግባብ መረቀቁ፤ እንዲሁም በሽግግር ፍትሕ ሂደት የተጎጂዎችንና ለሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ተሳትፎ የሚመራ ረቂቅ ስትራቴጂ በመዘጋጀት ላይ መሆኑ ኢሰመኮ በበጎ የሚመለከታቸው መልካም እመርታዎች ናቸው፡፡

48. በሌላ በኩል በሽግግር ፍትሕ ትግበራ ፍኖተ ካርታው መሠረት በ2017 በጀት ዓመት ሊተገበሩ ይገባቸው የነበሩ የሽግግር ፍትሕ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ማቋቋም፣ የትግበራ ቅደም-ተከተል ጥቅል ዕቅድ ማውጣት፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን፣ የሕዝብን እንዲሁም የባለድርሻ አካላትን ድጋፍና የባለቤትነት ስሜት የሚያጠናክሩ ሥራዎችን የማከናወን ተግባራት በታቀደላቸው ጊዜ አለመከናወናቸው አሳሳቢ ነው፡፡ የተዘጋጁት ረቂቅ ሕጎችና ሰነዶችም ለሕዝብ ውይይት እስከ አሁን አለመቅረባቸው እንዲሁም ፍትሕ ሚኒስቴር እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን እና አጠቃላይ

ሂደቱ እየተመራ ያለበትን ሁኔታ በበቂ ግልጽነት እያከናወነ አለመሆኑ ትኩረት የሚሹ ተጨማሪ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

## ምክረ ሐሳቦች

49. ኢሰመኮ በ2017 በጀት ዓመት የታዩ አሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮችን በሚመለከት በየመብት ዘርፉ ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች ያመላከተ ሲሆን በተለይም በትጥቅ ግጭት ዐውድ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕጎችን ማክበርን፣ ለግጭቶች ሰላማዊ መፍትሔዎችን ማፈላለግን፣ ከዚህ ቀደም የተፈረሙ የሰላም ስምምነቶችን ተፈጻሚነት ማጠናከርን፣ ለመልሶ ግንባታ እና መልሶ ማቋቋም ሥራዎች ተገቢውን ትኩረት መስጠትን፣ ሰው ሠራሽ እና የተፈጥሮ አደጋዎችን መከላከልና ምላሽ መስጠትን እንዲሁም የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦትን ማረጋገጥን፣ ለሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች በር የሚከፍቱ የሕግና መዋቅር ክፍተቶችን መፍትሔ መስጠትን በተመለከተ እንዲሁም በቀጣይ ጊዜያት ከብሔራዊ ምክክር፣ የሽግግር ፍትሕ እና በ2018 በጀት ዓመት እንደሚካሄድ ከሚጠበቀው 7ኛው ዙር ጠቅላላ ምርጫ ጋር የተያያዙ ምክረ ሐሳቦችን አቅርቧል፡፡

WWW.EHRC.ORG



# ክፍል ፪

# ክፍል ሁለት

# አጠቃላይ መግቢያ

1. የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(14) መሠረት ነጻ እና ገለልተኛ የፌዴራል ተቋም ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 210/1992 (በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው) የተቋቋመ እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆነ፣ ለሰብአዊ መብቶች መስፋፋት፣ መከበር እና ጥበቃ የሚሠራ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ነው፡፡ የተቋቋመባቸው ዋና ዋና ዓላማዎቹም የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ ሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ እንዲኖረው ማስተማር፣ ሰብአዊ መብቶች እንዳይጣሱ መጠበቅ/መከታተል እና ሳይሸራረፉ ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ እንዲሁም መብቶቹ ተጥሰው ሲገኙ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ናቸው፡፡
2. ኢሰመኮ የኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች፣ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ የስደተኞች እና የፍልሰተኞች መብቶች፣ የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን መብቶች፣ የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች፣ የሰብአዊ መብቶች ትምህርት፣ እንዲሁም የሰብአዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ የሥራ ዘርፎችን የሚመሩ የሥራ ክፍሎች አሉት፡፡ በተጨማሪም በመዋቅሩ መሠረት የተቋቋሙ የሃብት አስተዳደር፣ የታለንት እና የሰው ኃይል አስተዳደር፣ የአጋርነት እና የፕሮግራም ዕቅድ፣ የፋይናንስ እና ጠቅላላ አገልግሎት፣ የኢንፎርሜሽን እና ቴክኖሎጂ፣ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን፣ የሕግና የፖሊሲ ሥራ ክፍሎች እና የዋና ኮሚሽነር ጽሕፈት ቤት አሉት፡፡ ኢሰመኮ በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኘው ዋና ቢሮ በተጨማሪ በአሶሳ፣ በባሕር ዳር፣ በጋምቤላ፣ በሃዋሳ፣ በጅማ፣ በጅግጅጋ፣ እና በሰመራ ከተሞች ጽሕፈት ቤቶች ያሉት ሲሆን፣ ከአገልግሎት ውጪ የቆየው የመቐለ ከተማ ጽሕፈት ቤት በ2017 በጀት ዓመት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡
3. ይህ 4ኛው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ዓመታዊ ሪፖርት ከሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. እስከ ሰኔ ወር 2017 ዓ.ም. ያለውን ሀገራዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ የሚሸፍን ሲሆን፣ በኢሰመኮ ልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች እና ጽሕፈት ቤቶች አማካኝነት በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ሪፖርቱ ኢሰመኮ በሚንቀሳቀስባቸው የሥራ ዘርፎች የተስተዋሉ ዋና ዋና ቁልፍ እመርታዎችን፣ አሳሳቢ ጉዳዮችን እንዲሁም ምክረ ሐሳቦችን አቅርቧል፡፡ ሆኖም የበጀት ዓመቱን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በጥቅሉ የሚያሳይ እንጂ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን ዝርዝር፣ ብዛት እና ዐይነት ሙሉ በሙሉ የሚያስረዳ አይደለም፡፡

### ሪፖርቱ የቀረበበት የሕግ ማዕቀፍ

4. ይህ ሪፖርት በኢሰመኮ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 210/1992 (በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው) መሠረት የተዘጋጀ ነው፡፡ በሰብአዊ መብቶች ጉዳይ እና የኢሰመኮን የሥራ አካሄድ አስመልክቶ ዋና ኮሚሽነሩ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት እንዲያቀርቡ የአዋጁ አንቀጽ 19(2)(ሰ) ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም በአዋጁ አንቀጽ 39(2) መሠረት ኢሰመኮ መደበኛ ሪፖርቶችን ማቅረብ እና አሠራሩን ለሕዝብ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡ ይህን ኃላፊነት ከሚያሳካባቸው መንገዶች አንዱ ኢትዮጵያ በበጀት ዓመቱ ከሰብአዊ መብቶች አኳያ

የነበረችበትን ሁኔታ የሚዳስስ ዓመታዊ ሪፖርቱን ተጠሪነቱ በቀጥታ ለሕዝብ ለሆነው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማቅረብ ነው። በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ደረጃ እ.ኤ.አ. በ1993 በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀው የብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት መርሖች ስብስብ (በአጭሩ "የፓሪስ መርሖች") ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት ለመንግሥት፣ ለፓርላማ እንዲሁም ለሌሎች አካላት አስተያየቶችን፣ ምክረ ሐሳቦች እና ሪፖርቶችን የማቅረብ አጠቃላይ ኃላፊነት እንዳለባቸው ያመለክታል። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የክትትል እና ቁጥጥር ሥራ ከሚያደርግባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ በሀገሪቱ ውስጥ ያለው የሰዎች መሠረታዊ መብቶችና ነጻነቶች አከባበር ሁኔታ መሆኑን የምክር ቤቱ የአሠራርና የአባላት ሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 ይደነግጋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55 (16) ላይ በተቀመጠው መሠረት የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን ሊያስቆምና ሊቆጣጠር ባልቻለ ክልል ላይ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የክትትል እና ቁጥጥር ሥራዎች ሊያከናውን እንደሚችል ከላይ የተጠቀሰው ደንብ ይደነግጋል። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እነዚህን የቁጥጥር እና የክትትል ሥራዎች ለማከናወን ያግዘው ዘንድ እንደ ኢሰመኮ ያሉ በሕግ መሠረት በቀጥታ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ ከሚገባቸው መንግሥታዊ አካላት፤ በዓመቱ የተከናወኑ ተግባራትን፣ የተገኙ ውጤቶችን፣ ያጋጠሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶችን እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚያካትት ይዘት ያለው ሪፖርት ይቀበላል።

5. ስለዚህም ኢሰመኮ ተፈጻሚነት ያላቸውን ሕጎች፣ ደንቦች እና ዓለም አቀፍ መርሖችን ተከትሎ ይህንን ሪፖርት አዘጋጅቷል። ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፋዊ እና አህጉራዊ ስምምነቶች፣ በዋነኛነትም ሁሉ አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ፣ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን፣ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ እና ባህላዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን፣ የአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር፣ በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውንም አድሎአዊ ልዩነት ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት፣ የአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል (ማፑቶ ፕሮቶኮል)፣ አድሎአዊ የዘር ልዩነቶችን ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት፣ የማሰቃየት እና ሌሎች የጭካኔ፣ ኢ-ሰብአዊ የሆነና ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ለማስቀረት የተደረገ ስምምነት፣ የሕፃናት መብቶች ስምምነት፣ የአፍሪካ የሕፃናት መብቶች እና ደኅንነት ቻርተር፣ ዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት፣ የአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የአረጋውያን መብቶች ፕሮቶኮል፣ የአፍሪካ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጥበቃ እና ድጋፍን አስመልክቶ የተደረገው የአፍሪካ ኅብረት ስምምነት (ካምፓላ ስምምነት) እና የዓለም-አቀፍ የተለምዶ ሕግ (International Customary Law) እንዲሁም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ-መንግሥትን ጨምሮ አግባብነት ባላቸው የሀገሪቱ ሕጎች የተደነገጉ የሰብአዊ መብቶችን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሪፖርት ነው። የሰብአዊ መብቶች ትምህርትን በመደበኛው የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ማካተትን በሚመለከት የተባበሩት መንግሥታት የዓለም የሰብአዊ መብቶች መርኃ ግብር (World Programme for Human Rights Education, (2005- ongoing))፤ እንዲሁም የሰብአዊ መብቶችን ትምህርት አፈጻጸምን ለመከታተል የተዘጋጀው የመከታተያ ዘዴ (the SDG 4.7 /Human Rights Education Monitoring Tool) ከሚያስቀምጧቸው የትግበራና የመከታተያ አመላካቾች አንጻር በመዳሰስ መረጃዎች ተካትተዋል።

## ሥነ-ዘዴ

6. ኢሰመኮ በሪፖርቱ ላይ የተካተቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ከባለመብቶች፣ ከተጎጂዎች፣ ከዐይን ምስክሮች፣ ከታራሚዎች እና ከተጠርጣሪዎች ወይም ከአቤቱታ አቅራቢዎች እና ቁልፍ የመረጃ ምንጮች ከሆኑ እንደ ሀገር ሽማግሌዎች፣ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ ሠራተኞች እና ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር ቃለ መጠይቆችን አካሂዷል፤ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ስደተኞች በሚገኙባቸው መጠለያ ጣቢያዎች፣ በሰው ሠራሽ ወይም ተፈጥሯዊ አደጋ ሳቢያ ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች፣ በፖሊስ ጣቢያዎች፣ ማረሚያ ቤቶች እና ሌሎች ማቆያ ሥፍራዎች እንዲሁም ለክትትልና ምርመራው አስፈላጊ ሆነው በተገኙ ሌሎች ሥፍራዎች የአካል ምልከታ አድርጓል፤ በተጨማሪም ከሚመለከታቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች እና ባለድርሻ አካላት ጋር የቡድን ውይይቶችን በማካሄድ፤ ሰነዶችን በማሰባሰብና በመመርመር፤ እንደ አስፈላጊነቱ ጥናቶችን በማካሄድ ይህን ሪፖርት አጋጅቷል። ኢሰመኮ በዚህ ሂደት በገለልተኝነት፣ ግልጽነትና ታማኝነት መርሖች እንዲሁም [በስትራቴጂክ ዕቅዱ](#) (ከ2014 ዓ.ም. — 2018 ዓ.ም.) በተዘረዘሩት እሴቶች እና መመሪያዎች በመመራት፣ የመረጃ ምንጭ የነበሩትን ምስክሮች እና ተጎጂዎች በመለየት እና መረጃ በመሰብሰብ ሂደት ምስጢራዊነትን፣ የምስክሮች ደኅንነት ጥበቃን እና ለተጨማሪ ጉዳት አለማጋለጥ መርሕን ተከትሏል።

7. ኢሰመኮ በዚህ ሪፖርት ያካተታቸው የምርመራ መረጃዎችና ግኝቶች በብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት እና በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ምርመራዎችና ክትትሎች እንዲሁም በዓለም አቀፍ አጣሪ ኮሚሽኖች ወይም እውነት አፈላላጊ አካላት ጥቅም ላይ የሚውሉ የማስረጃ ምዘና መስፈርቶችን መሠረት ያደረጉ ናቸው። ኢሰመኮ ለምርመራ "ምክንያታዊ አሳማኝነት" (reasonable grounds to believe) በመባል የሚታወቀውን የማስረጃ ምዘና ስልት የሚጠቀም ሲሆን፣ ይህም ከአንድ ተአማኒ ምንጭ የተገኘውን መረጃ ቢያንስ ከሁለት ተጨማሪ ገለልተኛ እና አስተማማኝ ምንጮች በተገኘ ተመሳሳይ ወይም የማይጣረስ መረጃ በመደገፍ/በማረጋገጥ (corroboration)፣ አንድ ምክንያታዊ የሆነን ሰው ስለ አንድ ነጠላ ክስተት ወይም ተደጋጋሚ ጥሰት መፈጸም ሊያሳምን በሚችል አግባብ ድምዳሜ ላይ የሚደረስበት የማስረጃ ምዘና ስልት ነው። ኢሰመኮ ለክትትል ሥራዎች "ምክንያታዊ ጥርጣሬ" (reasonable suspicion) ተብሎ የሚታወቀውን የማስረጃ ምዘና ደረጃን የሚከተል ሲሆን ይኸውም ድርጊቱ መፈጸሙን ወይም መድረሱን የሚያጠራጥሩ ሁኔታዎች መኖራቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ሲቻል ነው። በዚህም መሠረት በአንድ ቀጥተኛ ከሆነ ምንጭ ተፈጸመ ወይም ደረሰ የተባለ ድርጊት ወይም የሰብአዊ መብት ጥሰት ቢያንስ በሌላ በአንድ ነጻ ወይም ገለልተኛ እና ተዓማኒ የሆነ ምንጭ ሲረጋገጥ ነው።

## ውስንነቶች

8. በሪፖርቱ በተሸፈነው በጀት ዓመት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በቀጠሉ የትጥቅ ግጭቶች እና የጸጥታ መደፍረሶች ሳቢያ ኢሰመኮ እንደአስፈላጊነቱ ተንቀሳቅሶ ሥራውን ማከናወን ባለመቻሉ በሁሉም የሀገሪቷ ክፍሎች ያሉትን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ መመርመርና መከታተል እንዳይችል አድርጓል። በ2016 በጀት ዓመት ተፈጻሚ የነበረው የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ቁጥር 6/2015 የኢሰመኮ መደበኛ በሆኑና መደበኛ ያልሆኑ የተጠርጣሪዎች እና የታራሚዎች ማቆያ ቦታዎችን ክትትል ሥራውን አዳጋች አድርጎት የነበረ መሆኑ

ይታወሳል። ምንም እንኳን በ2017 በጀት ዓመት ተፈጻሚ በመሆን ላይ የሚገኝ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ባይኖርም፣ የኢሰመኮን ክትትሎች በከፍተኛ ሁኔታ የሚገድቡ ተግዳሮቶች አጋጥመዋል። ለምሳሌ ኢሰመኮ በሕግ ከተሰጡት ሥልጣንና ኃላፊነቶች አንዱ ፖሊስ ጣቢያዎችን፣ ጊዜያዊ ማቆያ ቦታዎችን እና ማረሚያ ቤቶችን በመደበኛነት በመጎብኘት የታራሚዎችን እና የተጠርጣሪዎችን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታ መከታተል ነው። በዚህ በጀት ዓመት በግጭቶችና በጸጥታ ችግሮች ሳቢያ ያለቅድመ ማስታወቂያ የሚደረጉ ድንገተኛ ጉብኝቶችን (unannounced visits) ጨምሮ የክትትል ተግባራትን በተሟላ ሁኔታ ለማድረግ አመቺ ሁኔታ ያልነበረ ከመሆኑ በተጨማሪ በአንዳንድ ቦታዎች ክትትል ለማድረግ ጥያቄ ቀርቦ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት አዎንታዊ ምላሽ አልተገኘም። በዚህም ምክንያት ለምሳሌ በኢሰመኮ ባሕር ዳር ጽሕፈት ቤት አማካኝነት በአማራ ክልል ከ5 ማረሚያ ቤቶች በስተቀር በሌሎች ማረሚያ ቤቶች፣ ፖሊስ ጣቢያዎች እና ኢመደበኛ ማቆያ ሥፍራዎች ክትትል ማድረግ አልተቻለም።

9. መንግሥታዊ አካላት የኢሰመኮን ተደራሽነት የሚያቀላጥፍ በቂ ትብብር ካለማድረጋቸው በተጨማሪ ኢሰመኮ በሕግ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት ልክ ሥራዎቹን ለመከወን የሚያስችለውን በቂ የሰው ኃይል እና ፋይናንስ በማሟላት ረገድ ውስንነቶች መቀጠላቸው በምርመራና ክትትል ሥራዎቹ ላይ ተጽእኖ አድርጓል። የኢሰመኮ ጽሕፈት ቤቶች በሌሉበት ወይም ከላይ በተጠቀሱትና በሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶች በአካል ተደራሽ መሆን ባልተቻለባቸው አካባቢዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን አሠራሮች መሠረት በማድረግ በርቀት የመከታተል እና የመመርመር ተግባር ቢቀጥልም የሚሰበሰቡት መረጃዎችና ማስረጃዎች በዐይነት፣ ብዛት እና ጥራት ውስን እንዲሆኑ አድርጓል።

WWW.EHRC.ORG



# ክፍል ፫

# ክፍል ሦስት

# ቁልፍ እመርታዎች እና አሳሳቢ ጉዳዮች

## የቁልፍ እመርታዎች አጠቃላይ ምልከታ

**10.** በኢትዮጵያ አጠቃላይ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ጉልህ አዎንታዊ አንድምታ ያላቸው የተወሰኑ እርምጃዎች በ2017 በጀት ዓመት የተከናወኑ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ምንም እንኳን የየራሳቸው ውስንነቶች ያሉባቸው ቢሆንም የሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሥራዎች መጀመር፣ የሀገራዊ ምክክር ሂደት ተጠናክሮ መቀጠል እንዲሁም ለኢሰመኮ የውትወታ ሥራዎች አዎንታዊ ምላሽ የሚሰጡ እርምጃዎች መከናወን ይገኙበታል።

**11.** በኢትዮጵያ በሰብአዊ መብቶች ላይ የተመሠረተ እና ተጎጂዎችን ማዕከል ያደረገ የተሟላ የሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሂደትን ለመምራት ያለመ የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ በሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. ጸድቆ ወደ ትግበራ ምእራፍ ተሸጋግሯል። ፖሊሲው ተግባራዊ እንዲሆን በማመቻቸት እና በሽግግር ፍትሕ ሂደቱ የተለያዩ ተግባራትን የሚያከናወኑ አካላትን በመደገፍ ረገድ የዋና አስተባባሪነት ሚና የተሰጠው የፍትሕ ሚኒስቴር ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት እና አጋሮች ጋር በመሆን የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ላይ መሆኑ የሚታወቅ ነው። ከእነዚህ ክንዋኔዎች መካከል የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ትግበራ ፍኖተ ካርታ በሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. ይፋ በማድረግ፣ በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው የተመላከቱትን ዋና ዋና ተቋማት ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጆች መቅረጽ፣ ፖሊሲውን ለማስፈጸም ቁልፍ የሆነውን የዓለም አቀፍ ወንጀሎች ረቂቅ አዋጅ፣ እንዲሁም ተጎጂዎችንና ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተሳትፎ ረቂቅ ስትራቴጂ በመዘጋጀት ላይ ይገኛሉ። ኢሰመኮ በዚህ የሕግ ዝግጅት የአርቃቂ ቡድን አባል በመሆን ተሳትፎ በማድረግና ድጋፍ በመስጠት እንዲሁም አጠቃላይ የአተገባበር ሂደቱን በመከታተል ላይ ይገኛል። እነዚህ ተግባራት የተጎጂዎችን ፍትሕ የማግኘት፣ እውነቱን የማወቅ፣ ሁሉ አቀፍ ማካሻ የማግኘት መብትን በማረጋገጥ ያለመደገም ዋስትናን ለመስጠት በአጠቃላይ ሰብአዊ መብቶችን መሠረት ያደረገ ተጎጂ ተኮር የሽግግር ፍትሕ እውን ለማድረግ የትግበራ የመጀመሪያ እርምጃዎች በመሆናቸው በበጀት ዓመቱ የተከናወኑ ቁልፍ እመርታዎች ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞ በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው ላይ በተመለከተው መሠረት በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ውስጥ ያልተካተቱ ዓለምአቀፍ ወንጀሎችን በተመለከተ ሀገሪቱ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ የዓለም አቀፍ ሕግን በመጣስ የሚፈጸሙ መሠረታዊ ወንጀሎች ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቷል። ይህ ረቂቅ አዋጅ ከዚህ ቀደም የዓለም አቀፍ ሕግን በመጣስ በተፈጸሙ ወንጀሎች ላይ በሽግግር ፍትሕ ዐውድ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ አስተዋጽዖ የሚያደርግ በመሆኑ እንዲሁም በሽግግር ፍትሕ ዐውድ ሳይገደብ በኢትዮጵያ በተለይም ከባድ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን የሚያስከትሉ ዓለም አቀፍ ወንጀሎችን በመቅጣትና የአጥፊዎችን ተጠያቂነት በማረጋገጥ ረገድ የነበሩ የሕግ ማዕቀፍ ክፍተቶችን በመሙላት ዘላቂ የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር ተደርጎ መቀረጹ የሚበረታታ ነው።

ኢሰመኮ እርምጃውን በተለያየ ጊዜ ያወጣቸው የሰብአዊ መብቶች ሪፖርቶች፣ መግለጫዎች እንዲሁም ውትወታዎች ውጤት አድርጎ የሚወስደው ነው።

12. ሀገራዊ ምክክር ፖለቲካዊና ማኅበራዊ አለመግባባቶችን እንዲሁም ልዩነቶችን በመፍታት በምክክር ላይ የተመሠረተ ሰላማዊ ግንኙነትን ለመፍጠር የሚረዳ በመሆኑ በሂደቱም ሆነ በውጤቱ ለሰብአዊ መብቶች መከበር አዎንታዊ ሚና የሚጫወት ነው። ሀገራዊ ምክክር ለሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ጨምሮ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላትን የሚያሳትፍ ሂደት በመሆኑ፣ በሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ የመሳተፍ መብት፣ የእኩልነት እና ከአድልዎ ነጻ የመሆን መብት፣ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ እና መረጃ የማግኘት መብትን ጨምሮ በርካታ ሰብአዊ መብቶች እና መሠረታዊ ነጻነቶች የሚተገበሩበት ሂደት ነው። ለግጭቶችና ቅራኔዎች መነሻ የሆኑ ጉዳዮች ላይ በውይይት ላይ የተመሠረተ መፍትሔ በመስጠት የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እንዳይፈጸሙ አስተዋጽዖ ያደርጋል።

13. የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከግንቦት 2016 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 2017 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ በ11 ክልሎች እና በ2 ከተማ አስተዳደሮች ሕዝባዊ ውይይት በማድረግ ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች አጀንዳ አሰባስቧል። ኢሰመኮ አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደቶቹ ላይ በመገኘት የሰብአዊ መብቶች ክትትል ያከናወነ ሲሆን ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ አርሶ አደሮች፣ የመንግሥት ሠራተኞች፣ የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች፣ ነጋዴዎች፣ መምህራን፣ የማኅበረሰብ መሪዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ ማኅበራት እንዲሁም የባሕላዊ አደረጃጀቶች ተወካዮች፣ ተጽእኖ ፈጣሪ ግለሰቦች ወዘተ. በሂደቶቹ ላይ መሳተፋቸው በሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ የመሳተፍ መብትን ለማረጋገጥ ዕድል ሰጥቷል። በሂደቱ የቡድን ሰብሳቢዎች በውይይቶች ጊዜ ያለምንም አድሎአዊ ልዩነት ለሁሉም ተሳታፊዎች አጀንዳ የሚያቀርቡበትን እኩል ዕድል መስጠታቸው፣ ምንም እንኳን በሂደቱ የተሳተፉ ሴቶች ቁጥር አጠቃላይ ተሳትፎ ከ50 በመቶ የሚያንስ ቢሆንም የምክክር ኮሚሽኑ ለቡድኖች ውይይት ጸሐፊ እና ሰብሳቢ ሲመረጥ ሴቶችን መምረጥ ግዴታ በማድረግ፣ ሴቶች ለብቻ ተወያይተው የሴቶችን አጀንዳ እንዲያቀርቡ በማድረግ እና ለዋናው ምክክር የሚወከሉ ሰዎች ሲመረጡ ከየቡድኑ 30 በመቶ የግድ ሴቶች እንዲመረጡ ኮታ በመስጠት የሴቶችን ተሳትፎ የሚያበረታታ ሥራ መሥራቱ ኢሰመኮ በክትትሉ የለያቸው መልካም እርምጃዎች ሲሆኑ ከሂደቱ ጋር የተያያዙ አሳሳቢ ጉዳዮች በዚህ ሪፖርት በሌላ ክፍል ተመላክተዋል።

14. ኢሰመኮ የውትወታ ሥራ ሲያከናውንባቸው የቆዩ የተወሰኑ ጉዳዮች አዎንታዊ ምላሽ ማግኘታቸው በበጀት ዓመቱ ከታዩ ቁልፍ እመርታዎች መካከል ሊጠቀስ የሚችል ነው። ለአብነትም ኢሰመኮ በአማራ ክልል በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ዳኞች ላይ የሚፈጸሙ የመብቶች ጥሰቶችን አስመልክቶ በተደጋጋሚ ከደረሱት አቤቱታዎች በመነሳት በክልሉ ያለው የዳኝነት ነጻነት እንዲከበር እና ለዚህም ጠንካራ የሕግ ማዕቀፍ እንዲዘጋጅ ሲያሳስብ የቆየ ሲሆን፤ በዚሁ መሠረት በ2017 በጀት ዓመት የክልሉ ምክር ቤት ለዳኞች ያለመከሰስ መብት የሕግ ከለላ የሚሰጥ የአማራ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች የማጠናከሪያ አዋጅ ማጽደቁ መልካም እርምጃ ነው።

15. ኢሰመኮ አማራ እና ኦሮሚያ ክልሎችን ጨምሮ በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች ለሚካሄዱ ግጭቶች ሰላማዊ እና ዘላቂ መፍትሔ በመስጠት የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ የሚሻሻልበትን ዐውድ ለመፍጠር የበኩላቸውን እንዲወጡ ለመንግሥት እና ለታጠቁ ቡድኖች ተደጋጋሚ

ማሳሰቢያዎችን ሲያቀርብ ቆይቷል። በዚህ ረገድ በበጀት ዓመቱ በኦሮሚያ ክልል መንግሥትና “ጃል ሰኚ ነጋሳ” በተባለ ግለሰብ በሚመሩ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) አባላት መካከል የተደረገው ስምምነት መልካም ጅማሮ ሲሆን፤ ስምምነቱን ተከትሎ በክልሉ የምዕራብ፣ ምሥራቅ፣ ሰሜን እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ እንዲሁም በአርሲ ዞኖች ያለው የጸጥታ ሁኔታ መሻሻል ማሳየቱ፤ “ወቅታዊ ጉዳይ” በሚል በተራዘመ እስር ላይ የነበሩ ሰዎች ከእስር መለቀቅ መጀመራቸው እና አዳዲስ ሕገወጥ እስራቶችም መቀነሳቸው፤ በተጨማሪም ለረዥም ጊዜ በአፋር እና ሶማሊ ክልል እንዲሁም በአፋር ክልል አውሲ ረሱ እና አማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን አጎራባች ወረዳዎች አዋሳኝ አካባቢ የሚነሳውን ግጭት በዘላቂነት ለመፍታት የክልሎቹ አመራሮች የሃይማኖት አባቶች እና የሀገር ሽማግሌዎች የተውጣጣ ኮሚቴ በማቋቋም ግጭቶችን በዘላቂነት ለመፍታት ጥረት መደረጉ ኢሰመኮ በመልካም እመርታነት የሚመለከታቸው ጉዳዮች ናቸው።

**16.** ኢሰመኮ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን በኅዳር ወር 2017 ዓ.ም. እና ታኅሣሥ 14 ቀን 2017 ዓ.ም. በሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ በሚሠሩ 4 የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ላይ እገዳ ማስተላለፉን ተከትሎ በቀረቡለት አቤቱታዎች እና ባሰባሰባቸው መረጃዎች መሠረት ታኅሣሥ 18 ቀን 2017 ዓ.ም. ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ፤ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ላይ የሚተላለፉ እገዳዎች በሲቪክ ምኅዳሩ እና በማኅበር የመደራጀት መብቶች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳይፈጥሩ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስቦ ነበር። ኢሰመኮ በዚሁ መግለጫው የድርጅቶቹን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ አደጋ ላይ በማይጥል መልኩ ባለሥልጣኑ የምርመራ ሥራዎቹን በተቻለ ፍጥነት አጠናቆ ወደ ሥራቸው የሚመለሱበትን ሁኔታ እንዲያመቻች ጥሪ ያቀረበ ሲሆን፤ ለጉዳዩ መፍትሔ ለማስገኘት ከባለሥልጣኑ እንዲሁም እገዳ ከተጣለባቸው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጋር ተደጋጋሚ ውይይቶችን አድርጓል። ይህ ጥረት ውጤት በማስገኘቱ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ላይ ተጥሎ የነበረው እገዳ ከየካቲት 24 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ ተነስቷል። ይህን መሰሉ የሰብአዊ መብቶች ጥበቃን በማስቀደም ችግሮችን በውይይት የመፍታት ሂደት ሊጎለብት የሚገባው መልካም እመርታ ነው።

**17.** ኢሰመኮ የክትትል እና ምርመራ ግኝቶቹን በመረጃ አሰባሰብ ሥነ ዘዴው መሠረት የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ምላሽ እንዲሰጡበት ሲጠይቅ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ከፌደራልና የክልል የመንግሥት አካላት ምላሽ ማግኘት ከፍተኛ ክፍተት የሚስተዋልበት ሂደት የነበረ ቢሆንም በዚህ በጀት ዓመት የክትትልና የምርመራ ግኝቶች ላይ ምላሽ የመስጠት እና የእርምት እርምጃዎችን ለመውሰድ ተነሳሽነት ያሳዩ መሆኑ የሚበረታታና ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው መልካም እመርታ ነው።

## የቁልፍ አሳሳቢ ጉዳዮች አጠቃላይ ምልከታ

**18.** በቀደሙት ዓመታት የኢሰመኮ ሪፖርቶች እንደተመላከተው ሁሉ ከሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. እስከ ሰኔ ወር 2017 ዓ.ም. ባለው የሪፖርት ዘመንም በአጠቃላይ በሀገራዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ በማሳደር ረገድ ቀዳሚውን ስፍራ ይዞ የቀጠለው የትጥቅ ግጭቶች እንዲሁም የጸጥታ ችግሮች ጉዳይ ነው። የፌዴራል መንግሥት እና የክልል መንግሥታት የጸጥታ ኃይሎች በአማራ ክልል ከሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ቡድኖች (በተለምዶ “ፋኖ”) እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ከኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”)

ታጣቂዎች ጋር የሚያካሂዱት የትጥቅ ግጭት በሪፖርት ዘመኑም ቀጥሏል። በዚህም ምክንያት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በየዘርፉ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች የተመዘገቡ ሲሆን በግጭቶች ዐውድ ውስጥ እና ውጪ የሚፈጸሙ ጥቃቶች በተለይም በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደኅንነት፣ የነጻነት እና ሌሎች የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ላይ ከሚያደርሱት ጉዳት በተጨማሪ የመኖሪያ እና የንግድ ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የጤና አገልግሎት ማእከላት እንዲሁም ሌሎች አገልግሎት መስጫ ተቋማት እና መሠረተ ልማቶች ውድመት የሚደርስባቸው በመሆኑ በማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ዘርፍም በርካታ ጥሰቶች ተመዝግበዋል። በሁለቱ ክልሎች በተራዘመ የትጥቅ ግጭት ዐውድ ውስጥ በሚፈጸሙ ጥቃቶች በበርካታ ሰዎች ላይ ከሕግ ውጭ ግድያ መፈጸሙን፤ በበርካታ ሰዎች ሕይወት፣ አካል እና ንብረት ላይ ጉዳት መድረሱን ኢሰመኮ በበጀት ዓመቱ ባወጣቸው የሩብ ዓመት ሪፖርቶችና ሌሎች መግለጫዎች አመላክቶ ግጭቶች በውይይት እንዲፈቱ ጥሪ ሲያቀርብ የቆየ ቢሆንም ችግሩ አሁንም መቀጠሉ አሳሳቢ ነው።

19. የትጥቅ ግጭት ከሚካሄድባቸው የአማራ እና የኦሮሚያ ክልሎች በተጨማሪ በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎችም አልፎ አልፎ በሚያገረሹ ግጭቶችና የጸጥታ መደፍረስ ሁኔታዎች ውስጥ አልፈዋል። ከእነዚህ መካከል በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፣ በጉራጌ ዞን፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ በተለይም ከጥቅምት 2 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ የተከሰተውን የጸጥታ መደፍረስ ተከትሎ ከጥቅምት 3 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ ወልቂጤ ከተማ እና ዙሪያው "በኮማንድ ፖስት" እንዲተዳደሩ ተወስኖ የእንቅስቃሴ ሰዓት ገደብ ታውጆ የነበረ ሲሆን ከግንቦት 22 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ እንዲራዘም ተደርጓል። ኢሰመኮ በእነዚህ "በኮማንድ ፖስት" በሚተዳደሩ የማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል አካባቢዎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችና ሥጋቶችን በተመለከተ በርካታ አቤቱታዎችን ሲቀበልና ሲመረምር ቆይቷል። ከዚህ በተጨማሪ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ሳይታወጅ በመብቶች ላይ ገደብ የማድረግ ክስተቶችም ተስተውለዋል። የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ሳይታወጅ የእንቅስቃሴ ነጻነትን ጨምሮ ሌሎችም ሰብአዊ መብቶች የሚታገዱበት አሠራር በብሔራዊም ሆነ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ማዕቀፎች መሠረት ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ ሁኔታው በሰዎች በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደኅንነት፣ ነጻነት እንዲሁም የንብረትና ሌሎች መሠረታዊ መብቶች ላይ ጥሰቶች የሚፈጸሙበትን በር ከፍቷል። አሠራሩ በሌሎችም የሀገሪቱ አካባቢዎች ተግባራዊ የሚደረግበት ሁኔታ ያለ ሲሆን፤ ለምሳሌ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ኧሌ ዞን እና ጋርዱላ ዞን "በኮማንድ ፖስት የተጠረጠራችሁ ናችሁ" ተብለው በቁጥጥር ሥር የዋሉ ሰዎች አካልን ነጻ የማውጣት አቤቱታ ሲያቀርቡ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ባልታወጀበት ስለአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ የሚደነግገውን የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 93 በመጥቀስ አቤቱታቸውን ውድቅ ማድረጋቸውን ኢሰመኮ አረጋግጧል።

20. በፕሪቶሪያ የተፈረመውን የዘላቂ ተኩስ አቁምና የሰላም ስምምነት ተከትሎ በትግራይ ክልል አንጻራዊ ሰላምና መረጋጋት መስፈኑ የክልሉን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ለማሻሻል ዕድል መስጠቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በ2017 በጀት ዓመት በስምምነቱ የተሟላ ተፈጻሚነት ላይ ተግዳሮት የሚፈጥሩ እና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች አደጋዎችንና ሥጋቶችን የፈጠሩ ክስተቶች ታይተዋል። በተለይም በትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ውስጥ እና ውጪ በሚገኙ እና በአሁኑ ወቅት በምርጫ ቦርድ ከምዝገባ መሰረዙ የተገለጸው የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) መሪዎች መሆናቸውን በሚገልጹ አካላት መካከል ከተከሰተው አለመግባባት ጋር ተያይዞ በክልሉ ነዋሪዎች ሰብአዊ መብቶች ላይ አደጋ እና ሥጋት

መፈጠሩን ኢሰመኮ [በመጋቢት ወር 2017 ዓ.ም. ባወጣው መግለጫ] ማስታወቁ የሚታወስ ነው። በክልሉ በዚህ እና ሕወሓት ከፖለቲካ ፓርቲነት ምዝገባ ከመሰረዙ ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ አንዳንድ ሁኔታዎችና አዝማሚያዎች በክልሉ አጠቃላይ ሰላም እና የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ የፈጠሩት ሥጋት አሳሳቢ ነው።

21. በአሁኑ ወቅት ግጭቶች ከሚካሄዱባቸው የአማራ እና ኦሮሚያ ክልሎች እንዲሁም ጥቃቶችና የጸጥታ ችግሮች በተደጋጋሚ ከሚያገረሹባቸው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ማእከላዊ ኢትዮጵያ እና ደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ባሻገር ከዚህ ቀደም ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ በትጥቅ ግጭት ውስጥ ባለፉ የአፋር፣ የአማራ እና የትግራይ ክልል አካባቢዎች የመልሶ ግንባታና ማቋቋም ሥራ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት እየተከናወነ አለመሆኑም አሳሳቢ ነው። ይህም የትምህርት እና የጤና አገልግሎቶችን ጨምሮ በበርካታ የሰብአዊ መብቶች ዘርፎች ያሉ ችግሮች ባሉበት ወይም ተባብሰው እንዲቀጥሉ የሚያደርግ ሲሆን በተለይም ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እንዲሁም ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ጉዳትና ሥጋት የሚያባብስ ነው።

22. ከጸጥታ ችግሮች በተጨማሪ ድርቅ፣ ጎርፍ እና የመሬት መንቀጥቀጥን የመሳሰሉ የተፈጥሮ አደጋዎች በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ለሰዎች ሞት፣ የአካል ጉዳት፣ መፈናቀል እንዲሁም የንብረት ውድመት ምክንያት ሆነዋል። ለምሳሌ በመስከረም ወር 2017 ዓ.ም. በበርካታ ክልሎች የተከሰተው ከባድ ጎርፍ በተለይም በአፋር፣ ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ጋምቤላ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ እና ሶማሊ ክልሎች ከፍተኛ የንብረት ውድመት እና መፈናቀልን አስከትሏል። የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦቶች በሚፈለገው መጠን አለመቅረብ፣ መሠረታዊ የሆኑ የምግብ ፍጆታዎችን ጨምሮ የሸቀጦች ዋጋ መናር እና የኑሮ ውድነት ለሰብአዊ መብቶች ሁኔታው መባባስ አስተዋጽዖ አድርገዋል። በኢትዮጵያ አጠቃላይ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ጉልህ አሉታዊ ተጽእኖ እያደረሱ ከቀጠሉ ሌሎች አሳሳቢ ጉዳዮች መካከል ተደጋጋሚ የውትወታ ሥራዎች ቢደረግባቸውም እስካሁን እልባት ያልተሰጣቸው በተለይም ለመብቶች ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች መብቶችን ጥበቃ የሚመለከቱ የሕግና ተቋም ማዕቀፍ ክፍተቶች ይጠቀሳሉ። ለምሳሌ ሠራተኞች ፍትሐዊ፣ አመቺና ጤናማ የሥራ ሁኔታ በማግኘት ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን በበቂ ሁኔታ ለማኖር የሚያስችል ክፍያ የማግኘት መብትን ከማረጋገጥ አንጻር በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሠረት የደመወዝ ቦርድን የሚያቋቁም እና ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል ሥርዓትን የሚዘረጋ ሕግ አለመውጣቱ፤ ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በቅድመ መፈናቀል፣ በመፈናቀል እንዲሁም በድኅረ-መፈናቀል ወቅት ተገቢውን ጥበቃ እና ድጋፍ በማድረግ ረገድ የሕግና የመዋቅር ክፍተቶችን መፍትሔ ሊሰጥ የሚችለውን የካምፓላ ስምምነት ማስፈጸሚያ ብሔራዊ ረቂቅ አዋጅ የማዘጋጀትና ማጽደቅ ሂደት መንተቱ፤ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ያዘጋጀው የአካል ጉዳተኞች ረቂቅ አዋጅ ኢሰመኮና የአካል ጉዳተኞች ማኅበራትን ጨምሮ ሌሎች ባለድርሻ አካላት በሰጧቸው አስተያየቶች መሠረት ዳብሮ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አለመቅረቡ አሁንም ትኩረት የሚሹ ቁልፍ ጉዳዮች ናቸው።

23. በኢትዮጵያ በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚነሱ ጥያቄዎችን ፈጣን እና በውይይት ላይ የተመሠረተ ምላሽ በመስጠት ረገድ ክፍተቶች መኖራቸው በበጀት ዓመቱም የቀጠለ አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ለምሳሌ ከጤና ባለሙያዎች የደመወዝ፣ ጥቅማጥቅም፣ የሙያ ዕድገት ዕድል እንዲሁም ምቹ የሥራ ቦታ እና ነጻነት ጥያቄዎች በወቅቱ አለመመለስ ጋር ተያይዞ

የተከሰተው የጤና ባለሙያዎች የሥራ ማቆም አድማ በጤና መብት ዘርፍ ላይ ጉዳት በማድረስ ላይ ይገኛል። ሚያዝያ 3 ቀን 2017 ዓ.ም. ባለ 12 ነጥብ ጥያቄዎችን ለጤና ሚኒስቴር አቅርበው በጥያቄያችን መሠረት በ30 ቀናት ውስጥ ምላሽ አልተሰጠንም ያሉ የሕክምና ባለሙያዎች ከግንቦት 5 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ ለአንድ ወር ገደማ ከፊልና ሙሉ የሥራ ማቆም አድማ አድርገዋል። በዚህ የተነሳ በአንዳንድ የሕክምና ተቋማት በጽኑ ሕሙማን ማእከል የሚገኙትን ጨምሮ ታማሚዎች በሐኪሞች እጥረት ተገቢውን ሕክምና ማግኘት አለመቻላቸውን፤ ከክልል ከተሞች ረጅም ቀጠሮ ጠብቀው ለሕክምና የመጡ ታካሚዎች ለእንግልት የተዳረጉ መሆኑን፤ በባለሙያዎች እጥረት ምክንያት አንዳንድ የሕክምና ተቋማት ባለሙያዎችን ለረጅም ፈረቃዎች እንዲሠሩ ለመመደብ የተገደዱ መሆኑን እንዲሁም ታካሚዎች ሕክምና ለማግኘት ለረጅም ሰዓታት ለመጠበቅ መገደዳቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል። ኢሰመኮ ጉዳዩን አስመልክቶ [ግንቦት 13 ቀን 2017 ዓ.ም. ባወጣው መግለጫ] የሕክምና ባለሙያዎች ያቀረቧቸውን ጥያቄዎች መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ ግልጽ እና አሳታፊ በሆነ መንገድ መፍትሔ የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዲያመቻች እንዲሁም የሕክምና ባለሙያዎች የኅብረተሰቡን የጤና እና በሕይወት የመኖር መብቶች አደጋ ላይ በማይጥል መልኩ ጥያቄዎቻቸውን እንዲያቀርቡ ጥሪ አስተላልፎ የነበረ ሲሆን፣ ችግሩ ከዚህ የከፋ የሰብአዊ መብቶች ጉዳት ሳያደርስ በዘላቂነት እንዲፈታ ለማድረግ የተጀመሩ እርምጃዎችና ጥረቶችን ማጠናከር አስፈላጊ ነው።

24. በሪፖርቱ የተለያዩ ክፍሎች በዝርዝር እንደተመላከተው በሰብአዊ መብቶች ላይ አሉታዊ አንድምታ ያላቸው አዳዲስ ሕጎች እየወጡ፣ ነባር ሕጎችም ለውጦችና ማሻሻያዎች እየተደረጉባቸው መሆኑ በበጀት ዓመቱ የተስተዋለ አሳሳቢ ሁኔታ ነው። የተወሰኑት የሕግ ማሻሻያዎች በይዘታቸው ከጥቂት ዓመታት በፊት የተከናወኑ ሰብአዊ መብቶች ተኮር የሕግ ማሻሻያዎችን ወደኋላ እንዳይመልሱ ሥጋት የፈጠሩ ሲሆኑ፤ ተገቢው ውይይት ሳይደረግባቸው እና የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ግብአትን ትርጉም ባለው መልኩ ባላካተተ ሁኔታ የሚዘጋጁ እና የሚጸድቁ ሕጎች መኖራቸውን ኢሰመኮ ተገንዝቧል። ይህ ዓይነት የሕግ አወጣጥ ሂደት የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ፣ መስፋፋት እና መከበር ላይ አሉታዊ ተጽእኖ በመፍጠር ለጥሰት በር ከፋች እንዳይሆን ሕጎች ተገቢው ጥልቅ ጥናት ተደርጎባቸው የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን ትርጉም ያለው ተሳትፎ ባረጋገጠ አግባብ ዳብረውና ውይይት ተደርጎባቸው ሊዘጋጁ እና ሊጸድቁ ይገባል።

# በሕይወት የመኖር መብት



ዝርዝር የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች

# ዝርዝር የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች

## ሀ) በሕይወት የመኖር መብት

25. በ2017 በጀት ዓመት ውስጥ በሕይወት የመኖር መብት ሁኔታ አሳሳቢ ሆኖ መቀጠሉን የሚያሳዩ በርካታ ክስተቶች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ተስተውለዋል። በግጭት ዐውድ ውስጥ በቆዩ ወይም በግጭት ውስጥ በሚገኙ አካባቢዎች በመንግሥት ኃይሎች፣ በየአካባቢው በሚንቀሳቀሱ የታጠቁ ቡድኖች፣ ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች እንዲሁም በእርስ በእርስ ግጭቶች በሰዎች ላይ የሞት እና የአካል ጉዳት ደርሷል።
26. በአማራ ክልል በአብዛኛው አካባቢዎች በመንግሥት ኃይሎች እና በታጣቂ ቡድኖች (በተለምዶ "ፋኖ") መካከል ከ2015 ዓ.ም. መጨረሻ ወራት ጀምሮ በቀጠለው የተራዘመ የትጥቅ ግጭት ዐውድ ውስጥ በተፋላሚ ወገኖች የሚፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ቀጥለዋል። ከእነዚህም መካከል በሰዎች ላይ ከሕግ ውጭ ግድያ መፈጸሙን እንዲሁም በሚፈጸሙ ጥቃቶች በሰዎች ሕይወት፣ አካል እና ንብረት ላይ ጉዳት መድረሱን ኢሰመኮ በተለያዩ ጊዜያት ይፋ ባደረጋቸው *ሪፖርቶችና* *መግለጫዎች* አመላክቷል።
27. በክልሉ በተራዘመ የትጥቅ ግጭት ውስጥ በቆዩ አካባቢዎች በመንግሥት ኃይሎች እና በታጣቂ ቡድኑ መካከል በተደረጉ የተኩስ ልውውጦች የግጭቱ አካል ያልነበሩ ሰላማዊ ሰዎች ለሞት እና ለአካል ጉዳት ተዳርገዋል። በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች በትጥቅ የታገዘ ግጭት ሲካሄድባቸው በቆዩ ቦታዎች የመንግሥት ኃይሎች በሚቆጣጠሩበት ወቅት "ፋኖን ትደግፋላችሁ፣ ትቀልባላችሁ" ያሏቸው ሰዎች ላይ ግድያ የፈጸሙ ሲሆን፣ መኖሪያ ቤቶችን በእሳት በማቃጠል ጭምር የተፈጸሙ ጥቃቶች ተመዝግበዋል።
28. በክልሉ የሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") አባላት በበቀል ስሜት በወሰዷቸው እርምጃዎች እና "ለሀገር መከላከያ ሰራዊት መንገድ አሳይታችኋል፤ ሰዎችን ጠቁማችሁ አስይዛችኋል" በማለት በሰዎች ላይ ግድያ ፈጽመዋል። እንዲሁም የመንግሥት ሠራተኞች ወደ ሥራቸው እንዳይመለሱ ማስፈራራታቸውን፣ ወደ ሥራቸው የተመለሱ ሠራተኞች ላይ ግድያ መፈጸማቸውን፣ በተለያዩ አካባቢዎች በመግባት ዘረፋ ማድረጋቸውን፣ በእሳት በማቃጠል ከፍተኛ የንብረት ውድመት ማድረሳቸውን እና ነዋሪዎችን ማፈናቀላቸውን ኢሰመኮ ባከናወናቸው ምርመራዎች አረጋግጧል።
29. በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በተከሰቱ ግጭቶች፣ ማንነታቸው ባልታወቁ ኃይሎች እንዲሁም በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") በተወሰዱ እርምጃዎች በሲቪል ሰዎች ላይ የሞት፣ እገታ፣ የአካል ጉዳት እና የንብረት ውድመት ደርሷል። በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በምሥራቅ ጉራጌ ዞን መስቃን ወረዳ እና በማረቆ ልዩ ወረዳ አዋሳኝ ቀበሌዎች በአካባቢው የሚንቀሳቀሱ የታጠቁ ግለሰቦች/ቡድኖች በየጊዜው በሚያደርሱት ጥቃት በነዋሪዎች ላይ ሞት እና የአካል ጉዳት ማስከተሉን ቀጥሏል። በጋምቤላ ክልል በአኝዋ እና ኑዌር ብሔረሰብ ዞን የተለያዩ አካባቢዎች መነሻቸውን ከደቡብ ሱዳን ያደረጉ የሙርሌ ታጣቂዎች ግድያ፣ እገታ እና ዝርፊያ የሚፈጽሙ ሲሆን ሕፃናትንና ሴቶችን ጨምሮ በርካታ ሰዎች ጉዳት እንዲደርስባቸው እና ማኅበረሰቡ ተረጋግቶ መደበኛ ሕይወቱን እንዳይመራ አድርጓል።
30. በኦሮሚያ ክልልም በተለያዩ አካባቢዎች በመንግሥት ኃይሎችና በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") መካከል ከሚደረገው የትጥቅ ግጭት ጋር በተያያዘ በሰዎች ላይ

የሚፈጸሙ ጥቃቶች ቀጥለዋል፡፡ በተለያዩ ምክያቶች በሰዎች ላይ የሞት፣ የአካል እና የንብረት ጉዳት ደርሷል፡፡

31. የመንግሥት ኃይሎች በአንዳንድ አካባቢዎች "ለኦነግ ሸኔ ድጋፍ ታደርጋላችሁ፤ መንገድ ታሳያላችሁ" በሚል በወሰዱት እርምጃ በሰዎች ላይ የሞት ጉዳት ደርሷል፡፡ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") ታጣቂዎች በተለያየ ምክንያት በተወሰዱ እርምጃዎች በሰዎች ላይ የሞት፣ እገታ፣ የአካል ጉዳት እና የንብረት ውድመት ደርሷል፡፡ ከተለያዩ ከተሞች ወደ አዲስ አበባ ከተማ የሚጓዙ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶብሶችን በማስቆም የሚፈጽሟቸው እገታዎች በበጀት ዓመቱ የቀጠሉ ሲሆን፤ አጋቾች ከፍተኛ የማስለቀቂያ ገንዘብ ክፍያ በመጠየቅ፤ ገንዘብ ለመክፈል ባልቻሉ ታጋቾች ላይ ግድያን ጨምሮ በርካታ ጥቃቶችን ፈጽመዋል፡፡

32. በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በተለያየ ጊዜ በተነሱ ግጭቶች ሳቢያ፣ ማንነታቸው ባልታወቀ የታጠቁ ኃይሎች፣ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") እንዲሁም ከኬንያ ወደ ኢትዮጵያ ድንበር ዘልቀው በገቡ ታጣቂዎች ሰዎች ለሞት ተዳርገዋል፡፡

33. እነዚህ ከላይ የቀረቡት ከሰኔ 2016 ዓ.ም. እስከ ሰኔ 2017 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ በሕይወት የመኖር መብት ሁኔታን በጥቅሉ ለማሳየት የተቀመጡ በመሆናቸው በበጀት ዓመቱ የተፈጠሩ በሕይወት ከመኖር መብት ጋር የተያያዙ ዝርዝር ክስተቶች ከዚህ በታች ተካተዋል፡፡

### አፋር ክልል

34. በአፋር ክልል በተለይም ከሰሜኑ ጦርነት በፕሪቶሪያ ስምምነት መጠናቀቅ በኋላ አንጻራዊ ሰላም የሰፈነ መሆኑ እንዲሁም ክልሉ ከትግራይ እና ከሶማሊ ክልሎች በሚዋሰንባቸው አካባቢዎች ይከሰቱ የነበሩ ግጭቶች መቆማቸው በአዎንታዊነት የሚጠቀሱ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ሆኖም በሕይወት ከመኖር መብት ጋር የተያያዙ ጥሰቶችና ሥጋቶች በ2017 በጀት ዓመትም ተስተውለዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል ጥር 12 ቀን 2017 ዓ.ም. በአፋር እና አርጎባ ብሔር አባላት መካከል በተፈጠረ ግጭት 2 ሰዎች የሞቱ ሲሆን፣ ግጭቱ በመንግሥት እና ሕዝብ ጥረት እንዲቆም ተደርጎ አጥፊዎችም ለሕግ ቀርበው ተጠያቂነት የማረጋገጥ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

### አማራ ክልል

35. በአማራ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች በመንግሥት ኃይሎች እና በታጣቂ ቡድኖች (በተለምዶ "ፋኖ") መካከል ከ2015 ዓ.ም. መጨረሻ ወራት ጀምሮ በቀጠለው የተራዘመ የትጥቅ ግጭት ዐውድ ውስጥ በተፋላሚ ወገኖች የሚፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ቀጥለዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል በሰዎች ላይ ከሕግ ውጭ ግድያ መፈጸሙን እንዲሁም ሰዎች ሕይወት፣ አካል እና በንብረት ላይ ጉዳት መድረሱን ኢሰመኮ በተለያዩ ጊዜያት ይፋ ባደረጋቸው ሪፖርቶችና መግለጫዎች አመላክቷል፡፡ በእነዚህ ሪፖርቶች የተካተቱ ጉዳዮች በተፋላሚ ወገኖች ሲቪል ሰዎችን ከታጠቁ ኃይሎች ያለዩ ጥቃቶች እና ከሕግ ውጭ የሚፈጸሙ ግድያዎች መቀጠላቸውን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

36. በክልሉ በሰሜን ሸዋ ዞን በኤፍራታና ግድም፣ ቀወት፣ ጣርማ በር፣ መንዝ ማማ ወረዳዎች፤ በምዕራብ ጎንደር ቋራ ወረዳ፤ በአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ትሊሊ ከተማ፣ ፋግታ ለኮማ ወረዳ፤ በምሥራቅ ጎጃም ዞን ሁለት እጁ እነብሴ ወረዳ፣ እነብሴ ሳር ምድር፣ ስናን፣ ቢቡኝ፣

ደባይ ጠላትግን፣ እናርጅ እናውጋ፣ ጎዛምን ወረዳዎች፣ ደብረ ወርቅ ከተማ፤ በሰሜን ጎጃም ዞን ሰሜን ሜጫ ወረዳ፣ አዴት ከተማ፣ ባሕር ዳር ዙሪያ ወረዳ፣ ደቡብ ሜጫ ወረዳ፤ ባሕር ዳር ከተማ፤ በምዕራብ ጎጃም ዞን ጅጋ ከተማ፣ ቋሪት ወረዳ፣ ደጋ ዳሞት ወረዳ፤ ሰሜን ወሎ ዞን ውርጌሳ ከተማ አካባቢ፣ ራያ ቆቦ ከተማ፣ ጉባላፍቱ ወረዳ፣ ቃሊም ከተማ፣ ላስታ ወረዳ ብልባላ ከተማ፣ ዳውንት ወረዳ ኩርባ ከተማ፤ በኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን ከሚሴ ከተማ፤ ደቡብ ጎንደር ዞን እስቴ፣ አንዳቤት፣ ፎገራ፣ ሊቦ ከምከም፣ ወረዳዎች፣ በጉና በየምድር ወረዳ ክምር ዴንጋይ ከተማ፤ ማእከላዊ ጎንደር ዞን ጎንደር ዙሪያ ወረዳ፣ አለፋ ወረዳ ሻውራ ከተማ፤ ጎንደር ከተማ፤ ሰሜን ጎንደር ዞን ደባርቅ ከተማ፣ ዳባት ከተማ እንዲሁም በሌሎች ግጭት በተካሄደባቸው አካባቢዎች በሰዎች ላይ የሞት፣ የአካል እና የንብረት ጉዳት ደርሷል።

37. የመንግሥት ኃይሎች በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች የሚንቀሳቀሰውን የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") "ትደግፋላችሁ፣ ትቀልባላችሁ" በማለት በሲቪል ሰዎች ላይ ግድያ መፈጸማቸውን ኢሰመኮ አረጋግጧል። እንዲሁም በክልሉ የሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን አባላት በበቀል ስሜት በወሰዷቸው እርምጃዎች እና "ለሀገር መከላከያ ሰራዊት መንገድ አሳይታችኋል፤ ሰዎችን ጠቁማችሁ አስይዛችኋል" በማለት በሰዎች ላይ ግድያ ፈጽመዋል።
38. በአዊ ብሔረሰብ ዞን፣ ቲሊሊ ከተማ በ8 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ወንጀላ ቀበሌ ሰኔ 5 ለሰኔ 6 ቀን 2016 ዓ.ም. አጥቢያ ሌሊት ላይ በመንግሥት ኃይሎች እና በክልሉ በሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") አባላት መካከል የተደረገውን የተኩስ ልውውጥ ተከትሎ የመንግሥት ኃይሎች በ 5 ሰዎች ላይ ግድያ ፈጽመዋል።
39. በበጀት ዓመቱ በመንግሥት ኃይሎችና በክልሉ በሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") መካከል በተለያዩ ቦታዎች በተለያየ ጊዜ በተደረገ የትጥቅ ግጭት ሰዎች ለሞት ለአካል ጉዳት እና ለንብረት ውድመት ተዳርገዋል፤ በቁጥጥር ሥር የነበሩ የሁለቱም ተፋላሚ ወገኖች አባላትም ተገድለዋል። በመንግሥት ኃይሎችና በክልሉ በሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") አባላት መካከል ሰኔ 17 ቀን 2016 ዓ.ም. ሰሜን ጎጃም ዞን፣ አዴት ከተማ ላይ በተካሄደ የትጥቅ ግጭት ጋር በተያያዘ በግጭቱ ተሳትፎ የሌላቸው ሰዎች የተገደሉ ሲሆን በመንግሥት ኃይሎች ከ3 ወር በፊት ተይዘው ካምፕ ውስጥ ታስረው የነበሩ 3 የ"ፋኖ" አባላት ተገለዋል። በተመሳሳይ በክልሉ የሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") አባላት በቁጥጥር ሥር አውለዋቸው የነበሩትን ቢያንስ 8 የሚሊሻና የአድማ ብተና አባላት ሰኔ 19 ቀን 2016 ዓ.ም. ተገድለዋል።
40. በሰሜን ሸዋ ዞን፣ ጣርማ በር ወረዳ፣ ከደብረ ሲና ከተማ ወጣ ብላ በምትገኝ "ሾላ ሜዳ" በተባለች ቦታ ሰኔ 19 ቀን 2016 ዓ.ም. የመንግሥት ኃይሎች በክልሉ የሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") አባላት መካከል በተካሄደ ግጭት በተለያዩ ምክንያቶች በ15 ሰዎች ላይ ግድያ ተፈጽሟል።
41. ሰኔ 25 ቀን 2016 ዓ.ም. ሰሜን ወሎ ዞን፣ ውርጌሳ ከተማ አካባቢ በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች እና በክልሉ በሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") አባላት መካከል የትጥቅ ግጭት መካሄዱን ተከትሎ በአካባቢው ከነበረው የመንግሥት ኃይል የተተኮሰ የጦር መሣሪያ መኖሪያ ቤቶች ላይ ወድቆ የ1 ሰው ሞት እና 5 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል።
42. የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ዋና አስተዳዳሪ የሆኑት አህመድ አሊ ሰኔ 28 ቀን 2016 ዓ.ም. ከቀኑ 7:00 ሰዓት አካባቢ ማንነታቸው ባልታወቁ ታጣቂዎች ተገድለዋል።

43. ሰኔ 30 ቀን 2016 ዓ.ም. የመንግሥት ኃይሎች በሰሜን ጎጃም ዞን፣ ሰሜን ሜጫ ወረዳ፣ ወተት አባይ ቀበሌ 1 ሰው መግደላቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡
44. በምዕራብ ጎንደር ዞን፣ ቋራ ወረዳ ከግንቦት ወር መጀመሪያ 2016 ዓ.ም. ጀምሮ የአማራ እና የአገው ብሔረሰብ ተወላጆች በሚኖሩባቸው ቀበሌዎች ማለትም ይካዎ፣ አብተጋሆ፣ አጋም ውሃ፣ ገለሎ፣ ባምባ ውሃ እና ሌሎች ቀበሌዎች ላይ በክልሉ የሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") አባላት እና በመንግሥት ኃይሎች መካከል ግጭት ተቀስቅሶ በአካባቢው የሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") በአብተጋሆ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑ 23 ሲቪል ሰዎችን አፍነው ወደ ቴዎድሮስ ከተማ በመውሰድ የተወሰኑት ሲመለሱ ሌሎችን ገድለዋል፡፡ ይህ ግጭት ተባብሶና ወደ ማኅበረሰብ ግጭት ተሸጋግሮ ሐምሌ 3 ቀን 2016 ዓ.ም. ባይካዎ እና አጋም ውሃ ቀበሌዎች ከአገው እና አማራ ብሔር ተወላጆች ብዛታቸው ያልታወቀ ሰዎች ሕይወት አልፏል፡፡ በዚሁ ግጭት ቤቶች እና በማሳ ላይ የሚገኝ ሰብል ተቃጥሏል፡፡
45. ሐምሌ 5 ቀን 2016 ዓ.ም. በሰሜን ወሎ ዞን፣ ጉባ ላፍቶ ወረዳ፣ ውድመን ቀበሌ ላይ በመንግሥት ኃይሎች እና በክልሉ በሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") አባላት መካከል የተጥቀ ግጭት መካሄዱን ተከትሎ በአካባቢው ከነበረው የመንግሥት ኃይል በተተኮሰ የጦር መሣሪያ 7 ሰዎች ተገድለዋል፡፡
46. ሐምሌ 15 ቀን 2016 ዓ.ም. በአማራ ክልል ሰሜን ጎጃም ዞን ደቡብ ሜጫ ወረዳ በሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ 'ፋኖ') 17 የአካባቢው ነዋሪዎችን ይዘው በመውሰድ በማግስቱ ሐምሌ 16 ቀን 2016 ዓ.ም. ከእነዚህ ውስጥ 4 ሰዎች ተገድለው አስከሬናቸው ተጥሎ ሲገኙ የቀሩት ሰዎች ደግሞ ገንዘብ በመክፈል ከቀናት በኋላ ተለቀዋል፡፡
47. ሐምሌ 15 ቀን 2016 ዓ.ም. አክሽን ፎር ሶሻል ዴቨሎፕመንት ኤንድ ኢንቫሮመንታል ፕሮቴክሽን (Action for Social Development and Environmental Protection Organization (ASDEPO) የተባለ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት 4 ሠራተኞች በሰሜን ወሎ ዞን ዳውንት ወረዳ በሥራ ላይ በነበሩበት ወቅት በታጠቁ ሰዎች በሌሊት ታፍነው ከተወሰዱ በኋላ 3 ታጋቾች ሲለቀቁ 1 ሠራተኛ ግን ነሐሴ 3 ቀን 2016 በጥይት ተገድሎ ተገኝቷል፡፡
48. በምሥራቅ ጎጃም ዞን፣ እነብሴ ሳር ምድር ወረዳ፣ ዶማ በተባለ አካባቢ የነበረውን ግጭት ተከትሎ ሐምሌ 19 ቀን 2016 ዓ.ም. 1 የ"ፋኖ" ታጣቂ አባል ቆስሎ 2 ወንድሞቹ ሊያነሱት ሲሄዱ 3ቱም ሰዎች በመንግሥት ኃይሎች መገደላቸው ኢሰመኮ ማረጋገጥ ችሏል፡፡
49. ነሐሴ 6 ቀን 2016 ዓ.ም. በምዕራብ ጎጃም ዞን፣ ቋሪት ወረዳ፣ ገነት አቦ ከተማ በመንግሥት ኃይሎች እና በአካባቢው በሚንቀሳቀሱ ታጣቂዎች (በተለምዶ ፋኖ) መካከል ሲካሄድ የዋለው ውጊያ ተከትሎ የመንግሥት ኃይሎች በ1 ሰው ላይ ግድያ እና በ2 ሴቶች ላይ የአካል ጉዳት አድርሰዋል፡፡
50. በሰሜን ጎጃም ዞን፣ ሰሜን ሜጫ ወረዳ፣ ወተት ዓባይ ቀበሌና በአካባቢው በመንግሥት ኃይሎች እና በክልሉ በሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") አባላት መካከል ከነሐሴ 6 እስከ 7 ቀን 2016 ዓ.ም. ከተካሄደ ውጊያ ተከትሎ በመንግሥት ኃይሎች 7 ሰዎች ተገድለዋል፡፡ በተጨማሪ ነሐሴ 13 ቀን 2016 ዓ.ም. ከንጋቱ 11፡30 ሰዓት አካባቢ 1 ሰው በመንግሥት ኃይሎች እንደተገደለ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
51. ነሐሴ 8 ቀን 2016 ዓ.ም. በደቡብ ጎንደር ዞን፣ እስቴ እና አንዳ ቤት ወረዳ አስተዳደር አመራሮች ለስብሰባ ወደ ደብረ ታቦር ከተማ በጉዞ ላይ እንዳሉ በክልሉ የሚንቀሳቀሰው

የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") አባላት ባደረሱት ጥቃት 1 አመራረ ላይ የሞትና 3 አመራሮች ላይ የመቁሰል አደጋ እንደደረሰባቸው ለመረዳት ተችሏል።

52. በባሕር ዳር ከተማ፣ አባይ ማዶ ዘንዘልማ በሚባለው አካባቢ ሰሳ በረት በሚባል ቦታ 4 ወጣቶች እና አሽራፍ በሚባል አካባቢ 2 ወጣቶች በድምሩ 6 ወጣቶች ለጊዜው ባልታወቁ አካላት በጥይት እና በስለት ተገድለው ነሐሴ 12 ቀን 2016 ዓ.ም. ተገኝተዋል።
53. ነሐሴ 14 ቀን 2016 ዓ.ም. በባሕር ዳር ከተማ፣ በተለምዶ ቀበሌ 5 በግ ተራ አካባቢ የመንግሥት ኃይሎች በከፈቱት ተኩስ በ2 ሰዎች ላይ የሞት እና 10 የአካል ጉዳት እንደደረሰ ለማረጋገጥ ተችሏል።
54. ነሐሴ 15 ቀን 2016 ዓ.ም. በክልሉ በሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") አባላት እና በመንግሥት ኃይሎች መካከል የነበረውን የትጥቅ ግጭት ተከትሎ በሰሜን ወሎ ዞን፣ ራያ ቆቦ ከተማ ዙሪያ የቆቦ ከተማ እና የዋጃ ከተማ ነዋሪ የሆኑ 4 ወጣቶች ባልታወቁ ሰዎች ተገድለዋል።
55. በማእከላዊ ጎንደር ዞን፣ አለፋ ወረዳ፣ ሻውራ ከተማ ነሐሴ 16 ቀን 2016 ዓ.ም. ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 7፡30 ሰዓት ድረስ በክልሉ በሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") አባላት እና በመንግሥት ኃይሎች መካከል በተደረገው ውጊያ ከ10 በላይ ሲቪል ሰዎች ከየትኛው ወገን እንደተተኮሰ ባልታወቀ ተባራሪ ጥይት፤ እንዲሁም ግጭቱን ተከትሎ በመንግሥት ኃይሎች 3 ሰዎች ተገድለዋል።
56. ነሐሴ 22 ቀን 2016 ዓ.ም. ከምሽቱ 3፡00 ሰዓት ላይ በአማራ ክልል፣ ጎንደር ከተማ፣ ማራኪ ክፍለ ከተማ፣ ቀበሌ 16 ልደታ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ማንነታቸው ያልታወቀ የታጠቁ ቡድኖች የግለሰብ መኖሪያ ቤት በኃይል በመግባት ሁለት ሰዎችን በጥይት ገድለዋል።
57. ነሐሴ 24 ቀን 2016 ዓ.ም. በአማራ ክልል፣ ጎንደር ከተማ፣ ቀበሌ 03 ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ላይ ሕፃን ኖላዊት ዘገየ የተባለች የ2 ዓመት ታዳጊ በወላጆቿ መኖሪያ ቤት ግቢ ውስጥ በመጫወት ላይ እያለች ለጊዜው ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች ታግታ የሕፃኗ ወላጅ አባት ነሐሴ 25 ቀን 2016 ዓ.ም. ስልክ ተደውሎ ለሕፃኗ ማስለቀቂያ 1 ሚሊዮን ብር እንዲከፍሉ ከተጠየቁ በኋላ በስልክ በመደራደር 300,000 ብር ለመክፈል ይስማማሉ። የሕፃኗ ቤተሰቦች የተጠየቀውን ገንዘብ አሰባስበው ነሐሴ 27 ቀን 2016 ዓ.ም. ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ላይ ሸዋ ዳቦ ከተባለ አካባቢ በመሄድ በባጃጅ ገንዘቡን ለአጋቾች በመላክ ልጃቸውን እንዲሰጧቸው ሲጠይቁ "መኖሪያ ቤታችሁ ታገኟታላችሁ" የሚል ምላሽ ተሰጥቷቸው ወደ መኖሪያ ቤታቸው በመመለስ ላይ እያሉ ሕፃኗ መኖሪያ ቤታቸው አካባቢ ተገድላ ተጥላ ተገኝታለች። ይህንን ተከትሎ የከተማው ነዋሪዎች ወደ አደባባይ በመውጣት ማእከላዊ ጎንደር ዞን አስተዳደር ጽሕፈት ቤት አካባቢ በመሰባሰብ ድርጊቱን በማውገዝ በጎንደር ከተማ እየተፈጸመ ያለው እገታ እንዲቆም ድምጻቸውን በሰላማዊ ሰልፍ አሰምተዋል። የመንግሥት ኃይሎች ሰልፈኞቹን ለመበተን በተኮሱት ጥይት 3 ሰልፈኞች የተገደሉ ሲሆን ከ11 በላይ የሚሆኑ ሰዎች ላይ ደግሞ የአካል ጉዳት የደረሰ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።
58. ጳጉሜን 2 ቀን 2016 ዓ.ም. በጎንደር ከተማ አስተዳደር፣ አዘዞ ጸዳ ክፍለ ከተማ፣ ጸዳ ቀበሌ ጤና ጣቢያ አካባቢ 1 የመንግሥት የጸጥታ አባል ተገድሎ መገኘቱን ተከትሎ ከቀኑ 5፡00 ሰዓት እስከ 6፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ የመንግሥት ኃይሎች ቢያንስ 11 ሰዎችን የገደሉ መሆኑን ኢሰመኮ አረጋግጧል።

59. መስከረም 6 ቀን 2017 ዓ.ም. በሰሜን ጎንደር ዞን፣ ደባርቅ ከተማ በመንግሥት ኃይሎች እና በክልሉ በሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") አባላት መካከል ከጠዋት እስከ እኩለ ቀን ድረስ ከተካሄደው የትጥቅ ግጭት ጋር በተያያዘ ዒላማቸውን ባልጠበቁ ተኩሶች እና በተባራሪ ጥይቶች ቢያንስ 29 ሰዎች እንደተገደሉ ኢሰመኮ ባደረገው ማጣራት ማረጋገጥ ችሏል። በተጨማሪ ዒላማቸውን ባልጠበቁ ተኩሶች እና በተባራሪ ጥይቶች 36 ሰዎች ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት ደርሶባቸው ደባርቅ አጠቃላይ ሆስፒታል ገብተው የሕክምና አገልግሎት ያገኙ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 2 ሰዎች ሞተዋል።
60. ከመስከረም 6 እስከ 7 ቀን 2017 ዓ.ም. በጎንደር ከተማ፣ ቀበሌ 18፣ አዲስ ዓለም፣ ገንፎ ቁጭ፣ ቆሽ ሰፈር፣ ፋሲል ካምፓስ፣ አማኑኤል፣ ሎዛ ማርያም፣ አጣጥ እና አዘዞ በተባሉ የከተማው አካባቢዎች በመንግሥት ኃይሎች እና በአካባቢው በሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") መካከል በነበረው የትጥቅ ግጭት በሁለቱም ወገን በነበረው የተኩስ ልውውጥ ምክንያት ሕፃናትን እና ሴቶችን ጨምሮ ቢያንስ 10 ሲቪል ሰዎች እንደተገደሉና በአካል እና በንብረት ላይ ጉዳት ደርሷል። ከአንድ ሆስፒታል በተገኘ መረጃ ብቻ በግጭቱ ምክንያት 6 ሴቶች እና 6 ሕፃናትን ጨምሮ በአጠቃላይ 32 ሲቪል ሰዎች ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት ደርሶባቸው የሕክምና አገልግሎት ያገኙ ሲሆን ከነዚህ መካከል 1 ሰው ሆስፒታሉ ውስጥ ሕይወቱ አልፏል።
61. ከመስከረም 6 እስከ 7 ቀን 2017 ዓ.ም. በሰሜን ጎንደር ዞን፣ ዳባት ከተማ በመንግሥት ኃይሎች እና በአካባቢው በሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") አባላት መካከል ከነበረው የተኩስ ልውውጥ ተከትሎ 4 ሰዎች የተገደሉ ሲሆን በ5 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል። በተጨማሪ 6 የመኖሪያ ቤቶች ላይ ጉዳት ደርሷል።
62. መስከረም 8 ቀን 2017 ዓ.ም. በምሥራቅ ጎጃም ዞን፣ ስናን ወረዳ በአካባቢው የሚንቀሳቀሰው ታጣቂ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") አባላት ከምሽቱ 2:30 ሰዓት አካባቢ 2 የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራንን ከመኖሪያ ቤታቸው በመውሰድ የገደሏቸው ሲሆን በሌሎች 4 መምህራን ላይ ድብደባ ፈጽመዋል። በመምህራኑ ላይ የተፈጸመው ግድያ እና ድብደባ በ2017 ዓ.ም. ትምህርት ለማስጀመር ካደረጉት እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል።
63. መስከረም 23 ቀን 2017 ዓ.ም. ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት አካባቢ በደቡብ ጎንደር ዞን፣ ጉና በጌምድር ወረዳ፣ ክምር ድንጋይ ከተማ በመንግሥት ኃይሎች የተተኮሰ የጦር መሣሪያ የግለሰብ መኖሪያ ቤት ግቢ ላይ በማረፉ 2 የቤተሰቡ አባላት ሲገደሉ ሌሎች 2 ሕፃናት ደግሞ ከባድ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል።
64. መስከረም 26 ቀን 2017 ዓ.ም. በምዕራብ ጎንደር ዞን፣ በቋራ ወረዳ በአካባቢው የሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ "ፋኖ") አባላት 8 ሰዎች ላይ ግድያ ፈጽመዋል። በተጨማሪም 60 የሚሆኑ ሰዎችን ገለጉ በሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ ለቀናት እንዳሰሩ እንዲሁም በርካታ የቀንድና የጋማ ከብቶችን እንደዘረፉ ኢሰመኮ ለማረጋገጥ ችሏል። ጥቃቱን በመፍራት በርካታ ነዋሪዎች ከአካባቢያቸው ተፈናቅለው የነበረ ሲሆን ከቀናት ቆይታ በኋላ ወደ ቀያቸው እንደተመለሱ ለመረዳት ተችሏል።
65. መስከረም 27 ቀን 2017 ዓ.ም. ከቀኑ 7:00 ሰዓት አካባቢ በሰሜን ጎጃም ዞን፣ በሰሜን ሜጫ ወረዳ፣ ዳጊ ቀበሌ ላይ በመንግሥት ኃይሎች በተፈጸመ ጥቃት 1 ሰው ሲገደል 2 ተጨማሪ ሰዎች የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። በተጨማሪም ዳጊ ጤና ጣቢያ ላይ እና 4 መኖሪያ ቤቶች ጉዳት ደርሶባቸዋል።

66. መስከረም 29 ቀን 2017 ዓ.ም. በምዕራብ ጎጃም ዞን፣ ደጋ ዳሞት ወረዳ በአካባቢው የሚንቀሳቀሱ ታጣቂዎች (በተለምዶ “ፋኖ”) ወደ ወረዳው መቀመጫ ፈረስ ቤት ከተማ በመግባት በርካታ የወረዳ አመራሮችን፣ ሥራ ኃላፊዎችን እና “የመንግሥት የመረጃ ምንጭ ናቸው” ያሏቸውን ቢያንስ 80 ሰዎች አስረዋል፡፡ እንዲሁም የወረዳ አስተዳዳሪውን ጨምሮ 3 መኖሪያ ቤቶችን በእሳት አቃጥለዋል፡፡ ከመስከረም 29 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ በቁጥጥር ሥር ውለው ከነበሩት ሰዎች መካከል 38 ሰዎች ኅዳር 27 ቀን 2017 ዓ.ም. በግምት ከጠዋቱ 1:00 እስከ 2:00 ሰዓት አካባቢ ልዩ ቦታው ፈረስ ቤት ሚካኤል 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በታጣቂዎች (በተለምዶ “ፋኖ”) እንደተገደሉ ኢሰመኮ ማረጋገጥ ችሏል፡፡
67. ኅዳር 11 ቀን 2017 ዓ.ም. በማእከላዊ ጎንደር ዞን፣ ጎንደር ዙሪያ ወረዳ፣ ለምባ አርባይቱ ቀበሌ፣ አርባ ተንሳይ ጎጥ በአካባቢው የሚንቀሳቀሱ ታጣቂዎች (በተለምዶ “ፋኖ”) በመንግሥት ኃይሎች ላይ የደፈጣ ጥቃት መፈጸማቸውን ተከትሎ የመንግሥት ኃይሎች 3 ሰዎችን ገድለዋል፡፡
68. ኅዳር 28 ቀን 2017 ዓ.ም. በምሥራቅ ጎጃም ዞን፣ እናርጅ እናውጋ ወረዳ በመንግሥት ኃይሎች እና በአካባቢው በሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ “ፋኖ”) መካከል የተከሰተውን የተኩስ ልውውጥ ተከትሎ ኅዳር 29 ቀን 2017 ዓ.ም. በመንግሥት ኃይሎች የተተኮሰ ወታደራዊ ዒላማን ያልለየ የጦር መሣሪያ ቡሽት ኮኛ ቀበሌ፣ ግራርጌ ሰፈር 1 ሕፃን የሞተች ሲሆን 1 ሕፃን ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡ በተመሳሳይ ቀን በዚሁ ቀበሌ በሌላ መንደር በተፈጸመ ወታደራዊ ዒላማን ያልለየ የጦር መሣሪያ ጥቃት 1 ሴት የሞቱ ሲሆን 1 ወጣት ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡
69. ታኅሣሥ 3 ቀን 2017 ዓ.ም. በደቡብ ጎንደር ዞን አንዳቤት ወረዳ ገነተ-ማርያም ቀበሌ አርክን በተባለ ቦታ 5 ሰዎች በመንግሥት ኃይሎች ተገድለዋል፡፡
70. ታኅሣሥ 11 ቀን 2017 ዓ.ም. ከደብረ ማርቆስ ከተማ ወደ ደብረ ኤልያስ ወረዳ በጭነት መኪና ተሳፍረው በመጓዝ ላይ የነበሩ የደብረ ኤልያስ ወረዳ የመንገድ ትራንስፖርት ጽሕፈት ቤት 2 ሴት ሠራተኞች ጎዛመን ወረዳ ውግር ቀበሌ ሲደርሱ በአካባቢው የሚንቀሳቀሱ የታጣቂ ቡድን (በተለምዶ “ፋኖ”) አባላት ከመኪና አስወርደው ከወሰዷቸው በኋላ በማግሥቱ ታኅሣሥ 12 ቀን 2017 ዓ.ም. ተገድለው ተገኝተዋል፡፡ ሠራተኞቹ የመንግሥት ኃይሎች ወደ ደብረ ኤልያስ ወረዳ መግባታቸውን ተከትሎ ቀደም ሲል ወረዳው በአካባቢው በሚንቀሳቀሰው ታጣቂ ቡድን (በተለምዶ “ፋኖ”) ቁጥጥር ሥር በነበረበት ወቅት ለወራት ለቀው የነበሩት ሁሉም የወረዳው የመንግሥት ሠራተኞች ወደ ሥራ ገበታቸው እንዲመለሱ በተደረገው ጥሪ መሠረት በመመለስ ላይ የነበሩ ናቸው፡፡ የመንግሥት ሠራተኞች ወደ ሥራ ገበታቸው እንዲመለሱ ማስታወቂያ በወጣበት ወቅት የታጣቂ ቡድኑ (በተለምዶ “ፋኖ”) አባላት በበኩላቸው ሠራተኞች እንዳይመለሱ ያስጠነቅቁና ያስፈራሩ እንደነበር ኢሰመኮ ለመረዳት ተችሏል፡፡
71. ታኅሣሥ 25 እና 26 ቀን 2017 ዓ.ም. በምሥራቅ ጎጃም ዞን ደባይ ጥላትግን ወረዳ ናብራ ቀበሌ በመንግሥት ኃይሎች እና በታጣቂዎች (በተለምዶ “ፋኖ”) መካከል የተካሄደውን ግጭት ተከትሎ 3 ሰዎች መገደላቸው ታውቋል፡፡ በተጨማሪም በ2 ሕፃናት ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡
72. ታኅሣሥ 28 ቀን 2017 ዓ.ም. በአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ዳንግላ ዙሪያ ወረዳ ጊሳ ቀበሌ ለመስክ ሥራ የተሰማሩ 4 የወረዳው የሥራ ኃላፊዎች (የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ እና 3 የጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች) በአካባቢው በሚንቀሳቀሰው የታጣቂ ቡድን (በተለምዶ “ፋኖ”)

ከተያዙ በኋላ ጥር 3 ቀን 2017 ዓ.ም. ተገድለው አስከሬናቸው ተገኝቷል። በወቅቱ ከሚኞች ጋር አብሮ ታግቶ የነበረው አሽከርካሪ ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አይታወቅም።

**73.** ጥር 5 ቀን 2017 ዓ.ም. በምሥራቅ ጎጃም ዞን፣ ስናን ወረዳ ወይበይኝ ተብሎ በሚጠራው ጎጥ በፋኖ ኃይሎች እና በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች መካከል የተጥቅ ግጭት የነበረ ሲሆን በሰዓቱ 2 ሰዎች በመንግሥት ኃይሎች ተገድለዋል። ከሮቡ ገበያ ድጎጺዮን የሚወስደውን ዋናውን መስመር ተከትሎ የሚገኙ መኖሪያ ቤቶችን በእሳት አቃጥለዋል። በእሳት ቃጠሎው የቤት እንስሳት ጭምር ተቃጥለው የሞቱ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።

**74.** ጥር 29 ቀን 2017 ዓ.ም. በምዕራብ ጎጃም ዞን ሰከላ ወረዳ ሮቢት ቀበሌ በግጭት ዐውድ ውስጥ በመንግሥት ኃይሎች የተተኮሰ የጦር መሣሪያ በ1 መኖሪያ ቤት ላይ አርፎ 3 ሰዎች ተገድለዋል እንዲሁም 7 የቁም ከብቶች ሞተዋል።

**75.** በደቡብ ወሎ ዞን ወረባቡ ወረዳ በአካባቢው የሚንቀሳቀሱ ታጣቂዎች (በተለምዶ ፋኖ) መጋቢት 2 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት አካባቢ 3 ሰዎችን (የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ፣ የወረዳው ፖሊስ ጽሕፈት ቤት የወንጀል ምርመራ ክፍል ኃላፊ እና ሾፌር) ለሥራ ጉዳይ ከወረዳው ዋና ከተማ ቢስቲማ ወደ ቦኬክስ ሲሄዱ ልዩ ቦታው ጠቢሳ ከሚባል ቦታ ላይ ተኩስ ከፍተው ገድለዋቸዋል።

**76.** መጋቢት 8 ቀን 2017 ዓ.ም. በምዕራብ ጎንደር ዞን ቋራ ወረዳ የሚንቀሳቀሱ ታጣቂዎች (በተለምዶ ፋኖ) የይካሆ ቀበሌ ነዋሪዎችን "ከመከላከያ ሰራዊት ጋር በመሆን ፋኖን ትዋጋላችሁ" በሚል የጦር መሣሪያ ለመውሰድ ሲሞክሩ የተነሳውን ግጭት ተከትሎ ታጣቂዎች መጋቢት 11 ቀን 2017 ዓ.ም. በድጋሚ ወደ ይካሆ ቀበሌ በመግባት በፈጸሙት ጥቃት 6 ሰዎችን (2 ወንድና 4 ሴት) ገድለዋል፤ 2 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት አድርሰዋል፣ በጥቃቱ በርካታ ሰዎች ተፈናቅለው በወረዳው ዋና ከተማ ገለጉ እንደሚገኙ እንዲሁም መኖሪያ ቤቶች እንደተቃጠሉ ኢሰመኮ አረጋግጧል።

**77.** መጋቢት 11 ቀን 2017 ዓ.ም. በሰሜን ጎጃም ዞን፣ ሰሜን ሜጫ ወረዳ መራዊ ከተማ አስተዳደር በአካባቢው በሚንቀሳቀሱ የታጠቂ ቡድን አባላት (በተለምዶ "ፋኖ") ከቀኑ 6:00 እስከ 7:00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ወደ ከተማው ዘልቀው በመግባት 4 የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራንን ጨምሮ 6 ሲቪል ሰዎችን ገድለዋል እንዲሁም 1 ግለሰብ አግተው ወስደዋል።

**78.** መጋቢት 23 ቀን 2017 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2፡30 ሰዓት ደቡብ ጎንደር ዞን፣ ፎገራ ወረዳ፣ ወረታ ከተማ የሚሊሻ አባላት የአንጉኮ ማርያም ቀበሌ ነዋሪ የሆነ 1 ሰው ገድለዋል።

**79.** መጋቢት 28 ቀን 2017 ዓ.ም. ከቀኑ 9፡00 ሰዓት ጀምሮ በአማራ ክልል፣ ደቡብ ጎንደር ዞን፣ ፎገራ ወረዳ፣ ዓለም በር ከተማ ታጣቂዎች (በተለምዶ ፋኖ) ዘልቀው በመግባት 2 የአባይ ባንክ የጥበቃ ሠራተኞችን እንደገደሉ፣ አባይ ባንክ ላይ ዘረፋ እንደፈጸሙ እንዲሁም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክና በፀደይ ባንክ ላይ የዘረፋ ሙከራ ማድረጋቸውን ኢሰመኮ አረጋግጧል።

**80.** ግንቦት 2 ቀን 2017 ዓ.ም. ከንጋቱ 11፡30 ሰዓት ጀምሮ በአማራ ክልል፣ በማዕከላዊ ጎንደር ዞን፣ ጭልጋ ወረዳ፣ ኳበር ሎምጌ ቀበሌ ልዩ ስሙ ባረንጎ በተባለ መንደር ታጣቂዎች (በተለምዶ የፋኖ) 2 ሰዎች ገድለዋል፣ 4 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት አድርሰዋል፣ የቤት እንስሳ ዘርፈው ወስደዋል፣ 7 የመኖሪያ ቤቶችን እ እንዲሁም 34 የሚሆኑ የመንደሩ አባወራዎችን እንዳፈናቀሉ ኢሰመኮ አረጋግጧል።

## ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል

**81.** በበጀት ዓመቱ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በተከሰተ ግጭት፣ ማንነታቸው ባልታወቁ ኃይሎች እንዲሁም በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") በተወሰዱ እርምጃዎች በሲቪል ሰዎች ላይ የሞት፣ እገታ፣ የአካል ጉዳት እና የንብረት ውድመት ደርሷል። ከእነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፦

**82.** በክልሉ አሶሳ ዞን ኩርሙክ እና ሆሞሻ ወረዳዎች በ2016 ዓ.ም. ሐምሌ እና ነሐሴ ወራት ከወርቅ ማውጫ ቦታ ይዞታ ይገባኛል ጥያቄ ጋር ተያይዞ እርስ በርስ እና ከመንግሥት ኃይሎች ጋር ግጭት ተፈጥሮ 2 ሰዎች ሕይወታቸው ሲያልፍ በ16 ሰዎች ላይ የአካል ላይ ጉዳት ደርሷል።

**83.** ጥር 3 ቀን 2017 ዓ.ም. በግምት ከጠዋቱ 12:00 ሰዓት አካባቢ በመተከል ዞን ቡለን ወረዳ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") እና በመንግሥት ኃይሎች መካከል በተደረገው የተኩስ ልውውጥ 1 ሰው ተገድሏል።

**84.** ጥር 12 ቀን 2017 ዓ.ም. በመተከል ዞን ማንዱራ ወረዳ ጅግዳ ቀበሌ ማንነታቸው ለጊዜው ባልታወቁ አካላት በተተኮሰ ጥይት የ1 ሰው ሕይወት ሲያልፍ በሌላ 1 ሰው ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል። በተመሳሳይ በዕለቱ በግምት ከጠዋቱ 1:00 ሰዓት ገደማ ከግልገል በለስ ከተማ ሰዎችን አሳፍሮ በመጓዝ ላይ በነበረ ሚኒባስ መኪና ላይ ማንነታቸው ያልታወቁ ታጣቂዎች በከፈቱት ተኩስ 1 ሰው የተገደለ ሲሆን፣ ሌላ 1 ሴት የአካል ጉዳት ደርሷል።

**85.** ጥር 14 ቀን 2017 ዓ.ም. በመተከል ዞን ድባጤ ወረዳ ጊጾ ቀበሌ ማንነቱ ባልታወቀ ኃይል ሦስት ሰዎች ለ 3 ቀናት ታግተው ሲለቀቁ አንድ መኪና ተቃጥሏል።

**86.** ጥር 17 ቀን 2017 ዓ.ም. በመተከል ዞን በድባጤ ወረዳ ጫንጮ/ጌሽ ቀበሌ 2 ሰዎች ማንነቱ ባልታወቀ ታጣቂ ኃይል በጥይት ተገድለዋል።

**87.** ጥር 19 ቀን 2017 ዓ.ም. በድባጤ ወረዳ በጫቲ ቀበሌ ውስጥ ለጊዜው ማንነታቸው በውል ባልታወቁ ታጣቂ ኃይሎች ከ1 ሰው አንድ የጦር መሣሪያ መውሰዳቸው እና 1 ሰው ደግሞ መሣሪያ የለኝም በማለቱ ለ3 ቀን ታግቶ ተለቋል።

**88.** ጥር 25 ቀን 2017 ዓ.ም. በመተከል ዞን ቡለን ወረዳ ማጣ ቀበሌ በግምት ከምሽቱ 2:00 ሰዓት ገደማ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") አባላት ባደረሱት ጥቃት 1 ሴት ተገድላለች።

**89.** መጋቢት 14 ቀን 2017 ዓ.ም. ከጠዋቱ 1:00 ሰዓት አካባቢ በመተከል ዞን ቡለን ወረዳ ኤጳር ቀበሌ ከወርቅ ማውጫ ሳይት ቅኝት በሞተር ሳይክል በመመለስ ላይ የነበሩ 3 ሰዎች በመንግሥት ኃይሎች ተገድለዋል። በዚህም ጥቃቱን ፈጽመዋል ተብለው የተጠረጠሩ 3 ሰዎች ተይዘው ምርመራ የተጀመረባቸው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

**90.** ግንቦት 12 ቀን 2017 ዓ.ም. ከንጋቱ 11:20 ሰዓት በካማሽ ዞን ምዥጋ ወረዳ አይሻንጅድም በተባለ ቀበሌ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") በመባል የሚጠራው ታጣቂ ቡድን 18 ሰዎች ተገድለዋል። በተጨማሪም ሌሎች 12 ሰዎች ደግሞ በተፈጸመው ጥቃት የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል።

**91.** ግንቦት 21 ቀን 2017 ዓ.ም. ከንጋቱ 11:30 ሰዓት በመተከል ዞን ዳንጉር ወረዳ ቆታ ቀበሌ በተለምዶ ቡል ወንዝ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የእርሻ ቦታ ላይ "ሻባን" በመባል በሚታወቀው ግለሰብ በሚመራው የጉሙዝ ታጣቂ ቡድን በተፈጸመ ጥቃት 8 ሲቪል ሰዎች ተገድለዋል፤ በ 1 ሰው ላይ ደግሞ የአካል ጉዳት ደርሷል።

## ማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል

**92.** በምሥራቅ ጉራጌ ዞን ምሥራቅ መስቃን ወረዳ እና በማረቆ ልዩ ወረዳ አዋሳኝ ቀበሌዎች ላይ የሚነሱ ግጭቶችን ለማስቀረት የክልሉ፣ የዞን እና ልዩ ወረዳ የአስተዳደርና የጸጥታ አካላት እንዲሁም የሀገር ሽማግሌዎች በተገኙበት የካቲት 5 ቀን 2016 ዓ.ም. “በመስቃን እና ማረቆ ብሔረሰብ” መካከል የተካሄደውን እርቅ የማፅናት ሥነ ሥርዓት ተከናውኖ ለተጎጂዎችም ካሳ መከፈሉ እንዲሁም በግጭቱ ተሳትፈዋል ተብለው የተጠረጠሩ ግለሰቦችና የመንግሥት አመራሮችን ጭምር በቁጥጥር ሥር በማዋል ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ሥራዎች በመከናወን ላይ መሆናቸው የሚበረታታ ቢሆንም በአካባቢው ላይ የሚንቀሳቀሱ ማንነታቸው የማይታወቅ የታጠቁ ግለሰቦች/ቡድኖች በየጊዜው በሚያደርሱት ጥቃት በነዋሪዎች ላይ ሞት እና የአካል ጉዳት ማስከተሉን ለመረዳት ተችሏል።

**93.** ሰኔ 26 ቀን 2016 ዓ.ም. ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት አካባቢ በኢንሴኖ ከተማ ማንነታቸው በውል ያልታወቁ የታጠቁ ሰዎች ባደረሱት ጥቃት አንድ ሰው የተገደለ ሲሆን 3 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል።

**94.** ነሐሴ 19 ቀን 2016 ዓ.ም. በማረቆ ልዩ ወረዳ ሆቤ ጃር ደምቦቃ የተባለ ቦታ አራት የአንድ ቤተሰብ አባላት የተገደሉ ሲሆን ዲዳ ሀሊቦ በተባለ ቀበሌ 7 የሁለት ቤተሰብ አባላት ማንነታቸው ያልታወቁ ታጣቂዎች በፈጸሙት ጥቃት ተገድለዋል።

**95.** በጉራጌ ዞን ከወልቂጤ ከተማ የይገባኛል ጥያቄ ጋር በተያያዘ ተከስቶ የነበረውን የጸጥታ ችግር ተከትሎ ከጥቅምት 3 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ ወልቂጤ እና ዙሪያዋ በኮማንድ ፖስት እንዲተዳደሩ ተወስኖና የእንቅስቃሴና የሰዓት እላፊ ገደብ ታውጆ የነበረ ሲሆን የኮማንድ ፖስት አስተዳደሩና የሰዓት ገደቡም ከግንቦት 22 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ በድጋሚ ተራዝሟል። ኢሰመኮ በእነዚህ በኮማንድ ፖስት በሚተዳደሩ አካባቢዎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችና ሥጋቶች አሉብን በማለት ነዋሪዎች ያቀረቧቸውን በርካታ አቤቱታዎች መሠረት በማድረግ ምርመራ አድርጓል።

**96.** በዚህም መሠረት ኅዳር 29 ቀን 2017 ዓ.ም. በጉራጌ ዞን በአበሽጌ ወረዳ ቦረር ቀበሌ ቁርጥ አምባ ተብሎ በሚጠራው ቦታ በመንግሥት ኃይሎች እና በአካባቢው በሚገኙ የታጠቁ ሰዎች ጋር የተካሄደውን የተኩስ ልውውጥ ተከትሎ 1 ሰው በመንግሥት ኃይሎች መገደላቸውን ኢሰመኮ ለማረጋገጥ ችሏል። በተመሳሳይ ኅዳር 30 ቀን 2017 ዓ.ም. በጉራጌ ዞን በአበሽጌ ወረዳ ነዋሪ የሆኑ 1 ሰው በቦረር ቀበሌ በመንግሥት ኃይሎች መገደላቸውን ኢሰመኮ ለማረጋገጥ ችሏል።

**97.** ግድያዎቹን አስመልክቶ ምላሽ የተጠየቁት የአካባቢው ኃላፊዎች አንደኛው ሟች በአካባቢው በመንቀሳቀስ ላይ የነበረ የመከላከያ ተሽከርካሪ ላይ የተከፈተ ጥቃትን ተከትሎ በተወሰደ እርምጃ እና አንደኛው ደግሞ ከታጣቂዎች ጋር በተደረገ የተኩስ ልውውጥ በታጣቂዎች ተገድለዋል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።

## ጋምቤላ ክልል

**98.** ሐምሌ 2 ቀን 2016 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ገደማ በጋምቤላ ክልል፣ ጋምቤላ ወረዳ፣ ጀዊ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ አካባቢ ማንነታቸው ባልተለየ የታጠቁ አካላት በተፈጸመ ጥቃት 3 የደቡብ ሱዳን ስደተኞች ተገድለዋል፣ 3 ሰዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ የአካል ጉዳት ደርሷል።

99. በአኝዋ እና ኑዌር ብሔረሰብ ዞን የተለያዩ አካባቢዎች ከደቡብ ሱዳን በሚመጡ የሙርሌ ጎሳ ታጣቂዎች በሚፈጽሙት ግድያ፣ ሕፃናትንና ሴቶችን በኃይል አፍኖ የመውሰድ ድርጊት በመኖሩ ማኅበረሰቡ ተረጋግቶ መደበኛ ሕይወቱን እንዳይመራ አድርጓል። ለምሳሌ ጥቅምት 4 ቀን 2017 ዓ.ም. ጠዋት 2፡00 ሰዓት አካባቢ በጋምቤላ ክልል አኝዋ ብሔረሰብ ዞን ጎግ ወረዳ ቴዶ ቀበሌ አጉልመኖ ተብሎ በሚጠራ ስፍራ በሙርሌ ጎሳ ታጣቂዎች 1 ሕፃን ተገድሏል።

100. ታኅሣሥ 20 ቀን 2017 ዓ.ም. ጋምቤላ ከተማ 01 ቀበሌ እና ጋምቤላ ወረዳ ቦንጋ ቀበሌ መካከል ሰርቲ ሚኒትስ (30 Minutes) ተብሎ በሚጠራ የእርሻ ስፍራ ውስጥ በእርሻ ሥራ ላይ ተሰማርተው የነበሩ 2 ሰዎች ማንነታቸው ባልታወቁ ታጣቂዎች ተገድለዋል።

101. ጥር 3 ቀን 2017 ዓ.ም. በኢታንግ ልዩ ወረዳ አቹዋ ቀበሌ ቁጠባ ቤቶች ተብሎ በሚጠራው ሰፈር ማንነታቸው ባልተለየ ታጣቂዎች በተከፈተ ተኩስ 1 ሰው ተገድሏል።

102. የካቲት 10 ቀን 2017 ዓ.ም. በጎግ ወረዳ ቴዶ ቀበሌ ውስጥ ከደቡብ ሱዳን በመጡ የሙርሌ ጎሳ ታጣቂዎች 1 ሕፃን መገደሉን፣ የካቲት 18 ቀን 2017 ዓ.ም. በኑዌር ብሔረሰብ ዞን አኮቦ ወረዳ 1 ሰው መገደሉን ኢሰመኮ አረጋግጧል።

103. ሚያዝያ 30 ቀን 2017 ዓ.ም. የደቡብ ሱዳን ዜጋ የሆኑ 5 ሴት ስደተኞች ለጊዜው ማንነታቸው ባልተለየ አካላት በጥይት ተመትተው ሕይወታቸው አልፏል።

104. ግንቦት 17 ቀን 2017 ዓ.ም. ከጠዋቱ 1፡00 ሰዓት አካባቢ ከዲማ ከተማ ወደ ጎግ ወረዳ ፒኙዶ ከተማ ሰዎችን አሳፍሮ ሲጓዝ በነበረ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ላይ ከደቡብ ሱዳን የመጡ የሙርሌ ጎሳ ታጣቂዎች በከፈቱት ተኩስ 5 ሰዎች ተገድለዋል፣ 7 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል።

### ኦሮሚያ ክልል

105. በኦሮሚያ ክልል በዋነኛነት በመንግሥትና በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት "ኦነግ ሸኔ" መካከል በሚደረገው የትጥቅ ግጭት ዓውድ ውስጥ በሰሜን ሸዋ ዞን፣ በምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ ምስራቅ ወለጋ፥ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፥ አርሲ እና በሌሎች ዞኖች በሲቪል ሰዎች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች አሳሳቢነታቸው ቀጥሏል።

106. ሐምሌ 26 ቀን 2016 ዓ.ም. ከአማራ ክልል ባሕርዳር ከተማ ወደ አዲስ አበባ 66 ተሳፋሪዎችን የያዘ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ በፊቼ እና ገበረ ጉረቻ መሃል ሲደርስ በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ" ተብሎ በሚጠራው ታጣቂ ቡድን እገታ ተፈጽሞ 2 ሰዎች ተገድለዋል፤ ቀሪዎቹን አግቶ የወሰደ ሲሆን ለእያንዳንዱ ታጋች መለቀቂያ እስከ አንድ ሚሊየን ብር መክፈል እንዳለባቸው ለቤተሰባቸው በማሳሰብ ደጋግመው እየደወሉ ክፍያው በቶሎ ካልተፈጸመ ግድያ እንደሚፈጽሙባቸው ሲያስፈራሩ እንደነበር በወቅቱ ከታጋች ቤተሰቦች ማረጋገጥ ተችሏል።

107. ነሐሴ 3 ቀን 2016 ዓ.ም. በግምት ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት አካባቢ በኦሮሚያ ክልል፣ በሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን፣ አቤ ዶንጎሮ ወረዳ፣ ጨሩ ቀበሌ በአካባቢው እንደሚንቀሳቀስ የተገለጸ በተለምዶ "ፋኖ" ተብሎ የሚጠራው ታጣቂ በአካባቢው ነዋሪዎች ላይ በከፈቱት ተኩስ 22 ሰዎች ተገድለዋል በ4 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል፤ 540 መኖሪያ ቤቶች ተቃጥለዋል እንዲሁም በግምት 800 አካባቢ ከብቶች በታጣቂ ቡድኑ ተወስደዋል።

108. ነሐሴ 7 ቀን 2016 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል፣ አርሲ ዞን፣ አሰኮ ወረዳ፣ ጠለፋ ጨፋ ቀበሌ ራሱን የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በማለት የሚጠራው ቡድን (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") ታጣቂዎች

ወደ ቀበሌው ገብተው የቀበሌው አስተዳደር ሲቪል ሠራተኞች እና ከመንግሥት ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው የተጠቆሙ ነዋሪዎችን ለይተው በፈጸሙት ጥቃት 3 ሰዎችን ገድለዋል፣ 1 ሰው ላይ የአካል ጉዳት አድርሰዋል፤ ለጊዜው ብዛታቸው በትክክል ያልተረጋገጠ የነዋሪዎች መኖሪያ ቤቶችን አቃጥለዋል። እንዲሁም ብዛታቸው ያልታወቀ ሰዎች ጥቃቱን በመሸሽ አካባቢውን ለቀው ወደ አሰኮ ከተማ አካባቢ ሠፍረው እንደነበር ለመረዳት ተችሏል። በ2017 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ወቅት የመንግሥት ኃይሎች ቀበሌውን እንደተቆጣጠሩ፣ ታጣቂዎቹ ቦታውን ለቀው እንደወጡ እና የወረዳው አስተዳደር ተጎጂዎችን አወያይቶ ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ ስለመደረጉ ለመረዳት ተችሏል።

**109.** ነሐሴ 13 ቀን 2016 ዓ.ም. ሰሜን ሸዋ ዞን፣ አቦቴ ወረዳ፣ ኤጄሬ ከተማ ነዋሪ የሆነ 1 ሰው በመንግሥት ኃይሎች ተገድሏል።

**110.** ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ውስጥ በሚገኙት አመያ፣ ቀርሳ ማሊማ፣ ሰደን ሶዶ እና ቶሌ ወረዳዎች ራሱን የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በማለት በሚጠራው ቡድን (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) ታጣቂዎች በሐምሌ እና በነሐሴ ወር 2016 ዓ.ም. ብቻ 14 ሲቪል ሰዎች ላይ ግድያ ስለመፈጸሙ ለማረጋገጥ ተችሏል።

**111.** ነሐሴ 19 ቀን 2016 ዓ.ም. ምሥራቅ ወለጋ ዞን፣ ጊዳ አያና ወረዳ አንዶዴ ዲቾ ቀበሌ የ03 ቀበሌ በአካባቢው እንደሚንቀሳቀስ የተገለጸ በተለምዶ “ፋኖ’ ተብሎ የሚጠራው ታጣቂ በተፈጸመባቸው ጥቃት 3 ሰዎች ተገድለዋል።

**112.** መስከረም 25 ቀን 2017 ዓ.ም. ቄለም ወለጋ ዞን፣ ሳዷ ወለል ወረዳ፣ የላሎ ገለታ ቀበሌ ነዋሪ 2 ሰዎች በመንግሥት ኃይሎች ተገድለዋል።

**113.** መስከረም 28 ቀን 2017 ዓ.ም. በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን፣ አመያ ወረዳ ኢተያ ገምባ ጆቴ፣ ኢላላ እና ጢሮ ኢላላ ቀበሌዎች የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) ታጣቂዎች 5 ሲቪል ሰዎችን ገድለዋል።

**114.** መስከረም 29 ቀን 2017 ዓ.ም. በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን፣ አመያ ኢተያ ገምባ ጆቴ ቀበሌ የመንግሥት ኃይሎች 9 ሰዎችን ገድለዋል።

**115.** ጥቅምት 9 ቀን 2017 ዓ.ም. በምዕራብ ወለጋ ዞን፣ ቤጊ ወረዳ፣ የኮበሬ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑ 1 ሰው ለኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) “ድጋፍ አድርገሃል” በሚል በመንግሥት ኃይሎች ተገድሏል።

**116.** ጥቅምት 12 ቀን 2017 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት ላይ በምዕራብ ወለጋ ዞን፣ ቆንዳላ ወረዳ፣ የወንዲ ዶቾ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑ 1 ሰው “ለኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) “ድጋፍ አድርገሃል” በሚል በመንግሥት ኃይሎች ተገድሏል።

**117.** ጥቅምት 21 ቀን 2017 ዓ.ም. በምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ ዱግዳ ወረዳ፣ ብርቢሣ እና ጋሌ በተባሉ ቀበሌዎች የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) አባላት 38 ሲቪል ሰዎችን ገድለዋል፤ ለጊዜው ቁጥራቸው ያልታወቀ ሲቪል ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት አድርሰዋል። 78 መኖሪያ ቤቶችንም አቃጥለዋል።

**118.** ጥቅምት 29 ቀን 2017 ዓ.ም. በምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ ዱግዳ ወረዳ፣ መጃ ላሉ ቀበሌ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) አባላት በቀበሌው የሚኖሩ 12 ሰዎችን ገድለዋል።

**119.** ጥቅምት 29 ቀን 2017 ዓ.ም. ምሽት 2:00 ሰዓት አካባቢ በምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ በመቂ ከተማ 02 ቀበሌ ማንነታቸው በውል ባልታወቀ የታጠቁ አካላት በፈጸሙት ጥቃት 3 ሰዎች ተገድለዋል 4 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል።

**120.** ኅዳር 19 ቀን 2017 ዓ.ም. የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") ታጣቂዎች በአርሲ ዞን፣ ሽርካ ወረዳ፣ ሶሌሳ ረከታ እና መከና ቀበሌዎች በፈጸሙት ጥቃት 13 ሰዎችን ገድለዋል፡፡

**121.** ታኅሣሥ 27 ቀን 2017 ዓ.ም. ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት በቄለም ወለጋ ዞን ጋዎ ቂቤ ወረዳ ሺሜላ ቀበሌ በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") 1 ሰው ገድለዋል፡፡

**122.** የካቲት 5 ቀን 2017 ዓ.ም. ከሌሊቱ 9፡00 ሰዓት በጅማ ዞን ጌራ ወረዳ ዋላ ቀበሌ ቦሬ ከተማ አቶ ዛኪር አባኦሊ የተባሉ ሰው በመኖሪያ ቤታቸው እያሉ ማንነታቸው ባልታወቀ ግለሰቦች በተተኮሰባቸው ጥይት ሕይወታቸው አልፏል፡፡ ይህንን ተከትሎ በተከሰተው ግጭት የካቲት 6 ቀን 2017 ዓ.ም. 293 መኖሪያ ቤቶች፣ 11 የእህል ወፍጮዎችና 7 ትራክተሮች ተቃጥለዋል፡፡ ከቃጠሎ የተረፉ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች፣ የምግብ እህሎች እና የቀንድ ከብቶችም የተዘረፉ ሲሆን፤ የአካባቢው ነዋሪ የሆኑ ወደ 10 ሺህ የሚጠጉ የአማራ ብሔር ተወላጆች ወደ አጎራባች አካባቢዎች ተፈናቅለዋል፡፡ የተከሰተውን አለመረጋጋት ተከትሎ 1 ሰው በክልሉ የጸጥታ አካላት የካቲት 9 ቀን 2017 ዓ.ም. ተገድለዋል፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ ግድያውን በተመለከተ በሰጠው ምላሽ በግድያው የተጠረጠሩ 4 ሰዎች ላይ የምርመራ መዝገብ ተጣርቶ ክስ የተመሠረተባቸው መሆኑን ገልጿል፡፡ እንዲሁም በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳትን በተመለከተ የምርመራ ቡድን ተቋቁሞ የምርመራ ሥራ በማከናወን ላይ እንደሚገኝ ተገልጿል፡፡

**123.** ጥቃቱን በመሸሽ ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ተፈናቅለው የነበሩት ሰዎች ከጅማ ዞን እና ከጌራ ወረዳ አስተዳደር አካላት ጋር በተደረገ ውይይት በተፈናቀሉ በ4 ቀናት ውስጥ ወደ ቀዬአቸው እንዲመለሱ መደረጉ፤ ከመፈናቀል የተመለሱ ሰዎችን ለማቋቋም በተደረገ ጥረት በማኅበረሰቡ ትብብር 300 ኩንታል የምግብ እህል ተሰብስቦ መከፋፈሉ፤ 63 መኖሪያ ቤቶች መሠራታቸው እና ሌሎች ተጨማሪ ቤቶችም በመሠራት ላይ መሆናቸው ታውቋል፡፡ ከመፈናቀል የተመለሱ ነዋሪዎች ወደ እርሻ ሥራቸው መመለስ መጀመራቸውንም ኢሰመኮ ያሰባሰባቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ሆኖም ከተመላሾች መካከል 1 ሰው ተገድሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የወንጀል ምርመራ ተከናውኖ በግድያው የተጠረጠሩ ሰዎች በቁጥጥር ሥር መዋላቸው እና በጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ ቀርቦባቸው በክርክር ሂደት ላይ ይገኛል፡፡ ዋና አስተዳዳሪውን ጨምሮ ችግሩ እንዳይከሰት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ አልተወጡም የተባሉ 5 የወረዳው የሥራ አስፈጻሚዎች ከኃላፊነት እንዲነሱ መደረጋቸው ተጠያቂነትን ከማረጋገጥ አንጻር መልካም ጅምር ነው፡፡

**124.** የካቲት 13 ቀን 2017 ዓ.ም. ከቀኑ 9፡00 ሰዓት አካባቢ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ")ታጣቂ ቡድን በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ግራር ጃርሶ ወረዳ የጤና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ተገድሏል፡፡

**125.** መጋቢት 4 ቀን 2017 ዓ.ም. ከሌሊቱ 8፡00 እስከ 11፡00 ሰዓት በጅማ ዞን ሰጠማ ከተማ አንዲት ሴት እምነት በመቀየሯ ሳቢያ ድብደባ ተፈጽሞባታል በሚል በነዋሪዎች በተፈጸመ ጥቃት የጋቲራ መካነ እየሱስ ቤተ ክርስቲያን ተቃጥሏል፡፡ በዚሁ ጥቃት በ12 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት የደረሰ ሲሆን፣ በከተማው በሚገኙ 14 የመካነ እየሱስ ኅብረት አባላት መኖሪያ ቤቶች ውስጥ ያሉ ንብረቶች ከቤት እንዲወጡ ከተደረጉ በኋላ በእሳት ተቃጥለዋል፡፡ የደረሰውን ጥቃት ተከትሎ የጅማ ዞንና የሰጠማ ወረዳ አስተዳደሮች ከሙስሊም እና ከመካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት መሪዎችና የአካባቢ ሽማግሌዎች ጋር በመሆን በወሰዱት እርምጃ ወዲያውኑ ዕርቅ እንዲፈጸም በማድረግ፣ ጉዳት የደረሰበት የጋቲራ መካነ እየሱስ

ቤተክርሲቲያን በማኅበረሰቡ ትብብር መልሶ እንዲገነባ አስተባብረዋል። ጥቃቱን ያደረሱ ግለሰቦች ላይ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ከዞን እና ከወረዳ የተቋቋመ የምርመራ ቡድን በቦታው በመገኘት የወንጀል ምርመራ ሥራውን የጀመረ ሲሆን፣ የተወሰኑ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር ውለው ክስ የተመሠረተባቸው መሆኑን ኢሰመኮ አረጋግጧል።

126. መጋቢት 8 ቀን 2017 ዓ.ም. በአማራ ክልል የሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ “ፋኖ”) አባላት በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ግንደበረት ወረዳ ጭረቻ ገቶ ቀበሌ በመግባት በ2 ሰዎች ላይ ግድያ ፈጽመዋል።

127. መጋቢት 29 ቀን 2017 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ ዞን ሀሮ ሊሙ ወረዳ ጎርባ ጉዲና ቀበሌ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ ኦነግ ሸኔ) ታጣቂዎች መጋቢት 26 ቀን 2017 ዓ.ም. ‘ሾድ’ ተብሎ የሚጠራ የታጣቂ ቡድኑ አዛዥ በመከላከያ ሰራዊት የመገደሉ ምክንያት ‘የአቶ ሂርጶ ቤተሰብ’ ለመንግሥት መረጃ በማቀበሉ ነው በሚል የበቀል እርምጃ ለመውሰድ ወደ ቀበሌው ዘልቀው በመግባት 5 ሰዎች ገድለዋል።

128. በድጋሚ ሚያዝያ 1 ቀን 2017 ዓ.ም. የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) ወደ ሀሮ ወረዳ ሱጌ ቀበሌ በመግባት 10 ሰዎችን ገድለዋል። በተመሳሳይ ሚያዝያ 2 ቀን 2017 ዓ.ም. የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ቀበሌው ዘልቆ በመግባት 3 ሰዎችን ገድለዋል።

129. ሚያዝያ 28 ቀን 2017 ዓ.ም. በግምት ከቀኑ 10፡00 ሰዓት አካባቢ አርሲ ዞን ሮቤ ወረዳ እንደቶ ቀበሌ ልዩ ቦታው ደንበል ቂሊሳ በተባለ ቦታ፤ በአካባቢው የሚንቀሳቀሰው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) ታጣቂ ቡድን ወደ ቀበሌው ዘልቆ በመግባት 1 ሰውን ገድለዋል።

130. ማንነታቸውን በውል ማወቅ ያልተቻለ የታጠቁ ኃይሎች ግንቦት 1 ቀን 2017 ዓ.ም. በሰሜን ሸዋ ዞን ወረ ጃርሶ ወረዳ፣ ከወረዳ ዋና ከተማ ጎሀጽዎን ልዩ ስሙ አገምሳ ተብሎ በሚታወቅ ቦታ ወደ ንጋት አካባቢ ወደ ነዋሪዎች ቤት ላይ በመተኮስ ከ8 ሰዎች በላይ መግደላቸውን እና ቤቶች ማቃጠላቸውን እንዲሁም ከብቶችና እህል መዝረፋቸውን ማረጋገጥ ተችሏል።

131. ግንቦት 9 ቀን 2017 ዓ.ም. በኢሉባቦር ዞን ዳሪሙ ወረዳ ቤና ቶኮፋ እና ቤና ለመፋ በሚባሉ ቀበሌዎች የመንግሥት ኃይሎች 7 ሰዎችን ገድለዋል።

132. ግንቦት 9 ቀን 2017 ዓ.ም. ከጠዋቱ በግምት ከ12፡00-1፡00 ሰዓት ላይ የምሥራቅ ወለጋ ዞን ሳሲጋ ወረዳ ከአንገር ሜጢ የመጡ አምስት ታጣቂዎች በሳሲጋ ወረዳ ሐረዋታ 3 ሰዎችን በመግደል ካመለጡ በኋላ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) በማግስቱ ከቀኑ በግምት 6፡00 ሰዓት አካባቢ ወደ አንገር ሜጢ ቀበሌ በመሄድ ተኩስ ከፍተው 2 ሰዎችን ገድለው 14 ሰዎችን የአካል ጉዳት አድርሰዋል።

133. ይህንም ተከትሎ ግንቦት 14 ቀን 2017 ዓ.ም. ከሰዓት በኋላ ላይ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ የቀድሞ ልዩ ኃይል ልብስ የለበሱ ታጣቂዎች ወደ ሐረዋታ ቀበሌ በመምጣት የነዋሪዎችን ቤቶች ማቃጠል እና ከብቶቻቸውን መውሰድ በመጀመራቸው በቁጥር 5180 ሰዎች (740 አባወራ) ከቀበሌው ተፈናቅለው ወደ ኦዳ ጉዲና ቀበሌ አንገር ከተማ የሚገኝ የመንግሥት መጋዘን ማረፋቸውን ማረጋገጥ ተችሏል።

134. ግንቦት 27 ቀን 2017 ዓ.ም. ከቀኑ 7፡00 ሰዓት አካባቢ ሲሆን ጅማ ከተማ አጅፕ ባጃጅ ተራ ተብሎ የሚጠራ አካባቢ በሚሊሻ እና የባጃጅ ሹፌር ከሆነ ግለሰብ ጋር በተነሳ ጸብ በሚሊሻ ጭንቅላቱ የተመታ ሲሆን ይህን የሰማው የባጃጅ ሹፌሩ ወንድም ወደ ቦታው ሂዶ ለመገላገል

ሲል በሚሊሻ በተተኮሰ ጥይት ሆዱ ላይ ተመትቶ ሁለቱም ወንድማማቾች ሆስፒታል ገብተው የባጃጅ ሹፌሩ ሕይወቱ ማለፉን ለመረዳት ተችሏል።

## ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል

**135.** በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ነሐሴ 11 ቀን 2016 ዓ.ም. ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት ጀምሮ "የጉማይዴ ልዩ ወረዳ አስመላሽ" ተብሎ የሚጠራው እና በጋርዱላ ዞን ሀይበና ቀበሌ በዋናነት የሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ኃይል፣ ልዩ ወረዳ ይሰጠን በሚል በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ ኮንሶ ዞን፣ የሰገን ዙሪያ ወረዳ መቀመጫ የሆነችውን ሰገን ከተማን በመክበብ እና ተኩስ በመክፈት በፈጸመው ጥቃት የወረዳው ፖሊስ ጽሕፈት ቤት፣ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት እና ማዘጋጃ ቤት ሙሉ በሙሉ በእሳት ወድመዋል። የሰገን ሆስፒታል እና ሌሎች የመንግሥት ተቋማት ላይ ዝርፊያና ከፊል ውድመት ደርሷል። በተጨማሪም ብዛታቸው ለጊዜው በትክክል ያልታወቀ የወረዳው የፖሊስ አባላት እና ነዋሪዎች በዚሁ ቡድን በተፈጸመባቸው ጥቃት መገደላቸውን ኢሰመኮ አረጋግጧል።

**136.** መስከረም 2 ቀን 2017 ዓ.ም. በኮሬ ዞን ጎርካ ወረዳ ሻሮ ቀበሌ፣ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጉጂ ዞን ገላና ወረዳ መነሻቸውን ያደረጉ በቁጥር 13 የሚሆኑ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") ታጣቂዎች ወደ ኮሬ ዞን ጎርካ ወረዳ በመግባት 4 ሰዎችን ገድለዋል።

**137.** መስከረም 26 ቀን 2017 ዓ.ም. ኮሬ ዞን ጎርካ ወረዳ ዳኖ ቀበሌ፣ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጉጂ ዞን ገላና ወረዳ መነሻቸውን ያደረጉ ማንነታቸው ያልታወቀ የታጠቁ ኃይሎች በፈጸሙት ጥቃት 1 ሰው ተገድሏል።

**138.** መስከረም 27 ቀን 2017 ዓ.ም. ኮሬ ዞን ጎርካ ወረዳ ኬረዳ ቀበሌ፣ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጉጂ ዞን ገላና ወረዳ መነሻቸውን ያደረጉ ማንነታቸው ያልታወቀ የታጠቁ ኃይሎች በፈጸሙት ጥቃት 1 ሰው ተገድሏል።

**139.** ጥቅምት 2 ቀን 2017 ዓ.ም. ኮሬ ዞን ጎርካ ወረዳ ጎልቤ ቀበሌ፣ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጉጂ ዞን ገላና ወረዳ መነሻቸውን ያደረጉ ማንነታቸው ያልታወቀ የታጠቁ ኃይሎች በፈጸሙት ጥቃት 1 ሰው ተገድሏል።

**140.** ጥቅምት 4 ቀን 2017 ዓ.ም. ኮሬ ዞን ጎርካ ወረዳ ኬረዳ ቀበሌ፣ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጉጂ ዞን ገላና ወረዳ መነሻቸውን ያደረጉ ማንነታቸው ያልታወቀ የታጠቁ ኃይሎች በፈጸሙት ጥቃት 3 ሰዎች ተገድለዋል።

**141.** ታኅሣሥ 13 ቀን 2017 ዓ.ም. በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ኮሬ ዞን ጎርካ ወረዳ ቆሬ ቀበሌ፣ መነሻቸውን ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጉጂ ዞን ሱሮ ባርጉዳ ወረዳ ያደረጉ የታጠቁ ኃይሎች በፈጸሙት ጥቃት 2 ሰዎች የተገደሉ እና ከብቶቻቸው መዘረፋቸውን ኢሰመኮ አረጋግጧል።

**142.** በተመሳሳይ በዚሁ በኮሬ ዞን ጎርካ ወረዳ ኬረዳ እና ጃሎ ቀበሌዎች፣ መነሻቸውን ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጉጂ ዞን ገላና ወረዳ ባደረጉ የታጠቁ ኃይሎች ታኅሣሥ 28 እና 29 ቀን 2017 ዓ.ም. በተፈጸመ ጥቃት በድምሩ 2 ሰዎች መገደላቸውን እና ከብቶች መዘረፋቸውን ኢሰመኮ አረጋግጧል።

**143.** የካቲት 12 ቀን 2017 ዓ.ም. በደቡብ ኦሞ ዞን ዳሰነች ወረዳ ስየስ እና ቀቸም በተባሉ የኢትዮጵያና የኬንያ ድንበር አካባቢዎች ከኬንያ ወደ ኢትዮጵያ በገቡ የታጠቁ አካላት በተፈጸመ ጥቃት 13 ሰዎች ተገድለዋል፤ በሌሎች 3 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል። 6 የዓሳ ማስገሪያ ጀልባዎች ተዘርፈዋል። ጉዳዩን አስመልክቶ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በሰጠው ምላሽ በኬንያ ቱርካና ሐይቅ አካባቢ መንግሥት የጋራ መድረክ በመፍጠር ለግጭቱ

ምክንያት የሆኑ አካላትን በሕግ ተጠያቂ የማድረግ ሥራ እየተከናወነ ሲሆን በየጊዜው የሚከሰተውን ግጭት በዘላቂነት ለመፍታት ውይይት እየተደረገ መሆኑን ገልጿል።

**144.** የካቲት 29 እና መጋቢት 3 ቀን 2017 ዓ.ም. በኮሬ ዞን ጎርካ ወረዳ ጃሎ ቀበሌ፣ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጉጂ ዞን ገላና ወረዳ መነሻቸውን ያደረጉ ማንነታቸው ያልታወቀ የታጠቁ ኃይሎች በፈጸሙት ጥቃት 2 ሰዎች ተገድለዋል።

**145.** መጋቢት 19 ቀን 2017 ዓ.ም በጋሞ ዞን አርባምንጭ ዙሪያ ወረዳ ዘይሴ ወዘቃ ቀበሌ በተለያዩ መንደሮች ማንነታቸው ባልታወቁ የታጠቁ አካላት በአንድ ቤት ላይ በተለኮሰ እሳት ቃጠሎ የ2 ሕፃናት ሕይወት አልፏል።

**146.** በመጋቢት 22 ቀን 2017 ዓ.ም. በጋርዱላ ዞን ሆልቴ፣ ቀያማ፣ ኦኖታ እና ሃይበና ቀበሌያት ማንነታቸው ባልታወቁ የታጠቁ ኃይሎችና በተወሰኑ ነዋሪዎች መካከል በተፈጠረ ግጭት ቁጥራቸው በውል ያልታወቁ ሰዎች ሞተዋል።

**147.** ግንቦት 3 እና ግንቦት 21 ቀን 2017 ዓ.ም.በጋሞ ዞን አርባምንጭ ዙሪያ ወረዳ ዛይሴ ኤልጎ ቀበሌ ማንነታቸው ባልታወቀ የታጠቁ ቡድኖች 1 የክልሉ ፖሊስ አባል እና ሌላ 1 ሰው ተገድሏል።

### ትግራይ ክልል

**148.** በትግራይ ክልል በተለያዩ የሀገር ውስጥ ተፈናቃይ መጠለያ ጣቢያዎች በተለይ በሽረ እና በዓብይ ዓዲ ያሉ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ እርዳታ በእጅጉ በመቀነሱ ተፈናቃዮች ለሞትና ለተለያዩ በሽታዎች እየተዳረጉ ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ ምንም እንኳን በቅርቡ የደቡብ ትግራይና የጸለምት ተፈናቃዮች ወደ መኖሪያ አካባቢያቸው የተመለሱ ቢሆንም ከፍተኛ የጸጥታ ስጋት አለባቸው።

**149.** የካቲት 27 ቀን 2017 ዓ.ም. በግምት ከሌሊቱ 10:30 ሰዓት በደቡባዊ ዞን ጥሙጋ ከተማ በምትገኘው ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት ኃይሎች 4 ሰዎች ተገድለዋል በ4 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት መድረሱን ኢሰመኮ አረጋግጧል።

**150.** መጋቢት 1 ቀን 2017 ዓ.ም. የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት የነበሩት በከፍተኛ ወታደራዊ አዛዦች ላይ ጊዜያዊ እገዳ ማስተላለፋቸውን እንዲሁም የሕወሓት ተወካይ መሆናቸውን የሚገልጹ አካላት በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች የጊዜያዊ አስተዳደሩን የመንግሥት ተቋማት ለመቆጣጠር እንቅስቃሴ ማድረጋቸውን ተከትሎ በተፈጠረ አለመግባባት በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች በሰዎች ላይ ግድያ እና የአካል ጉዳት ደርሷል። ለምሳሌ በክልሉ ደቡባዊ ዞን መኾኒ ከተማ በተለምዶ መቐለ መውጫ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ኃራጅ በሚጠብቁ ሚሊሻዎች እና በትግራይ የጸጥታ ኃይሎች መካከል መጋቢት 7 ቀን 2017 ዓ.ም. በግምት ከምሽቱ 4:00 ሰዓት አካባቢ "የያዛችሁትን ንብረት አስረክቡ አናስረክብም" በሚል እንደጀመረ በተገለጸ ግጭት 1 ሚሊሻ እና የትግራይ የጸጥታ አባል ለሞት የተዳረጉ ሲሆን፣ በተጨማሪም ሌላ 1 ሰው ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል።

**151.** መጋቢት 2 ቀን 2017 ዓ.ም. በደቡብ ምሥራቅ ዞን የዓዲጉዶም ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር የከተማው ነዋሪዎች ሆነው ታጣቂ ለነበሩ ወጣቶች መሬት ለመስጠት ያደረገውን ጥሪ ተከትሎ በጥሪው ልንካተት ይገባናል ካሉ ከተወሰኑ ታጣቂዎች ጋር የተፈጠረውን አለመግባባት ለማብረድ ሚሊሻዎች ጥረት በማድረግ ላይ በነበሩበት ወቅት በሥፍራው የደረሱ የትግራይ ታጣቂዎች መካከል በነበረ የተኩስ ልውውጥ 4 ሰዎች በጥይት ቆስለው እንዲሁም 2 ተጨማሪ ሰዎች የአካል ጉዳት እንደደረሰባቸው ለመረዳት ተችሏል።

152.መጋቢት 3 ቀን 2017 ዓ.ም. በደቡብ ምሥራቅ ዞን ዓዲጉዶም ከተማ በሚገኝ የነዳጅ ማደያ ይሠራ የነበረ 1 ሰው ታጣቂዎች መጥተው ነዳጅ ቅዳልን ሲሉት የድጋፍ ደብዳቤ ካልያዛችሁ ብሎ በመጠየቁ በጥይት እንደገደሉት ኢሰመኮ አረጋግጧል።

# የነጻነት መብት



ዝርዝር የሰብአዊ መብቶች
ጉዳዮች

# ለ) የነጻነት መብት

153.በዘፈቀደ ያለመያዝ ወይም ያለመታሰር እና በሕግ ከተደነገገው ምክንያትና ሥርዓት ውጪ ነጻነትን ያለመነፈግ መብት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ሲያሳድር የቆየው የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጅ ቁጥር 6/2015 በ2016 በጀት ዓመት የመጨረሻ ወራት ተፈጻሚነቱ ማብቃቱን ተከትሎ ኢሰመኮ ባወጣው መግለጫ በአዋጁ አተገባበር ዐውድ ውስጥ በእስር የቆዩ ሰዎች እንዲለቀቁ ማድረግን ጨምሮ ወደ መደበኛው የሕግ አተገባበር ሂደት ለመመለስ እርምጃዎች እንዲወሰዱ፣ እንዲሁም በተለያዩ የክልል አካባቢዎች የተጣሉ የእንቅስቃሴ ገደቦች እንዲነሱ እና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች እንዲመለሱ ጥሪ አቅርቦ ነበር። በዚሁ መሠረት አዋሽ አርባን ጨምሮ በተለያዩ መደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ ማቆያዎች በቁጥጥር ሥር ውለው የነበሩ አብዛኛዎቹ ተጠርጣሪዎች ከእስር የተለቀቁ እና ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ የተደረጉ ቢሆንም፣ እስከ መስከረም ወር 2017 ዓ.ም. ድረስ በርካታ ሰዎች ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ታስረው እንደቆዩ ኢሰመኮ በወቅቱ ባወጣው ሪፖርት አመላክቷል።በበጀት ዓመቱ በነጻነት መብቶች ላይ እየተፈጸሙ የቀጠሉ ጥሰቶች ከዚህ በታች በተለያዩ ክፍሎች በዝርዝር ማሳያዎች ቀርበዋል።

### ግጭት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች በ"ኮማንድ ፖስት" እና በ"ወቅታዊ ጉዳዮች" በሚል የሚፈጸሙ እስሮች እና ተያያዥ የነጻነት መብት ጥሰቶች

154.በ2016 በጀት ዓመት ታውጆ የነበረው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከግንቦት 28 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈጻሚነቱ ያበቃ ቢሆንም፤ በአማራ ክልል የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ያለ በሚመስል መልኩ በሁሉም አካባቢዎች የዘፈቀደ፣ የጅምላና የተራዘመ እስር ቀጥሏል። በዚሁ ምክንያት እየተፈጸሙ ያሉ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በሚመለከት ኢሰመኮ በመስከረም 15 ቀን 2017 ዓ.ም.፣ በመስከረም 26 ቀን 2017 ዓ.ም. እና በጥር 16 ቀን 2017 ዓ.ም. ይፋ ባደረጋቸው ሪፖርቶቹ በስፋት ገልጿል።

155.በወቅቱ ከተያዙ ሰዎች ውስጥ ጥቂት ሰዎች ከሰዓታት ወይም ከቀናት እስር በኋላ ሲለቀቁ በርካታ ሰዎች በጊዜያዊ ማቆያነት በተመረጡ (በዳንግላ፣ ጭልጋ (ሰራባ ወታደራዊ ካምፕ)፣ ኮንቦልቻ እና ሸዋ ሮቢት ከተሞች በሚገኙ) ኢመደበኛ ማቆያ ሥፍራዎች እንዲቆዩ ተደርገው ነበር። ክስ እንዲመሠረትባቸው የተወሰነባቸው ጥቂት ሰዎች ከጊዜያዊ ማቆያ ማእከላቱ ወደ ማረሚያ ቤቶች ተዘዋውረው ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ሲደረጉ ሌሎች በርካታ እስረኞች ከወራት እስራት በኋላ በሂደት ተለቀዋል።

156.አማራ እና ኦሮሚያ ክልሎችን ጨምሮ ግጭቶች በሚካሄዱባቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች የዘፈቀደ እስሮች በ2017 በጀት ዓመትም ቀጥለዋል። በመያዙ ወይም በመታሰሩ ምክንያት ነጻነቱን የተነፈገ ማንኛውም ሰው ስለእስራቱ ሕጋዊነት እና ያለአግባብ መታሰሩ ከተረጋገጠም በነጻ እንዲለቀቅ እንዲወሰንለት ጉዳዩን ለፍርድ ቤት የማቅረብ መብት ያለው ቢሆንም በቁጥጥር ሥር ከሚውሉት ሰዎች አብዛኞቹ ይህ መብታቸው አይከበርላቸውም። ለምሳሌ በአማራ ክልል በደቡብ ጎንደር ዞን፣ ሊቦ ከምከም ወረዳ፣ አዲስ ዘመን ከተማ፣ ቀበሌ 03 ነዋሪ የሆኑትን አቶ አይቸው ፈረደ እና አቶ ይሰጣል ሻረው የተባሉ ሰዎች ሐምሌ 22 ቀን 2016 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት ላይ በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ተይዘው ፎገራ ወረዳ

ፖሊስ ጽሕፈት ቤት በአደራ ታስረው ቆይተው አቶ ይሰጣል መስከረም 6 ቀን 2017 ዓ.ም.፣ አቶ አይቸው ደግሞ መስከረም 8 ቀን 2017 ዓ.ም. ተለቀዋል፡፡

157.በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች ካለው የትጥቅ ግጭት ጋር ተያይዞ "ወቅታዊ ጉዳይ" በሚል ምክንያት ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ተይዘው በየፖሊስ ጣቢያዎች የሚገኙ በርካታ ሰዎች ያሉ ሲሆን የዋስትና መስፈርቱን በማሟላታቸው በፍርድ ቤት ዋስትና የተፈቀደላቸው ሰዎች በተወሰኑ ፖሊስ ጣቢያዎች አሁንም ተይዘው መገኘታቸው እንዲሁም ከአንድ ፖሊስ ጣቢያ ወደ ሌላ ፖሊስ ጣቢያ ተዛውረው ታስረው እንዲቆዩ መደረጋቸው አሳሳቢነቱ ቀጥሏል፡፡

158.በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፣ ጉራጌ ዞን፣ ወልቂጤ እና አበሽጌ ወረዳዎች እንዲሁም በዳልጋ ከተማ "በኦሮሚያ እና በማእከላዊ ኢትዮጵያ አካባቢ ባሉ ግጭቶች ተሳትፈዋል" እና "በግጭቱ ለተሳተፉ ሰዎች ድጋፍ አድርገዋል" በሚል ጥርጣሬ ከሐምሌ 28 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ በቁጥጥር ሥር ውለው የነበሩ 71 ወንዶች እና 11 ሴቶች ከ20 ቀናት በላይ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ በእስር እንዲቆዩ ተደርገዋል፡፡

159.ኢሰመኮ በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል አካባቢዎች የነጻነት መብትን ጨምሮ በሌሎችም መብቶች ላይ የሚደርሱ ጥሰቶችና ሥጋቶችን በተመለከተ በርካታ አቤቱታዎችን ሲቀበልና ሲመረምር የቆየ ሲሆን፤ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ሳይታወጅ ሰብአዊ መብቶች የሚታገዱበት አሠራር በብሔራዊም ሆነ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ማዕቀፎች መሠረት ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ ሁኔታው በሰዎች በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደኅንነት እና ነጻነት መብቶች ላይ ጥሰቶች የሚፈጸሙበትን በር ከፍቷል፡፡

160. በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ኮሬ ዞን ሰርማሌ ወረዳ፣ ጎርካ ወረዳ፣ ኬሌ ከተማ አስተዳደር፣ ኧሌ ዞን፣ እንዲሁም ቡርጂ ዞን ሶያማ ዙሪያ ወረዳ ፍርድ ቤቶች "በኮማንድ ፖስቱ የተጠረጠራችሁ ናችሁ" በሚል ምክንያት ሰዎች ለተራዘመ እስር እየተዳረጉ መሆኑን ኢሰመኮ በታኅሣሥ እና ጥር ወራት 2017 ዓ.ም. ባከናወነው ክትትል ለመረዳት ችሏል፡፡ ለምሳሌ በክልሉ ኧሌ ዞን እና ጋርዱላ ዞን "በኮማንድ ፖስት የተጠረጠራችሁ ናችሁ" ተብለው በቁጥጥር ሥር የዋሉ ሰዎች አካልን ነጻ የማውጣት አቤቱታ ሲያቀርቡ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ባልታወጀበት ስለአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ የሚደነግገውን የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 93 በመጥቀስ አቤቱታቸውን ውድቅ በማድረጋቸው ለተራዘመ እስር ተዳርገዋል፡፡

161.በሀገሪቱ በነጻነት መብት ላይ የሚፈጸሙ ጥሰቶች የአስገድዶ መሰወር እና ያሉበት ቦታ ሳይታወቅ ሰዎችን አስሮ የማቆየት ሁኔታዎችን የሚያካትቱ ናቸው፡፡ ኢሰመኮ በጉዳዩ ላይ በጥር ወር 2017 ዓ.ም. ባወጣው መግለጫ በተለያዩ አካባቢዎች የተፈጸሙ ጥሰቶች የመብት ሁኔታው የሚገኝበትን ደረጃ የሚያሳዩ መሆናቸውን በመጠቆም፤ "ከወቅታዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ" በሚል የተያዙና ተአማኒ ክስ ያልቀረበባቸው ታሳሪዎች እንዲሁም በማስገደድ የተሰወሩና ያሉበት ቦታ ሳይታወቅ የታሰሩ ሰዎች ሁሉ በአፋጣኝ ከእስር እንዲለቀቁ ወይም ጉዳያቸው በመደበኛው የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት እንዲታይ፣ የመንግሥት የጸጥታና የአስተዳደር አካላት በቁጥጥር ሥር የሚውሉ ሰዎችን በመደበኛ ማቆያዎች ብቻ እንዲይዙና የተያዙ ሰዎች ያሉበት ቦታና ሁኔታ ለቤተሰቦቻቸው እንዲገለጽ እንዲያደርጉ፤ እንዲሁም የአጥፊዎችን ተጠያቂነት እና የተጎጂዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ ውጤታማ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ጥሪ አቅርቧል፡፡

162.ኢሰመኮ ከመከላከያ ሰራዊት መስፈርቶች ውጪ "ለምልመላ" በሚል ሕፃናትን ጨምሮ ሰዎችን ከሕግ ውጪ መያዝን አስመልክቶ ኅዳር 26 እና ታኅሣሥ 8 ቀን 2017 ዓ.ም. ባወጣቸው ጋዜጣዊ መግለጫዎች፣ በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች ከኅዳር 4 እስከ 20 ቀን 2017 ዓ.ም. ያደረገውን ክትትል እና ምርመራ ግኝቶችን መሠረት በማድረግ ከመከላከያ ሰራዊት መስፈርቶች ውጪ "ለምልመላ" በሚል ሕፃናትን ጨምሮ በርካታ ሰዎችን በግዳጅ በመያዝ የተሳተፉ፣ የተያዙ ሰዎችን ለመልቀቅ የገንዘብ ክፍያ የጠየቁ ወይም የተቀበሉ እንዲሁም ይህንን ድርጊት የመከላከልና የመቆጣጠር ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ያልተወጡ የጸጥታና አስተዳደር አካላት ላይ ተገቢው ምርመራ ተደርጎ ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ አሳስቧል። በተጨማሪም በቀጣይ በኦሮሚያም ሆነ በሌሎች ክልሎች የሚከናወኑ የመከላከያ ሰራዊት አባላት ምልመላ ሥራዎች በሰራዊቱ መስፈርቶችና የአሠራር ሥርዓቶች መሠረት ብቻ ሕግን በተከተለ እና ሰብአዊ መብቶችን ባከበረ ሁኔታ መከናወናቸው እንዲረጋገጥ ምክረ ሐሳብ የሰጠ መሆኑ ይታወሳል።

163.ኢሰመኮ በምርመራው ግኝቶች እና ምክረ ሐሳቦች ላይ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሜቴ እና ከውጭ ግንኙነትና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አመራሮች እና አባላት ጋር ኅዳር 29 ቀን 2017 ዓ.ም. ምክክር አካሂዷል። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መከላከያ ሚኒስቴርም በሁሉም ክልሎች የሚከናወኑ የሰራዊት አባላት ምልመላ ሥራዎች በሕግ በተቀመጡት መስፈርቶች መሠረት ብቻ የተከናወኑ ስለመሆናቸው በማረጋገጥ የሚረከብ መሆኑን ለኢሰመኮ ኅዳር 30 ቀን 2017 ዓ.ም. በደረሰው ደብዳቤ ገልጿል።

### አንጻራዊ ሰላም ባለባቸው አካባቢዎች የሚፈጸሙ የነጻነት መብት ጥሰቶች

164.በአዲስ አበባ ከተማ የሚከበሩ ሕዝባዊና ሃይማኖታዊ በዓላት፣ የሚደረጉ ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ጉባኤዎች እንዲሁም ከሌሎች ተመሳሳይ ኹነቶች ጋር በተያያዘ ውሎና አዳራቸውን በጎዳና ላይ ያደረጉ ሰዎችን በኃይል በማንሳት በአንድ ስፍራ እንዲቆዩ የማድረግ፤ ወደመጡበት አካባቢ የመመለስ እንዲሁም በማእከሉ ከመቆየት እና የእርሻ ሥራ ከመሥራት እንዲመርጡ በማድረግ፤ የእርሻ ሥራ ለመሥራት የመረጡ ሰዎች በተለያዩ አካባቢዎች ወደሚገኙ እርሻ ጣቢያዎች ተወስደው እንዲሠሩ የማድረግ ጥሰቶችን አሳሳቢነት አስመልክቶ ኢሰመኮ ጥር 2 ቀን 2017 ዓ.ም. ባወጣው መግለጫ ድርጊቱ እንዲቆም አሳስቦ ነበር ።

165.በበጀት ዓመቱ የአስገድዶ መሰወር ድርጊትን ወይም ያሉበት ሳይታወቅ ሰዎችን አስሮ የማቆየት ጥሰቶችን ሊያቋቁሙ የሚችሉ ሁኔታዎችን ጨምሮ የዘፈቀደና ሕገ-ወጥ እስር ተግባራት አንጻራዊ ሰላም ባለባቸው አካባቢዎችም ቀጥሏል። ለምሳሌ፦ ከየካቲት 9 ቀን 2017 ዓ.ም. እስከ የካቲት 18 ቀን 2017 ዓ.ም. ባሉት ጊዜያት በምስረታ ላይ የነበረ የንጋት ኮከብ ለኢትዮጵያ የተባለ ፓርቲ አደራጅ ኮሚቴ አባላት የሆኑት አማኑኤል የማነብርሃን፣ ሰብስቤ ዓለሙ፣ ሱራፌል ብሩክ እና ክፍሎም ሀብቴ አስገድዶ መሰወርን ሊያቋቁም በሚችል ያሉበት ሁኔታ ሳይታወቅ በእስር ላይ ይገኛሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ አቶ ተስፋሁነኝ ከድር፣ አቶ ደረጀ ታደሰ ተሾመ፣ አቶ ዘላለም ወልደ ጨርቆስ በአዲስ አበባ ከተማ ልዩ ስሙ ዑራኤል እና ካዛንችስ አካባቢዎች በተጨማሪም አቶ ይስሀቅ ክንፈሚካኤል የካቲት 13 ቀን 2017 ዓ.ም. በሰመራ ከተማ በቁጥጥር ውለው ይህ ሪፖርት እስከ ወጣበት ጊዜ ድረስ የሚገኙበት እና ያሉበት ሁኔታ ሳይታወቅ በእስር ላይ ይገኛሉ።

166.በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከየካቲት 9 እስከ 11 ቀን 2017 ዓ.ም. በተካሄደው የክልል ምክር ቤት ጉባኤ የቀረበው ስለክልሉ ምክር ቤት መቀመጫ እና እያንዳንዱ ወረዳ ስለሚኖረው

የመቀመጫ ብዛት የሚደነግገው ረቂቅ ሕግ እንዳይጸድቅ የተቃወሙ የቦሮ ዴሞክራቲክ ፓርቲ (ቦዴፓ) አመራሮችና የክልሉ ምክር ቤት አባላት ለእስራት ተዳርገዋል:: የቦዴፓ አመራርና የክልሉ ምክር ቤት አባል የሆኑት አቶ ዮሐንስ ተሰማ ያለመከሰስ የሕግ ከለላቸው ባልተነሳበት እና የፍርድ ቤት የእስር ትእዛዝ ባልወጣበት ሁኔታ የካቲት 30 ቀን 2017 ዓ.ም. በክልሉ መንግሥት የጸጥታ አካላት ከሕግ አግባብ ውጪ በቁጥጥር ሥር ውለዋል:: ከአንድ ሳምንት እስር በኋላ በክልሉ ምክር ቤት ያለመከሰስ የሕግ ከለላቸው ተነስቶ በመጀመሪያ በአሶሳ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 2 ፖሊስ ጣቢያ ቆይተው ቀጥሎም በጊዜ ቀጠሮ በማረሚያ ቤት በእስር እንዲቆዩ ተደርገዋል:: ከዚህ ቀደም አቶ አጠይብ መሐመድ የተባሉ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት አባል ያለመከሰስ ከለላቸው ሳይነሳ እና የፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ ሳይወጣባቸው ተይዘው ለ15 ቀናት ታስረው ቆይተው ወደ ማረሚያ ቤት ተዛውረዋል::

**167.** በትግራይ ክልል የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር የቀድሞ ፕሬዚደንት በከፍተኛ ወታደራዊ አዛዦች ላይ ጊዜያዊ እገዳ ማስተላለፋቸውን እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ከፖለቲካ ፓርቲነት ምዝገባ መሰረዙ በምርጫ ቦርድ የተገለጸው የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) ተወካይ መሆናቸውን የሚገልጹ አካላት በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች የጊዜያዊ አስተዳደሩን የመንግሥት ተቋማት ለመቆጣጠር እንቅስቃሴ ማድረጋቸውን ተከትሎ በተፈጠረ አለመግባባት በክልሉ የዘፈቀደ እስራቶች ተፈጽመዋል:: ለምሳሌ መጋቢት 2 ቀን 2017 ዓ.ም. የምሥራቃዊ ዞን የጸጥታ ኃላፊ በትግራይ ታጣቂዎች የታሰሩና በነጋታው የተፈቱ ቢሆንም በድጋሚ ለቀናት ታስረው እንደተፈቱ ለማወቅ ተችሏል:: መጋቢት 3 ቀን 2017 ዓ.ም. የዓዲጉዶም ከተማ ከንቲባ የሆኑት ዓምዶም ወልዱ፣ የከተማዋ ምክትል ከንቲባ ወይዘሮ ዓወት ተወልደ፣ የከተማዋ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ይርጋ ሕሉፍ እና የከተማዋ ጸጥታ ኃላፊ የሆኑት አቶ አባዲ በትግራይ የጸጥታ ኃይሎች አራ ቆላ ወደ ተባለ ቦታ ተወስደው ከታሰሩ በኋላ በተመሳሳይ ዕለት ተለቀዋል:: መጋቢት 3 ቀን 2017 ዓ.ም. “የትግራይ የጸጥታ ኃይል አባላት” ናቸው የተባሉ ታጣቂዎች ወደ ሰሓርቲ ወረዳ ጊዜያዊ መስተዳድር በመሄድ “ማኅተማችሁን አስረክቡ፤ ሕግ ለማስከበር ነው የመጣነው” በሚል በተፈጠረ አለመግባባት የወረዳው የጸጥታ ጉዳይ ኃላፊ ሰለሞን እምባየ ከበደ እና የነጻነት ፓርቲ አባልና በወረዳው የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር የሆኑት መንገሻ ግርማይ መጋቢት 5 ቀን 2017 ዓ.ም. ታስረው ወደ አልታወቀ ቦታ ተወስደው የነበረ ቢሆንም ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ መጋቢት 5 ቀን 2017 ዓ.ም. ተፈትተዋል:: በዚሁ ወረዳ መጋቢት 8 ቀን 2017 ዓ.ም. አቶ ረታ አታኽልቲ ተኽለ የተባሉ የሳምረ ወረዳ የመንግሥት አገልግሎት ዘርፍ ኃላፊ በትግራይ ሰራዊት ባልታወቀ ሥፍራ ለቀናት ታስረው ተፈተዋል::

## በታጠቁ ቡድኖችና ሰዎች የሚፈጸሙ እገታዎች

**168.** በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ከሚፈጸሙ ሕገ ወጥ እና የዘፈቀደ እስር ጎን ለጎን በታጣቂ ቡድኖች እና ለዝርፊያ በተደራጁ ቡድኖች የሚፈጸሙ እገታዎች በኢትዮጵያ በሰዎች የነጻነት፣ የአካል ደኅንነት፣ በሕይወት የመኖር እና ሌሎች መሠረታዊ መብቶች ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን ቀጥለዋል:: በተለይም ኢሰመኮ በአማራና ኦሮሚያ ክልሎች ከተራዘሙ የትጥቅ ግጭቶች ጋር ተያይዞ በተወሰኑ አካባቢዎች የተፈጠረው የሕግ ማስከበር እና የመንግሥት መዋቅር መላላት ለእገታ ተግባራት ተስፋፍቶ መቀጠል ምቹ ሁኔታ መፍጠራቸውን ነሐሴ 28 ቀን 2016 ዓ.ም. በጉዳዩ ላይ ባወጣው መግለጫ አሳስቦ ነበር::

አጋቾች ሰላማዊ ሰዎችን በአብዛኛው በጉዞ (ትራንስፖርት) ላይ እያሉ አንዳንዴም ከመኖሪያ ቤታቸው ወይም ከሥራ ቦታቸው አግተው ወዳልታወቀ ቦታ በመውሰድ ከፍተኛ የማስለቀቂያ ገንዘብ ክፍያ እንደሚጠይቁ፤ ገንዘብ መክፈል ያልቻሉ በርካታ ታጋቾች ግድያን ጨምሮ በርካታ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እንደሚፈጸምባቸው፤ እገታው በአብዛኛው እንደ ገቢ ማስገኛ የተወሰደ መሆኑን፤ በተደጋጋሚ፣ በተንሰራፋና በተደራጀ መልኩ እንደሚፈጸም፤ አልፎ አልፎም እንደ በቀል፣ ለፖለቲካ ዓላማ ወይም የታገተ ሌላ ሰውን ለማስለቀቅ በሚል እንደሚፈጸም፤ በተለይ ታጋች ሴቶች ለአስገድዶ መደፈር እና ለተለያየ ጾታዊ ጥቃት እንደሚዳረጉ ተገልጿል፡፡

**169.** በአማራ ክልል ቃልኪዳን ግርማው የተባሉ የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን (አሚኮ) የቴሌቪዥን ክፍል ጋዜጠኛ ሐምሌ 2 ቀን 2016 ዓ.ም. ከመኖሪያ ቤታቸው ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች ታግተው መወሰዳቸው፤ በተመሳሳይ የአሚኮ ምክትል ሥራ አስፈጻሚ የሆኑት አቶ አንተነህ መንግሥቴን እና የአሚኮ የስትራቴጂክ ልማት ምክትል ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ደምሳቸው ፈንታን በክልሉ የሚንቀሳቀሰው ታጣቂ ቡድን (በተለምዶ “ፋኖ”) አባላት ነሐሴ 21 ቀን 2016 ዓ.ም. ወደ ሥራ ቦታ በመንቀሳቀስ ላይ እያሉ አግተው እንደወሰዷቸው እና ነሐሴ 27 ቀን 2016 ዓ.ም. መለቀቃቸው፤ እንዲሁም በነሐሴ ወር 2016 ዓ.ም. በሰሜን ሸዋ ዞን፣ ቀወት ወረዳ 1 የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጋዜጠኛ እና 3 የካሜራ ባለሙያዎች ማንነታቸው ባልታወቀ አካላት ታግተው ከ13 ቀናት በኋላ ነሐሴ 21 ቀን 2016 ዓ.ም. መለቀቃቸው፤ እንዲሁም ኅዳር 16 ቀን 2017 ዓ.ም. በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን፣ ጣርማ በር ወረዳ፣ መሃል አምባ አካባቢ የሚንቀሳቀሱ የታጣቂ ቡድን (በተለምዶ “ፋኖ”) አባላት አቶ ሳሙኤል ኪሮስ የተባሉ የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን የአዲስ አበባ ማእከል ዘጋቢ ላይ እገታ መፈጸማቸው ተረጋግጧል፡፡

**170.** የካቲት 5 ቀን 2017 ዓ.ም. በአማራ ክልል ሰሜን ጎጃም ዞን፣ ጎንጅ ቆለላ ወረዳ፣ በኮሬ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በማስተማር ላይ የነበሩ የኮሬ፣ የገረገራ እና የመንታ ደብር መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 12 መምህራን እና የሸባ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር (በአጠቃላይ 13 መምህራን) “ለምን ትምህርት አስጀመራችሁ” በማለት በአካባቢው በሚንቀሳቀሱ ታጣቂዎች (በተለምዶ “ፋኖ”) ከታገቱ በኋላ የካቲት 13 ቀን 2017 ዓ.ም. ተለቀዋል፡፡

**171.** መጋቢት 11 ቀን 2017 ዓ.ም. በሰሜን ጎጃም ዞን፣ ሰሜን ሜጫ ወረዳ መራዊ ከተማ አስተዳደር በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች እና በአካባቢው በሚንቀሳቀሱ የታጠቂ ቡድን አባላት (በተለምዶ “ፋኖ”) መካከል የተኩስ ልውውጥ ከተደረገ በኋላ ታጣቂዎቹ ከቀኑ 6:00 እስከ 7:00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ወደ ከተማው ዘልቀው በመግባት ከፈጸሚቸው ግድያዎች በተጨማሪ የወረዳው የጤና መድኅን አስተባባሪ ሆኖ ይሠራ የነበረን ሰው አግተው የወሰዱ መሆኑን የአካባቢው ነዋሪዎች አስረድተዋል፡፡

**172.** መጋቢት ወር 2017 ዓ.ም በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አዲስ ለተቋቋመው የደብረ ማርቆስ ምድብ ችሎት ዳኛ ሆነው የተሾሙት ሁለት ዳኞች በታጣቂዎች (በተለምዶ “ፋኖ”) ታግተው ከሳምንታት በኋላ ተለቀዋል፡፡ በክልሉ የሚካሄደውን የትጥቅ ግጭት ተከትሎ በተስፋፋው የጸጥታ ችግር ሳቢያ ሰዎች የደኅንነት ሥጋት ያለባቸው ሲሆን በተለያዩ የክልሉ ከተሞች የሚፈጸሙ እገታዎች፣ እገታውን ተከትሎ የሚቀርቡ የማስለቀቂያ ገንዘብ ክፍያ ጥያቄዎች እንዲሁም የመንገድ ላይ ዘረፋዎች በነዋሪዎች ሕይወት እና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሯል፡፡

**173.** በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን አሊ ዶሮ ከተማ መጋቢት 8 ቀን 2017 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ወደ ደብረማርቆስ ተሳፋሪዎችን ጭኖ በመጓዝ ላይ በነበረ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶብስ ላይ በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) ታጣቂዎች በተፈጸመ እገታ ሹፌሩን እና ረዳቱን ጨምሮ ሁሉም ተሳፋሪዎች ታፍነው ተወስደዋል። በዚሁ ዕለት በምዕራብ ሸዋ ዞን ከአቡና ግንደበረት እና ከግንደበረት ወረዳ ወደ ጊንጪ እንዲሁም ከጊንጪ ወደ ግንደበረት ይጓዙ በነበሩ 2 የሕዝብ ማመላለሻ እና 1 የጭነት ተሽከርካሪዎች ላይ በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) ታጣቂዎች በተፈጸመ እገታ ሹፌሮችና መንገደኞች ታፍነው ተወስደዋል።

**174.** መጋቢት 12 ቀን 2017 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ሱሉልታ ወረዳ ከጎርፎ ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኝ ሥፍራ በአንድ መለስተኛ የሕዝብ ተሽከርካሪ ላይ በተፈጸመ እገታ 8 ተሳፋሪዎች በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) ታጣቂዎች ታፍነው ተወስደዋል።

**175.** ሚያዝያ 20 ቀን 2017 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ስሬ ወረዳ አሞላ ታቦ አካባቢ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) ከአዳማ ከተማ ወደ ጮሌ ከተማ በጉዞ ላይ የነበረን የሕዝብ ማመላለሻ አውቶብስ ከስሬ ከተማ ‘አሞላ ታቦ’ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ በማስቆም፣ ሴቶችንና ሕፃናትን በመተው ቁጥራቸው በግምት 40 የሚሆኑ ተሳፋሪዎችን አግቶ ወደ ማይታወቅ ቦታ ወስዷል። ከተሳፋሪዎቹ አንድ ሰው በእገታ ወቅት ለማምለጥ ሲሞክር በታጣቂ ቡድኑ በተተኮሰበት ጥይት ተመቶ ተገድሏል።

**176.** ሚያዝያ 26 ቀን 2017 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ወለጋ ዞን ጊዳ አያና ወረዳ ዶሮ ቦሮ ቀበሌ “አንዶዬ ዲቾ” በተባለ ቦታ፣ በአማራ ክልል እና ኦሮሚያ አጎራባች አካባቢዎች የሚንቀሳቀሰው የታጠቀ ቡድን (በተለምዶ “ፋኖ”) ከጊዳ አያና ወደ አዲስ አበባ ከተማ በመጓዝ ላይ የነበረ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶብስ ውስጥ ያሉ ተሳፋሪዎችን በማገት ወደ ጫካ ይዞ በሚሄድበት ወቅት የተወሰኑት ሩጠው ሲያመልጡ 6 ሰዎች ታግተው ተወስደዋል። በተመሳሳይ ሚያዝያ 29 ቀን 2017 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት በዚሁ አካባቢ ከጊዳ አያና ወደ ጉትን በመጓዝ ላይ የነበረ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶብስ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) ታጣቂ ቡድን ተሳፋሪዎችን አስወርዶ የያዙትን ገንዘብና የተለያዩ ንብረቶች እንደወሰደ ማወቅ ተችሏል።

**177.** ሚያዝያ 30 ቀን 2017 ዓ.ም. ከነጌሌ ቦረና ወደ ጉሜ ኤልደሎ ወረዳ በሕዝብ ማመላለሻ አውቶብስ ሲጓዙ የነበሩ 22 የሚሆኑ አብዛኛዎቹ የወረዳው ግብርና ጽሕፈት ቤት እና የመንገድ ትራንስፖርትና ሎጂስትክ ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች የሆኑት ጉሚ ኤልደሎ ወረዳ ድንበር ላይ በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) ታጣቂ ቡድን ታግተዋል። ከታጋቾቹ መካከል የመኪናው ሹፌርና ረዳት እንዲሁም 2ቱ የታጣቂ ቡድኑ አባላት የነበሩና በሰላማዊ መንገድ ለመንግሥት እጅ የሰጡ መሆናቸውን ማወቅ ተችሏል።

**178.** ግንቦት 25 ቀን 2017 ዓ.ም. ሁለት የምዕራብ ጉጂ ዞን የመንግሥት ቢሮ ኃላፊዎች የሆኑት ቅጤሳ ዱቤ እና ከበደ ከሹፌራቸው አላማዮ ቦኮ ከቀርጫ ወረዳ ወደ ብርብርሳ ኮጆዋ ወረዳ በመጓዝ ላይ ሳሉ ብሊዳ ቀበሌ ላይ በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) ታጣቂዎች ተይዘው ሹፌሩ ወዲያው በታጣቂዎቹ በተተኮሰ ጥይት የተገደለ ሲሆን 2ቱ የመንግሥት ኃላፊዎች ማምለጥ ችለዋል። በተመሳሳይ ጊዜና ቦታ በወንጀል የተጠረጠረን 1 ሰው፣ 2 መደበኛ ፖሊሶችን፣ 1 ሚሊሻ እና 1 ኃላፊን ይዞ ሲጓዝ የነበረ ተሽከርካሪ በታጣቂዎቹ ተይዞ አንድ ፖሊስ በታጣቂ ቡድኑ በተተኮሰ ጥይት የተገደለ ሲሆን ሌላኛው

ፖሊስ ሲያመልጥ ቀሪዎቹ 3 ሰዎች በታጣቂ ቡድኑ ታግተው ተወስደዋል፡፡ በተመሳሳይ ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ በፖሊስ እና በታጣቂ ቡድኑ መካከል በነበረ የተኩስ ልውውጥ አንድ ሰው በጥይት ተመቶ ሕይወቱ ማለፉን ማወቅ ተችሏል፡፡

**179.** ግንቦት 27 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀጁ/አርቦዬ ወረዳ አርቦዬ ከተማ ነዋሪዎች የሆኑ ሰዎች ከማኅበር እየተመለሱ እያለ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") ታጣቂዎች በከፈቱባቸው ተኩስ በጋሻው ስዩም፣ ተስፉ አለሙ፣ ክፍሌ ገብረ ክርስቶስ እና ሳህሌ ሙሉጌታ የተባሉ ሰዎች ሕይወታቸው ሲያልፍ፣ ድንቁ ኃይሌ የተባሉ ሰው ከፍተኛ አካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ ታጣቂ ቡድኑ ከላይ በተገለጸው ስፍራ በዕለቱ የቀበሌው ሊቀ-መንበር የሆኑትን ሁሴን ረሺድ ባለቤት እና ልጃቸውን ጨምሮ የአካባቢውን ነዋሪዎች በማገት ወደ ጫካ ወስዶ ካቆየ በኋላ ሌሎች ነዋሪዎችን ሲለቅ፣ የቀበሌው ሊቀ መንበር ባለቤት ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ አልተለቀቁም፤ በሕይወት ስለመኖራቸውም አልተረጋገጠም፡፡

**180.** ግንቦት 29 ቀን 2017 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል ሱሉልታ ወረዳ በተለምዶ "ሙሎ መገንጠያ" ተብሎ የሚጠራ ቦታ ባለው ፋብሪካ 3 የቻይና ዜጎችን ጨምሮ ቁጥራቸው በውል የማይታወቁ ሠራተኞች በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") ታጣቂ ቡድን ታግተዋል፡፡

**181.** በጋምቤላ ክልል አኝዋ ብሔረሰብ ዞን ጎግ ወረዳ ቴዶ ቀበሌ ጥቅምት 4 ቀን 2017 ዓ.ም. ከጠዋት "አጉልመኖ" ተብሎ በሚጠራ ስፍራ በሙርሌ ታጣቂ ቡድኖች 2 ሕፃናት እና የካቲት 10 ቀን 2017 ዓ.ም. ከቀኑ 9፡00 ሰዓት 1 ሕፃን በኃይል ተይዘው ተወስደዋል፡፡ የካቲት 18 ቀን 2017 ዓ.ም. በኑዌር ብሔረሰብ ዞን አኮቦ ወረዳ ካንካን መንደር ከደቡብ ሱዳን በመጡ የሙርሌ ጎሳ ታጣቂዎች 2 ሴቶች ታግተው ተወስደዋል፡፡ መጋቢት 16 ቀን 2017 ዓ.ም. በጎግ ወረዳ ፒኙዶ ከተማ 04 ቀበሌ ውስጥ 5 የሚሆኑ ማንነታቸው ያልተወቀ የታጠቁ ቡድኖች ወደ አንድ ሰው መኖሪያ ቤት በመግባት በከፈቱት ተኩስ 1 ሰው በጥይት መትተው ከባድ የአካል ጉዳት በማድረስ 1 ሕፃን በኃይል ነጥቀው ወስደዋል፡፡ መጋቢት 28 ቀን 2017 ዓ.ም. ከቀኑ 11፡00 ሰዓት አካባቢ በጎግ ወረዳ ኡቴየል ቀበሌ ውስጥ የሙርሌ ጎሳ ታጣቂዎች 2 ሕፃናት አግተው ወስደዋል፡፡ በሌላ በኩል የካቲት 7 ቀን 2017 ዓ.ም. ከቀኑ 12፡00 ሰዓት አካባቢ አኝዋ ብሔረሰብ ዞን አቦቦ ወረዳ ፖዋተላም ቀበሌ ውስጥ ከደቡብ ሱዳን የመጡ የሙርሌ ታጣቂዎች 2 ሕፃናትን በኃይል በማስገደድ ከወሰዱ በኋላ የአካባቢው የጸጥታ ኃይል ባደረገው ክትትል ሁለቱም ሕፃናት በሦስተኛው ቀን መመለሳቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

**182.** በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ ዞን ባምባሲ ወረዳ መንደር 53 ቀበሌ ከአዋሳኝ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች የመጡ ታጣቂዎች የካቲት 6 ቀን 2017 ዓ.ም. 19 ሰዎችን አግተው የወሰዱ ሲሆን፤ 9 ሰዎች ወዲያውኑ ሲለቀቁ 10 ታጋቾች ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ያሉበት ሁኔታ አይታወቅም፡፡

# በጥበቃሥርያሉ (የታሰሩ) ሰዎች ሰብአዊ መብቶችአያያዝ



ዝርዝር የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች

## ሐ) በጥበቃ ሥር ያሉ (የታሰሩ) ሰዎች ሰብአዊ መብቶች አያያዝ

183.ኢሰመኮ በሕግ ከተሰጡት ሥልጣንና ኃላፊነቶች አንዱ ፖሊስ ጣቢያዎችን፣ ጊዜያዊ ማቆያ ቦታዎችን እና ማረሚያ ቤቶችን በመደበኛነት በመጎብኘት የታራሚዎችን እና የተጠርጣሪዎችን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታ መከታተል ነው:: ኢሰመኮ በሀገር አቀፍ ደረጃ በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ በ67 ማረሚያ ቤቶች እና 473 ፖሊስ ጣቢያዎች እንዲሁም 9 መደበኛ ያልሆኑ ማቆያ ስፍራዎች የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ክትትል አድርጓል:: ዝርዝሩ በሠንጠረዥ ውስጥ ቀርቧል::

| ተ.ቁ | ከተማ ጽ/ቤት | በፖሊስ ጣቢያ ላይ የተደረገ ክትትል | በማረሚያ ቤቶች ላይ የተደረገ ክትትል | ይፋዊ ያልሆኑ ማቆያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | አሶሳ | 32 | 4 | 2 |
| 2. | ጋምቤላ | 22 | 7 | 4 |
| 3. | ሃዋሳ | 139 | 6 | 3 |
| 4. | ጅግጅጋ | 38 | 8 | - |
| 5. | ጅማ | 137 | 18 | - |
| 6. | መቐለ | 31 | 10 | - |
| 7. | ሰመራ | 34 | 5 | - |
| 8. | ዋና ጽ/ቤት | 40 | 2 | - |
| 9. | ባህር ዳር | - | 7 | - |
| | ድምር | 473 | 67 | 9 |

ሆኖም በግጭቶችና የጸጥታ ችግሮች ሳቢያ ያለቅድመ ማስታወቂያ የሚደረጉ ድንገተኛ ጉብኝቶችን (unannounced visits) ጨምሮ የክትትል ተግባራትን በተሟላ ሁኔታ ለማድረግ አመቺ ሁኔታ ያልነበረ ከመሆኑ በተጨማሪ በተወሰኑ ቦታዎች ክትትል ለማድረግ ጥያቄ ቀርቦ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት አዎንታዊ ምላሽ አልተገኘም:: በዚህም ምክንያት ይህ ክፍል የዘርፉን ዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በተሟላ መልኩ አያሳይም::

184.በአዲስ አበባ ከተማ በ2016 በጀት ዓመት ተግባራዊ ከተደረገው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ አዋሽ አርባን ጨምሮ በተለያዩ መደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ ማቆያዎች ተይዘው የነበሩ አብዛኛዎቹ ተጠርጣሪዎች ከእስር የተለቀቁ እና ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ የተደረጉ መሆናቸው የሚበረታታ ነው። ሆኖም በእስር ቆይታቸው ለተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች የተዳረጉ መሆኑን ኢሰመኮ ለመረዳት ችሏል። ከዚህ በተጨማሪም ለበርካታ ወራት በእስር ቆይተው የተለቀቁ ሰዎች በእስር ለቆዩበት ጊዜ መረጃ ለማቅረብ ባለመቻላቸው ወደ ሥራቸውና ማኅበራዊ ሕይወታቸው ለመመለስ ከፍተኛ ችግር ያጋጠማቸው መሆኑን ኢሰመኮ ለመገንዘብ ችሏል።

185.በአፋር ክልል የፖሊስ አባላት በተጠርጣሪዎች ላይ የሚፈጽሟቸውን ድብደባዎች እና ሌሎች ኢ-ሰብአዊ ተግባራት ለመከላከል እንዲሁም ድርጊቱን በፈጸሙ የፖሊስ አባላት ላይ ተጠያቂነትን ለማስፈን የክልሉ ፖሊስ አመራሮች ቁርጠኝነት ማሳየታቸው አበረታች ነው። በጭፍራ ኮሪ አዋሽ አርባ ንኡስ ጣቢያ አርጎባ ልዩ ወረዳ ከአቅራቢያ ጤና ጣቢያዎች ጋር በተፈጠረ ስምምነት ለተጠርጣሪዎች ነጻ ሕክምና መጀመሩ፣ ክትትል በተደረገባቸው ሁሉም ፖሊስ ጣቢያዎች ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ እጅ ከፍንጅ ከሚያዙ ተጠርጣሪዎች በስተቀር በወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎች በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ እንዳይያዙ እና እንዳይታሰሩ ጥብቅ ክትትል በጣቢያ አዛዦች መደረጉ፣ ክትትል በተደረገባቸው በሁሉም ፖሊስ ጣቢያዎች የተጠርጣሪዎች ቃል የሚቀበሉ የፖሊስ አባላት ተጠርጣሪዎች ያለመናገር መብት እንዳላቸው እና የሚሰጡት ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት እንደሚቀርብባቸው መናገር መጀመራቸው በተጨማሪም ወጥነት ባይኖረውም በኢረብቲ፣ አፍዴራ በራህሌ፣ ቢዱ፣ አፋምቦ፣ ተላላክ፣ አርጎባ ልዩ ወረዳ፣ ያሎ እና ዱለቻ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያዎች ለተጠርጣሪዎች የምግብ አቅርቦት መጀመራቸው፤ ክትትል በተደረገባቸው በሁሉም ፖሊስ ጣቢያዎች ተጠርጣሪዎች አቤቱታ የሚያቀርቡበት ግልጽ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት ባይዘረጋም የፖሊስ አዛዦች በየዕለቱ እስረኞችን የሚጎበኙ እና ደኅንነታቸውን የሚያረጋግጡ መሆኑ እና በየፖሊስ ጣቢያው የነበሩ የሴት ፖሊስ አባላት ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ መሻሻሉ በጥበቃ ሥር የሚገኙ ሴቶችን አያያዝ ለማሻሻል ዕድል መስጠቱ ክትትል በተደረገባቸው የክልሉ ፖሊስ ጣቢያዎች የተለዩ መሻሻሎች ናቸው። ክልበቲ ረሱ እና አውሲ ረሱ ማረሚያ ቤቶች ውስጥ ለሚገኙት ክሊኒኮች አስፈላጊው የሰው ኃይል፣ የሕክምና መስጫ መሣሪያዎች እና መድኃኒት እንዲሟላ መደረጉ፤ በክልሉ በሚገኙ በሁሉም ማረሚያ ቤቶች ቀደም ሲል ከ36 ብር ወደ 50 ብር አድጎ የነበረው የአንድ ታራሚ የቀን የምግብ በጀት በ2017 በጀት ዓመት ወደ 100 ብር እንዲያድግ መደረጉ፤ በሃሪ ረሱ እና ገቢ ረሱ ታራሚዎች ከ1ኛ- 4ኛ ክፍል የቀለም ትምህርት የሚያገኙ መሆኑ፣በአውሲ ረሱ በልዩ ልዩ ማኅበራት በመደራጀት የሱቅ፣ ምግብ ቤት እና ሻይ ቡና ሽያጭ የመሳሰሉ ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎችን እየሠሩ የሚገኙ መሆኑ፤ በክልበቲ ረሱ ፈሳሽ ሳሙና በማምረት ታራሚዎች ገቢ የሚያገኙበት ሁኔታ መፈጠሩ። በአውሲ ረሱ ሃሪ ረሱ ክልበቲ ረሱ እና ገቢ ረሱ ታራሚዎች በማረሚያ ቤቶቹ አሠራር ላይ ለሚኖራቸው ቅሬታ እና አቤቱታ ጥያቄ የሚያቀርቡበት ሥርዓት መዘርጋቱ እና አፋጣኝ መፍትሔዎችን የመስጠት ጅማሮ መኖሩ፤ በሃሪ ረሱ፣ ክልበቲ ረሱ እና ፈንቲ ረሱ በልዩ ልዩ ማኅበራት በመደራጀት የሱቅ፣ ምግብ ቤት እና ሻይ ቡና ሽያጭ የመሳሰሉ ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎችን እየሠሩ የሚገኙ መሆኑ፤ በክልበቲ ረሱ ፈሳሽ ሳሙና በማምረት ታራሚዎች ገቢ የሚያገኙበት ሁኔታ መፈጠሩ ከተለዩት መሻሻሎች መካከል ናቸው። በአውሲ ረሱ ሃሪ ረሱ ክልበቲ ረሱ እና ገቢ ረሱ

ታራሚዎች በማረሚያ ቤቶቹ አሠራር ላይ ለሚኖራቸው ቅሬታ እና አቤቱታ ጥያቄ የሚያቀርቡበት ሥርዓት መዘርጋቱ እና አፋጣኝ መፍትሔዎችን የመስጠት ጅማሮ መኖሩ፤ በሃሪ ረሱ፣ ክልበቲ ረሱ እና ፊንቲ ረሱ ለታራሚዎች የይቅርታ አሰጣጥ ሂደቱን በተመለከተ ግልጽ የአሠራር ሥርዓት እና ግንዛቤ መፈጠሩ፣ በአውሲ ረሱ እና ገቢ ረሱ የማረሚያ ቤቶች ሕጎች እና ደንቦች ለታራሚዎች በጽሑፍ መሰጠታቸው፤ በገቢ ረሱ የማረሚያ ቤቱ የጥበቃ አባላት ታራሚዎችን ከመሳደብ፣ ማመናጨቅ እና መደብደብ ተግባራት መቆጠባቸው በበጀት ዓመቱ የተስተዋሉ መልካም እመርታዎች ናቸው፡፡

**186.** ሆኖም በክልሉ ክትትል ከተደረገባቸው 34 ወረዳ ፖሊስ ጣቢያዎች ውስጥ ከጭፍራ፣ ኮሪ፣ አዋሽ አርባ እና አርጎባ ልዩ ወረዳ በፖሊስ ጣቢያዎች ውጪ የሚታሰሩ ተጠርጣሪዎች የሕክምና አገልግሎት በመንግሥት ወጪ የሚያገኙበት ሁኔታ አለመኖር፤ ከደዌ ወረዳ ውጭ ተጠርጣሪዎች ከጠያቂዎቻቸው ጋር በቂ ቆይታ የሚያደርጉበት በቂ ስፋት ያለው የጥየቃ ቦታ አለመመቻቸት፤ በሁሉም ክትትል በተደረገባቸው ፖሊስ ጣቢያዎች ለተጠርጣሪዎች የሚቀርብ ፍራሽ፣ አልባሳት እና የንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁሶች አለመኖር፤ ከ ቢዱ፣ ኤሊደአር እና ደዌ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያዎች ውጭ ተጠርጣሪዎች ለሚመለከተው አካል አቤቱታ የሚያቀርቡበት ግልጽ የአሠራር ሥርዓት አለመዘርጋት፤ በአበአላ ከንቲባ፣ ቢዱ ወረዳ፣ ሰመራ ንኡስ፣ ሎግያ ንኡስ፣ አውራ ወረዳ፣ እዋ ወረዳ፣ ያሎ ወረዳ፣ አዋሽ ፈንታሌ ውረዳ፣ ገዋኔ ወረዳ እና ዱለቻ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያዎች ለተጠርጣሪዎች የሌሊት መጸዳጃ አገልግሎት አለመኖር እና የመጸዳጃ አገልግሎት ጊዜ ያነሰና በሰዓት የተገደበ መሆኑ ከተስተዋሉ አሳሳቢ ጉዳዮች ውስጥ ናቸው፡፡ እንዲሁም ከኢረብቲ ወረዳ፣ አሌደአር ወረዳ፣ ገዋኔ እና ገለአሎ ወረዳ ውጭ ባሉ ክትትል በተደረገባቸው ፖሊስ ጣቢያዎች በወንጀል ነክ ነገር ውስጥ ገብተዋል ተብለው የተጠረጠሩ ሕፃናት ለአካለ መጠን ከደረሱ ተጠርጣሪዎች ተለይተው የሚያዙበት የተለየ ክፍል አለመኖር፤ የአብዓላ ወረዳ፣ የአብዓላ ከንቲባ፣ አደአር ወረዳ፣ አይሳይታ ወረዳ፣ አይሳይታ ከንቲባ፣ ዱብቲ ከንቲባ፣ የዱብቲ ወረዳ፣ ዲችኦቶ፣ ጋላፊ፣ ኮሪ ወረዳ፣ ሰመራ ክፍለ-ከተማ፣ ሎግያ ክፍለ ከተማ፣ ዳለ ፋጌ ወረዳ፣ ዳዌ ወረዳ፣ አውራ ወረዳ፣ እዋ ወረዳ፣ አዋሽ ፋቲዓሌ ወረዳ፣ አዋሽ ከንቲባ፣ አሚበራ ወረዳ አዋሽ አርባ፣ ገዋኒ ወረዳ፣ ገላእሉ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያዎች ለተጠርጣሪዎች በመንግሥት ወጪ የሚቀርብ ምግብ አለመኖር፤ እንዲሁም በኤረብቲ ወረዳ፣ አፍዴራ ወረዳ፣ አብዓላ ወረዳ፣ አብዓላ ከንቲባ፣ በራህሌ ወረዳ፣ አደአር ወረዳ ኤሊውሃ፣ አይሳይታ ወረዳ፣ አይሳይታ ከንቲባ፣ ዱብቲ ከንቲባ፣ ዲችኦቶ፣ ኮሪ ወረዳ፣ ዳለ ፋጌ ወረዳ፣ ታላላክ ወረዳ፣ ዳዌ ወረዳ፣ አውራ ወረዳ፣ እዋ ወረዳ፣ ጎሊና ወረዳ፣ ያሎ ወረዳ፣ አዋሽ ፋቲዓሌ ወረዳ፣ አዋሽ ከንቲባ፣ አሚበራ ወረዳ አዋሽ አርባ፣ ገዋኒ ወረዳ፣ ዱለላሳ ወረዳ፣ ፖሊስ ጣቢያዎች የተጠርጣሪዎች ማደሪያ ክፍሎች የአየር ማቀዝቀዣ (ቬንቲሌተር) የሌላቸው መሆኑ ይገኙበታል፡፡

**187.** በተጨማሪም በአብዓላ ከንቲባ፣ አይሳይታ ወረዳ፣ አውራ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያዎችአይሳይታ ከንቲባ፣ እና አርጎባ ልዩ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያዎች የሴቶችና የወንዶች መጸዳጃ እና መታጠቢያ ክፍሎች አለመገንባት፤ ቢዱ ወረዳ፣ አፋምቦ ወረዳ፣ ዲችኦቶ፣ኮሪ ወረዳ፣ ሎግያ ክፍለ ከተማ፣ አውራ ወረዳ፣ እዋ ወረዳ፣ አዋሽ ፋቲዓሌ ወረዳ፣ አዋሽ ከንቲባ፣ ገዋኒ ወረዳ፣ ዱለላሳ ወረዳ፣ ፖሊስ ጣቢያዎች በመጸዳጃ ቤቶች የተጠራቀሙ ቆሻሻዎች ባለመወገዳቸው ምክንያት ንጽሕና የሌላቸው መሆን፤ የአብዓላ ከንቲባ፣ እና አይሳይታ ከንቲባ ፖሊስ ጣቢያዎችፖሊስ ጣቢያዎች ተጠርጣሪዎች በተያዙ በ48 ሰዓት ውስጥ ወደ ፍርድ ቤት ማቅረብ ላይ ክፍተቶች መኖር፤ የአብዓላ ከንቲባ፣ አፋምቦ ወረዳ፣ ኤሊዳር ወረዳ፣ ዲችኦቶ፣

ጋላፊ፣ ኮሪ ወረዳ፣ ሎግያ ክፍለ ከተማ፣ ታላላክ ወረዳ፣ ዳዌ ወረዳ፣ አዋሽ ፋቲዓሌ ወረዳ፣ አዋሽ ከንቲባ፣ ገዋኒ ወረዳ፣ዱለላሳ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያዎች ተጠርጣሪዎች የመጠጥና የንጽሕና መጠበቂያ ውሃ የሚያገኙበት ሁኔታ አለመኖር በበጀት ዓመቱ በክልሉ ፖሊስ ጣቢያዎች የታዩ ችግሮች ናቸው፡፡

188. ኢሰመኮ በበጀት ዓመቱ ክትትል ካደረገባቸው በክልሉ የሚገኙ ሁሉም ማረሚያ ቤቶች ለታራሚዎች የሚቀርበው ምግብ በቂ፣ የተመጣጠነ እና ጥራቱን የጠበቀ አለመሆኑን እንዲሁም የየእለት ምግብ ዝርዝር ለታራሚዎች በመመገቢያ እና ማደሪያ ክፍል በጽሑፍ አለመለጠፉን እና ንጹሕ የመጠጥና የንጽሕና መጠበቂያ ውሃ የሚያገኙበት ሁኔታ አለመመቻቸቱ ለማወቅ ችሏል፡፡ ከጤና አገልግሎት ጋር በተያያዘ የአንቡላንስ አገልግሎት በአውሲ ረሱ፣ ክልበቲ ረሱ፣ ፈንቲ ረሱ እና ገቢ ረሱ አለመኖሩን፤ በሁሉም ማረሚያ ቤቶች ወደ ማረሚያ ቤት በሚገቡበት ወቅት በተለይም ወንድ ታራሚዎች የጤና ምርመራ ተደርጎ መረጃቸው ከፋይላቸው ጋር እንደማይያያዝ፤ ክትትል በተድረገብቻእው ሁሉም ማረሚያ ቤቶች ለታራሚዎች ከማረሚያ ቤት ውጭ መገዛት ያለባቸው መድኃኒቶች በፍጥነት (በሐኪም በታዘዘበት ቀን) እንደማይቀርቡ እና መድኃኒት ሳያገኙ ለበርካታ ቀናት የሚቆዩ እንዳሉ ኢሰመኮ ተረድቷል፡፡ በተጨማሪም በአውሲ ረሱ፣ሃሪ ረሱ፣ ፈንቲ ረሱ እና ገቢ ረሱ ታራሚዎች በማደሪያ ክፍሎች ወቅቱን የጠበቀ የፀረ ተባይ ርጭት እንደማይከናወን፤ ተከታታይነት ያለው የቅድመ በሽታ መከላከል ትምህርት እንደማይሰጥ እንዲሁም የኤች.አይ.ቪ.፣ የስኳር እና ሌሎች በሽታዎች ተጠቂ ለሆኑ ታራሚዎች አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችን በበቂ ሁኔታ እንደማያገኙ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

189. በክልሉ በሚገኙ ማረሚያ ቤቶች ለታራሚዎች የቀረበ አልጋ እና አንሶላ የሌለ መሆኑን ለማየት የተቻለ ሲሆን፣ አልፎ አልፎ በለጋሽ ድርጅቶች ከሚቀርቡ ድጋፎች በስተቀር ታራሚዎች የልብስና የገላ ሳሙና እንዲሁም ሌሎች የንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን እንደማያገኙ፤ በማደሪያ ክፍሎች ውስጥ የተገጠሙ አብዛኞቹ የአየር ማቀዝቀዣዎች /ventilators/ ተበላሽተው መሥራት ያቆሙ በመሆኑ በአካባቢው ባለው ከፍተኛ ሙቀት ታራሚዎች እንደሚቸገሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

190. ለአካለ መጠን ላልደረሱ ታራሚዎች የተለዩ ማደሪያ ክፍሎች አለመመቻቸታቸው፤ ታራሚዎች እና በጊዜ ቀጠሮ የሚገቡ ተጠርጣሪዎች ቁጥር በመብዛቱ የተነሳ በአንድ ማደሪያ ክፍል ውስጥ እስከ 90 በላይ ሰዎች መመደባቸው፤ ለአካል ጉዳተኛ ታራሚዎች ፍላጎታቸውን መሠረት ያደረገ ልዩ ድጋፍና እንክብካቤ አቅርቦት አለመኖሩ፣ የአእምሮ ሕሙማን ታራሚዎች ከሌሎች ታራሚዎች ተለይተው የሚያዙበት እና ልዩ እንክብካቤ የሚያገኙበት ሁኔታ አለመመቻቸቱ፣ ለሚያጠቡ እናቶችና ለነፍሰጡር ታራሚዎች እና ከወላጆቻቸው ጋር ለሚኖሩ ሕፃናት በማረሚያ ቤቱ በኩል የሚደረግላቸው ልዩ ድጋፍ አለመኖሩ በክትትሉ ተለይቷል፡፡ ታራሚዎች ከጠያቂዎቻቸው ጋር የሚገናኙበት ምቹና ሰፋት ያለው ስፍራ ባለመዘጋጀቱ ሳቢያ የሚገናኙበት ሁኔታ ነጻነታቸውንና ምስጢራቸውን ያልጠበቀ መሆኑ፤ ቤተሰቦች ስለታራሚዎች ሁኔታ መረጃ የሚያገኙበት ወጥ ሥርዓት አለመዘርጋቱ፤ ለታራሚዎች የስፖርት ማዘውተሪያና መዝናኛ ቦታዎች አለመመቻቸታቸው፤ ታራሚዎችን ከማረምና ማነጽ አንጻር ይሰጡ የነበሩ ልዩ ልዩ የሙያ ስልጠናዎች ከመስከረም ወር 2016 ዓ.ም. ጀምሮ መቆማቸው፤ እንዲሁም የይቅርታ አሰጣጥ ሂደትን በተመለከተ የማረሚያ ቤት የሥራ ኃላፊዎች "ግልጽ የአሠራር ሥርዓት ፈጥረናል፤ ለታራሚዎችም ግንዛቤ ሰጥተናል" በማለት ለኢሰመኮ የገለጹ ቢሆንም አሁንም ግልጽነት

የሌለው መሆኑን ታራሚዎች ለኢሰመኮ አስረድተዋል። የማረሚያ ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ከጤና አገልግሎት እንዲሁም ከሙያ ስልጠናዎች ጋር የተያያዙ ክፍተቶች መኖራቸውን ተቀብለው በተለይም የበጀት እና ቁሳቁስ እጥረትን በምክንያትነት አንስተዋል።

191.**በአማራ ክልል** በጊዜያዊ ማቆያ ማእከላት ከ3 ወር ለሚበልጥ ጊዜ ታስረው ከቆዩ በርካታ ሰዎች መካከል ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ዕድሜአቸው ከ50 ዓመት በላይ የሆኑ እንዲሁም የከፋ የጤና ችግር ያለባቸው ሰዎች ታኅሣሥ 27 ቀን 2017 ዓ.ም. ከእስር ተለቀዋል። ኢሰመኮ እርምጃውን በበጎ የሚመለከተው ሲሆን ሌሎች በእስር ላይ የሚገኙ ሰዎችም የሰብአዊ መብቶችን መርሖዎችና ድንጋጌዎች ባከበረ መልኩ ፍርድ ቤት ቀርበው የተፋጠነ ፍትሕ እንዲያገኙ የማድረግን አስፈላጊነት የሚያስታውስ ነው። በግጭቶችና በጸጥታ ችግሮች በክልሉ ከ5 ማረሚያ ቤቶች በስተቀር በሌሎች ማረሚያ ቤቶች፣ ፖሊስ ጣቢያዎች እና ኢመደበኛ ማቆያ ሥፍራዎች ክትትል ማድረግ አልተቻለም።

192.ክትትል በተደረገባቸው ማረሚያ ቤቶች በተጠርጣሪዎችና ታራሚዎች ሰብአዊ መብቶች አያያዝ ረገድ የታዩ መሻሻሎች ያሉ ቢሆንም ከበጀት ውስንነት፣ ከአሠራር እና ከሕግ የሚመነጩ አሳሳቢ ጉዳዮች እንዳሉ ለመገንዘብ ተችሏል። በወንጀል ነክ ነገር ውስጥ ገብተው የተገኙ ሕፃናት/ታዳጊዎች ለአካለ መጠን ከደረሱ ሰዎች ጋር አብረው የሚያዙ መሆናቸው፤ የተወሰኑ ማረሚያ ቤቶች የተጨናነቁ መሆናቸው፤ ለታራሚዎች ለምግብ የሚመደበው በጀት ወቅታዊውን የገበያ ሁኔታ ያገናዘበ አለመሆኑ፤ በማረምያ ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ክሊኒኮች የሰው ኃይል፣ መድኃኒት፣ የሕክምና መሣሪያዎችና መገለገያ ቁሳቁሶች እና ላቦራቶሪ አለመሟላት፤ ታራሚዎች ለተሻለ ሕክምና ወደ አዲስ አበባ ከተማ እንዲሄዱ ሲታዘዙ (ሪፈር ሲባሉ) በበጀት እጥረት ምክንያት እና በጸጥታ ችግር የተነሳ መሄድ አለመቻላቸው፤ የጎንደር ማረሚያ ቤት በታራሚዎች በደረሰበት የመሠረተ ልማት ውድመት እንዲሁም የባሕር ዳር ማረሚያ ቤት ከጸጥታ ጋር በተያያዘ ትምህርትና የተግባር ስልጠና መቋረጡ፤ በፌደራል ፍርድ ቤቶች ተፈርዶባቸው በዝውውር አማራ ክልል ማረሚያ ቤቶች የሚገኙ ታራሚዎች የይቅርታ ተጠቃሚ አለመሆን፤ ማረሚያ ቤቶች ለአካል ጉዳተኛ ታራሚዎች አመቺና ተደራሽ አለመሆናቸው፤ የአእምሮ ሕሙማን ወደ አማኑኤል ሆስፒታል ልኮ ለማሳከም የበጀት እጥረት መኖሩ እና በጀት ቢገኝም ለዓመታት ወረፋ መጠበቅ የግድ መሆኑ ተጠቃሽ ናቸው።

193.**በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል** ኢሰመኮ የሚሰጣቸውን ምክረ ሐሳቦች ተቀብሎ ከመፈጸም አኳያ መሻሻሎች ታይተዋል። ከዚህም አንጻር በኢሰመኮ በተደረጉ ክትትሎችና በተሰጡ ምክረ ሐሳቦች ማንነት ላይ ያተኮሩ የጅምላና የዘፈቀደ እስር እየቀነሰ መምጣቱ፤ ለታራሚዎች የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎችን በወታደር በማጀብ ከጥቃት ለመጠበቅ ጥረት መደረጉ፤ የታራሚዎች ማቆያ ክፍሎችና የተጠርጣሪዎች ማረፊያ ክፍሎች ንጽሕና መሻሻሉ፤ በመተከል እና አሶሳ ዞን ማረሚያ ቤቶች የታራሚዎች መኖሪያ ክፍሎች ማስፋፊያ ግንባታ መደረጉ፤ በማረሚያ ቤቶች የአንድ ታራሚ የዕለት በጀት ከነበረበት 41 ብር ወደ 65 ብር ከፍ እንዲል መደረጉ፤ በፖሊስ ጣቢያ ከ48 ሰዓታት በላይ የሚቆዩ ተጠርጣሪዎች ቁጥር መቀነሱ፤ በፖሊስ ጣቢያዎች በፖሊስ አባላት የሚፈጸሙ ድብደባዎች እና ኢ-ሰብአዊ አያያዞች እየቀነሱ መምጣታቸው እንዲሁም በማረሚያ ቤቶች የታራሚዎች የሌሊት ሕክምና አገልግሎት መጀመሩ አዎንታዊ መሻሻሎች ናቸው።

194.ነገር ግን በክልሉ ኢሰመኮ በበጀት ዓመቱ ያደረጋቸው ክትትሎች እንደሚያሳዩት መጥሪያ፣ የፍርድ ቤት መያዣ እና የብርበራ ትእዛዝ የመሳሰሉ በሕግ የተቀመጡ ሁኔታዎች ሳይሟሉ

በቀላል ወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎችን ጨምሮ በርካታ ሰዎች በቁጥጥር ሥር ይውላሉ፡፡ የተያዙ ሰዎች የተጠረጠሩበት የወንጀል ድርጊት የማይገለጽላቸው ከመሆኑ በተጨማሪ በ48 ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብታቸው ሳይከበር ለረጅም ጊዜ በጣቢያዎች እንዲቆዩ ይደረጋሉ፡፡ በተወሰኑ ፖሊስ ጣቢያዎች በፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ሰዎች ለእስር ተዳርገው ቀናትን ያሳልፋሉ፤ የተወሰኑ ፖሊስ ጣቢያዎች የተጠርጣሪ ማቆያዎች አጥር የሌላቸው እና ያረጁ ከመሆናቸው የተነሳ ተጠርጣሪዎች በተለይ ሴቶች ለጥቃት ተጋላጭ ሊሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ አለ፡፡

195.በበጀት ዓመቱ በክልሉ ክትትል በተደረገባቸው ከ20 በላይ ፖሊስ ጣቢያዎች ለተጠርጣሪዎች የምግብ በጀት እና የሕክምና አገልግሎት አለመኖሩ ታውቋል፡፡ በአብዛኞቹ ፖሊስ ጣቢያዎች ውስጥ ተጠርጣሪዎች በተጨናነቀ ሁኔታ የሚያዙ ሲሆን ምንጣፍ እና ፍራሽ የመሳሰሉ የመኝታ ቁሳቁሶች ባለመሟላታቸው ምክንያት ወለል ላይ ለመተኛት ይገደዳሉ፡፡ ፖሊስ ጣቢያዎቹ ደረጃቸውን የጠበቁ የመጸዳጃና የመታጠቢያ ክፍሎች እንዲሁም ለንጽሕና መጠበቂያ የሚሆን በቂ ውሃና ቁሳቁስ አልተሟላላቸውም፡፡

196.በተለይም በቤኒሻንጉል ክልል ካማሽ ዞን ማረሚያ ቤትና ክትትል በተደረገባቸው ሁሉም የክልሉ ፖሊስ ጣቢያዎች በወንጀል ነክ ነገር ውስጥ ገብተዋል ተብለው የተጠረጠሩ/ገብተው የተገኙ ሕፃናት/ታዳጊዎች ለአካለ መጠን ከደረሱ ሰዎች ጋር አብረው የሚያዙ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ክትትል በተደረገባቸው ሁሉም የክልሉ ማረሚያ ቤቶች በቅበላ ወቅት የአደገኛነትና ልዩ ፍላጎት ሁኔታ ግምገማ ሳይደረግ ድልደላ የሚከናወን መሆኑ፤ ክትትል በተደረገባቸው ሁሉም ማረሚያ ቤቶችና ፖሊስ ጣቢያዎች ለነፍሰ ጡሮች፣ ከወላጆቻቸው ጋር ማረሚያ ቤት ለገቡ ሕፃናት እና ለሚያጠቡ እናቶች የሚደረግ ልዩ እንክብካቤ የሌለ መሆኑ፤ በቀላልና የዋስትና መብትን በማያስከለክሉ ወንጀሎች የሚያዙ ተጠርጣሪዎችን በፍጥነት ቃል ተቀብሎ በዋስ ከመልቀቅ ይልቅ ከብዙ ቀናት እስር በኋላ በነጻ የሚለቀቅበት ሁኔታ የሚስተዋል መሆኑ የኢሰመኮ የበጀት ዓመቱ ክትትል ከለያቸው አሳሳቢ ጉዳዮች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

197.በክልሉ በሚገኙ በሁሉም ማረሚያ ቤቶች ከምግብ ጥራት፣ ደረጃውን የጠበቀ መጠለያ ከማቅረብ፣ አልባሳት እና አስፈላጊ የመኝታና የንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን ከማሟላት እንዲሁም ከሕክምና በተለይም የሪፈር አገልግሎት ጋር የተያያዙ ውስንነቶች አሉ፡፡ በፖሊስ ጣቢያዎችም ምግብ፣ ንጹሕ የመጠጥ ውሃ እና ሕክምናን ጨምሮ ለተጠርጣሪዎች አስፈላጊ የሆኑ መሠረታዊ ሁኔታዎች አልተሟሉም፡፡

198.በክልሉ ክትትል በተደረገባቸው ሁሉም ማረሚያ ቤቶች ለትምህርት አገልግሎት የሚውሉ የመማሪያ መጻሕፍት፣ ጠረጴዛዎች፣ ኮምፒውተሮች፣ ቤተ ሙከራዎችና ቤተ መጻሕፍት ወዘተ. ባለመሟላታቸው ምክንያት ተደራሽና ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት አሰጣጥ ላይ ክፍተቶች ተስተውለዋል፡፡

199.የካማሽ ዞን ማረሚያ ቤት ክሊኒክ የባለሙያ፣ የቁሳቁስ እና የመድኃኒት እጥረት ያለበት በመሆኑ ለታራሚዎች ተገቢውን ሕክምና አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ እንዲሁም ሪፈር የሚባሉ ታካሚዎችን ወደሌሎች ከተሞች ወዳለ ሆስፒታል ለመውሰድ አለመቻሉ እና በመተከል ዞን ማረሚያ ቤት በማረሚያ ቤቱ በኩል የማይገዙ እንደ የቲቢ እና ወባን የመሳሰሉ በሽታዎች መድኃኒቶች እጥረት መኖሩ በበጀት ዓመቱ ከቀጠሉ አሳሳቢ ጉዳዮች መካከል ናቸው፡፡

200. **በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል** በምሥራቅ ጉራጌ ዞን እና በማረቆ ልዩ ወረዳ የሚገኙ 8 ፖሊስ ጣቢያዎች የተጠርጣሪዎች አያያዝ ላይ ኢሰመኮ በበጀት ዓመቱ ባደረገው ክትትል ከዚህ ቀደም በተደረጉ ክትትሎች መሠረት የተሰጡ ምክረ ሐሳቦችን ተግባር ላይ መዋል ተከትሎ ለውጦች የታዩ ሲሆን፦ ለምሳሌ ያህል ሁሉም ተጠርጣሪዎች ፍርድ ቤት መቅረባቸው፣ ከተጠርጣሪዎች ምዝገባ እና አያያዝ አንጻር መሻሻሎች መታያታቸው፣ በሁሉም ፖሊስ ጣቢያዎች ለተጠርጣሪዎች ምግብ የሚቀርብ መሆኑ፣ የፖሊስ ጣቢያ ኃላፊዎች፣ ዐቃብያነ ሕግ እንዲሁም የወረዳ ምክር ቤት አባላት በፖሊስ ጣቢያዎች በየወቅቱ ጉብኝት የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የታራሚን መሠረታዊ ፍላጎት ከማሟላት አንጻር ታራሚዎች የቀለምና የሙያ ትምህርት እንዲያገኙ እንዲሁም የጤና ሁኔታቸው እንዲጠበቅ በማድረግ ረገድ አወንታዊ መሻሻሎች ተስተውለዋል፡፡

201. በሌላ በኩል "በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል አካባቢ ባሉ ግጭቶች ተሳትፈዋል እና በግጭቱ ለተሳተፉ ሰዎች ድጋፍ አድርገዋል በሚል" ከሐምሌ 28 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ በቁጥጥር ሥር ውለው የነበሩ 71 ወንዶች እና 11 ሴቶች ከ20 ቀናት በላይ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ በእስር እንዲቆዩ መደረጋቸው፣ የተጠርጣሪዎች ማደሪያ ክፍሎች ንጽሕናቸው ያልተጠበቀ፤ በቂ ብርሃንና አየር የማያስገቡ፤ ፍራሽም ሆነ ምንም ዐይነት ምንጣፍ ያልተሟሉላቸው እና የተለያዩ ተባዮች ያሉባቸው መሆናቸው፤ በሁሉም ጣቢያዎች የንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁሶች አቅርቦት ችግር መኖሩ እንዲሁም በመንግሥት ወጪ የሚሰጥ የሕክምና አገልግሎት አለመኖሩ የተጠርጣሪዎችን ሰብአዊ መብቶች በማሟላት ረገድ የተለዩ ክፍተቶች ናቸው፡፡

202. **በጋምቤላ ክልል** ኢሰመኮ በ2017 በጀት ዓመት ክትትል በተደረገባቸው ሁሉም ማረሚያ ቤቶች እና ፖሊስ ጣቢያዎች ውስጥ የሚገኙ ታራሚዎች እና ተጠርጣሪዎች በቤተሰባቸው፣ በጠበቆቻቸው፣ በሃይማኖት አባቶቻቸው እና በሌሎች አካላት ያለምንም ክልከላ እንዲጎበኙ የተፈቀደ መሆኑ፤ በጎደሬና ጋምቤላ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያዎች አዳዲስ የተጠርጣሪዎች የማቆያ ክፍሎችን ጨምሮ የፖሊስ አባላት ቢሮዎች ተገንብተው አገልግሎት መስጠት መጀመራቸው፤ በዲማ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ ቀደም ሲል በር የሌለው በመሆኑ የደኅንነት ሥጋት የነበረበት የሴት ተጠርጣሪዎች ማደሪያ ክፍል ኢሰመኮ ባደረገው ውትወታ በር ተገጥሞለት አገልግሎት እየሰጠ መሆኑ፤ አላግባብ በሕግ ቁጥጥር ሥር ውለው የነበሩ ከ50 በላይ ሰዎች ከእስር መለቀቃቸው፤ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር ሲውሉ የተያዙበት ምክንያት የሚገለጽላቸው መሆኑ፤ በፍርድ ቤት የተፈቀደ ዋስትና በፖሊስ ጣቢያዎች የሚከበር መሆኑን፤ በጋምቤላ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ፣ በኢታንግ ልዩ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ የተጠርጣሪዎች ማቆያ ክፍሎች በመገንባት ላይ መሆኑ እና በጎደሬ ወረዳ የተጠርጣሪዎች ማቆያ ክፍሎች መገንባታቸው፤ በጋምቤላ ወረዳ ቦንጋ ቀበሌ ፖሊስ ጣቢያ መርማሪ ፖሊስ፣ ዐቃቢ ሕግ የተመደበ መሆኑ፤ ክትትል በተደረገባቸው ሁሉም ፖሊስ ጣቢያዎች ተጠርጣሪዎች ቋንቋ የማይረዱ ከሆነ አስተርጓሚ ተፈልጎ የሚተረጉምላቸው መሆኑ፣ በኑዌር ብሔረሰብ ዞን ጂካዎ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ አዲስ የመጸዳጃ ቤት መገንባቱ እንዲሁም በማጃንግ ብሔረሰብ ዞን ማረሚያ ቤት የውሃ አቅርቦት አገልግሎት መጀመሩ ከተስተዋሉት አወንታዊ እመርታዎች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡

203. በሌላ በኩል በጋምቤላ ክልል የሚገኙ ሁሉም ማረሚያ ቤቶች ለሕግ ታራሚዎች ምግብ የማያቀርቡ ሲሆን በምትኩ ከወቅቱ የገበያ ሁኔታ ጋር የማይመጣጠን 41 ብር ከ97 ሣንቲም ጥሬ ገንዘብ የሚሰጥ መሆኑ ታራሚዎችን ለበርካታ ችግሮች የሚዳርግ ነው፡፡ በክልሉ የሚገኙ አብዛኛው ማረሚያ ቤቶችና ፖሊስ ጣቢያዎች መኖሪያ ክፍሎች በርካታ ቁጥር

ያላቸውን ታራሚዎች ወይም ተጠርጣሪዎች በመያዛቸው ምክንያት የተጨናነቁ ከመሆናቸው ባሻገር የማደሪያ ክፍሎችንና መጸዳጃ ቤቶችን ጨምሮ ግቢዎቹ የንጽሕና ጉድለት ያለባቸው መሆኑ፤ በጋምቤላ ክልል አብዛኛው ማረሚያ ቤቶች የሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ ዝቅተኛ መሆኑ፣ በኑዌር ብሔረሰብ ዞን እና በጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ማረሚያ ቤቶች ለታራሚዎች የሚቀርበው ውሃ የንጽሕና ጉድለት ያለበት መሆኑ፤ በክልሉ የሚገኙ አብዛኛው ፖሊስ ጣቢያዎች እና ኢ-መደበኛ ማቆያዎች ውስጥ የመጠጥ እና የንጽሕና መጠበቂያ ውሃ አቅርቦት አለመኖሩ፤ በተለይም በተወሰኑ ፖሊስ ጣቢያዎች የመጠጥ ውሃ እና የመጸዳጃ ቤት አቅርቦት አለመኖሩ፣ በጋምቤላ ክልል የሚገኙ ሁሉም ማረሚያ ቤቶች እና ፖሊስ ጣቢያዎች አልጋ፣ ፍራሽ፣ አንሶላ፣ አጎበር የመሳሰሉ የመኝታ ግብአቶች ያልተሟላላቸው መሆኑ፤ በአኝዋ ብሔረሰብ ዞን ማረሚያ ቤት ውስጥ ክብርን የሚያዋርድ ቅጣት የሚፈጸም መሆኑ፤ የጋምቤላ ከተማ ፖሊስ ጣቢያን ጨምሮ በዲማ፣ አቦቦ፣ ላሬ፣ ዋንቱዋ፣ ጎግ፣ ጎደሬና ጋምቤላ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያዎች ተጠርጣሪዎችን በመያዝ ሂደት እና በቁጥጥር ሥር ከዋሉ በኋላ አልፎ አልፎ ድብደባ እና ኢ-ሰብአዊ አያያዝ የሚፈጸምባቸው መሆኑ፤ በአብዛኛዎቹ ፖሊስ ጣቢያዎች ተጠርጣሪዎች በ48 ሰዓት ውስጥ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ለተራዘመ ቀናት የሚታሰሩ መሆኑ፤ በተወሰኑ ማረሚያ ቤቶች በጊዜ ቀጠሮ ገብተው ከ1 እስከ 4 ዓመት ለሚደርስ ጊዜ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ የተቀመጡ ሰዎች መገኘታቸው፤ በክልሉ በሚገኙ ሁሉም ማረሚያ ቤቶች እና ፖሊስ ጣቢያዎች ልዩ ትኩረት ለሚፈልጉ ተጠርጣሪዎችና ታራሚዎች ፍላጎቶቻቸውን መሠረት ያደረገ ድጋፍና እንክብካቤ የማይደረግ መሆኑ፤ እንዲሁም ኢ-መደበኛ በሆኑ የማቆያ ማእከላት ውስጥ ሰዎችን አስሮ የማቆየት ልማድ መኖሩ ኢሰመኮ ከለያቸው አሳሳቢ ጉዳዮች መካከል ናቸው፡፡

**204.** **በኦሮሚያ ክልል** መንግሥትና “ጃል ሰኚ ነጋሳ” በተባሉ ግለሰብ በሚመሩ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) አባላት መካከል የተደረገውን ስምምነት ተከትሎ በክልሉ የምዕራብ፣ ምሥራቅ፣ ሰሜን እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች እንዲሁም በአርሲ ዞን ያለው የጸጥታ ሁኔታ መሻሻል ማሳየቱ፤ “ወቅታዊ ጉዳይ” በሚል በተራዘመ እስር ላይ የነበሩ ሰዎች ከእስር መለቀቅ መጀመራቸው እና አዳዲስ ሕገ ወጥ እስራቶችም መቀነሳቸው፤ ዕድሜቸው ለውትድርና ያልበቁ ሕፃናት ምልመላ አስመልክቶ ኢሰመኮ በደረሰው ጥቆማ መሠረት ተይዘው የነበሩ ሕፃናት ማጣራት በማድረግ እንዲለቀቁ መደረጉ፤ እንዲሁም በጅማ ዞን ጌራ ወረዳ፣ የወረዳው ወንጀል መከላከል ፖሊስ አባል አንድ ተጠርጣሪ ላይ ባደረሰው ድብደባ ኢሰመኮ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ባደረገው ውትወታ ተጠርጣሪው በፖሊስ ተይዞ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ መደረጉ ኢሰመኮ በመልካም እመርታነት የሚመለከተው ነው፡፡

**205.** በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች ካለው የትጥቅ ግጭት ጋር ተያይዞ “ወቅታዊ ጉዳይ” በሚል ምክንያት ተይዘው በየፖሊስ ጣቢያዎች የሚገኙ ሰዎች በሙሉ መፍትሔ አለማግኘታቸው፣ የዋስትና መስፈርቶችን በማሟላታቸው በፍርድ ቤት ዋስትና የተፈቀደላቸው ሰዎች በተወሰኑ ፖሊስ ጣቢያዎች አሁንም ተይዘው መገኘታቸው እንዲሁም ከአንድ ፖሊስ ጣቢያ ወደ ሌላ ፖሊስ ጣቢያ ተዛውረው ታስረው እንዲቆዩ መደረጋቸው አሳሳቢነቱ ቀጥሏል፡፡

**206.** **በሲዳማ ክልል** በይርጋለም ማረሚያ ቤት የነበረውን ከፍተኛ መጨናነቅ ለመቅረፍ በበንሳ ዳዬ ማረሚያ ቤት ግንባታ በማካሄድ ከ500 በላይ ታራሚዎችን መቀነስ መቻሉ፣ የታራሚዎች የምግብ በጀት ላይ ማሻሻያ መደረጉ፣ የውሃ ችግር መቀረፉ እና የትምህርት አሰጣጥ ተሻሽሎ እስከ 12ኛ ክፍል ማደጉ የተስተዋሉ አበረታች መሻሻሎች ናቸው፡፡ ክትትል

በተደረገባቸው ፖሊስ ጣቢያዎች ከተጠርጣሪዎች ምዝገባ፣ በ48 ሰዓት ውስጥ ፍርድ ቤት ከመቅረብ እንዲሁም ከተጠርጣሪዎች ኢ-ሰብአዊ አያያዝ አንጻር መሻሻሎች ተስተውለዋል፡፡

207. **በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል** የታራሚ የምግብ በጀት ማሻሻያ መደረጉ እና የአዳዲስ ማረሚያ ቤቶች ግንባታዎች መጀመራቸው በአዎንታዊ እመርታነት ተለይቷል፡፡ ነገር ግን ለታራሚዎች የተሻሻለውን በጀት ለሚመለከታቸው ማረሚያ ተቋማት በማውረድ ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ክፍተት መኖሩን ማወቅ ተችሏል፡፡

208. **በሶማሊ ክልል** ኢሰመኮ ለታራሚዎች ለምግብ የሚመደበው በጀት ወቅታዊውን የገበያ ሁኔታ ያገናዘበ እንዲሆን በሰጠው ምክረ ሐሳብ መሠረት፣ በጀረር እና ቆረሃይ ዞኖች ማረሚያ ቤቶች የታራሚዎች የምግብ በጀት በቀን 60 ብር የነበረው ወደ 100 ብር ከፍ እንዲል መደረጉ፤ እንዲሁም በቆረሃይ ዞን ማረሚያ ቤት ለታራሚዎች አጫጭር የቴክኒክና ሞያ ስልጠና እንዲሰጥ በተሰጠው ምክረ ሐሳብ መሠረት ስልጠናው መሰጠት መጀመሩ በምክረ ሐሳብ አፈጻጸም ክትትል ተረጋግጧል፡፡

209. **በትግራይ ክልል** በማረሚያ ቤቶች ከመደበኛ የወንጀል ሕግ ሂደት ውጪ ታስረው የቆዩ ሰዎች እንዲለቀቁ ለማስቻል የይቅርታ ደንብ እንዲወጣ መደረጉ፤ የሕክምና አገልግሎት መሻሻል መጀመሩ፤ ታራሚዎች ዕድሜና የወንጀል ቅጣት መጠንን በመሳሰሉ መስፈርቶች ተለይተው መያዛቸው እንዲሁም ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት መጀመሩ መልካም ጅማሬዎች መሆናቸው ታይቷል፡፡

210. በፖሊስ ጣቢያዎች ያሉ ተጠርጣሪዎች ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ መደረጋቸው፣ ተጠርጣሪዎች በ48 ሰዓት ውስጥ ፍርድ ቤት መቅረብ መቻላቸው፣ በፖሊስ የሚፈጸሙ ድብደባዎች መቀነሳቸው፣ ለሴት ተጠርጣሪዎች የተለየ ማቆያ ክፍል መኖሩ እና በሁሉም ፖሊስ ጣቢያዎች የምግብ አቅርቦት መጀመሩ አዎንታዊ መሻሻሎች ናቸው፡፡

211. በጦርነቱ በደረሰው ውድመት ምክንያት ማረሚያ ቤቶች የደረሰባቸው ጉዳት ከፍተኛ መሆኑ እና የዳግም ግንባታ፣ እድሳት እና ጥገና አለመጀመሩ፣ የበጀትና የተሽከርካሪ እጥረት፣ ለሠራተኞች የ17 ወር ደመወዝ አለመከፈሉ እና የማረሚያ ቤት ሠራተኞች እጥረት የታራሚዎች መብቶች ማስከበር ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖን ፈጥሯል፡፡ ከዚህ አልፎ በክልሉ ማረሚያ ቤቶች የፍራሽ አቅርቦት የለም፡፡

212. በፖሊስ ጣቢያ የበጀት፣ የሰው ኃይልና የተሽከርካሪ እጥረት፣ ለሠራተኞች የ17 ወር ደመወዝ አለመከፈል እና የወደመ ንብረት ጥገና እና ግንባታ ከማረሚያ ቤቶች ጋር ተመሳሳይ ሆኖ የውሃ እጥረት፣ የተጠርጣሪዎች ማደሪያ ክፍሎች፣ መታጠቢያና መጸዳጃ ቤቶች የንጽሕና ጉድለት ያለባቸው መሆኑ፤ እንዲሁም የማደሪያ ክፍሎች ከተጠርጣሪዎች ቁጥር አንጻር ተመጣጣኝ አለመሆኑ በተጠርጣሪዎች መብቶች አያያዝ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖን አሳድሯል፡፡

# የመደራጀት መብት እና የሲቪክ ተሳትፎ ምኅዳር



## ዝርዝር የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች

# መ) የመደራጀት መብት እና የሲቪክ ተሳትፎ ምኅዳር

213.የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን በኅዳር ወር 2017 ዓ.ም. የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማእከል፣ የሕግ ባለሙያዎች ለሰብአዊ መብቶች እና ስብስብ ለሰብአዊ መብቶች በኢትዮጵያ የተባሉ 3 በሰብአዊ መብቶች ላይ የሚሠሩ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶን "ከተቋቋሙበት ዓላማ ውጪ እና የሀገር ጥቅም የሚጎዳ እንቅስቃሴ ላይ ተሰማርተዋል" በሚል አግዷቸው ቆይቷል፡፡ ባለሥልጣኑ ታኅሣሥ 2 ቀን 2017 ዓ.ም. በጻፈው ደብዳቤ በ3ቱም የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ላይ የጣለውን እግድ አንስቶ የነበረ ቢሆንም ታኅሣሥ 7 ቀን 2017 ዓ.ም. በድጋሚ በጻፈው ደብዳቤ የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማእከልን እና የሕግ ባለሙያዎች ለሰብአዊ መብቶችን ከማንኛውም እንቅስቃሴ ለ2ተኛ ጊዜ አግዷል፡፡ በተጨማሪም ታኅሣሥ 14 ቀን 2017 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ በሰብአዊ መብቶች ላይ የሚሠሩትን የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ እና የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾች ማእከልን አግዷል፡፡

214.ኢሰመኮ የባለሥልጣኑን እርምጃ ተከትሎ ባወጣው መግለጫ "የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ላይ የሚተላለፉ ተደጋጋሚ እገዳዎች የሲቪክ ምኅዳሩን በማጥበብ በማኅበር የመደራጀት መብት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳያሳድሩ ባለሥልጣኑ የድርጅቶቹን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ አደጋ ላይ በማይጥል መልኩ የምርመራ ሥራዎቹን በተቻለ ፍጥነት አጠናቆ ወደ ሥራቸው የሚመለሱበትን ሁኔታ እንዲያመቻች" ጥሪ ማቅረቡ ይታወሳል፡፡

215.ኢሰመኮ በድርጅቶቹ እገዳ ላይ ባከናወነው ምርመራ የደረሰባቸውን ግኝቶች እና ምክረ ሐሳቦች ለሚመለከታቸው አካላት ያጋራ ሲሆን በተለይም ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን እና እገዳ ከተጣለባቸው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጋር ተደጋጋሚ ውይይቶችን አድርጓል፡፡ ይህንኑ ተከትሎ ባለሥልጣኑ የካቲት 24 ቀን 2017 ዓ.ም. በማኅበራቱ ላይ ጥሎት የነበረውን እገዳ አንስቷል፡፡

216.በሌላ በኩል በሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ ለመሥራት በምሥረታ ሂደት ላይ የሚገኙ ድርጅቶች ምዝገባ ምክንያታዊ ያልሆነ ረጅም ጊዜ እንደሚወስድ ኢሰመኮ ተገንዝቧል፡፡ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን "የአሠራር ሥርዓት ማሻሻያ (system upgrade) ማድረግ" ወይም "በጊዜያዊነት ምዝገባ ማቆም" በሚሉ ምክንያቶች ምዝገባና ፈቃድ የማግኘት ሂደታቸውን እንደሚያስተጓጉልባቸው እና በዚህም ምክንያት እስከ 1 ዓመት ለሚደርስ ጊዜ ምዝገባ ሳያገኙ የቆዩ መኖራቸውን ኢሰመኮ አረጋግጧል፡፡ በልማትና በማኅበራዊ ፕሮጀክቶች ላይ ያተኮሩ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምዝገባ በአግባቡ መከናወኑ የቀጠለ ሲሆን፣ በሌሎች ዘርፎች ላይ ምዝገባና ፈቃድ ለማግኘት በሂደት ላይ ያሉ ማኅበራት ተወካዮች ለምዝገባ በሚያመለክቱበት ወቅት የሰብአዊ መብቶች ተግባራትን ከመርኃ ግብሮቻቸው (ፕሮግራሞቻቸው) ዝርዝር ውስጥ እንዲያወጡ ባለሥልጣኑ የሚጠይቃቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

217.ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ የኅዳጣን ብሔረሰቦች መብቶች እንዲሁም ሌሎች ከወቅታዊ የፖለቲካዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዙ ዘርፎች ላይ የሚሠሩ የሲቪል ማኅበራት በመንግሥት አካላት ማስፈራሪያ እንደሚደርስባቸው እንዲሁም በተለያዩ ስልቶች የገንዘብ ልገሳ እንዳያገኙ እንደሚደረግ የኢሰመኮ የበጀት ዓመቱ ክትትሎች ያሳያሉ፡፡ የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበርን የመሳሰሉ የሠራተኛ ማኅበራት አመራሮች በመንግሥት ተቋማትና ባለሥልጣናት ለእንግልት

የሚዳረጉ ሲሆን፣ የማኅበራት አመራሮች የማደራጀት ሥራቸውን እንዲያቆሙ ጫና የሚደርስባቸው መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።

**218.**በሰኔ ወር 2017 ዓ.ም. ለውይይት የቀረበው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ማሻሻያ ረቂቅ ሕግ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያደርጉ የሚችሉ ድንጋጌዎችን ያልያዘ፤ በሲቪክ ምኅዳሩ እንዲሁም በማኅበር የመደራጀት መብት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር እንዳይሆን ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ አለበት። በተለይም ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በተመዘገቡበት ዓላማ መሠረት ሥራቸውን ማከናወናቸውን የመከታተልና የመቆጣጠር ሥልጣን ያለው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን በአዋጁ በግልጽ የተቀመጠውን የመደራጀት መብት በተሟላ ሁኔታ እንዲረጋገጥ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን የመፍጠር፤ ድርጅቶች ዐቅማቸው እንዲጎለብትና ተልዕኮአቸውን በብቃት እንዲወጡ የማስቻል የማበረታታትና የመደገፍ የመሳሰሉ ዐላማ በአግባቡ እንዲወጣ ለማስቻል የባለሥልጣኑ ከፍተኛ ወሳኔ ሰጪ የሆነው ቦርድ አደረጃጀት እና ስብጥር ቁልፍ ጉዳይ ነው። በዚህ አግባብ በቦርዱ አደረጃጀት እና ስብጥር ላይ የሚደረጉ ማሻሻያዎች በአዋጁ በግልጽ የተቀመጠ ዐላማውን በሚያጠናክርና ትርጉም ያለው የሴቶች እና የአካል ጉዳተኞች እንዲሁም የተጋላጭ ማሕበረሰብ ክፍሎች እና የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ውክልናን በሚያረጋግጥ አግባብ ማደራጀት፣ ላልተፈለገ ትርጉም እና አፈጻጸም የሚያጋልጡ ድንጋጌዎችን ማስቀረት፣ የሲቪክ ምኅዳሩን የሚያጣብቡ እንደ የምዝገባ እድሳት ግዴታ፣ ለተለያዩ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎቻቸው የባለሥልጣኑን ፈቃድ የማግኘት ግዴታን የሚጥሉ ድንጋጌዎች አለመኖራቸውን ማረጋገጥ፣ ከፖለቲካ እና ምርጫ ጋር ተዛማጅ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መሳተፍን፤ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን በነጻነት በመንቀሳቀስ ሀብት የማፍራት እና ንብረት የማንቀሳቀስ መብታቸውን የሚያጣብቡ ድንጋጊዎች አለማካተቱን ማረጋገጥ ይገባል። በተጨማሪም ጥፋት የፈጸሙ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ላይ የሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ላይ ለፍርድ ቤት አቤቱታ የሚቀርብበትን ሥርዓት መኖሩን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

**219.**ኢሰመኮ በተለይም እንደ ሽግግር ፍትሕ፣ ሀገራዊ ምክክር እና በ2018 ዓ.ም. እንደሚካሄድ በሚጠበቀው ሀገር አቀፍ ጠቅላላ ምርጫን የመሳሰሉ ለስኬታማ አተገባበራቸው ጠንካራ የሲቪል ማሕበረሰብ ድርጀቶችን ተሳትፎ እና ሚና የሚጠይቁ ሀገራዊ ጉዳዮች እየተካሄዱ ባለበት ሁኔታ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ላይ የሚደረግ ማሻሻያ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳያሳድር እንዲሁም የሲቪክ ምኅዳሩን እና በማኅበር የመደራጀት መብትን ተፈጻሚነት የሚያጣብብ እንዳይሆን በጥናት ላይ የተመሰረተ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጀቶች እና ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ትርጉም ያለው ተሳትፎ ባረጋገጠ እንዲሁም የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን ያከበረ ሊሆን እንደሚገባ ያሳስባል።

# ሌሎች የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች



## ሠ) ሌሎች የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች

220. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ 10 ቀን 2017 ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ የመገናኛ ብዙኃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 ማሻሻያ አዋጅን አጽድቋል። ኢሰመኮ በማሻሻያ አዋጁ ድንጋጌዎች ላይ በተለይም የቦርድ አደረጃጀት አመራረጥ አሿሿም እና ስብጥር ላይ እንዲሁም ፈቃድ የመስጠትና የመሰረዝ ሥልጣን በተመለከተ ማሻሻያ የተደረገባቸው ድንጋጌዎች የባለሥልጣኑ ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ የሆነውን ቦርድ የአባላት አመራረጥ እና ስብጥርን ሙሉ በሙሉ በመቀየር የመገናኛ ብዙኃን ተቆጣጣሪ አካል ነጻነትና ገለልተኛነትን ባላረጋገጠ አግባብ አዲስ ዐይነት ቦርድ የሚያዋቅር በመሆኑ እንዲሁም ፈቃድ የመስጠትና የመሰረዝ ሥልጣን መገናኛ ብዙኃን በሕግ አግባብ እንዲሠሩ በማስቻል የመገናኛ ብዙኃንን ህልውና የሚወስን በመሆኑ በባለስልጣኑ ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል በሆነ ቦርድ በኩል ሊታይ የሚገባ እንጂ በውክልና ሊሰጥ የሚገባ ሥልጣን አለመሆኑን በመግለጽ ዝርዝር አስተያየትና ምክረ ሐሳብ በጽሑፍ የላከ እና በአካልም አስረድቷል። ማሻሻያ አዋጁ በዚህ አግባብ የተስተካከለ ስለመሆኑ የተጸደቀው አዋጅ ታትሞ ስላልተሰራጨ ማረጋገጥ አልተቻለም።

221. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግሥት እና የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ ጨምሮ በሌሎች የሰብአዊ መብቶች ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ስምምነቶች የተረጋገጠው ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ትርጉም ያለው ጥበቃ የሚያገኘው የመገናኛ ብዙኃን በዴሞክራቲክ ማሕበረሰብ ያላቸው ሚና በአግባቡ መወጣት ሲችሉ ነው። መንግሥት ለመብቱ መከብር ጣልቃ አለመግባት ብቻ ሳይሆን የመገናኛ ብዙኃን ሚናቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ምቹ ሁኔታን ሲፈጥር ጭምር ነው። በዚህ ረገድ ለዴሞክራሲ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ሐሳቦችና አመለካከቶች በነጻ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ የመገናኛ ብዙኃን ተቆጣጣሪ አካል ነጻነትና ገለልተኝነትን በሕግ ማረጋገጥ ተቀዳሚ ተግባር ነው። ተቋማዊና የአሠራር ነጻነትን የሚረጋገጠው የተቆጣጣሪ አካል/የመገነኛ ብዙኃን ባለሥልጣን አባላት ምልመላ እና ሹመት/ምደባ አሳታፊ፣ የማሕበረስቡ ተውካዮች ውክልና ያለው መሆኑ በሕግ በግልጽ ሲቀመጥ፤ የመገናኛ ብዙኃንን የሚቆጣጠሩ አካላት ገለልተኛ እና ከማንኛውም አካል ጣልቃ ገብነት በተለይም ከፖለቲካ እና ኢኮኖሚያዊ ጣልቃ ገብነት ሲጠበቁ በተጨማሪም የተቆጣጣሪ አካል አባላት ምርጫ ግልጽ እና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ሲኖር በመሆኑ የሚደረጉ ማሻሻያዎች የባለሥልጣኑን አደረጃጀት፣ ተቋማዊና የአሠራር ነጻነቱን እንዲሁም ከፈቃድና ቁጥጥርን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ሐሳብን በነጽነት የመግለጽ መብትንና የመገናኛ ብዙኃን ነጽነት መብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖን እንዳያስከትሉ ጥብቅ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

222. በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልልም በመንግሥት ውሳኔ እና አሠራር ላይ ቅር በመሰኘት ተቃውሚቸውን በሰላማዊ ሰልፍ ለመግለጽ የሞከሩ ሰዎች ተከልክለዋል፣ እስራት ተፈጽሞባቸዋል። ለምሳሌ ኮሬ ዞን ከቀድሞው የአማሮ ልዩ ወረዳ አዲስ ወደተደራጀው ጎርካ ወረዳ ዝውውር የተሰጣቸው ከ200 የሚበልጡ የመንግሥት ሠራተኞች፣ የዝውውሩ አካሄድ ላይ የተሰማቸውን ተቃውሞ ለማሰማት ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ለኮሬ ዞን አስተዳደር እና ለኬሌ ከተማ አስተዳደር አመልክተው የነበሩ ቢሆንም ሰላማዊ ሰልፍ እንዳያካሂዱ ተከልክለዋል። በዚሁ ዞን አዲስ በተደራጀው ሰርማሌ ወረዳ "ደመወዛችን ያለ አግባብ ተቆርጦብናል" ያሉ መምህራንን በመወከል ቅሬታቸውን ለማሰማት ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ሰዎች

በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በመታሰራቸው፣ ይህን ለመቃወም የወረዳው መምህራን የተቃውሞ ሰልፍ ወጥተው የነበረ ሲሆን በመንግሥት ኃይሎች እንዲበተኑ ተደርጓል፤ ለእስራት የተዳረጉም ይገኙበታል፡፡ በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል 6 ዞኖች (ጋሞ፣ ጋርዱላ፣ ኮንሶ፣ ኧሌ፣ ኮሬ እና ቡርጂ) እንዲሁም በማእከላዊ ሕዝቦች ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ ዞን በተለምዶ 'ኮማንድ ፖስት' በሚባለው አስተዳደር ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ፣ የመሰብሰብ እና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት ላይ ገደቦች እንደሚደረጉ በኢሰመኮ ክትትል ተለይቷል፡፡

223.በአማራ ክልል በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የሚሠሩ ዳኞች ከዳኝነት ሥራቸው ጋር በተያያዘ በሚሰጡት ውሳኔና ትእዛዝ ሳቢያ በመንግሥት አስፈጻሚ አካላት ሕገ ወጥ እስራት፣ ጥቃት፣ ማስፈራራት እና ጣልቃ ገብነት እንደሚፈጸምባቸው፤ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡትን ውሳኔና ትእዛዝ አለማክበር እንደሚስተዋል እና ከዳኝነት ሥራቸው ጋር በተያያዘ የሚሰጧቸውን ውሳኔዎችና ትእዛዞች ተቀብሎ ያለመፈጸም ችግር መኖሩ በክትትል ተለይቷል፡፡ በኦሮሚያ ክልል እንዲሁ በዳኞች እና በዐቃብያነ ሕግ ላይ ለተጠርጣሪዎች ዋስትና "ፈቅዳችኋል" ወይም "እንዲፈቀድ ተባብራችኋል" በሚል እስራት፣ ድብደባ እና ማዋከብ እንደሚፈጸምና ይህም በአጠቃላይ የሰዎችን የፍትሕ ተደራሽነት እንደሚሸረሽር ኢሰመኮ ጥር 16 ቀን 2017 ዓ.ም. ባወጣው ሪፖርት ጠቁሟል፡፡

224. በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሀዲያ ዞን፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ዞን፣ በሲዳማ ክልል ደቡባዊ ሲዳማ እና ማእከላዊ ሲዳማ ዞኖች፣ ደመወዝ እና ሌሎች ክፍያዎች በአግባቡ አልተከፈለንም ያሉ የመንግሥት ሠራተኞች አቤቱታቸውን ለክልሉ የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት ቢወስዱም፣ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ ለመዳኘት ፈቃደኛ አለመሆኑን እና ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ይዘው የሄዱ የተወሰኑ የመንግሥት ሠራተኞች ላይ እስራት እና ከሥራ ማፈናቀል እንደተፈጸመባቸው ለኢሰመኮ አስረድተዋል፡፡

225. በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ኮሬ ዞን አዲስ በተደራጀው ጎርካ ወረዳ ከ2015 ዓ.ም. ወዲህ ብቻ ከ30 በላይ በሚሆኑ ሴቶች ላይ ጠለፋ የተፈጸመ ሲሆን ተበዳዮች እና ቤተሰቦቻቸው፣ አጥፊዎች በሕግ እንዲጠየቁ በተደጋጋሚ የዞኑን እና የወረዳውን የፍትሕ አካላት ቢጠይቁም፣ ጠለፋውን በፈጸሙት አብዛኞቹ አጥፊዎች ላይ ምንም ዐይነት የወንጀል ምርመራ አልተጀመረም፡፡

226. በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ኮሬ ዞን እና ቡርጂ ዞን ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጉጂ ዞን ጋር በሚዋሰኑባቸው አካባቢዎች በታጠቁ ሰዎች ሞት፣ የአካል ጉዳት፣ የንብረት መውደም፣ መፈናቀል እና ከእርሻ ሥራ መፈናቀል የተፈጸመባቸው ሰዎች አጥፊዎች በሕግ እንዲጠየቁና ለደረሰባቸው ጉዳት እንዲካሱ ክሶችን ለሚመለከታቸው የፍትሕ አካላት ቢያቀርቡም ተገቢውን ምላሽ አለማግኘታቸውን ማወቅ ተችሏል፡፡

227.በነጻነት ከመንቀሳቀስ መብት ጋር በተገናኘ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች እንዲሁም ሌሎች አካባቢዎች ወደ ክልሉ የሚመጡ ሰዎችን በጅምላ ማሰር እንዲሁም "የጸጥታ ሥጋት ይሆናሉ" በሚል ምክንያት ወደ መጡበት አካባቢ በኃይል የመመለስ ሁኔታዎች መኖራቸውን ኢሰመኮ በተለያዩ ጊዜያት ባደረጋቸው ክትትሎች ለማረጋገጥ ችሏል፡፡ በመተከል ዞን ማንዱራ፣ ድባጤ እና ቡለን ወረዳዎች ከጥር ወር 2017 ዓ.ም. ጀምሮ ማንነታቸው በውል ባልታወቁ ታጣቂዎች እና የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") እየተባለ በሚጠራው ታጣቂ ቡድን በሲቪል ሰዎች ላይ በሚፈጸም ግድያ፣ የሰዎች እገታና የንብረት ውድመት ሳቢያ እንዲሁም በክልሉ አልፎ አልፎ በሚፈጠር

የጸጥታ ችግርና ሥጋት ሰዎች ከቦታ ቦታ በነጻነት ለመንቀሳቀስና ለመኖር የደኅንነት ሥጋት ያለባቸው መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል።

**228.** በአማራ እና ኦሮሚያ ክልሎች በገጠራማ አካባቢዎች በሚገኙ ነዋሪዎች ላይ "ታጣቂዎችን ትደግፋላችሁ" ወይም "የቤተሰብ አባላችሁ የታጣቂው ቡድን አባል ነው" በሚል ወይም ሌላ ሕገ ወጥ ተግባር ውስጥ ተሳትፎ አላቸው በሚሉ ምክንያቶች ከመኖሪያ ቤታቸው የማስወጣት ተግባር የሚፈጸም መሆኑ፦ ለምሳሌ በአማራ ክልል ኅዳር 13 ቀን 2017 ዓ.ም. በደቡብ ጎንደር ዞን የሐሙሲት ከተማ አስተዳደር የጸጥታ አካላት የከተማው ነዋሪ የሆኑ 10 ሴቶችን "የፋኖ አባላት ሚስቶች ናችሁ" በሚል የመኖሪያ ቤታቸውን ከእነ ሙሉ ንብረቱ በማሸግ ከመኖሪያ ቤታቸው እንዲወጡ ተደርጓል። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ጥያቄ የቀረበለት የክልሉ መንግሥት በአካባቢው ታጥቀው ለሚገኙ ቡድኖች የሰላም ጥሪ መደረጉንና ይህንንም ለማሳካት የሕዝብ ግንኙነት ሥራ እየተሰራ ከመሆኑ ውጪ "የፋኖ ሚስት ናችሁ" በሚል የትዳር አጋሮቻቸው እጃቸውን ለመንግሥት እንዲሰጡ ለማስገደድ መኖሪያ ቤታቸውን ከነ ሙሉ ንብረቱ የማሸግ ተግባር አለመከናወኑን ገልጸዋል። የክልሉ መንግሥት ይህን ቢልም ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ 3 ሴቶች ብቻ ወደ መኖሪያ ቤታቸው የተመለሱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል።

### ምክረ ሐሳቦች

ኢሰመኮ ከላይ ባቀረባቸው በሕይወት የመኖር መብት፣ የነጻነት መብት፣ በጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎች መብት፣ የመደራጀት መብት እንዲሁም የሲቪክ ተሳትፎ ምኅዳርን ጨምሮ ሌሎች የሲቪልና የፖለቲካ መብቶችን በተመለከተ የሚከተሉትን ምክረ ሐሳቦች ያቀርባል፦

**229.** የመንግሥት ኃይሎች እንዲሁም ታጣቂዎች በሲቪል ሰዎች በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደኅንነትና ነጻነት እንዲሁም ንብረት መብቶች የሚያደርሷቸውን ጥሰቶች በአስቸኳይ እንዲያቆሙ፤

**230.** በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በመካሄድ ላይ በሚገኘው የትጥቅ ግጭት፣ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕጎች ጥሰት የፈጸሙ እና ያስፈጸሙ ኃላፊዎችን እና አባላትን እንዲሁም የታጣቂ ቡድኖች አባሎች ተጠያቂ ለማድረግ ተዓማኒ እና የሰብአዊ መብቶች ደረጃን የሚያሟላ የወንጀል ምርመራ እና የክስ ሂደት እንዲጀመር፤

**231.** በግጭቱ በሰው ሕይወት፣ በአካል፣ በሥነ-ልቦና እና በንብረት ላይ የደረሰውን ጉዳት በማጣራት ተጎጂዎች እንዲካሱ እና መልሰው እንዲቋቋሙ እንዲደረግ፤

**232.** ተዓማኒ ክስ ያልቀረበባቸው ታሳሪዎች እንዲሁም በማስገደድ የተሰወሩና ያሉበት ቦታ ሳይታወቅ የታሰሩ ሰዎች ሁሉ ከእስር እንዲለቀቁ፣ የመንግሥት የጸጥታና የአስተዳደር አካላት በቁጥጥር ሥር የሚውሉ ሰዎችን በመደበኛ ማቆያዎች ብቻ እንዲይዙና ሁልጊዜም የተያዙ ሰዎች ያሉበትን ቦታና ሁኔታ ለቤተሰቦቻቸው እንዲገልጽ፤

**233.** መንግሥት በጸጥታ አካላቱ ላይ ብቻ ሳይሆን የታጠቁ ቡድኖችን ጨምሮ በ3ኛ ወገኖች ከእገታ ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን ለመከላከል እንዲሁም የአጥፊዎችን ተጠያቂነት እና የተጎጂዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ ውጤታማ እርምጃዎችን እንዲወስድ፤

**234.** በማረሚያ ቤቶች ከምግብ ጥራት፣ ደረጃውን የጠበቀ መጠለያ ከማቅረብ፣ አልባሳት እና አስፈላጊ የመኝታና የንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን ከማሟላት፣ ከሕክምና አገልግሎት

እንዲሁም ለነፍሰ ጡሮች፣ ከወላጆቻቸው ጋር ማረሚያ ቤት ለገቡ ሕፃናት እና ለሚያጠቡ እናቶች የሚደረግ ልዩ እንክብካቤ ጨምሮ ከእስረኞች አያያዝ ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶችን ምላሽ ለመስጠት በሀገሪቱ ለሚገኙ ማረሚያ ቤቶች ተገቢ የሆነ የበጀት ጭማሪ ማድረግ እንዲሁም በሂደት ማረሚያ ቤቶች የገቢ ምንጫቸውን በማስፋት የተለያዩ ወጪያቸውን የሚሸፍኑበትን አግባብ ማመቻቸት ይገባል፤

235.የመገናኛ ብዙኃን አዋጁ ላይ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ከዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መስፈርቶች፣ በተለይም የመገናኛ ብዙኃንን ነጻነት ግምት ውስጥ በማስገባት እንደገና እንዲገመገም እና ማሻሻያ እንዲደረግበት እንዲሁም መንግሥት ጥሰትን የማያስከትል የአፈጻጸም አቅጣጫን እንዲከተል፤

236.የሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾች ተገቢውን ጥበቃ እንዲያገኙ የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፍ ተዘጋጅተው ተግባራዊ እንዲደረጉ፤ የሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾች እና ጋዜጠኞች በተለይም ግጭት በሚካሄድባቸው እና "በኮማንድ ፖስት" በሚተዳደሩ አካባቢዎች ተገኝተው መረጃ እንዲሰበስቡና ሪፖርቶችን እንዲያቀርቡ እንዲፈቀድላቸው፤

237.በመሻሻል ላይ ያለው የሲቪክ ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ከዚህ በፊት የሲቪክ ምኅዳሩን ለማስፋት እና አሳታፊ ለማድረግ የተወሰዱ እምርጃዎችን በማይቀለብስ መልኩ እና በሕገ መንግሥቱ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ላይ የተቀመጡ የመደራጀት መብትን የሚመለከቱ መመዘኛዎችን በሚያሟላ መልኩ እንዲሻሻል እንዲደረግ፣

238.የመሰብሰብ እና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት በሀገራዊ ይሁን ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ እና አህጉር አቀፍ ሕጎች የተረጋገጠ እና በመንግሥት በዘፈቀደ ሊገደብ የሚገባው መብት እንዳልሆነ በመረዳት የመንግሥት የጸጥታ አካላት ይሄንን ክልከላ ከማድረግ እንዲታቀቡ ኢሰመኮ ያሳስባል።

# ለኢሰመኮ የቀረቡ አቤቱታዎች

ዝርዝር የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች



## ሯ) ለኢሰመኮ የቀረቡ አቤቱታዎች

**239.**ኢሰመኮ እንደ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም በራሱ አነሳሽነት ከሚያከናውነው የሰብአዊ መብቶች ምርመራ በተጨማሪ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በተመለከተ አቤቱታዎችን ያለምንም ክፍያ የመቀበልና የመመርመር እንዲሁም መፍትሔ የመስጠት ሥልጣን እና ኃላፊነት አለው::[1] ይህ ሥልጣንና ኃላፊነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በክልል ወይም በፌዴሬሽን ምክር ቤቶች፣ አልያም በማንኛውም ፍርድ ቤት በየትኛውም ደረጃ በመታየት ላይ ካሉ ጉዳዮች በስተቀር የሰብአዊ መብቶች መጣስን አስመልክቶ በማንኛውም ሰው ወይም ተቋም ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ሁሉ ያካትታል::[2] አቤቱታዎች ሊቀርቡ የሚችሉት መብቴ ተጥሶብኛል በሚል ማንኛውም ሰው ወይም በትዳር አጋሩ ወይም በቤተዘመዱ ወይም በወኪሉ ወይም በሦስተኛ ወገን አማካኝነት ሲሆን፣ ኢሰመኮ እንደተፈጸመው የሰብአዊ መብት ጥሰት ጉዳይ ክብደት የአመልካች ማንነት ሳይገለጽ የሚቀርብ አቤቱታን የሚቀበልበት አሠራር በሕግ ተደንግጓል::

**240.** በዚህ መሠረት ኢሰመኮ በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ በ1524 ሰዎች የቀረቡ 1258 አቤቱታዎችን ተቀብሎ አስተናግዷል:: በበጀት ዓመቱ በየጽሕፈት ቤቱ የቀረቡ አቤቱታዎች ብዛት በሠንጠረዡ ላይ ተመላክተዋል::

| አቤቱታው የቀረበበት የኢሰመኮ ከተማ ጽሕፈት ቤት | በ2017 በጀት ዓመት የቀረቡ አቤቱታዎች ብዛት |
|---|---|
| **አዲስ አበባ (ዋና መሥሪያ ቤት)** | 416 |
| **አሶሳ** | 47 |
| **ባሕር ዳር** | 121 |
| **ጋምቤላ** | 70 |
| **ሃዋሳ** | 168 |
| **ጅግጅጋ** | 28 |
| **ጅማ** | 273 |
| **መቀሌ** | 37 |
| **ሰመራ** | 98 |

ከአጠቃላይ አቤቱታ ካቀረቡ ሰዎች መካከል 77.2% ወንዶች ሲሆኑ የተቀሩት ሴቶች ናቸው:: ከእነዚህ ውስጥ 79 የሚሆኑት አቤቱታ አቅራቢዎች አካል ጉዳተኞች ናቸው::

**241.**ከተስተናገዱት 1258 ጉዳዮች መካከል 968 ጉዳዮች መፍትሔ ያገኙ ሲሆን 39 ጉዳዮች ደግሞ በተቋሙ ሥልጣን ሥር የሚወድቁ ቢሆንም የተሟላ መፍትሔ እንዲያገኙ ታስቦ በሌሎች ተቋማት እንዲስተናገዱ ተመርተዋል::

**242.** አቤቱታ ከቀረበባቸው የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች አብዛኞቹ (55.3%) የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ናቸው:: ከእነዚህም መካከል በእስር ላይ የሚገኙ ሰዎች መብቶች ጥሰቶች፣ የነጻነት መነፈግ፣ የተፋጠነ ፍትሕ እጦት እና በሕይወት የመኖር መብት ጥሰትን የሚመለከቱት ከፍተኛውን ቁጥር ይይዛሉ:: አቤቱታ ከቀረበባቸው ተቋማት መካከል ከፍተኛ ቁጥር

[1] ኢሰመኮን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 210/1992 (በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው)፣ አንቀጽ 6(4)፣ 22፣ 24 እና 26
[2] ኢሰመኮን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 210/1992 (በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው)፣ አንቀጽ 7

የሚይዙት የሕግ አስከባሪ አካላት ሲሆኑ 440 አቤቱታዎች በክልል እና ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽኖች፣ 67 አቤቱታዎች በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ 58 አቤቱታዎች በፌዴራል ማረሚያ ቤቶችና ኮሚሽን፣ 58 አቤቱታዎች በከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም 56 በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ላይ የቀረቡ ናቸው።

# ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች



ዝርዝር የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች

# ሰ) ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች

### ቁልፍ እመርታዎች

ከሰኔ 30 ቀን 2016 ዓ.ም. እስከ ሰኔ 30 ቀን 2017 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ በኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች ዘርፍ የተወሰኑ መልካም እመርታዎች ተመዝግበዋል። ከእነዚህም መካከል፦

**243.** ትምህርት የማግኘት መብት አፈጻጸምን በተመለከተ ሐምሌ 11 ቀን 2016 ዓ.ም. በኢሰመኮ አዘጋጅነት የትምህርት ሚኒስቴር፣ የክልል ትምህርት ቢሮዎች እንዲሁም የሴቶች እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርን ጨምሮ የሌሎች መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ተወካዮች በተገኙበት የምክክር መድረክ ግጭቶችን ጨምሮ በተለያዩ ምክንያቶች የወደሙ ትምህርት ቤቶችን መልሶ ለመገንባት እና ከትምህርት ገበታ ውጪ የሆኑ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ለመመለስ መግባባት ላይ መደረሱ፤

**244.** የትምህርት ሚኒስቴር በበጀት ዓመቱ ባቀረበው የ9 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት መሠረት ከቅድመ አንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ያሉ 6.3 ሚሊዮን ተማሪዎችን የምገባ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉ፤ በትምህርት ዘመኑ 5 ሺህ 906 ቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ 832 አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ፣ 712 ሁለተኛ ደረጃ በድምሩ 6 ሺህ 815 አዳዲስ ትምህርት ቤቶች መገንባታቸው፤ 22 ሺህ 348 ለሚሆኑ ከቅድመ አንደኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ያሉ ትምህርት ቤቶች ደግሞ እድሳት መከናወኑ፤ በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ከተጎዱ ትምህርት ቤቶች መካከል በአማራ ክልል 45 እና በአፋር ክልል 4 ትምህርት ቤቶች ተገንብተው መጠናቀቃቸው፤

**245.** ፍትሕ ሚኒስቴር ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የንግድ እና የሰብአዊ መብቶች ብሔራዊ የድርጊት መርኃ ግብር ዝግጅት አካል የሆነውን የመነሻ ጥናት ሥራ (baseline assessment) እያከናወነ መሆኑ በማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ዘርፍ በበጀት ዓመቱ ከተከናወኑ አዎንታዊ ተግባራት መካከል ነው። ፍትሕ ሚኒስቴር ከኢሰመኮ ጋር በመተባበር ከመጋቢት 30 እስከ ሚያዝያ 1 ቀን 2017 ዓ.ም. ባካሄደው የባለድርሻ አካላት የምክክር መድረክ ላይ የንግድ እና የሰብአዊ መብቶች ብሔራዊ የድርጊት መርኃ ግብር ዝግጅት አካል የሆነው የመነሻ ጥናት ሥራ (baseline assessment) ግኝቶች እንዲሁም የሌሎች አፍሪካ ሀገራት ተሞክሮዎች ቀርበው ውይይት የተደረገባቸው እና ቀጣይ የድርጊት መርኃ ግብሩ ሂደቶች ሰብአዊ መብቶች ተኮር እና አካታች በሆነ መልኩ ሊከናወኑ እንደሚገባ መግባባት ላይ መደረሱ፤

**246.** በበጀት ዓመቱ የተከናወኑ የተወሰኑ የሕግ ማሻሻያዎች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መብቶችን በማረጋገጥ ረገድ ቁልፍ እመርታዎች የታዩባቸው ናቸው። ለምሳሌ የጤና አገልግሎት አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1362/2017 የጤና መብትን በማረጋገጥ እንዲሁም የአገልግሎቱን ጥራትና ተደራሽነት በማጠናከር ረገድ አስተዋጽዖ ሊያደርጉ የሚችሉ ድንጋጌዎችን ይዟል። በተመሳሳይ የአጠቃላይ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1368/2017 ትምህርት የማግኘት መብትን መደንገጉ እና በተለይም የሰብአዊ መብቶች ይዘቶች የሆኑትን ጥራት፣ ተገኝነት፣ ተደራሽነት እና ተለማጭነትን ያካተተ መሆኑ መልካም እምርታ ነው። በተጨማሪም አዋጁ ዕድሜው ለትምህርት የደረሰ ማንኛውም ሕፃን በመንግሥት ትምህርት

ቤቶች የቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ የአንደኛ ደረጃና የመካከለኛ ደረጃ ትምህርትን በነጻ የመማር መብትና ትምህርቱንም የመከታተል ግዴታ ያለበት መሆኑን መደንገጉ፤

247. የቤት ሠራተኞችን የማኅበራዊ ዋስትና ተጠቃሚነት ማረጋገጥን ጨምሮ መሠረታዊ የመብት ጥሰቶችን በመቅረፍ ረገድ አስተዋጽዖ ሊያደርግ እንደሚችል የሚጠበቅ የቤት ሠራተኞችን የሥራ ሁኔታ የሚመራ ደንብ ለማርቀቅ በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በኩል ዝግጅት መጀመሩ፤ እንዲሁም

248. በ2009 ዓ.ም. መቅረብ የነበረበትን 4ኛ ወቅታዊ ሪፖርት ጨምሮ የኢትዮጵያ የዓለም አቀፉ የኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና የባህል መብቶች ቃል ኪዳን አፈጻጸም ጥምር ሪፖርት ረቂቅ ተዘጋጅቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት እየተደረገበት መሆኑ ተጠቃሽ ቁልፍ እመርታዎች ናቸው።

### አሳሳቢ ጉዳዮች

249. በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች እየተካሄዱ ያሉ የትጥቅ ግጭቶች እና የጸጥታ መደፍረስ ሁኔታዎች፣ ተያይዘው የሚከሰቱ የንብረትና መሠረተ ልማት ውድመቶች፣ የእንቅስቃሴ ገደብና የምርት ሥራ መቀዛቀዝ ሁኔታዎች እንዲሁም ድርቅና ጎርፍን ጨምሮ በበጀት ዓመቱ ያጋጠሙ የተፈጥሮ አደጋዎች በማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደራቸውን ቀጥለዋል። በመስከረም ወር 2017 ዓ.ም. በአብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ክልሎች የተከሰተው ከባድ ጎርፍ ለምሳሌ በአፋር፣ ጋምቤላ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ ሶማሊ እና ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ክልሎች ከፍተኛ የንብረት ውድመት እና መፈናቀልን አስከትሏል።

250. በበጀት ዓመቱ አሳሳቢ ሆነው ከቀጠሉት የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ጉዳዮች መካከል አንዱ በቂ ምግብ የማግኘት መብት ነው። የጸጥታ ችግሮችና የትጥቅ ግጭቶች፣ ድርቅን ጨምሮ የተፈጥሮ አደጋዎች፣ በተለይም በምግብ ፍጆታዎች ላይ የሚስተዋለው የዋጋ ንረት ምክንያት የምግብ ዋስትና እና የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ተስተውሏል። የኢትዮጵያ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን መረጃ እንደሚያመለክተው በበጀት ዓመቱ በተለይም ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች በሆኑ ሕፃናት ላይ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ተስተውሏል።

251. ኢሰመኮ በ2016 በጀት ዓመት ባወጣው ዓመታዊ የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተከሰቱና በቀጠሉ ግጭቶች እንዲሁም የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት በርካታ ቁጥር ያላቸው ሕፃናት ከትምህርት ገበታ ውጭ መሆናቸውን እና በርካታ ትምህርት ቤቶችም አገልግሎት መስጠት ማቆማቸውን ገልጾ ነበር። በ2017 በጀት ዓመት መጀመሪያ ኢሰመኮ ትምህርት የማግኘት መብት አፈጻጸምን በተመለከተ በተለያዩ ክልሎች ባሉ አሳሳቢ ሁኔታዎች እና ሊወሰዱ በሚገባቸው የመፍትሔ እርምጃዎች ላይ የባለድርሻ አካላት ምክክር አድርጎ የነበረ ሲሆን፤ በአማራ ክልል 4178፣ በትግራይ ክልል 648፣ በኦሮሚያ ክልል 420፣ በሶማሊ ክልል 195፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 50፣ በጋምቤላ ክልል 40፣ በአፋር ክልል 26 እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል 8 ትምህርት ቤቶች መዘጋታቸው ተገልጾ ነበር። ሁኔታው ተጨባጭ መሻሻል ሳያሳይ በዚህኛው የትምህርት ዘመንም የቀጠለ ሲሆን ለምሳሌ የትጥቅ ግጭት በሚካሄድበት አማራ ክልል ብቻ በክልሉ ትምህርት ቢሮ መረጃ መሠረት ከ3 ሺህ 600 በላይ ትምህርት ቤቶች ተዘግተው ይገኛሉ።

252. በመጋቢት ወር 2017 ዓ.ም. በመላ ሀገሪቱ ከ7.8 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታ ውጪ መሆናቸውን እንዲሁም በአማራ ክልል ብቻ ከ3700 በላይ ትምህርት ቤቶች በክልሉ በሚካሄደው ግጭት ሳቢያ አገልግሎት እንደማይሰጡ የትምህርት ሚኒስትሩ ገልጸዋል፡፡ በአማራ ክልል ከ4.5 ሚሊዮን በላይ እንዲሁም በትግራይ ክልል ከ1.2 ሚሊዮን በላይ ሕፃናት ከትምህርት ገበታ ውጪ መሆናቸውን የየክልሎቹ ትምህርት ቢሮዎች መግለጻቸው ችግሩ ያለበትን አሳሳቢ ሁኔታ የሚያሳይ ነው፡፡ በተጨማሪም የመምህራን ደመወዝ በወቅቱ እና በአግባቡ ካለመከፈሉ፣ በሰው ሠራሽ እና የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት የተፈናቀሉ ሰዎች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ከመዘጋታቸው እንዲሁም ከሌሎች ተዛማጅ ምክንያቶች ጋር ተያይዞ በትምህርት መብት አፈጻጸም ላይ ያሉ ክፍተቶች የቀጠሉ ሲሆን፤ ከትምህርት ገበታ ውጪ የሚሆኑ ሕፃናት በተለይም ሴት ሕፃናት ያለ ዕድሜ ጋብቻን ጨምሮ ለሌሎች ዘርፈ ብዙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እና ጥቃቶች ተጋላጭ እንደሚሆኑ፣ ከገጠር ወደ ከተማ እንደሚፈልሱ እና ለጉልበት ብዝበዛ፣ ለተለያዩ ሱሶች እንዲሁም ሥነ-ልቦናዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች እንደሚጋለጡ የኢሰመኮ ክትትሎች ውጤቶች ያመላክታሉ፡፡

253. በሀገሪቱ የቀጠሉ ሰው ሠራሽ እና ተፈጥሯዊ አደጋዎች አሉታዊ ተጽዕኖ በጤና መብቶች ዘርፍም ላይ ጉዳት ማድረሱን ቀጥሏል፡፡ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የወባ፣ ኮሌራ እና ኩፍኝ በሽታዎች በስፋት ተከስተዋል፡፡ የኢትዮጵያ የጤና ክላስተር የሚያዝያ ወር 2017 ዓ.ም. ሪፖርት ከጥር ወር እስከ ሚያዝያ ወር ባለው ጊዜ ብቻ በሀገሪቱ 1,978,505 የወባ በሽታ ክስተቶች እንደተመዘገቡ፣ 77 ሰዎች በበሽታው ምክንያት ሕይወታቸው እንዳለፈ ገልጿል፡፡ ወረርሽኙ በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች የተከሰተ ሲሆን፣ በተለይም ግጭት በሚካሄድባቸው እና የጤና አገልግሎት ሁኔታው በተጎዳባቸው አካባቢዎች ያለው ስርጭት አሳሳቢ ነው፡፡ በአማራ ክልል ከሐምሌ ወር 2016 ዓ.ም. እስከ ታኅሣሥ ወር 2017 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ከ1 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በወባ በሽታ መያዛቸውን የክልሉ የኅብረተሰብ ጤና ተቋም መረጃ የሚያሳይ ሲሆን፣ ይህም ከቀደመው በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር የበሽታው ስርጭት በ65 በመቶ መጨመሩን ያመለክታል፡፡ በኦሮሚያ ክልል ግጭት ባለባቸው አካባቢዎችም የወባ በሽታ ስርጭት መጨመሩን መረጃዎች የሚያመለከቱ ሲሆን ለምሳሌ የክልሉ ጤና ቢሮ በክልሉ የሚገኙ 94 ወረዳዎች እና 1594 ቀበሌዎች የጸጥታ ችግር ያለባቸው እና የወባ ስርጭቱ የጨመረባቸው አካባቢዎች መሆናቸውን ገልጿል፡፡ በሌሎች አካባቢዎችም ያለው የበሽታው ስርጭት አሳሳቢ ሲሆን ለምሳሌ፣ በጋምቤላ ክልል ከዚህ ቀደም ተከስቶ በማያውቅ መልኩ የበሽታው ስርጭት መስፋፋቱን የክልሉ ጤና ቢሮ ገልጿል፡፡

254. በተመሳሳይም የኮሌራ ወረርሽኝ በተለያዩ ክልሎች በጤና መብት ላይ አሁንም አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ ሲሆን፣ አዲስ አበባን ጨምሮ በተወሰኑ ትላልቅ ከተሞች ወረርሽኙ መከሰቱን የጤና ሚኒስቴር መረጃ ያመለክታል፡፡ ከጥር ወር እስከ ሚያዝያ ወር 2017 ዓ.ም. ድረስ 4,056 የኮሌራ ክስተት መኖሩን እና 42 ሰዎች ደግሞ በበሽታው ምክንያት ሕይወታቸው ማለፉን የኢትዮጵያ የጤና ክላስተር የሚያዝያ ወር 2017 ዓ.ም. ሪፖርት ገልጿል፡፡ በተለይም ወረርሽኙ በአማራ እና በጋምቤላ ክልሎች ጎልቶ መስተዋሉን ሪፖርቱ ያመለክታል፡፡ በአማራ ክልል በምዕራብ ጎንደር ዞን ቋራ ወረዳ እና ባሕርዳር ዙሪያ ወረዳዎች ከየካቲት ወር 2017 ዓ.ም. መጨረሻ ጀምሮ በኮሌራ ወረርሽኝ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር መጨመሩን የክልሉ የኅብረተሰብ ጤና ተቋም ገልጿል፡፡ በተለይም በባሕርዳር ዙሪያ ወረዳዎች ወረርሽኙ ጎልቶ መስተዋሉን ተቋሙ ጨምሮ አስታውቋል፡፡ በሌላ በኩል

በመጋቢት ወር 2017 ዓ.ም. በጋምቤላ ክልል በኑዌር ዞን በተከሰተው የኮሌራ ወረርሽኝ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የሞቱ ሰዎች ቁጥር ከ30 በላይ መሆኑን የዞኑ ጤና መምሪያ አስታውቋል፡፡

**255.** በኢትዮጵያ በጤና መብት ዘርፍ ከፍተኛ አደጋ ደቅነው ከሚገኙ በሽታዎች ውስጥ ኩፍኝ አንዱ ሲሆን ከጥር ወር እስከ ሚያዝያ ወር 2017 ዓ.ም. ብቻ 3,908 ክስተቶች በመላ ሀገሪቱ መመዝገባቸውን እና ከበሽታው ጋር በተያያዘ የ22 ሰዎች ሕይወት ማለፉን የኢትዮጵያ የጤና ክላስተር ያመለክታል፡፡ የበሽታው ስርጭት በአሁኑ ወቅት በአማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ ሶማሊ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና ትግራይ ክልሎች እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር መቀጠሉን መረዳት ተችሏል፡፡ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች የኩፍኝ ክትባት ሽፋኑ ዝቅተኛ መሆኑ ሁኔታውን ይበልጥ አሳሳቢ ያደርገዋል፡፡

**256.** በግጭቶች ምክንያት የጤና አገልግሎት ተቋማት፣ መሠረተ ልማቶች እና እንደ አንቡላንስ ያሉ አስፈላጊ መገልገያዎች ጉዳት የሚደርስባቸው እና በከፊል ወይም በሙሉ ከአገልግሎት ውጪ መሆናቸው፤ የትጥቅ ግጭቶች በሚከናወኑበት ሁኔታ የእንቅስቃሴ ገደቦች መኖራቸው እንዲሁም የመድኃኒትና የሕክምና ቁሳቁሶች አቅርቦት እጥረት የሚያጋጥም መሆኑ በጤና መብት ላይ ጉዳት አስከትሏል፡፡ በሌላ በኩል ከጤና ባለሙያዎች የደመወዝ፣ ጥቅማጥቅም፣ የሙያ ዕድገት ዕድሎች እንዲሁም ምቹ የሥራ ቦታ እና ነጻነት ጥያቄዎች በወቅቱ አለመመለስ ጋር ተያይዞ የተከሰተው የጤና ባለሙያዎች የሥራ ማቆም አድማ በጤና መብት ዘርፍ ላይ ጉዳት ማስከተሉ በበጀት ዓመቱ የተከሰተ አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡ ኢሰመኮ በዚህ ጉዳይ ክትትል አድርጎ መግለጫ ማውጣቱ የሚታወስ ሲሆን በክትትሉ ለመረዳት እንደቻለው የሕክምና ባለሙያዎች ሚያዝያ 3 ቀን 2017 ዓ.ም. ለጤና ሚኒስቴር ባለ 12 ነጥብ ጥያቄዎችን አቅርበው "በ30 ቀናት ውስጥ ምላሽ በጠየቅነው መሠረት ምላሽ አልተሰጠንም" በማለት ከግንቦት 5 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ የሥራ ማቆም አድማ ጥሪ ተደርጓል፡፡ ይህንን ተከትሎ በተደረገው ከፊልና ሙሉ የሥራ ማቆም አድማ የተነሳ በተወሰኑ የሕክምና ተቋማት በጽኑ ሕሙማን ማእከል የሚገኙ ታማሚዎችን ጨምሮ በሐኪሞች እጥረት ተገቢውን ሕክምና ማግኘት አለመቻላቸውን፤ ከክልል ከተሞች ረጅም ቀጠሮ ጠብቀው ለሕክምና የመጡ ታካሚዎች ለእንግልት የተዳረጉ መሆኑን፤ በባለሙያዎች እጥረት ምክንያት የተወሰኑ የሕክምና ተቋማት ባለሙያዎችን ለረጅም ፈረቃዎች እንዲሠሩ ለመመደብ የተገደዱ መሆኑን እንዲሁም ታካሚዎች ሕክምና ለማግኘት ለረጅም ሰዓታት ለመጠበቅ መገደዳቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**257.** ከዚሁ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ፖሊስ "ሕገ-ወጥ የሥራ ማቆም አድማ አድርገዋል" ያላቸውን 47 የጤና ባለሙያዎች ማሰሩን ያስታወቀ ሲሆን፤ "ሕገ-ወጥ የሥራ ማቆም አድማ በማድረግ"፣ "ሌሎችም ሥራ እንዲያቆሙ ለአድማ በማነሳሳት"፣ "የታካሚዎች ሕይወት ለሞትና ለአደጋ እንዲጋለጥ በማድረግ"፣ "ሁከትና ብጥብጥ በመፍጠር" እንደተጠረጠሩ ገልጿል፡፡ ኢሰመኮ በጉዳዩ ላይ ክትትል ሲያደርግ የቆየ ሲሆን፣ ይህ ሪፖርት በሚጠናቀርበት ወቅት የታሰሩት ባለሙያዎች መለቀቃቸውን ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

**258.** በ2017 በጀት ዓመትም በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ሠራተኞች የሥራ እና ተያያዥ መብቶቻቸውን በአግባቡ መጠቀም ላይ ክፍተቶች ተስተውለዋል፡፡ በተለይም የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ በወቅቱና በአግባቡ ያለመክፈል ችግር ቀጥሏል፡፡ ለምሳሌ በትግራይ ክልል የበርካታ ወራት ደመወዝ ባለመከፈሉ ምክንያት ሠራተኞች ለተለያዩ

ችግሮች መጋለጣቸውን ለመረዳት ተችሏል። በአማራ ክልልም በተወሰኑ አካባቢዎች ከመስከረም እስከ ታኅሣሥ ወር የመምህራን ደመወዝ አለመከፈሉን የመምህራን ማኅበር ገልጿል። የጤና ባለሙያዎችም የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ ባለመከፈላቸው ችግር ገጥሟቸዋል። ለምሳሌ በታኅሣሥ ወር 2017 ዓ.ም. በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ቃሉ ወረዳ በ9 ጤና ጣቢያዎች ውስጥ የሚሠሩ የጤና ባለሙያዎች የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ ባለመከፈሉ ሳቢያ ለችግር መጋለጣቸውን፤ እንዲሁም በሲዳማ ክልል ማእከላዊ ሲዳማ ዞን ሎካአባያ ወረዳ ሀንጣጤ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ጤና ባለሙያዎች ከ6 እስከ 9 ወራት የትርፍ ሰዓት ክፍያ ባለመከፈሉ ምክንያት ሥራ ማቆማቸውን በሚያዝያ ወር 2017 ዓ.ም. ገልጸዋል። ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ማእከላዊ ኢትዮጵያና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች የመምህራንና የጤና ባለሙያዎችን ጨምሮ የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ ወቅቱን ጠብቆና በአግባቡ ያለመከፈል ችግር በመቀጠሉ፣ ሠራተኞች ለዘርፈ ብዙ ችግር ተጋልጠዋል።

**259.** ሠራተኞች ፍትሐዊ የሥራ ሁኔታ በማግኘት ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን በበቂ ሁኔታ ለማኖር የሚያስችል ክፍያ የማግኘት መብትን ከማስከበር አንጻር ምንም እንኳ የኢትዮጵያ አሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል እንዲወሰን የሕግ መሠረት ያስቀመጠ ቢሆንም በዚህ በጀት ዓመትም ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል ሳይወሰን ቀጥሏል።

## ምክረ ሐሳቦች

ኢሰመኮ ከላይ በተገለጹት ማሳያዎች ለቀረቡት የበጀት ዓመቱ የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ሁኔታ አሳሳቢ ጉዳዮች እልባት በመስጠት የመብት ሁኔታውን ለማሻሻል፦

**260.** መንግሥት ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶችን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችል አስፈላጊ የሆኑ መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለኅብረተሰቡ በተለይም ለተጋላጭ እና አነስተኛ ገቢ ላላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ተደራሽ ለማድረግ አፋጣኝ እና የተቀናጀ እርምጃዎችን እንዲወስድ፤

**261.** መንግሥት ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች በመንግሥት አካላትም ይሁን በግለሰቦች እንዳይጣሱ የማክበርና የማስከበር ግዴታዎችን እንዲወጣ እና አፈጻጸማቸውንም እንዲከታተል፤

**262.** መንግሥት በተፈጥሮአዊ እና በሰው ሰራሽ አደጋዎች ምክንያት በማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ላይ ለደረሱ ጉዳቶች ከሀገር ውስጥም ሆነ እንደሁኔታው ከአጋር አካላት ሀብትን በማሰባሰብ ምላሽ እንዲሰጥ፤

**263.** በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች ያለውን የምግብ እና የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ለመቅረፍ መንግሥት ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጥ፤

**264.** መንግሥት በተፈጥሮ እና ሰው ሠራሽ ችግሮች ምክንያት ከትምህርት ገበታ ውጪ የሆኑ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት እንዲመለሱ ጠንክሮ እንዲሠራ እና እርምጃዎችን እንዲወስድ፤ የወደሙ ትምህርት ቤቶችን እንዲገነቡ እና መልሰው እንዲቋቋሙ ለማድረግ በቂ በጀት ተይዞላቸው በዕቅድ ውስጥ መካተታቸውን እንዲያረጋግጥ እና መደበኛ አገልግሎት መስጠት እስኪጀምሩ ድረስ ጊዜያዊ የመማሪያ አማራጮችን ጨምሮ የተለያዩ መፍትሔዎችን እንዲያመቻች እንዲሁም አስፈላጊ የትምህርት ቁሳቁሶችን እንዲያሟላ፤

265. መንግሥት በግጭት እና የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት የወደሙ የጤና ተቋማትን መልሶ እንዲገነባ እና በጤና መብት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደሩ ያሉ ወረርሽኞችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አፋጣኝ እርምጃዎችን ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲወስድ፤

266. መንግሥት በጤናው ዘርፍ የሚደረግ የሥራ ማቆም አድማ በማኅበረሰቡ የጤና እና በሕይወት የመኖር መብት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ የሕክምና ባለሙያዎች ያቀረቧቸውን ጥያቄዎች ትኩረት ሰጥቶ ግልጽ እና አሳታፊ በሆነ መንገድ ዘላቂ መፍትሔ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲያመቻች፤ የሕክምና ባለሙያዎችም የኅብረተሰቡን የጤና እና በሕይወት የመኖር መብቶችን አደጋ ላይ በማይጥል መልኩ ጥያቄዎቻቸውን እንዲያቀርቡ፤ እንዲሁም በመንግሥት በኩል ከሥራ ማቆም አድማው ጋር በተያያዘ የሚወሰዱ አስተዳደራዊ እና ሌሎች ማናቸውም እርምጃዎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች እና የሰብአዊ መብቶች መርሖችን የተከተሉ እንዲሆኑ፤

267. ሁሉም ችግሩ የተስተዋለባቸው የክልል መንግሥታት የሠራተኞች ደመወዝ ወቅቱን ጠብቆ በተገቢው ሁኔታ መከፈሉን እንዲያረጋግጡ፤

268. ሠራተኞች ፍትሐዊ፣ አመቺና ጤናማ የሥራ ሁኔታ በማግኘት ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን በበቂ ሁኔታ ለማኖር የሚያስችል ክፍያ የማግኘት መብትን ከማስከበር አንጻር ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል ሥርዓትን የሚዘረጋ ሕግ እና የደመወዝ ቦርድ ማቋቋሚያ ደንብ እንዲወጣ ምክረ ሐሳቡን ያቀርባል።

# የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች



# ሸ) የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች

## ቀልፍ እመርታዎች

**269.** የፍትሕ ሚኒስቴር በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ አተገባበር ሂደት ሴቶች እና ሕፃናትን ጨምሮ የተጎጂዎችና ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተሳትፎ ስትራቴጂን በበጀት ዓመቱ ያረቀቀ መሆኑ፤

**270.** የአፋር ክልል ረቂቅ የቤተሰብ ሕግ ኢሰመኮ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ባቀረቧቸው ምክረ ሐሳቦች መሠረት አስፈላጊ ማሻሻያዎች ተደርጎበት ወደ ማጽደቅ ሂደት ለመግባት ዝግጅት መጠናቀቁ፤

**271.** በኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን ሊሙ ወረዳ በሆራይዘን ፕላንቴሽን ኃ/የተ/የግ/ማኅበር ሥር በሚገኙ ሊሙ ኮሳ፣ ጉመር እና ሱንጡ የቡና እርሻ ጣቢያዎች እንዲሁም በሃይደር እና ፈይሰል የቡና እርሻ ልማት ሥር ባለው የሃይደር እርሻ ጣቢያዎች ኢሰመኮ ቀደም ሲል በሰጠው ምክረ ሐሳብ መሠረት ሕፃናትን በቡና ለቀማ ላይ የማሰማራት አሠራር እና የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ መቆሙ፤

**272.** በሴቶች እና በሕፃናት ላይ ከፍተኛ አካላዊ እና ሥነልቦናዊ ጉዳት የሚያደርሱ እንደ የሴት ልጅ ግርዛት ያሉ ጎጂ ልማዶችን ለማስቀረት ኢሰመኮ በበጀት ዓመቱ ከተለያዩ ባለድርሻዎች ጋር ውጤታማ የውትወታ ተግባራትን አከናወኗል። ለምሳሌ ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የዑለማ ጉባኤ ጽሕፈት ቤት እና ከምክር ቤቱ ሴቶችና ወጣቶች ዘርፍ ኃላፊዎች ጋር ጥቅምት 16 ቀን 2017 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ምክክር ያደረገ ሲሆን፣ የዑለማ ጉባኤ ጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ በግርዛት ሳቢያ ሴቶች እና ሕፃናት ለአካላዊም ሆነ ለሥነ-ልቦናዊ ጉዳት እንዲጋለጡ ማድረግ የሃይማኖቱ አስተምህሮ ባይሆንም የተሳሳቱ አካሄዶች መኖራቸውን ገልጸው እነዚህን አሠራሮች እና ልማዶች ለመቅረፍ ተቋሙ የበኩሉን አስተዋጽዖ እንደሚያደርግ ማስታወቁ፤

**273.** በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ሃዲያ ዞን ሻሸጎ፣ ሶሮ እና ምዕራብ ሶሮ ወረዳዎች የሚፈጸሙ የሴት ልጅ ግርዛት እና ዳግም ግርዛት ተግባራትን ለማስቀረት ኢሰመኮ በ2016 ዓ.ም. ባቀረበው ምክረ ሐሳብ መሠረት መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት በበጀት ዓመቱ የተሻለ ትኩረት ሰጥተው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን እየሠሩ የሚገኙ መሆናቸው በ2017 በጀት ዓመት በሴቶች እና በሕፃናት መብቶች ዘርፍ የታዩ ቁልፍ እመርታዎች ናቸው።

## አሳሳቢ ጉዳዮች

**274.** ከሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. እስከ ሰኔ ወር 2017 ዓ.ም. በተለይም ግጭቶች በቀጠሉባቸው አካባቢዎች፣ አስፈላጊው የመልሶ ግንባታ ባልተከናወነባቸው በድኅረ ግጭት ሁኔታ ውስጥ በሚገኙ የሀገሪቱ ክፍሎች፣ እንዲሁም ድርቅ እና ጎርፍን ጨምሮ በተለያዩ የተፈጥሮ አደጋዎች ሳቢያ ጉዳት በደረሰባቸው እና ነዋሪዎች መፈናቀልን ጨምሮ ለተለያዩ ችግሮች በተጋለጡባቸው አካባቢዎች ያለው የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ አሳሳቢነት ቀጥሏል። በዚህ ሪፖርት የተለያዩ ክፍሎች እንደተመላከተው በትጥቅ ግጭት እንዲሁም በጸጥታ መደፍረስ ሁኔታ ውስጥ ሴቶችና ሕፃናት በሕይወታቸው፣ በአካላቸው፣ በሥነ ልቦናቸው እንዲሁም በንብረታቸው ላይ ጉዳት ደርሶባቸዋል፤ እንዲሁም ትምህርት እና ጤናን ጨምሮ ሌሎችንም

አገልግሎቶች በሚያገኙባቸው መሠረተ ልማቶች እና ተቋማት ላይ በሚደርሱ ውድመቶች እና በሚያጋጥሙ ሙሉ ወይም ከፊል የአገልግሎት መቆራረጥ ምክንያት ለከፍተኛ ችግር እንደሚዳረጉ የኢሰመኮ ክትትሎች ያሳያሉ። በ2017 በጀት ዓመት አሳሳቢ ሆነው ከቀጠሉ ጉዳዮች መካከል እንደ ኩፍኝ፣ ወባ እና ኮሌራ ያሉ በሽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በከፍተኛ ሁኔታ መሰራጨት፤ ምግብን ጨምሮ ሌሎችም ሰብአዊ ድጋፎችን የሚያቀርቡ ድርጅቶች አገልግሎት መቋረጥ ወይም መስተጓጎል ተጠቃሽ ሲሆኑ በሴቶች እና በሕፃናት በሕይወት የመኖር፣ የትምህርት፣ የጤና እንዲሁም ምግብን ጨምሮ በቂ የኑሮ ደረጃ የማግኘት መብቶች ላይ ያሳደሩት አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው።

275. ይህ ጠቅላላ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኢሰመኮ በ2017 በጀት ዓመት ዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ እና ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ማዕቀፎችን መሠረት በማድረግ በተመረጡ የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች ጉዳዮች ላይ ክትትሎችን ያደረገ ሲሆን በየዘርፉ የተስተዋሉ አሳሳቢ ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### በአፋር እና በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች የሚፈጸም የሴት ልጅ ግርዛትን የተመለከተ ግልጽ የአቤቱታ መቀበያ መድረክ/ ሕዝባዊ መሰማት

276. ኢሰመኮ በአፋር እና በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች የሚፈጸመውን የሴት ልጅ ግርዛት አስመልክቶ የሕግ፣ የአፈጻጸም እና መዋቅራዊ ክፍተቶችን ጨምሮ ሌሎች መሠረታዊ ምክንያቶችን ለመለየት በአዲስ አበባ ከተማ ሰኔ 18 እና 19 ቀን 2017 ዓ.ም. ግልጽ የአቤቱታ መቀበያ መድረክ/ሕዝባዊ መሰማት ሥነ ዘዴን በመጠቀም ስልታዊ ምርመራ አከናውኗል። በመድረኩ ከተጠቀሱት ክልሎች የመጡ የግርዛት ተጎጂዎች፣ የባለሙያ ምስክሮች፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራል እና የተጠቀሱት ክልሎች ተቋማት ተወካዮች፣ የሃይማኖት እና የሀገር ሽማግሌዎች እንዲሁም በሴቶች እና በሕፃናት መብቶች ላይ የሚሠሩ ዓለም አቀፍ እና ሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ተገኝተዋል። በመድረኩ የባለሙያ ምስክርን ጨምሮ ሁለቱም ክልሎች ምስክርነት የሰጡ 15 ምስክሮች በግርዛት ምክንያት ስለሚደርስ/ ስለደረሰ የሞት አደጋ፣ በግብረ ስጋ ግንኙነት፣ በወሊድ እና በወር አበባ ወቅት ስለሚከሰቱ ውስብስብ የጤና ችግሮች እና የሥነልቦና ጫናዎች አስረድተዋል። በተጨማሪም በሁለቱ ክልሎች ስለሚፈጸም የግርዛት ዐይነት፣ ለግርዛት መፈጸም ምክንያቶች፣ ግርዛት የሚፈጸምበት የእድሜ ክልል እና ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች ተሰብስበዋል። ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራል እና የተጠቀሱት ክልሎች ተቋማት ተወካዮች፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና የሃይማኖት አባቶች ምስክርነት በተሰሙባቸው የመብት ጥሰቶች ላይ ምላሽ የሰጡ ሲሆን በዋናነትም በመድረኩ የተሰጠው ምስክርነት እውነት ስለመሆኑ ማረጋገጫ ሰጥተዋል። ኢሰመኮ በዚህ ስልታዊ ምርመራ በሁለቱ ክልሎች በሚፈጸም የሴት ልጅ ግርዛት ምክንያት የሴቶችና የሴት ሕፃናት በሕይወት የመኖር፣ የጤና፣ የአካል እና የአእምሮ ደኅንነት መብት እንዲሁም ከማንኛውም ኢሰብአዊ ወይም ክብርን ከሚያዋርድ አያያዝ እና የስቃይ እና የጭካኔ ተግባር የመጠበቅ መብቶቻቸውን ጨምሮ በርካታ መብቶቻቸው መጣሳቸውን መረዳት ችሏል።

### በኢንዱስትሪ ፓርኮች እና ፋብሪካዎች ውስጥ የሴት ሠራተኞች መብቶች አያያዝ

277. ኢሰመኮ በአዲስ አበባ ከተማ፣ ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ በሚገኘው የቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ እና በኦሮሚያ ክልል፣ ሸገር ከተማ ዓለም ገና ክፍለ ከተማ በሚገኙ 10

ፋብሪካዎች ውስጥ የሴት ሠራተኞች የሰብአዊ መብቶች አያያዝን በተመለከተ ከኅዳር 1 እስከ ኅዳር 14 ቀን 2017 ዓ.ም. ክትትል አድርጓል፡፡ በዚህም በመንግሥት አካላት መደረግ ያለበት ቁጥጥርና ክትትል አነስተኛ መሆኑ፤ በአብዛኞቹ ፋብሪካዎች የሠራተኞች ማኅበር አለመመሥረቱ፤ ወጥ የቅሬታ ማቅረቢያ አሠራር አለመኖሩ፤ የሥራ ላይ ደኅንነትን እና የሥነ ተዋልዶ ጤናን የተመለከቱ ስልጠናዎች በበቂ ሁኔታ የማይሰጡ መሆኑ፤ የአደጋ እና በሽታ መከላከያ መሣሪያዎች በበቂ ሁኔታ አለመሟላታቸው እንዲሁም ያሉትን መሣሪያዎች አጠቃቀም በተመለከተ በሠራተኞች ዘንድ የግንዛቤ ጉድለት መኖሩ፤ የደኅንነት እና የጤና ኮሚቴ አለመኖር፤ በፋብሪካዎች ውስጥ ያሉ የሕክምና ባለሙያዎች ከሠራተኞች ብዛት አንጻር አነስተኛ መሆኑ፤ በተወሰኑ ድርጅቶች ሠራተኞች በቀን ከ8 ሰዓት በላይ እንዲሠሩ ቢደረግም የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ የማይፈጸምላቸው መሆኑ፤ ነፍሰጡሮችን ጨምሮ ሠራተኞችን የትርፍ ሰዓት ሥራ ተገደው እንዲሠሩ የሚደረግ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በክትትሉ ከተለዩት ቁልፍ ችግሮች የተወሰኑት በሁሉም ሠራተኞች መብቶች ጥበቃ ላይ ተጽዕኖ ያላቸው ቢሆንም በሴት ሠራተኞች ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ከፍተኛ ነው፡፡

278.በሌላ በኩል ኢሰመኮ በ2014 ዓ.ም. በአዳም እና በሃዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚሠሩ የሴት ሠራተኞች የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ላይ ባካሄደው ክትትል የተሰጡ ምክረ ሐሳቦችን አፈጻጸም በተመለከተ በታኅሣሥ ወር 2017 ዓ.ም. ተጨማሪ ክትትል አድርጓል፡፡ በዚህም በበርካታ ጉዳዮች ላይ መሻሻሎች መታየታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይም በመንግሥት አካላት መደረግ ያለበት ቁጥጥር አነስተኛ መሆኑ፤ የኅብረት ስምምነት ሰነድ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ አለመግባቱ፤ ሴት ሠራተኞች ሕፃን ልጆቻቸውን የሚያጠቡበትና የሚንከባከቡበት የሕፃናት ማቆያ ማእከል በፋብሪካዎቹ ውስጥ አለመቋቋሙ፤ ሠራተኞች የጡረታ መለያ ቁጥር በተገቢው ጊዜ ማግኘት የሚችሉበት አሠራር አለመዘርጋቱ፤ እንዲሁም ለሠራተኞች የሚከፈለው ደመወዝ አሁን ካለው የኑሮ ውድነት ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ መሆኑ በሴት ሠራተኞች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩን መረዳት ተችሏል፡፡

### በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት መብቶች አያያዝ

279.ኢሰመኮ በ2015 ዓ.ም. በአፋር፣ ሐረሪ፣ ኦሮሚያ እና ሲዳማ ክልሎች በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት መብቶች አያያዝን በተመለከተ ባደረገው ክትትል መሠረት የምክረ ሐሳቦች አፈጻጸም ክትትል በ2017 ዓ.ም. አድርጓል፡፡ በዚህም መሻሻሎች ቢኖሩም በአሳሳቢነታቸው የቀጠሉ የመብቶች ጥሰቶችም ተለይተዋል፡፡ ለምሳሌ የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት ምስክር ሆኖ ከመሰማት ውጭ በፍትሕ ሂደቱ ያላቸው ተሳትፎ እጅግ አነስተኛ መሆን፤ በዐቃቤ ሕግ ምስክሮች አለመቅረብ፣ በተጠርጣሪዎች አለመገኘት፣ በዳኞች አለመሟላት፣ በተከላካይ ምስክሮች አለመቅረብ ወዘተ. ሳቢያ ተደጋጋሚ ቀጠሮ የሚሰጥ በመሆኑ የተፋጠነ ፍትሕን በማረጋገጥ ረገድ ክፍተት መፍጠሩ፤ የፍርድ ቤቶች የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 በአግባቡ አለመተግበር፤ እንዲሁም የጊዜ ቀጠሮ እና የዋስትና መብት አወሳሰን የተጎጂዎችን ደኅንነት ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ አለመሆን በአሳሳቢነታቸው የቀጠሉ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ናቸው፡፡

### በማሳደጊያ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት መብቶች አያያዝ

280. ኢሰመኮ በአዳማ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ፣ ሐረር፣ ሃዋሳ፣ ሻሸመኔ እና ወላይታ ከተሞች በሚገኙ 25 የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት በመጋቢት ወር 2015 ዓ.ም. ያደረገውን የሰብአዊ

መብቶች ክትትል መሠረት በማድረግ በ2017 ዓ.ም. ባደረገው የምክረ ሐሳቦች አፈጻጸም ክትትል መሻሻሎች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ አሳሳቢ ጉዳዮችም ተለይተዋል፡፡ በተለይ በድሬዳዋ አስተዳደር የሴቶች፣ ሕፃናት እና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ጊዜያዊ የሕፃናት ማቆያ እና ማገገሚያ ማእከል ከ6 ወር በታች ዕድሜ ያላቸው 6 ሕፃናት በምግብ እጥረት እና በባክቴሪያ ሕመም መሞታቸው፤ በሻሸመኔ ካቶሊክ የሕፃናት ማሳደጊያ 1 የተቋሙ ሠራተኛ ዕድሜያቸው ከ13 ዓመት በታች የሆኑ 3 ሕፃናትን "ልብስ ሰርቃችኋል" በሚል ከባድ አካላዊ ቅጣት (ድብደባ) መፈጸሙ እና በሠራተኛው ላይ ተገቢው የእርምት እርምጃ አለመወሰዱ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም በዳሩል ሂጅራ የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋም ለሕፃናት የሚዘጋጁ ምግቦች የሕፃናትን ዕድሜና የጤና ሁኔታ መሠረት ያደረጉ አለመሆናቸው እና በሐኪም ትእዛዝ የተለየ ምግብ እንዲመገቡ ለታዘዘላቸው ጨቅላ ሕፃናት በትእዛዙ መሠረት ምግብ የማይቀርብ መሆኑ፤ ብዛታቸው ከ10 በላይ የሚሆኑ ከ1 ዓመት በታች ዕድሜ ያላቸው ጨቅላ ሕፃናት ምቹ ባልሆነ ማደሪያ ክፍል ውስጥ መሬት ላይ ምንጣፍ ተነጥፎላቸው እንዲተኙ መደረጉ፤ ሕፃናት በአቅራቢያቸው የትምህርት አገልግሎት የሚያገኙ አለመሆናቸው እና የትራንስፖርት አገልግሎትም አለመመቻቸቱ፤ የትምህርት መሣሪያዎችና ዩኒፎርም በማግኘት ረገድ ሰፊ ክፍተት መኖሩ፤ ቤተ-መጻሕፍት እና ለሕፃናት ምቹ የሆነ የጥናት ቦታ አለመኖሩ፤ የተማሪዎች የትምህርት ውጤት ዝቅተኛ መሆን፤ ማሳደጊያ ተቋሙ ያለበት አካባቢ በገደል ጫፍ እና የቆሻሻ መጣያ አካባቢ በመሆኑ እና በግቢው ውስጥ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ለምሳሌ የቆርቆሮ ቁርጥራጭ፣ ጉድጓድ፣ ብረታ ብረት እና መጥፎ ጠረን ያለ በመሆኑ ሕፃናት በቀላሉ ለአደጋና ለበሽታዎች ተጋላጭ መሆናቸው የቀጠሉ አሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ናቸው፡፡

**281.** በአዲስ አበባ ክትትል ከተደረገባቸው ተቋማት መካከል በሚሽነሪ ኦፍ ቻሪቲ የሕፃናት ማሳደጊያ ከፍተኛ የሕክምና ክትትል እና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሕፃናት በመንግሥት መድኃኒት የማይቀርብላቸው በመሆኑ በውድ ዋጋ በመግዛት እንዲያቀርብ መገደዱ፤ በኮልፌ የወንድ ሕፃናት ማቆያ እና ማገገሚያ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ ወጣቶች ተቋቁመው እንዲወጡ ባለመደረጉ በዕድሜ ከእነርሱ ባነሱ ሕፃናት ላይ የሚያደርሱት ድብደባ፣ ማስፈራራት፣ ንብረት መስረቅ፣ ምግብ መቀማት ወዘተ. መቀጠሉ እና ሌሎች አሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችም መቀጠላቸው ታውቋል፡፡ በክበበ ፀሐይ የሕፃናት ማሳደጊያ በኩፍኝ ወረርሽኝ በሽታ ከተያዙ 58 ሕፃናት መካከል 4 ወንድ እና 2 ሴት በአጠቃላይ 6 ሕፃናት መሞታቸው ያልተሻሻሉ እና ተባብሰው የቀጠሉ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ማሳያዎች ናቸው፡፡

**282.** በሌላ በኩል አብዛኞቹ ማሳደጊያ ተቋማት የአካል ጉዳት ሁኔታን የቅበላ መሥፈርት በማድረጋቸው አካል ጉዳተኛ ሕፃናትን ተቀብለው የማያሳድጉ መሆኑ፤ ለሕፃናት የሚቀርበው ምግብ በተገቢው ጥራት አለመዘጋጀቱ፤ በቼንትሮ አዩ ፒ አር ኢትዮጵያ፣ ቢላቭድ ሁለገብ የዕድገት ማእከል፣ በሆፐ 360 የሕፃናት ማሳደጊያ፣ ሻሸመኔ ካቶሊክ የሕፃናት ማሳደጊያ እና ቤቴል የሕፃናት ማሳደጊያዎች የተሰባጠረ መረጃ አያያዝ ሥርዓት አለመኖሩ፤ በሻሸመኔ ካቶሊክ ለ50 ሕፃናት 1፣ በሐረር የሀገር ልጅ የሕፃናት ማሳደጊያ ለ95 ሕፃናት 4፣ በዳሩል ሂጅራ የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋም ደግሞ ለ99 ሕፃናት 6 ሞግዚቶች ብቻ በመመደባቸው አለመመጣጠን እንዲኖር እና ሞግዚቶች ለእያንዳንዱ ሕፃን አስፈላጊውን ትኩረት እና እንክብካቤ መስጠት እንዳይችሉ ያደረገ መሆኑ፤ ለሞግዚቶች እና ባለሙያዎች በሕፃናት አስተዳደግና እንክብካቤ ዙሪያ ተያያዥ እና ተከታታይ ስልጠናዎች በበቂ ሁኔታ የሚሰጥ

አለመሆኑ፤ አብዱል ሰመድ መሐመድ እና ዳሩል ሂጅራ የሕፃናት ማሳደጊያዎች በጽሑፍ የተዘጋጀ የሕፃናት ደኅንነት እና ጥበቃ ፖሊሲ አዘጋጅተው ተግባራዊ አለማድረጋቸው፤ ከኤስ.ኦ.ኤስ. የሕፃናት መንደር እና ከሐረር የሀገር ልጅ የሕፃናት ማሳደጊያ በስተቀር ሁሉም የምክረ ሐሳብ አፈጻጸም ክትትል የተደረገባቸው ማሳደጊያ ተቋማት የቅሬታና አቤቱታ ማቅረቢያ ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ አለማድረጋቸው በተመሳሳይ አሳሳቢ እና የቀጠሉ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች መሆናቸውን ኢሰመኮ አረጋግጧል።

## በወንጀል ነክ ነገር ውስጥ ገብተው በተሐድሶ ተቋም ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት መብቶች

**283.** ኢሰመኮ በ2016 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በወንጀል ነክ ነገር ውስጥ ገብተው በማቆያና ተሐድሶ ተቋም ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ላይ የተደረገውን ክትትል መሠረት በማድረግ በመጋቢት 2017 ዓ.ም. የምክረ ሐሳብ አፈጻጸም ክትትል አድርጓል። በተሰጠው ምክረ ሐሳብ መሠረት ለእያንዳንዱ ሕፃን አዲስ ፍራሽ፣ አንሶላ እና ብርድ ልብስ መቅረቡ፤ በቂና በሕፃናቱ ሰውነት ልክ ባይሆንም በዩኒፎርም አልባሳት ረገድ ከቀድሞው የተሻለ አቅርቦት መኖሩ፤ በማደሪያ ክፍሎች ያሉ ግላዊ ቁሳቁሶችን ማስቀመጫ ሳጥኖች (ሎከሮች) የተበላሹት እንዲጠገኑ እንዲሁም በር ያልነበራቸው እንዲገጠምላቸው መደረጉ፤ በተቋሙ የሚገኘው መድኃኒት ቤት የተሟላ ባይሆንም በተሻለ የመድኃኒት አቅርቦት መደራጀቱ እንዲሁም የሕፃናት የጸሎት ክፍሎች ከዚህ ቀደም ከነበረው በተሻለ ሁኔታ የተደራጁ መሆናቸው እና የሃይማኖት መሪዎችና አገልጋዮች እየተገኙ አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸው በምክረ ሐሳብ አፈጻጸም ክትትሉ የተለዩ አበረታች እርምጃዎች ናቸው።

**284.** ሆኖም በተቋሙ ሲያገለግሉ ከነበሩ 30 ሞግዚቶች ውስጥ በ2017 ዓ.ም. በተደረገ ድልድል 10 ሞግዚቶች በመቀነሳቸው ምክንያት የሞግዚቶች እጥረት ማጋጠሙ እና ለሕፃናቱ በሚቀርበው እንክብካቤ ላይ ክፍተት መፍጠሩ፤ የምግብ ዝርዝር (ሜኑ) በአዲስ የተቀየረ ቢሆንም በተቀየረው ዝርዝር መሠረት ለሕፃናት ምግብ የማይቀርብላቸው መሆኑ፤ በማደሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙት መጸዳጃ ቤቶች በውሃ እጥረት እና ንጽሕና ጉድለት የተነሳ መጥፎ ጠረን ያላቸው መሆኑ፤ ሁሉም መታጠቢያ ክፍሎች በመበላሸታቸው እና በውሃ አለመኖር ምክንያት አገልግሎት እየሰጡ አለመሆናቸው፤ የማደሪያ ክፍሎች ምደባ የሕፃናት ዕድሜን፣ አካላዊ እና አእምሮአዊ ጤንነትን፣ የእንክብካቤ ፍላጎትን፣ የወንጀል ክስ ጉዳይ ደረጃ እና ውጤትን ወዘተ. መሠረት ያደረገ አለመሆኑ በክትትሉ ተረጋግጧል። ከ8ኛ ክፍል በላይ ያሉ ተማሪዎች ከተሐድሶ ተቋሙ ቅጥር ግቢ ፊት ለፊት በሚገኘው አፍሪካ ኅብረት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይማሩ የነበረ ቢሆንም ተቋሙ ከቅጥር ግቢ ውጪ ላለው ጥበቃ እና የሕፃናት ደኅንነት ኃላፊነት አልወስድም በማለቱ ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ ወይም ያጠናቀቁትን 8ኛ ክፍል ደግመው እንዲማሩ መገደዳቸው፤ እንዲሁም የአመክሮ ጊዜያቸውን የጨረሱ ሕፃናት ወደ ጎዳና እንዳይወጡ ወይም የጸባይ ለውጥ አላመጡም በሚሉ ምክንያቶች በተቋሙ ውስጥ ከ1 ሳምንት እስከ 6 ወራት ለሚደርስ ተጨማሪ ጊዜ እንዲቆዩ መደረጉ በምክረ ሐሳብ አፈጻጸም ክትትሉ የተለዩ እና በአሳሳቢነታቸው የቀጠሉ ጉዳዮች ናቸው።

### የሕፃናት የትምህርት መብት

**285.** ኢሰመኮ ትምህርት ቤቶች ለሕፃናት ያላቸውን ምቹነት እና በትምህርት ቤቶች ውስጥ ያለውን የሕፃናት መብቶች አያያዝ በተመለከተ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ አፋር፣ አማራ፣ ጋምቤላ፣ ኦሮሚያ እና ደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች እንዲሁም የትምህርት ተገኝነትን (availablity) በተመለከተ በግጭት እና በተፈጥሮ አደጋዎች በተጎዱ የሶማሊ እና ትግራይ ክልሎች በሚገኙ የተመረጡ 77 የመንግሥት እና የግል አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ክትትል አከናውኗል።

**286.** ትምህርት ቤቶች ለሕፃናት ያላቸውን ምቹነት እንዲሁም በትምህርት ቤቶች ውስጥ ያለውን የሕፃናት መብቶች አያያዝ በተመለከተ ክትትል በተደረገባቸው ትምህርት ቤቶች የመማሪያ ክፍሎች ከተማሪዎች ብዛት ጋር አለመመጣጠን የተስተዋለ ሲሆን፤ ለምሳሌ በአዲስ አበባ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች በኮሪደር ልማት ምክንያት ከቅበላ ዐቅማቸው በላይ ከሌሎች ቦታዎች የመጡ ተማሪዎችን እንዲቀበሉ በመደረጋቸው በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ በአማካይ ከ85 እስከ 100 ተማሪዎች ምቹ ባልሆነ እና በተጨናነቀ ሁኔታ የሚማሩ መሆናቸው አሳሳቢ ነው። በአዲስ አበባ የትምህርት ቤት የምገባ ሥርዓት መኖሩ አበረታች ቢሆንም ተማሪዎች በሚቀርብላቸው ምግብ ጥራት ላይ ከፍተኛ ቅሬታ አላቸው። በክልሎች በሚገኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የምገባ ሥርዓት የሚተገበር አለመሆኑ ሕፃናት በምግብ እጥረት ምክንያት ከትምህርት ገበታ ውጭ እንዲሆኑ አስተዋጽዖ ማድረጉን ኢሰመኮ አረጋግጧል። ክትትል በተደረገባቸው በርካታ ትምህርት ቤቶች በቅርብ ርቀት ጫት እና ሺሻ ቤቶችን ጨምሮ ሕፃናትን ለሱስ የሚያጋልጡ እና ትምህርታቸውን በአግባቡ እንዳይከታተሉ ሊያደርጉ የሚችሉ ሁኔታዎች መኖራቸው፤ በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ወንድ ተማሪዎች በሴት ተማሪዎች ላይ ጾታዊ ትንኮሳ፣ የአስገድዶ መድፈር ሙከራ፣ በባጃጅ አፍኖ መውሰድ እንዲሁም ሌሎች አካላዊና ሥነልቦናዊ ጥቃቶችን የሚፈጽሙ መሆናቸው፤ ተማሪዎች ሲያጠፉ በዱላ ወይም በእንጨት መምታትን ጨምሮ አካላዊ ቅጣቶች የሚፈጸሙባቸው መሆኑ፤ ክትትል በተደረገባቸው ሁሉም ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች የቅሬታ ማቅረቢያ ሥርዓት በተሟላ መልኩ አለመዘርጋቱ በክትትሉ ከተለዩ ቁልፍ አሳሳቢ ጉዳዮች መካከል ይጠቀሳሉ።

**287.** በተጨማሪም ሴት ተማሪዎች በቤት ውስጥ የሥራ ጫና እና በድህነት ምክንያት ትምህርታቸውን አቋርጠው ጋብቻ እንዲፈጽሙ በቤተሰባቸው እንደሚገደዱ፤ ሁሉም ክትትል የተደረገባቸው ትምህርት ቤቶች ከአድሎ የመጠበቅ ፖሊሲ (anti-discriminatory policy) የሌላቸው መሆኑ ተማሪዎችን በአድልዎ ምክንያት ለሚፈጸሙ የመብት ጥሰቶች ተጋላጭ ማድረጉ፤ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች "ዐቅም እና የሰለጠኑ ባለሙያዎች ወይም መምህራን የለንም" በሚል ምክንያት አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን የማይቀበሉ መሆኑ፤ ሴት፣ አካል ጉዳተኛ እና ከኅዳጣን ማኅበረሰቦች የሚመጡ ተማሪዎችን ተሳትፎ ለማበረታታት በትምህርት ቤቶች በኩል የሚደረግ ምንም ዐይነት ጥረት አለመኖሩ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው።

**288.** በሌላ በኩል በትግራይ ክልል ክትትል የተደረገባቸው አብዛኞዎቹ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት መሥፈርቶችን የማያሟሉ መሆናቸው፤ ቤተ መጻሕፍቶች፣ ቤተ ሙከራዎች፣ ICT ማእከሎች፣ የመምህራን ቢሮዎች፣ የፔዳጎጂ ማዕከሎች፣ መጸዳጃ ቤቶች እና የመማሪያ ሕንፃዎች ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ የወደሙ እና በጥቂት ትምህርት

ቤቶች ከተደረገው የጣሪያ እድሳት በስተቀር የመልሶ ግንባታ ሥራ አለመከናወኑ እና ትምህርት ቤቶች የተፈናቃይ መጠለያ ሆነው እያገለገሉ መሆናቸው፤ የትምህርት ቤቶቹ ርቀት፣ ምቹ አለመሆን እና ጦርነቱ የፈጠረው የሥነ ልቦና ቀውስ እና አለመረጋጋት የሕፃናት የትምህርት ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ እና አብዛኞዎቹ ተማሪዎች በተከታታይ ከትምህርት ቤት እንዲቀሩ ወይም እንዲያቋርጡ ማድረጉ በክትትሉ ተለይቷል። በሶማሊ ክልል ክትትሉ በተደረገባቸው በቀላፎ ወረዳ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች በወረዳው በ2015 ዓ.ም. በደረሰ የጎርፍ ጉዳት ምክንያት ተቋርጦ የነበረው የመማር ማስተማር ሂደት በ2017 ዓ.ም. እንደገና የጀመረ ቢሆንም የመልሶ ግንባታ እና ጥገና ሥራው ባለመጠናቀቁ የተሟላ ትምህርት አገልግሎት እየሰጡ እንዳልሆነ፤ የመማሪያ ቁሳቁሶች፣ መጻሕፍት፣ የወረቀት፣ የተማሪ መቀመጫ ወንበሮች እጥረት መኖሩ እና ትምህርት ቤቶቹ ወደ ቀደምት ሁኔታቸው እስኪመለሱ ድረስ ጊዜያዊ የመማሪያ ቦታዎች እንዳልተዘጋጁ ለመረዳት ተችሏል። በተመሳሳይ በክልሉ በሚገኙ በሃሮሬስ እና ቀብሪበያህ ወረዳዎች በተከሰተ ድርቅ፣ የውሃ እና የግጦሽ እጥረት በመማር ማስተማሩ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያስከተለ ሲሆን ተማሪዎች ከወላጆቻቸው ጋር ውሃና የከብቶች ግጦሽ ፍለጋ በመሄዳቸው ምክንያት ትምህርት ለማቋረጥ ተገደዋል፤ ያቋረጡትን ትምህርት እንዲቀጥሉም እየተደረገ ያለ ጥረት የለም። ለሴት እና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችም የሚሰጥ የተለየ ድጋፍ አለመኖሩንም ለማረጋገጥ ተችሏል።

## ምክረ ሐሳቦች

**289.** በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በሚካሄዱ የትጥቅ ግጭቶችና የጸጥታ መደፍረስ ሁኔታዎች ዐውድ በሴቶች እና ሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን ለማስቆም እንዲሁም ለተፈጸሙ ጥሰቶች የሕግ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ውጤታማ እርምጃዎችን እንዲወስዱ፤

**290.** በተለያዩ አካባቢዎች እየተካሄዱ ባሉ የትጥቅ ግጭቶች ተሳታፊ የሆኑ አካላት በሴቶች እና በሕፃናት ላይ ማንኛውንም ዐይነት የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ከመፈጸም እንዲቆጠቡ፤ መንግሥት በተለይም ተደራራቢ ተጋላጭነት ያላቸውን አካል ጉዳተኞች፣ ተፈናቃይ ሴቶችና ሕፃናትን ጥበቃ እንዲያጠናክር፤

**291.** ጤና ሚኒስቴርና የክልል ጤና ቢሮዎችን ጨምሮ የሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በተመጣጠነ ምግብ እጥረት እንዲሁም እንደ ኩፍኝ፣ ወባ እና ኮሌራ ባሉ በሽታዎች መስፋፋት ሳቢያ ለተለያዩ ጉዳቶችና ሥጋቶች ለተጋለጡ ሕፃናትና ሴቶች በቂ እና ወቅታዊ ምላሽ ለመስጠት በቅንጅት እንዲሠሩ፤

**292.** በኢንዱስትሪ ፓርኮችና በፋብሪካዎች ያለውን የሴት ሠራተኞች መብቶች አያያዝ ለማሻሻል የሥራና ክህሎት ሚኒስቴርን ጨምሮ በአዲስ አበባ ከተማ እንዲሁም በኦሮሚያ እና ሲዳማ ክልሎች በየደረጃው የሚገኙ ተቋማት ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፤ ኢንዱስትሪ ፓርኮችና ፋብሪካዎች ከደመወዝና የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ ጋር የተያያዙ ማስተካከያዎችን ጨምሮ ኢሰመኮ በተለያዩ የክትትል ሪፖርቶች እንዲሁም የውይይት መድረኮች ያቀረባቸውን ምክረ-ሐሳቦች በአግባቡ ተፈጻሚ በማድረግ ሴት ሠራተኞች ሰብአዊ መብቶቻቸው ተከብረውላቸው የሚሠሩበትን ምቹ የሥራ አካባቢ መፍጠራቸውን እንዲያረጋግጡ፤


**293.** በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ የሚያልፉ የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት አቤቱታ ከማቅረብ እስከ ፍርድ አሰጣጥና አፈጻጸም ሂደቶች ድረስ ሰብአዊ መብቶቻቸው መከበራቸውን እንዲሁም ልዩ ፍላጎታቸውን ያማከለ ድጋፍ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ መንግሥት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ተደራሽ እና ምቹ የፍትሕ እና የአንድ ማእከል አገልግሎት ተቋማት በመዘርጋት፤ አስፈላጊ መረጃዎችን የሚያቀርቡ የመረጃ ማእከላትን እንዲያደራጅ፤ ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት በሂደቱ ሊከበሩላቸው የሚገቡ መብቶችንና ሊቀርቡላቸው የሚገቡ አገልግሎቶችን በተመለከተ ለፍትሕ ተቋማት እና ለአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ባለሙያዎች በቂ የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠና መሰጠቱን እንዲያረጋግጥ፤

**294.** በማሳደጊያ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ሕፃናትን በተመለከተ የሴቶች እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲሁም የክልል እና የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር አቻ ቢሮዎች በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት መደበኛ ክትትል እና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፤ የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት ኢሰመኮ በሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. ባወጣው የክትትል ሪፖርት እንዲሁም ቀጥሎ በተከናወኑ የውትወታ ተግባራት አማካኝነት የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት የቅበላ እና የሞግዚቶችና ሕፃናት ምጣኔን፤ ምግብ፣ መጠለያ እና ተገቢ አልባሳትን የማግኘት መብትን፤ የጤና፣ ሕክምና እና የሥነ ልቦና አገልግሎቶችን፤ የሕፃናት ደኅንነትና ጥበቃ እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ ያቀረባቸውን ምክረ ሐሳቦች በተሟላ ሁኔታ በመፈጸም የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎችንና መርሖችን ያከበረ የሕፃናት አስተዳደግን ተግባራዊ እንዲያደርጉ፤

**295.** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በወንጀል ነክ ነገር ውስጥ ገብተው የተገኙ ሕፃናት ማቆያና ተሐድሶ ተቋም ሕፃናት ጾታን፣ ዕድሜን፣ አካላዊ እና አእምሮአዊ ጤንነትን፣ የእንክብካቤ ፍላጎትን ወዘተ. መሠረት ባደረገ ሁኔታ ተለያይተው የሚያዙበትን አሠራር ተግባራዊ እንዲያደርግ፤ ተገቢው የትምህርት እና ሙያ ዝግጅት ያላቸውን ባለሙያዎች እንዲመድብ እና ተከታታይ ስልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤ ሕፃናት በተቋሙ የምግብ ዝርዝር (menu) መሠረት በቂ መጠን ያለው፣ ጥራቱን እና ንጽሕናውን የጠበቀ ምግብ እንዲሁም ንጹሕ የመጠጥ ውሃ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ አለበት። እንዲሁም የማደሪያ ክፍሎች አስፈላጊው ቁሳቁስ በበቂ ሁኔታ የተሟላላቸው እንዲሁም በቂ አየርና ብርሃን የሚያስገቡ መሆናቸውን፤ ሕፃናት በቂ፣ ወቅቱን የጠበቀ እና የአየር ሁኔታውን ያገናዘበ አልባሳት ማግኘታቸውን እንዲያረጋግጥ እንዲሁም ሕፃናት በር ተዘግቶባቸው በክፍላቸው ውስጥ እንዲቆዩ የሚደረጉበትን አሠራር ጨምሮ ከሕፃናት ደኅንነትና ሰብአዊ ክብር ተቃራኒ የሆኑ እርምጃዎችና ቅጣቶች እንዲቆሙ እርምጃዎችን እንዲወስድ፤ በተጨማሪም የአዲስ አበባ የሴቶች፣ ሕፃናት እና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ የተሐድሶ ተቋሙን መዋቅራዊ እና የአሠራር ክፍተቶች በየጊዜው በመገምገም ፈጣን ምላሽ እንዲሰጥ፤

**296.** በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በተለያየ ምክንያት የተዘጉ ትምህርት ቤቶች እንዲከፈቱ፤ በግጭት ወይም በተፈጥሯዊ አደጋዎች ምክንያት የወደሙ ትምህርት ቤቶች በቋሚነት እንዲገነቡ፤ ይህ ተግባራዊ እስኪሆን ድረስ ጊዜያዊ የመማሪያ አማራጮች እንዲዘጋጁ፤ ከትምህርት ገበታ ውጪ የሆኑ ተማሪዎች ወደ ትምህርት እንዲመለሱ እና የትምህርት ቤት ምገባ ሥርዓቶችን ተደራሽነት በማስፋፋት እና ጥራቱንም በማሻሻል ሕፃናት ምቹ የትምህርት ሁኔታ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የክልል ትምህርት ቢሮዎች እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻዎች በትብብር እንዲሠሩ ኢሰመኮ ያሳስባል።

# የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን መብቶች



ዝርዝር የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች

# ቀ) የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን መብቶች

**297.** በ2017 በጀት ዓመት በአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን መብቶች ዘርፍ ከታዩ አበረታች እርምጃዎች መካከል ኢትዮጵያ ፈርማ ያጸደቀችው[3] የአፍሪካ አረጋውያን መብቶች ፕሮቶኮል ወደ ሥራ ለመግባት የሚያስፈልገውን የፈራሚ ሀገራት ቁጥር ማግኘቱ የመጀመሪያው ነው። ፕሮቶኮሉ የአረጋውያንን ከአድልዎ ነጻ የመሆንና የእኩል እድል ተጠቃሚነት መብቶችን ጨምሮ ፍትሕ የማግኘት፣ በሕግ ፊት እኩል ጥበቃ የማግኘት፣ ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመወሰን፣ የሥራ ዕድልን ከተመለከቱ መድልዎች የመጠበቅ፣ የጤና፣ የትምህርትና የመሠረተ-ልማቶች ተደራሽነት፣ የማኅበራዊ ጥበቃ፣ እንክብካቤ እና ድጋፍ የማግኘት እንዲሁም በግጭትና በአደጋ ጊዜ ጥበቃ የማግኘት መብቶችን የሚደነግግ ሲሆን በዘርፉ የሚስተዋለውን የሕግ ማዕቀፍ ክፍተት በመሙላትና የአረጋውያን መብቶች ጥበቃ በማሻሻል ረገድ ቁልፍ አስተዋጽዖ ያደርጋል። በተጨማሪም ለሴት አረጋውያን፣ ለአካል ጉዳተኛ አረጋውያን፣ ሕፃናትን ለሚንከባከቡ አረጋውያን እና የቀደምት ነዋሪዎች (indigenous people) አባል ለሆኑ አረጋውያን የተለየ ጥበቃ ሊደረግላቸው እንደሚገባ የሚደነግግ በመሆኑ ድርብርብ ተጋላጭነት ላለባቸው አረጋውያን ዕውቅና የሚሰጥና የተሻለ ጥበቃ የሚያደርግ ነው።

**298.** በሀገር አቀፍ ደረጃ የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን መብቶችን ጥበቃ ለማሻሻል የሚረዱ የሕግ ማዕቀፎችና ሰነዶች ዝግጅት እንዲሁም የአሠራር ሥርዓት ማሻሻያዎችን በማድረግ ረገድ አበረታች እርምጃዎች ተወስደዋል። ለምሳሌ የአረጋውያን አዋጅ መረቀቁ፤ የአካል ጉዳተኞች ፖሊሲ የመጀመሪያ ረቂቅ መዘጋጀቱ፤ የአካል ጉዳተኞች የ10 ዓመት የድርጊት መርኃ ግብር መረቀቁ፤ የአፍሪካ የአረጋውያን መብቶች ፕሮቶኮል በሚደነግገው መሠረት አረጋውያን በቂ እንክብካቤና የሕመም ማስታገሻ ሕክምና ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የሚረዳው ብሔራዊ የጤና እንክብካቤ (palliative care) መምሪያ በቀደመው በጀት ዓመት መገባደጃ በጤና ሚኒስቴር መዘጋጀቱ እንዲሁም የአካል ጉዳተኝነትን ወቅታዊ እና አስተማማኝ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ወጥነት ባለው መልኩ ለማሰባሰብ የሚረዳ ረቂቅ መምሪያ በኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት መዘጋጀቱ ተጠቃሽ ናቸው። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ሕፃናት አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞች ሁኔታ ላይ ያተኮረ ሀገር አቀፍ ጥናት ማከናወኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ የአካል ጉዳተኞችን ሁኔታ አስመልክቶ ያለውን የመረጃ ክፍተት በመቅረፍ ረገድ አስተዋጽዖ የሚኖረው ነው።

**299.** ሕግ አርቃቂ አካላትም ኢሰመኮን ጨምሮ በተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሚሰጡ ምክረ ሐሳቦችን ለማካተት የተሻለ ቁርጠኝነት ማሳየታቸው እና አዳዲስ ሕጎች ከነባር ሕጎች በተሻለ የአረጋውያን እና አካል ጉዳተኞችን መብቶች አካተው በመረቀቅ ላይ መሆናቸው አበረታች ሲሆን ከእነዚህም መካከል በበጀት ዓመቱ የጸደቀው የትምህርት ሕግ አንዱ ነው። ኢሰመኮ በክትትል ሥራዎቹ ላይ ተመሥርቶ የሚያቀርባቸውን ምክረ ሐሳቦች ተፈጻሚ በማድረግ ረገድ ሌሎች ተጨማሪ ምሳሌዎች ያሉ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ:-

**300.** ኢሰመኮ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ለአካል ጉዳተኞች ያለውን ተደራሽነት አስመልክቶ ያደረገውን የሰብአዊ መብቶች ክትትል ተከትሎ በሰጠው ምክረ ሐሳብ መሠረት የኢትዮጵያ

[3] በአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር የአፍሪካ አረጋውያን መብቶች ፕሮቶኮል ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር 1182/2012።

አየር መንገድ የሞባይል መተግበሪያው ለዐይነ ስውራን ተደራሽ እንዲሆን ማድረጉ፣ መረጃ ሰጪ ሰነዶች በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች በብሬል ተዘጋጅተው በሁሉም አውሮፕላኖች እንዲቀመጡ መደረጉ፣ እድሳት በሚደረግባቸው የጅማ እና የጋምቤላ እንዲሁም አዳዲስ በሚገነቡት የጎዴ፣ ጂንካ እና ጎባ ከተሞች አየር ማረፊያዎች ተደራሽነትን ለማረጋገጥ እንደሚሠራ አየር መንገዱ ለኢሰመኮ በጽሑፍ ማስታወቁን ጨምሮ ሌሎች በርካታ አበረታች እርምጃዎችን መውሰዱ፤

301.ኢሰመኮ ሲከታተለው እና ተደጋጋሚ የውትወታ ሥራ ሲያካሂድበት የቆየው እና ለረጅም ጊዜ ሥራ ሳይጀምር የቆየው የአፋር ክልል ሰመራ ከተማ የአካል ጉዳተኞች ተሐድሶ ማእከልን አገልግሎት ለማስጀመር በክልሉ ሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ እና ጤና ቢሮ መካከል የነበረውን የይዞታ ይገባኛል ጥያቄ በክልሉ ፕሬዚደንት ጽሕፈት ቤት በኩል ውሳኔ እንዲያገኝ በማድረግ የክልሉ ጤና ቢሮ ማእከሉን እንዲያስተዳደር ተወስኖ ቢሮው ማእከሉን አገልግሎት ለማስጀመር የሰው ኃይል ምልመላ መጀመሩ፤

302. ኢሰመኮ በአዲስ አበባ የሚገኙ ሕንጻዎች ተደራሽነት ዙሪያ ባከናወነው ግልጽ የአቤቱታ ቅበላ ከዲዛይን እና ግንባታ ጋር በተገናኘ ኃላፊነት ያለባቸውን የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ በሕንጻ ባለቤቶች እና ተቆጣጣሪዎች ዘንድ ከፍተኛ መነቃቃት መፈጠሩ እና ባለግዴታዎች ሕንጻዎቻቸውን ተደራሽ ለማድረግ ተጨባጭ እርምጃዎችን መውሰድ መጀመራቸው፤ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፤ በባንኮች ላይ የቀረበውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ያከናወናቸውን ማሻሻያዎች እና እቅዶች በተለይም ደንብ እና መመሪያ ከማውጣት ረገድ የተጀመሩ ሥራዎችን በዝርዝር በማካተት ምላሽ በጽሑፍ ለኢሰመኮ መላኩ እና የቅድስተ ማሪያም ኮሌጅም አቤቱታ የቀረበባቸውን ካምፓሶቹን ተደራሽ ለማድረግ የወሰዳቸውን እርምጃዎች ጠቅሶ ለኢሰመኮ የጽሑፍ ማስረጃ መላኩ ተጠቃሽ ናቸው።

### የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን በተመለከተ የታዩ እመርታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በበርካታ ዘርፎች በአሳሳቢነታቸው የቀጠሉ ወይም ከ2016 በጀት ዓመት አንጻር ሲታዩ የተባባሱ ጉዳዮችም አሉ።

303. የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ያዘጋጀው የአካል ጉዳተኞች ረቂቅ አዋጅ ኢሰመኮና የአካል ጉዳተኞች ማኅበራትን ጨምሮ ሌሎች ባለድርሻ አካላት በሰጧቸው አስተያየቶች መሠረት ከዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት መርሖችና ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ዳብሮ በ2015 ዓ.ም. ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደሚቀርብ ተጠብቆ የነበረ ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ አልቀረበም። ለዚህም ምክንያቱ ከረቂቅ ሕጉ መጽደቅ አስቀድሞ የአካል ጉዳተኞች ፖሊሲ ሊኖር ይገባል የሚል አቋም በፍትሕ ሚኒስቴር በመያዙ ሂደቱ በመጓተቱ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል።

304. አስፈላጊውን የፈራሚ ሀገራት ቁጥር ያገኘው የአፍሪካ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ፕሮቶኮል (The Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Persons with Disabilities in Africa) ወደ ሥራ እንዲገባ ለማድረግ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ፕሮቶኮሉን እንዲያጸድቅ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጥያቄ ያቀረበ ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ አልጸደቀም።

305. የሰብአዊ መብቶች ሕጎችና ሰነዶች ሀገራት የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን ትክክለኛ ቁጥራዊ መረጃ በመያዝ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ምላሽ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው

መሆኑን ቢደነግጉም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ቁጥር በትክክል አለመታወቅ ሰብአዊ መብቶቻቸውን ከማስከበር እና ከማስጠበቅ አኳያ ተግዳሮት መሆኑ ቀጥሏል። እስካሁን መፍትሔ ያላገኘው ይህ ችግር ላለፉት ዓመታት የዘለቀና አሳሳቢነቱ በኢሰመኮ ሪፖርቶች ሲገለጽ የቆየ ነው።

306. ኢሰመኮ በ2017 በጀት ዓመት ከለያቸው አሳሳቢ ጉዳዮች መካከል በልዩ አዳሪ እና አካቶ ቅድመ መደበኛ፣ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያለው የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ተጠቃሽ ነው። በአዲስ አበባ፣ አምቦ፣ ባሕር ዳር፣ ቢሾፍቱ፣ ባኮ፣ ጋምቤላ፣ ሆሳዕና፣ መቐለ፣ ሰበታ እና ሻሸመኔ ከተሞች በተመረጡ ትምህርት ቤቶች የተከናወነው የሰብአዊ መብቶች ክትትል እንደሚያሳየው አብዛኞዎቹ ትምህርት ቤቶች የከባቢያዊ፣ ተቋማዊና የመረጃ ተደራሽነት ችግር አለባቸው። በተጨማሪም የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን የትምህርት መብት መረጋገጥ የሚያስተጓጉሉ የአመለካከት ተግዳሮቶች መኖራቸው፤ ለአካቶ ትምህርት ቤቶች ተብሎ የሚያዝ በቂ በጀት አለመኖሩ፤ በልዩ ፍላጎት ትምህርት ዘርፍ የሰለጠኑ በቂ መምህራን አለመኖራቸው እና የተማሪዎቹም ቁጥር አነስተኛ መሆኑ፤ በአካቶም ሆነ በልዩ አዳሪ ትምህርት ቤቶች በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት መሠረት የተዘጋጁ የመማሪያ መጻሕፍት በብሬል አለመታተማቸው፤ ለተማሪዎች በቂ ተመጣጣኝ ማመቻቸቶች የማይደረጉ መሆኑ እና በተለይ ለሴት አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተደራራቢ ተጋላጭነታቸውን መሠረት ያደረገ ድጋፍ የማይቀርብ መሆኑ በክትትሉ ተረጋግጧል። በተወሰኑ ልዩ አዳሪ እና አካቶ ትምህርት ቤቶች ሴት አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ጾታን መሠረት ላደረገ ጥቃት የሚያጋልጡ ሁኔታዎች መኖራቸው፣ እንዲሁም ጥቃቶች የተፈጸሙባቸው ሁኔታዎች ሲስተዋሉ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የተደረጉ ጥረቶች ደካማ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል።

307. በተለያዩ ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች የሚገኙ የአረጋውያን መንከባከቢያ ማእከላት በግጭቶች እና ተያይዘው በሚከሰቱ ችግሮች ሳቢያ ዐቅማቸው እየተዳከመ በመምጣቱ ለአረጋውያን በሚያቀርቡት አገልግሎት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ መኖሩን የኢሰመኮ ክትትሎች ያስረዳሉ። ለምሳሌ በአማራ ክልል በአጣዬ ከተማ የአጣዬ አረጋውያን እንክብካቤ ማእከል፤ በማእከሉ ለሚገኙ እንዲሁም ከማእከል ውጪ በመሆን ድጋፍ ለሚደረግላቸው አረጋውያን ያቀርብ በነበረው ድጋፍ ላይ ግጭቱ ከፍተኛ ጫናን እያሳደረ መሆኑ ተጠቃሽ ነው። በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ ከተማ ለአረጋውያን ማእከል ግንባታ ተሰጥቶ የነበረው ቦታ ከ3 ዓመታት በፊት በመንግሥት ተመልሶ የተወሰደ ሲሆን በ2017 በጀት ዓመትም ምትክ ቦታ አልተሰጠም።

308. አረጋውያን ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች መቀጠላቸው እና ይህንኑ ለማስቆም የሚደረጉ ጥረቶች አነስተኛ መሆናቸው፤ በተለይም በአብዛኛው ጥቃቶቹ በቅርብ ሰዎች እና ተንከባካቢዎች የሚፈጸሙ እንደመሆናቸው ሪፖርት ሳይደረጉ መታለፋቸው የአረጋውያን ሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ሁኔታ ላይ ከፍተኛ ጫናን እያሳደረ ቀጥሏል። ለዚህም ማሳያ ሊሆን የሚችለው ምንም እንኳ <u>የዓለም ጤና ድርጅት ባወጣው ሪፖርት በማኅበረሰብ ውስጥ ከሚኖሩ ስድስት አረጋውያን አንድ አረጋዊ/ት ላይ ጥቃት የሚፈጸም መሆኑን</u> የሚጠቅስ ቢሆንም በሀገር ደረጃ እንደ ኢሰመኮ ያሉ ጉዳዩን ለመመርመር ሥልጣን ላላቸው አካላት የሚቀርቡ አቤቱታዎች ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነው።

309. በነባር ሕጎች ላይ የሚስተዋሉ በአካል ጉዳተኞች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ እና በማኅበረሰቡ ዘንድ የተዘባ አመለካከትን የሚያስፋፉ አገላለጾች አዲስ ተረቀው ወደ ሥራ

በሚገቡ ሰነዶችም ላይ የሚስተዋሉ መሆኑ ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ለምሳሌ በነሐሴ ወር 2016 ዓ.ም. ወደ ሥራ የገባው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕፃናት ቀለብ አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2016 በአንቀጽ 2 ላይ "ልዩ ፍላጎት" የሚለውን ሲተረጉም "...የሕይወት እንቅስቃሴዎችን የሚገድቡ አካላዊ፣ ስሜታዊ ወይም አእምሯዊ ጉድለት..." በማለት አስቀምጧል። ይህም በተግዳሮቶች ምክንያት ከማኅበራዊ እንቅስቃሴ የሚገደቡ አካል ጉዳተኞችን አካላቸው ላይ ያለውን ጉዳት እንደ 'ጉድለት' በመቁጠር የተሳትፎ ገደቡ ከዚሁ የመነጨ አድርጎ ማቅረቡ ኢትዮጵያ ፊርማ ካጸደቀችው ዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት ጋር የሚጣጣም አይደለም። በተጨማሪም በግንቦት ወር 2017 ዓ.ም. ወደ ሥራ የገባው የጤና አገልግሎት አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1362/2017 አካል ጉዳትን እንደ ሕመም በመቁጠር "ጤና"ን 'የበሽታ ወይም የአካል ጉዳት አለመኖርን ጨምሮ የተሟላ የአካል፣ የአዕምሮ እና የማኅበራዊ ደኅንነት ሁኔታ ነው' ሲል ተርጉሞታል።

310.ከዚህ በላይ በዝርዝር በተዳሰሰበት ክፍል እንደተገለጸው ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው እና መስማት የተሳናቸው ሰዎች በተለይም በታጠቁ ኃይሎች የሚደርስባቸውን ጥቃት ማስቆም ባለመቻሉ በበጀት ዓመቱ የሚደርሱ ጉዳቶች ቀጥለዋል።

311.በተለያዩ ተቋማት ለሚሠሩ አካል ጉዳተኞች ሊቀርብ የሚገባው ተመጣጣኝ ማመቻቸት በተሟላ እና ፍላጎትን መሠረት ባደረገ መልኩ የማይተገበር መሆኑ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው።

## ምክረ ሐሳብ

312.ረቂቁን የአካል ጉዳተኞች ሕግ አጸድቆ ወደ ሥራ ለማስገባት እንዲቻል የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በጅምር ላይ ያለውን የአካል ጉዳተኞች ፖሊሲ አሳታፊ በሆነ መንገድ ግብዓት በመሰብሰብ በፍጥነት እንዲያጠናቅቅ እና ፍትሕ ሚኒስቴርም ረቂቅ ሕጉ ጸድቆ ወደ ሥራ መግባት የሚችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር ሁኔታዎችን እንዲያመቻች፤

313.የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአፍሪካ አካል ጉዳተኞች መብቶች ፕሮቶኮልን በማጽደቅ ወደ ሥራ እንዲገባ እንዲያደርግ፤

314.የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት የአረጋውያንን እና አካል ጉዳተኞችን ወቅታዊ እና አስተማማኝ ስታቲስቲካዊ መረጃ ለመያዝ የጀመረውን እንቅስቃሴ በማጠናከር መረጃውን እንዲያጠናቅር እና ለሕዝብና ለሚመለከታቸው አካላት ይፋ እንዲያደርግ፤

315.ትምህርት ሚኒስቴር እና በተዋረድ በየክልሉና ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የትምህርት ቢሮዎች እንዲሁም ትምህርት ቤቶች የአካቶ እና ልዩ ትምህርት ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚቀርብበት ሁኔታ ከአቻ ጉዳት አልባ ተማሪዎች እኩል መሆኑን እንዲያረጋገጡ፤ በተለይም የትምህርት ቤቶችን ከባቢያዊ፣ ተቋማዊ እና የመረጃ ተደራሽነት እንዲያረጋግጡ፤ በአመለካከት ችግሮች ሳቢያ የሚደርሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን ለመከላከል ስልጠና መስጠትን ጨምሮ አስፈላጊውን ተግባራት እንዲያከናውኑ እንዲሁም አስፈላጊውን የሰው ኃይል፣ የበጀት እና የቁሳቁስ አቅርቦት በማሟላት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ፤

316.የፍትሕ አካላት፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ የክልል ትምህርት ቢሮዎች፣ ትምህርት ቤቶች እና ሁሉም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በትምህርት ቤቶች አካባቢ የሚስተዋሉ እና በተለይም በሴት አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ላይ ጾታን መሠረት በማድረግ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለማስቆም ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ፤ ሴት አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ያለባቸውን ተደራራቢ

ተጋላጭነት መሠረት በማድረግ አስፈላጊውን ጥበቃ እና ጥንቃቄ እንዲያደርጉ፤ ጥቃቶች ሲፈጸሙ ተጠያቂነትን እንዲያረጋግጡ፤

317. መንግሥት ግጭቶች በአጠቃላይ በማኅበረሰቡ ላይ በተለይም በማእከላት በሚገኙ አረጋውያን ላይ እያሳደረ ያለውን ተጽዕኖ ከግምት በማስገባት፣ ከታጣቂ ኃይሎች ጋር ያለው ጉዳይ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ጥረት እንዲያደርግ እና በማእከላቱ የሚገኙ አረጋውያን ለከፋ ጉዳት ከመዳረጋቸው በፊት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያቀርብ፤

318. የፍትሕ አካላት በየአካባቢያቸው የሚገኙ አረጋውያንን ሁኔታ በንቃት በመከታተል ከጥቃት የመጠበቅ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ እና ሁሉም ባለድርሻ አካላት አረጋውያኑ ስለጥቃት ምንነት እና ዐይነት ያላቸውን ግንዛቤ በማሳደግ ለመብቶቻቸው መቆም የሚችሉበትን አቅም በመገንባት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ፤

319. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበር ዋነኛ ሚና የሚጫወቱትን እና አባላቶቻቸው ሲገለገሉባቸው የቆዩት የአካል ጉዳተኞች ማኅበራት ጽሕፈት ቤቶችን በኮሪዶር ልማት ምክንያት የማፍረስ ተግባር የመጨረሻ አማራጭ መሆኑን አረጋግጦ እንዲያስተገብር እና ተደራሽ የሆኑ ምትክ ቦታዎች መስጠታቸውን እንዲያረጋግጥ፤

320. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሕፃናት ቀለብ አወሳሰን መምሪያው ላይ የተጠቀመውን አግባብነት የሌለው አገላለጽ ከሰብአዊ መብቶች ሕጎች ጋር በሚጣጣም አገላለጽ በመተካት ማሻሻያ እንዲያደርግ፤ በዚሁ መሠረት የተዘጋጁ ማናቸውም ሰነዶች ላይ እርማት እንዲያደርግ፤

321. የጤና ሚኒስቴር በጤና አገልግሎት አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1362/2017 ላይ አካል ጉዳትን እንደ ሕመም በመቁጠር በሰጠው ያልተገባ ትርጉም ላይ ማሻሻያ እንዲያደርግ፤

322. የታጠቁ ኃይሎች በተለይም የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው እና መስማት የተሳናቸው ሰዎች ላይ ኢ-ምክንያታዊ በሆነ ጥርጣሬ ከሚፈጽሙት ጥቃት እንዲታቀቡ፤

323. መንግሥት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ለሚቀጥሯቸው አካል ጉዳተኛ ሠራተኞች አስፈላጊውን ተመጣጣኝ ማመቻቸት በተሟላ ሁኔታ እንዲያቀርቡ፤

324. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ አሶሳ ከተማ አስተዳደር ለአረጋውያን ማእከል ግንባታ ተብሎ ተሰጥቶ በነበረው እና ተመልሶ በተወሰደው ቦታ ምትክ እንዲሰጥ።

# የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶች



ዝርዝር የሰብአዊ መብቶች
ጉዳዮች

# በ) የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶች

## የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች

**325.**በ2017 በጀት ዓመት በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መብቶች ዘርፍ የታዩ የተወሰኑ መልካም እመርታዎች ያሉ ሲሆን ከእነዚህም መካከል በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ተጠልለው በሚገኙበት አካባቢ ብሔራዊ መታወቂያ የሚያገኙበት ሁኔታ መመቻቸቱ፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት ብሔራዊ ስትራቴጂ መዘጋጀቱ፤ በአፋር ክልል በበጀት ዓመቱ በተደጋጋሚ እያጋጠመ ከሚገኘው የመሬት መንቀጥቀጥ ጋር ተያይዞ ጉዳት በደረሰባቸውና ሥጋት ባለባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ የመፈናቀል ሥጋት ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን ወደ ሌሎች አካባቢዎች የማስፈር እና ሰብአዊ ድጋፍ የማቅረብ እንቅስቃሴዎች መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት እየተደረጉ መሆናቸው፤ በሐረሪ ክልል በሸንኮር ወረዳ በክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ቅጥር ግቢ በጊዜያዊነት ተጠልለው ከነበሩ ተፈናቃዮች አብዛኞቹ ወደ ቀድሞ መኖሪያቸው መመለሳቸው፤ በአማራ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች ለሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት እንዲቻል በክልሉ አደጋ መከላከል እና ምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ኮሚሽን እና በተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት (UNDP) አማካኝነት የዘላቂ መፍትሔ ስትራቴጂ የተዘጋጀ መሆኑ፤ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ለሚገኙ የተሟላ ዘላቂ መፍትሔ አግኝተው ራሳቸውን ማስተዳደር ላልጀመሩ ተፈናቃዮች ክልሉ የሚያደርገውን የድጋፍ እና ጥበቃ ተግባር መቀጠሉ በ2017 በጀት ዓመት በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መብቶች ዘርፍ የታዩ ተጨማሪ ቁልፍ እምርታዎች ናቸው፡፡

**326.**ኢሰመኮ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እንዲሁም የውጪ ግንኙነትና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ጋር በመሆን በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን ዳሰነች ወረዳ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በሚገኙባቸው መጠለያ ጣቢያዎች ከመስከረም 10 እስከ 14 ቀን 2017 ዓ.ም. በአካል ምልከታ በማድረግ ጭምር ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔ በሚያገኙበት ሁኔታ ላይ የተቀናጀ ውትወታ አካሂዷል፡፡ በምልከታው የተሳተፉ የምክር ቤቱ አባላት ለወከሏቸው የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች፣ አሳሳቢ ጉዳዮችን በማቅረብ ችግሩ ትኩረት እንዲያገኝ ከማድረጋቸው በተጨማሪ ኢሰመኮ ኅዳር 19 ቀን 2017 ዓ.ም. በምክር ቤቱ በመገኘት የተፈናቃዮቹን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በተመለከተ በክትትሎቹ የለያቸውን ግኝቶችና ምክረ ሐሳቦች ለዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት በማቅረብ አባላቱ ስለሁኔታው ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ እና ጉዳዩ የምክር ቤቱ አጀንዳ እንዲሆን ለማድረግ ችሏል፡፡

**327.**ኢትዮጵያ በአፍሪካ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጥበቃ እና ድጋፍን አስመልክቶ የተደረገውን የአፍሪካ ኅብረት ስምምነት (የካምፓላ ስምምነት) በአዋጅ ቁጥር 1187/2012 ማጽደቋ ይታወሳል፡፡ ኢሰመኮ የካምፓላ ስምምነት ማስፈጸሚያ ብሔራዊ ሕግ አለመኖሩ በተፈናቃዮች መብቶች ጥበቃ እና ድጋፍ ላይ ያሳደረውን ተጽእኖ እንዲሁም የብሔራዊ ሕጉን አስፈላጊነት እና በውስጡ ሊያካትታቸው የሚገቡ ጉዳዮችን አስመልክቶ ውትወታ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በሌላ በኩል ሰላም ሚኒስቴር ሲያስተባብረው በቆየው የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጥበቃ እና

ድጋፍ አዋጅ አርቃቂ ኮሚቴ ውስጥ በአማካሪነት ሚና በመሳተፍ በክትትልና ውትወታ ሥራዎቹ የደረሰባቸውን ግኝቶች መሠረት በማድረግ በተለይም የሕግ፣ የተቋማዊ አደረጃጀት እና ቅንጅታዊ አሠራር ክፍተቶችን የተመለከቱ ምክረ ሐሳቦችን ለአርቃቂ ኮሚቴው አባላት እንዲሁም ከ2013 ዓ.ም. ጀምሮ ለሌሎች ባለድርሻ አካላትም ሲያቀርብና ውትወታ ሲያደርግ ቆይቷል። በዚህም የስምምነቱ ማስፈጸሚያ ብሔራዊ ረቂቅ ሕግ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት መቅረቡ እንደ አዎንታዊ እርምጃ የሚጠቀስ ቢሆንም እስካሁን ጸድቆ በሥራ ላይ አለመዋሉ ከሕግ እና ተቋማዊ ማዕቀፍ ጉድለቶች ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ የተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ክፍተቶች ተባብሰው እንዲቀጥሉ አስተዋጽዖ አድርጓል።

**328.** በአፋር ክልል ተፈናቃዮች እና ተመላሾች በሚገኙባቸው በኪልበቲ ረሱ ዞን፣ በርሃሌ ወረዳ በሻሂጉቢ፣ ዴሳኮሪማ እንዲሁም ሙልሙል እና ገሀርታ ቀበሌዎች ለተፈናቃዮችና ተመላሾች እየተደረገ ስላለው የሰብአዊ ድጋፍ እንዲሁም ዘላቂ መፍትሔ የማፈላለግ ተግባራት ያሉበትን ደረጃ ለመረዳት ክትትል ተደርጓል። በዚህም ለተፈናቃዮች የሚቀርቡ ምግብ ነክ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ሰብአዊ ድጋፎች ወቅቱን የጠበቀ፣ በቂ እና ለሁሉም ተደራሽ አለመሆን፤ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ለሁሉም ተፈናቃዮች ተደራሽ በማድረግ ረገድ ክፍተቶች መኖራቸው፤ ልዩ ትኩረት ለሚያስፈልጋቸውና ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት ተጋላጭ ለሆኑ ተፈናቃዮች ፍላጎቶቻቸውን መሠረት ያደረገ ድጋፍ አለመኖሩ ከቁልፍ አሳሳቢ ጉዳዮች መካከል መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል። ተፈናቃዮች ወደ ቀድሞ ቀያቸው እንዲመለሱ በተደረገበት ወቅትም የሰብአዊ መብቶች መርሖችን በተከተለ ሁኔታ ተፈናቃዮች ስለዘላቂ መፍትሔ አማራጮች፣ ስለዕቅዱና ስለዝርዝር አተገባበሩ የተሟላ መረጃ እንዲያገኙ እንዲሁም የመመለስ ሂደቱን የተፈናቃዮችን ደኅንነት እና ሰብአዊ ክብር በጠበቀ መልኩ ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ክፍተቶች መኖራቸውን ኢሰመኮ ተረድቷል።

**329.** ከዚህም ሌላ በአፋር ክልል በተለይም ዞን ሦስት በአዋሽ ፈንታሌ እና ዱለቻ ወረዳዎች በተደጋጋሚ እየተከሰተ ባለው የመሬት መንቀጥቀጥ ሳቢያ ነዋሪዎች ቤት ንብረታቸውን ጥለው ለመፈናቀል የተገደዱ ሲሆን ከተፈናቃዮቹ ብዛት ጋር ተመጣጣኝነት ያለው ሰብአዊ ድጋፍ እየተደረገላቸው አለመሆኑ፤ በተለይም የውሃ አቅርቦት እጥረት በመኖሩ ተፈናቃዮች ባልታከመ የወንዝ ውሃ ላይ ጥገኛ በመሆናቸው ለውሃ ወለድ በሽታ መጋለጣቸው፤ በተጨማሪም በዚህ ወቅት ተፈናቃዮቹ እንዲሰፍሩ የተደረጉበት አካባቢ የእሳተ ገሞራ/መሬት መንቀጥቀጥ ክስተቶች መነሻ ከሆኑት ቦታዎች በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝ በመሆኑ ነዋሪዎች ተፈናቃዮቹ ዳግም የመፈናቀል ሥጋት ያለባቸው መሆኑ ትኩረትና አፋጣኝ ምላሽ የሚሹ አሳሳቢ ጉዳዮች ናቸው።

**330.** በአማራ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች 796,860 ተፈናቃዮች እና 725,163 ተመላሽ ተፈናቃዮች በተለያዩ አካባቢዎች በመጠለያ ጣቢያ ተጠልለው እና ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው እየኖሩ ይገኛሉ። ምግብና መጠለያን ጨምሮ በክልሉ ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በመንግሥትም ሆነ በተራድኦ ድርጅቶች የሚደረገው የምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆነ ድጋፍ በተወሰኑ አካባቢዎች ሙሉ በሙሉ መቋረጡ እንዲሁም በሌሎች አካባቢዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱ፣ ተፈናቃዮች አራት ዓመት እና ከዚያ በላይ በተራዘመ የመፈናቀል ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ መሆናቸው እና በክልሉ ባለው ግጭት ሳቢያ የደኅንነት ሥጋቶች መኖራቸው ለዘርፈ ብዙ ችግሮች የተጋለጡ አድርጓቸዋል። ለምሳሌ በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ኮምቦልቻ ከተማ እና ተሁለደሬ ወረዳ፣ በባሕር ዳር ከተማ፣ በምሥራቅ እና ሰሜን ጎጃም ዞኖች፣ በደቡብ፣ ማእከላዊ እና ሰሜን ጎንደር ዞኖች በተለያዩ መጠለያ ጣቢያዎች

ተጠልለው እና ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቀለው የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ወቅቱን የጠበቀ፣ በቂ እና ተከታታይነት ያለው የምግብ አቅርቦትና መጠለያ ድጋፍ እንዲሁም የትምህርት እና የጤና አገልግሎት እየቀረበላቸው እንዲሁም የዘላቂ መፍትሔ ሥራዎችም እየተሠሩ ባለመሆኑ የተፈናቀሉ ሰዎችን በከፋ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ውስጥ እንዲኖሩ አስገድዷቸዋል። ተፈናቃዮቹ በሚኖሩባቸው መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ከዚህ ቀደም ድጋፍ ያደርጉ የነበሩ የተራድዖ ድርጅቶች ሥራ ማቋረጣቸው የምግብ እና የሕክምና አገልግሎት እጥረት እንዲባባስ አድርጓል። በተጨማሪም ተፈናቃዮች የተጠለሉባቸው ጊዜያዊ ድንኳኖች በቆይታ ብዛት እየተጎዱ እና እየፈራረሱ በመሆኑ ከብርድ እና ዝናብ ባለፈ ለደኅንነት ሥጋት እንዲጋለጡ አድርጓቸዋል።

331. በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ ዞን ባምባሲ ወረዳ ከ2960 በላይ የሚገመት ቤተሰብ በ2013 ዓ.ም. እና 2014 ዓ.ም. በተለያየ ጊዜ ከኦሮሚያ ክልል፣ ምዕራብ ወለጋ ዞን፣ ጉሊሶ፣ ባቦ፣ መንዲ ወረዳዎች እንዲሁም ከባቦ ገምቤል ወረዳ፤ ቦኒ፣ ሙሜ ድልቢና ሲርባ ቀበሌዎች የተፈናቀሉ ሰዎች "በኦልድ ካምፕ" እና "ስቴድየም/ወርልድ ቪዥን" ተብለው በሚጠሩ የተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ይገኛሉ። ዘላቂ መፍትሔ ሳያገኙ በመጠለያ ጣቢያዎች መኖር ከጀመሩ ቢያንስ ከ3 ዓመት በላይ ከሆናቸው ተፈናቃዮች መካከል አብዛኞቹ ከመፈናቀላቸው በፊት በተሻለ የኢኮኖሚ ሁኔታ ላይ ይገኙ የነበሩ ሲሆኑ፣ ድጋፍ እየጠበቁ ለረጅም ጊዜ በመፈናቀል ሁኔታ ውስጥ በመቆየታቸው ምክንያት ከኢኮኖሚያዊ ችግሮች ባለፈ ለሥነ-ልቦናዊ ጉዳቶች ተዳርገዋል። በተጨማሪም "ኦልድ ካምፕ" በሚባለው መጠለያ ጣቢያ ወደ 2 ዓመት ለሚጠጋ ጊዜ የውሃ አቅርቦት በመቋረጡ ተፈናቃዮች ከወራጅ ውሃ ለመጠቀም የተገደዱ በመሆኑ ለውሃ ወለድ በሽታ ተጋልጠው ይገኛሉ።

332. በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ ዞን የተለያዩ ከተሞች ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ሰዎች ከአዋሳኝ የኦሮሚያ ክልል ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን አመያ እና ኖኖ ወረዳዎች በ2016 ዓ.ም. በተከሰተ ግጭት ተፈናቅለው ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው እየኖሩ ይገኛሉ። ተፈናቃዮቹ በሚገኙበት ቦታ አስፈላጊው ምዝገባ ያልተደረገላቸው እንዲሁም ሰብአዊ ድጋፍ ያልቀረበላቸው ከመሆኑ በተጨማሪ "ወደዚህ የመጣችሁት ትጥቅ ሳትፈቱ ነው" በሚል በአካባቢው በተቋቋመው "ኮማንድ ፖስት" ለእስር እንደሚዳረጉ እና ይህም ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ ሥጋት እንዳሳደረባቸው ኢሰመኮ ባደረጋቸው ክትትሎች አረጋግጧል።

333. በዚሁ ክልል ከማረቆ ልዩ ወረዳ ተፈናቅለው በእንሴኖ እና ቡታጅራ ከተማ የሚኖሩ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ሰብአዊ መብቶች ሁኔታን ለመረዳት በማረቆ ልዩ ወረዳ፣ በምሥራቅ መስቃን ወረዳ፣ በቡታጅራ ከተማ፣ በእንሴኖ ከተማ፣ በዲዳ ሚዶሬ ቀበሌ እንዲሁም በዱራሜ ከተማ በተደረገው ክትትል በዲዳ ሚዶሬ ቀበሌ የወደሙ የተፈናቃዮች ቤቶችን የመጠገን ሥራዎች የተጀመሩ ቢሆንም ቤቶቹ ተሠርተው ባለመጠናቀቃቸው ምክንያት ተፈናቃዮች ወደ ቀድሞ ቀያቸው አልተመለሱም። የክልሉ መንግሥት ተፈናቃዮች ድጋፍ ማግኘት ያለባቸው በቀድሞ ቀያቸው ነው በማለቱ ተፈናቅለው በሚኖሩበት አካባቢ ይደረግ የነበረው የሰብአዊ ድጋፍ ስለተቋረጠ ለችግር ተዳርገዋል። በተጨማሪም ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ካፋ ዞን ዴቻ ወረዳ ሻሎ ቀበሌ በ2011 ዓ.ም. ተፈናቅለው በማእከላዊ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ከምባታ ጠምባሮ ዞን ዶዮ ገና ወረዳ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ተገቢው የሰብአዊ ድጋፍ እየቀረበላቸው አለመሆኑን ለመረዳት ተችሏል። ከእነዚህ ተፈናቃዮች ውስጥ የተወሰኑት ወደ ቀድሞ ቀያቸው እንዲመለሱ የተደረገ ቢሆንም በዘላቂነት እስኪቋቋሙ ድጋፍ ባለመደረጉ ለዳግም መፈናቀል ተዳርገዋል።

334.ከሐረሪ ክልል አሚር ኑር ወረዳ ገንደፌሮ ከሚባል አካባቢ በ2011 ዓ.ም. በግለሰቦች መካከል በተነሳ ግጭት ተፈናቅለው በሸንኮር ወረዳ በክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ቅጥር ግቢ በጊዜያዊነት ተጠልለው ከነበሩ 18 ቤተሰቦች ውስጥ 14ቱ ወደ ቀድሞ ቀያቸው መመለሳቸው የሚበረታታ ቢሆንም ተመላሾች በዘላቂነት እስኪቋቋሙ ድረስ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎች እየተደረጉላቸው ባለመሆኑ ለችግር ተጋልጠዋል። በተጨማሪም ተፈናቃዮች በተመለሱበት አካባቢ የውሃ እና የመብራት አገልግሎት ማግኘት አለመቻላቸው አሳሳቢ ችግር ሆኖ ቀጥሏል።

335.ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ቦራ ወረዳ ባርታ ሳሚ ቀበሌ (አውራ ጎዳና) 189 ቤተሰቦች እና ከጂርሜ ቦራ ቀበሌ 93 ቤተሰቦች በድምሩ 282 ቤተሰቦች ከሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ከመኖሪያ አካባቢያቸው የተፈናቀሉ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ከዱግዳ ወረዳ ወዮ ገብርኤል ቀበሌ 290 ገደማ የሚሆኑ ቤተሰቦች ወይም 1305 ሰዎች ከመጋቢት ወር 2016 ዓ.ም. ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ከመኖሪያ አካባቢያቸው ተፈናቅለዋል። በተጨማሪም ከዱግዳ ወረዳ ጀዌ ቦፎ እና ኦዳ ፊላ ቀበሌዎች 244 አባዎራዎች እና 51 እማወራዎች በድምሩ 295 ቤተሰቦች ወይም 1302 ሰዎች ከሐምሌ 2015 ዓ.ም. ጀምሮ ከ689.82 ሄክታር የእርሻ መሬት ይዞታቸው ተፈናቅለው ይገኛሉ። እነዚህ ነዋሪዎች በአከባቢው የሚንቀሳቀሰው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") በሚያደርስባቸው ተደጋጋሚ ብሔር ተኮር ጥቃት ምክንያት ከመኖሪያቸው እና ከእርሻ ቦታቸው ተፈናቅለው በዞኑ የተለያዩ ከተሞች በመቂ፣ ሞጆ፣ ባቱ፣ ቦቴ (ዓለም ጤና) እና አዳማ ከተማ ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩ ናቸው። ተፈናቃዮች ከተፈናቀሉበት ጊዜ ጀምሮ ምንም ዐይነት የምግብ፣ የመጠለያ፣ የአልባሳት እና ሌሎች ቁሳቁሶች ድጋፍ ያልተደረገላቸው መሆኑ፤ ተፈናቃዮች መጠለያ ባለማግኘታቸው እንዲሁም ሌላ አማራጭ በማጣታቸው በዘመድ ቤት ተጠግተው እንዲሁም ቀደም ሲል ተከራይተው ይኖሩ የነበሩትም ቤት ኪራይ መክፈል ባለመቻላቸው ቤተክርስቲያናት ውስጥ ተጠልለው ለመቆየት መገደዳቸው፤ ለተፈናቃዮች የሚደረግ የሰብአዊ ድጋፍ ባለመኖሩ እና የተፈናቀሉ የሕፃናት ተማሪ ወላጆች የትምህርት ወጪ ለመሸፈን ባለመቻላቸው ተፈናቃይ ሕፃናት ከመማር ይልቅ ቤተሰባቸውን እና ራሳቸውን ለመደግፍ በሰው ቤት በሠራተኝነት ተቀጥሮ መሥራትን ጨምሮ ለጉልበት ብዝበዛ ሊያጋልጧቸው በሚችሉ ሌሎች ሥራዎች ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። በቦራ ወረዳ የባርታ ሳሚ እና ጂርሜ ቦራ ቀበሌ ነዋሪዎች ከመደበኛ የመኖሪያ አካባቢያቸው ሙሉ በሙሉ በመፈናቀላቸው ምክንያት በመፈናቀል ወቅት የወደሙ ቤቶቻቸው እና ንብረታቸው ጥገናም ሆነ እድሳት አልተደረገላቸውም። በሁለቱም ወረዳዎች የሚገኙ ተፈናቃዮች የእርሻ መሬታቸው ተቀላቅሎ በመታረሱ ምክንያት በይዞታ መብታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያደርስ ሁኔታ እንዳይፈጠርም ሥጋት አለባቸው።

336.በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ ደቡብ ኦሞ ዞን፣ ዳሰነች ወረዳ በኦሞ ወንዝ መሙላት ምክንያት ከ2012 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈናቅለው በ12 የተፈናቃዮች ጣቢያዎች ውስጥ የሚገኙ ከ79 ሺህ በላይ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ይገኛሉ። ተፈናቃዮቹ ይህ ሪፖርት እስከ ተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ ዘላቂ መፍትሔ ሳያገኙ በመፈናቀል ሁኔታ ውስጥ መገኘታቸው፣ ለመፈናቀል መንስኤው ዘላቂ መፍትሔ ካልተሰጠው በ2017 ዓ.ም. የክረምት ወቅትም ለከፋ ችግር የሚዳረጉ መሆኑ፣ እንዲሁም በኦሞራቴ ከተማ እና በአካባቢው በሚገኙ የተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያዎች ላይ የተጋረጠው የጎርፍ አደጋ ተፈናቃዮችን ዳግም የመፈናቀል ሥጋት ውስጥ የከተተ መሆኑ ከአሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች መካከል ናቸው።

**337.** በሰሜን ኢትዮጵያ በነበረው ጦርነት ምክንያት ተፈናቅለው በትግራይ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች ተጠልለው የቆዩ ተፈናቃዮችን ወደ ቀድሞ የመኖሪያ አካባቢያቸው ማለትም በደቡባዊ ዞን ሥር ኮረም ከተማ፣ ኦፍላ ወረዳ፣ ሕጉም ቡርዳ እና ፋላ ቀበሌ፣ ራያ አላማጣ ወረዳ፣ ዋጃ ጡሙጋ ቀበሌ፣ በአላማጣ ከተማ፣ 02 እና 03 ቀበሌ እንዲሁም በሰሜን ምዕራብ ዞን ጸለምት፣ ላዕላይ ጸለምት እና ማይፀብሪ ከተማ የመመለስ ሂደት የሰብአዊ መብቶች መስፈርቶችን መሠረት ያደረገ እና ያሟላ መሆኑን ለመመዘን ኢሰመኮ ክትትል አድርጓል፡፡ በአላማጣ፣ ኮረም፣ ኦፍላ፣ ራያ አላማጣ፣ ጨርጨር እና ዛታ አካባቢዎች እንዲመለሱ የተደረጉ ተፈናቃዮች የደኅንነት ሥጋት ያለባቸው በመሆኑ በትምህርት ቤቶች እንዲቆዩ የተደረገ መሆኑን፤ በጸለምት፣ ላዕላይ ጸለምት እና ማይፀብሪ ከተማ በተመላሾች እና በአካባቢው ማኅበረሰብ መካከል ያለው ግንኙነት ሰላማዊ ቢሆንም በሁለቱ ክልሎች አመራሮች መካከል የተፈጠረው አለመግባባት በተመላሾች ደኅንነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳደሩ ለዳግም መፈናቀል መዳረጋቸውን፤ እንዲሁም በሁሉም ቦታዎች በተመላሾች እና በተቀባይ ማኅበረሰብ መካከል ግጭት ባይኖርም አለመግባባቶች በውይይት የሚፈታበት ሁኔታ አለመመቻቸቱ በተመላሾች ደኅንነት ላይ ሥጋት ማሳደሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡

**338.** ተፈናቃዮች እንዲመለሱ በተደረጉባቸው አካባቢዎች የሚገኙ መሠረተ ልማቶች በጦርነት የወደሙ እና ጥገና ያልተደረገላቸው በመሆኑ ተገቢውን አገልግሎት እየሰጡ አይደለም፡፡ ለምሳሌ በአላማጣ የሚገኝ ሆስፒታል ከድንገተኛ ሕክምና እና የወሊድ አገልግሎት ውጭ ሌሎች አገልግሎቶችን እየሰጠ አይደለም፡፡ በተመሳሳይ ትምህርት ቤቶች በጦርነቱ የወደሙ በመሆኑ እና አንዳንድ አካባቢዎች የሲቪል አስተዳደር የሌለ በመሆኑ በአብዛኛው አካባቢ ትምህርት እየተሰጠ አይደለም፤ ጉዳት ያልደረሰባቸው ትምህርት ቤቶችም ለሌላ አገልግሎት እየዋሉ መሆኑንም ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለምሳሌ በራያ አላማጣ ወረዳ ዋጃ ጡሙጋ ቀበሌ 2 ትምህርት ቤቶች የመንግሥት ኃይሎች ካምፕ ሆነው የሚገኙ ሲሆን፤ በኦፍላ ወረዳ ፋላ ቀበሌ 1 ትምህርት ቤት የቀድሞ የህወሓት ታጣቂዎች መኖሪያ ሆኖ የሚያገለግል መሆኑን፤ እንዲሁም በአላማጣ ከተማ 1 የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋምን ጨምሮ ሌሎች 2 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተመላሾች ጊዜያዊ ማቆያ ሆነው ይገኛሉ፡፡ በደቡባዊ ዞን ሥር ወደሚገኙ አካባቢዎች እንዲመለሱ ከተደረጉ ተፈናቃዮች አብዛኞቹ በጦርነቱ ወቅት ቤቶቻቸው እና ሌሎች የግል ንብረቶቻቸው የወደሙባቸው እና የተዘረፉ በመሆኑ እንዲሁም በሌሎች ሰዎች የተያዙ በመሆኑ በጤና ጣቢያዎች እና በትምህርት ቤቶች ግቢ ውስጥ ለመኖር ተገደዋል፡፡

**339.** ለተመላሽ ተፈናቃዮች በዘላቂነት እስኪቋቋሙ ድረስ አስፈላጊ የሰብአዊ ድጋፍ እየተደረገላቸው ባለመሆኑ እንዲሁም የመንግሥት ሠራተኞች ወደ ቀድሞ ሥራቸው ባለመመለሳቸው እና በደኅንነት ሥጋት ምክንያት በሌሎች ሥራዎች ላይ ተሰማርተው ኑሯቸውን መምራት ባለመቻላቸው ለከፋ ችግር ተጋልጠው ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም የፍትሕ ተቋማት እና ፍርድ ቤቶች ወደ ሥራ ያልገቡ በመሆናቸው ተፈናቃዮች በመፈናቀል ወቅት ለደረሰባቸው የመብት ጥሰት ፍትሕ የሚያገኙበት ሁኔታ አልተመቻቸም፡፡

## ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች

**340.** በስደተኞች መብቶች ዘርፍ በበጀት ዓመቱ ከታዩ ቁልፍ እመርታዎች መካከል የኢትዮጵያ መንግሥት ስደተኞችን በተለይም በሱዳን የሚካሄደውን ግጭት ሸሽተው ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ስደተኞችን መቀበል እና ማስተናገዱን የቀጠለ መሆኑ፤ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ

ስደተኞች የብሔራዊ መታወቂያ፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎቶችን የሚያገኙበት ሁኔታ መመቻቸቱ፤ በኢትዮጵያ የሚገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎችን በኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ አገልግሎቶች አካታች ማድረግን ታሳቢ ያደረጉ ፕሮግራሞች መቀረጻቸው እንዲሁም ስደተኞች በተለያዩ ሥራዎች ላይ በመሰማራት ራሳቸውን እና ቤተሰቦቻቸውን በኢኮኖሚ የሚደግፉበት ሁኔታ እንዲኖር የሚያስችል የሕግ ማሻሻያ በተለይ የስደተኞችን እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የሥራ መብት የሚደነግግ መመሪያ መጽደቁ የሚጠቀሱ ናቸው። በአማራ ክልል ምዕራብ ጎንደር ዞን በደኅንነት ሥጋት ውስጥ ይገኙ የነበሩ የሱዳን ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎችን ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወሩ በማድረግ ሥጋታቸውን በአንጻራዊነት መቀነስ መቻሉ፤ በጋምቤላ ክልል አኩጉ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ ውስጥ የነበሩ የሙርሌ ጎሳ አባላት የሆኑ ደቡብ ሱዳናዊያን ስደተኞች የነበረባቸውን የጸጥታ እና ደኅንነት ችግር ለመቅረፍ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን ኛንጋቶም ወረዳ አይፓ ሳይት እንዲዛወሩ መደረጉ የስደተኞችን ደኅንነት በማስጠበቅ ረገድ የተወሰዱ መልካም እርምጃዎች ናቸው።

**341.** በአዲስ አበባ ከተማ ከ80,000 በላይ የሚሆኑ የከተማ ስደተኞች የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህም መካከል 73,000 ከኤርትራ፣ 2,466 ከየመን፣ 1,140 ከሶማሊያ፣ 720 ከደቡብ ሱዳን፣ 664 ከሶሪያ፣ 477 ከኮንጎ እና ከሌሎች ሀገራት ተሰደው የመጡ ናቸው። እነዚህ በከተማ የሚገኙ ስደተኞች በመንግሥት እና በተራድዖ ድርጅቶች ድጋፍ የሚደረግላቸው የከተማ ስደተኞች (Assisted urban refugees) እና በፍቃዳቸው ተዘዋውረው ከተማ የሚኖሩ ስደተኞች (self-relocated refugees) በመንግሥት ዕቅድ ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ እንዲኖሩ የተፈቀደላቸው (out of camp scheme) በሚል ተለይተው የሚታወቁ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ምዝገባ ያልተደረገላቸው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ጥገኝነት ጠያቂዎች በአዲስ አበባ ከተማ ይገኛሉ።

**342.** በአፋር ክልል 62,000 የሚደርሱ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የሚገኙ ሲሆን ኢሰመኮ ከኤርትራዊያን ስደተኞች በተደጋጋሚ የተቀበለውን አቤቱታ እና የሰበሰበውን መረጃ መሠረት በማድረግ በመስከረም ወር 2017 ዓ.ም. በአፋር ክልል አሳይታ እና በርሃሌ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ የሚገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ክትትል አከናውኗል። በዚህም በክልሉ ምንም ዐይነት የጥገኝነት ምዝገባ እንደማይከናወን እና በርካታ ጥገኝነት ጠያቂዎችም በአሳይታ እና በበርሃሌ በአፋር ክልል አሳይታ እና በርሃሌ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ የሚገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ክትትል አከናውኗል። በዚህም በክልሉ ምንም ዐይነት የጥገኝነት ምዝገባ እንደማይከናወን እና በርካታ ጥገኝነት ጠያቂዎችም በአሳይታ እና በበርሃሌ እየኖሩ መሆኑን ለመረዳት ችሏል። ከዚህ ቀደም በክልሉ የነበሩት በርካታ የስደተኞች መቀበያ ጣቢያዎችም (reception centers) ተዘግተዋል። በመሆኑም ጥገኝነት ጠያቂዎች ጥገኝነት የመጠየቅ መብታቸውን ከመነፈጋቸው ባሻገር፣ አካላዊ ጥበቃ እንደማይደረግላቸው፣ ለእስራት እንደሚዳረጉ፣ ሰብአዊ ድጋፍን ጨምሮ ሌሎች አገልግሎቶችን እንደማያገኙና የዕለት ተዕለት ኑሮአቸውን የሚመሩት በሌሎች ስደተኞች እገዛ መሆኑን፤ ይህ ደግሞ ስደተኞች ላይ ከፍተኛ ጫና መፍጠሩን ኢሰመኮ ለመረዳት ችሏል። በሰሜኑ ጦርነት ወቅት ስደተኞች ከበርሃሌ ወደ ሰርዶ የሸሹ ሲሆን፣ ከጦርነቱ በኋላ አብዛኛዎቹ ስደተኞች ወደ በርሃሌ የተመለሱ ሲሆን 300 የሚሆኑ ስደተኞች ደግሞ ወደ አሳይታ ተወስደዋል። በአሳይታ የስደተኞች ጣቢያ ውስጥም በሁለት መዋለ ሕፃናት ትምህርት ቤቶች ውስጥ

እንዲጠለሉ የተደረጉ በመሆኑ ትምህርት ተቋርጦ ከመቆየቱ ባሻገር የትምህርት ቤቶች ክፍሎች ለመጠለል አመቺ እና በቂ ባለመሆናቸው ስደተኞች በትምህርት ቤቶቹ ቅጥር ጊቢ ውስጥ በሸራ መጠለያ ውስጥ እየኖሩ ነው። በዚህም ምክንያት ለተለያዩ ሕመሞች እየተዳረጉ መሆኑን እንዲሁም ስደተኞቹ ያሉበት ሁኔታ ሰብአዊ ክብራቸውን ያልጠበቀ መሆኑን እና በተለይም ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋዊያን ለከፋ ችግር እየተጋለጡ መሆኑን ኢሰመኮ ተረድቷል።

**343.** በአማራ ክልል 43,000 ገደማ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች በምዕራብ እና ሰሜን ጎንደር ዞኖች ይገኛሉ። በክልሉ ያለው የትጥቅ ግጭት በስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ሰላም እና ደኅንነት፣ ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ መብት እንዲሁም በቂ የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦት ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ ከፍተኛ መሆኑን ኢሰመኮ በተለያየ ጊዜ በደረሱት አቤቱታዎች እና ከስደተኞች ተወካዮች ጋር ባደረጋቸው ውይይቶች ለመረዳት ችሏል። በተለይም በሱዳን ያለውን ጦርነት ሸሽተው በመተማ በኩል ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች በአማራ ክልል ባለው የጸጥታ ችግር ምክንያት ለደኅንነት ሥጋት እና የሰብአዊ ድጋፍ መስተጓጎል እንደተጋለጡ እንዲሁም ዘረፋ እና ሌሎችም የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እንደደረሰባቸው ኢሰመኮ ለመረዳት ችሏል። በተጨማሪም በክልሉ ሰሜን ጎንደር ዞን ዳባት ወረዳ ዓለም ዋጭ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ስደተኞች የታጠቁ ኃይሎች ወደ መጠለያ ጣቢያው በመግባት በሚያደርሱባቸው ጥቃት የሕይወት እና የአካል ጉዳትን ጨምሮ የተለያዩ የመብት ጥሰቶች እንደሚደርስባቸው እንዲሁም ለእስር እንደሚዳረጉ ኢሰመኮ ለመረዳት ችሏል።

**344.** በጋምቤላ ክልል ከ395,000 በላይ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች በ7 የስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ተጠልለው ይገኛሉ። ኢሰመኮ በጋምቤላ ክልል የሚገኙ ስደተኞችን በሚመለከት የሰብአዊ መብቶች ክትትል እና ውትወታን ሲያከናውን ቆይቷል። በዚህም ለስደተኞች የሚቀርበው መሠረታዊ ድጋፍ በመጠንም ሆነ በዐይነት ከጊዜ ወደ ጊዜ በመቀነሱ በስደተኞች የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል። ለስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች መብቶቻቸውን ማሳወቅን ጨምሮ፣ በሌሎች ጉዳዮችም ላይ በቂ እና ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠና እንደማይሰጥ ለመረዳት የተቻለ ሲሆን ለዚህም በምክንያት የተጠቀሰው ለስልጠና የሚውል በጀት አለመኖር ነው። በተጨማሪም ለስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች በተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት በቂ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ ፍትሕ የማግኘት መብታቸውን በማረጋገጥ ረገድ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል።

**345.** ኢሰመኮ በጋምቤላ ክልል ኦኩጉ የስደተኞች መጠለያ ይገኙ የነበሩ ደቡብ ሱዳናዊያን የሙርሌ ጎሳ ስደተኞችን በሚመለከት ከየካቲት 8 እስከ 19 ቀን 2016 ዓ.ም. ባከናወነው ክትትል ስደተኞች የጸጥታ እና ደኅንነት ሥጋት እንዳለባቸው፤ መጠለያው በደረሰበት ተደጋጋሚ ጥቃት እና ዘረፋ በከፊል በመውደሙ ምግብ፣ መጠለያ፣ ጤና እና ትምህርትን የመሳሰሉ አገልግሎቶች አቅርቦት ባለመኖሩ ስደተኞቹ ለሰብአዊ ቀውስ እንደተዳረጉ አመላክቶ ነበር። ኢሰመኮ በጉዳዩ ላይ ከስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት እንዲሁም ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጋር ምክክሮችን ጨምሮ የተለያዩ የውትወታ ተግባራትን ሲያከናውን የቆየ ሲሆን፣ ይህን ተከትሎ ስደተኞቹ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን ኛንጋቶም ወረዳ አይፓ ሳይት እንዲዘዋወሩ ተደርጓል።

**346.** በሶማሊ ክልል ከ360,000 በላይ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች በ8 የስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎች እና በ1 የስደተኞች ሳይት ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፤ ኢሰመኮ ቀብሪበያህ፣ ሼድር እና አውበሬ በተባሉ 3 የስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎች ከነሐሴ 12 እስከ 26 ቀን 2016 ዓ.ም. የሰብአዊ መብቶች ክትትል አከናውኗል፡፡ በዚህም የስደተኝነት ሁኔታ አወሳሰን ሳይከናወንላቸው በጥገኝነት ጠያቂነት በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ ያለ በቂ መሠረታዊ አገልግሎት ለረጅም ዓመታት የቆዩ በርካታ ሰዎች፣ የስደተኝነት ሁኔታ አወሳሰን እንዲከናወንላቸው የሚመለከታቸውን አካላት በማወያየት ለጉዳዩ እልባት እንዲሰጡ ውትወታ ሲያደርግ ቢቆይም ለውጥ አልመጣም፡፡ ምግብን ጨምሮ ለስደተኞች የሚቀርበው መሠረታዊ አገልግሎት እና ድጋፍ በከፍተኛ ሁኔታ መቀነሱ በስደተኞች የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ጫና ፈጥሯል፡፡ የስደተኞች መጠለያዎችን በሚመለከት በመጠለያዎቹ የሚገኙ ስደተኞች ከስደተኛ መቀበያ ጣቢያ ወደ መጠለያ ጣቢያዎቹ ሲገቡ የተሰጧቸው መሆኑን እና ከ10 ዓመት በላይ ምንም ዐይነት እድሳት ሳይደረግላቸው እንደቆዩ ለመረዳት ተችሏል፡፡ እነዚህ የስደተኛ መጠለያ ቤቶች ጥንካሬ የሌላቸው በመሆኑ በዝናባማ ወራት ጉዳት እንደሚደርስባቸው እና ስደተኞችን ለተለያዩ ችግሮች እንደሚያጋልጡ ኢሰመኮ ለመረዳት ችሏል፡፡ በመጠለያዎቹ ለሚገኙ አካል ጉዳተኛ ስደተኞች በቂ ትኩረት አለመሰጠቱ እና የሚያገኙት አገልግሎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱን አካል ጉዳተኛ ስደተኞች ለኢሰመኮ አስረድተዋል፡፡ ክትትል በተደረገባቸው ሁሉም የስደተኛ ጣቢያዎች የመዋዕለ ሕፃናት፣ የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንደሚገኙና ለስደተኞች የትምህርት አገልግሎት እንደሚሰጡ ነገር ግን ከትምህርት አሰጣጥ፣ ድጋፍ እና ተደራሽነት ጋር ተያይዞ የመማሪያ መጽሐፍት እጥረትን ጨምሮ የመማሪያ ግብዓት እጥረት መኖሩን፤ የላብራቶሪ እና የኮምፒዩተር መማሪያ ክፍሎች እንዲሁም ቤተ መጽሐፍት አለመኖሩን እና ለመምህራን የሚከፈለው ክፍያ ዝቅተኛ በመሆኑ ምክንያት ብቁ የሆኑ መምህራን እጥረት መኖሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡

**347.** በትግራይ ክልል ከ2,000 በላይ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች እንዳሉ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተ.መ.ድ.) የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር መረጃ ያመለክታል፡፡ በተለይም ከኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ ጥገኝነት ለመጠየቅ የሚመጡ ስደተኞች ቁጥር ከፍተኛ መሆኑን እና በትግራይ ክልል ምንም ዐይነት የጥገኝነት ጠያቂዎች ምዝገባ የማይከናወን ከመሆኑ በተጨማሪ ስደተኞች ጥበቃ እንደማይደረግላቸው፣ በርካቶችም ወደ አዲስ አበባ በማምራት ከተማ ውስጥ እንደሚገኙ ኢሰመኮ ከቀረቡለት አቤቱታዎች ጭምር ለመረዳት ችሏል፡፡ እነዚህ ምዝገባ ያልተደረገላቸውና በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች የዘፈቀደ እስርን ጨምሮ የደኅንነት ሥጋት ያለባቸው ከመሆኑ ባሻገር በኢ-መደበኛ ፍልሰት ወደ ጎረቤት ሀገራት እንደሚሄዱና ለሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እንደሚጋለጡ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## ፍልሰተኞች

**348.** በፍልሰተኞች መብቶች ዘርፍ በበጀት ዓመቱ ከታዩ ቁልፍ እመርታዎች መካከል፦ የኢትዮጵያ መንግሥት ከማላዊ መንግሥት ጋር በፍልሰት አስተዳደር እና በሰዎች የመነገድ እና በሕገ-ወጥ ድንበር የማሻገር ወንጀሎችን በጋራ በመከላከል ዙሪያ ተቀናጅቶ ለመሥራት የሚያስችል የሁለትዮሽ ስምምነት ሰነድ (Memorandum of Understanding) መዘጋጀቱ፤ የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት መዳረሻ ሀገራትን የማስፋት ጥረቶች መጀመራቸው በተለይም

ኢትዮጵያ የሁለትዮሽ ስምምነት (Bilateral Labour Agreement) ከተፈራረመቻቸው ነባር መዳረሻ ሀገራት ለምሳሌ ከተባበሩት አረብ ኤምሬቶች እና ካታር ጋር የነበረውን ስምምነት የማሻሻል ሥራዎች መጀመራቸው እንዲሁም እንደ ሊባኖስ፣ ኩዌት፣ ባህሬን ካሉ መዳረሻ ሀገራት እና በጀርመን እና ስዊዲን ሀገራት ከሚገኙ ቀጣሪ ድርጅቶች ጋር አዳዲስ የሁለትዮሽ ስምምነቶች መመሥረታቸው፤ እንዲሁም የተሻሻለ የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪትን የሚመለከት አዋጅ መቀረጹ ተጠቃሽ ሲሆኑ ደኅንነቱ የተጠበቀ፣ በሥርዓት የሚመራ እና መደበኛ የሆነ ፍልሰትን በማረጋገጥ ረገድ አዎንታዊ አስተዋጽዖ ሊያደርጉ የሚችሉ ናቸው።

349. በአፋር ክልል በተደረገው የፍልሰተኞች ሰብአዊ መብቶች አያያዝ ክትትል፣ በክልሉ ከዚህ ቀደም ለተጎጂ እና ተጋላጭ ፍልሰተኞች በዓለም አቀፍ የፍልሰተኞች ድርጅት (IOM) ይሰጥ የነበረው የጥበቃ (protection) አገልግሎት እና በክልሉ የነበረው የፍልሰተኞች ምላሽ መስጫ ጣቢያ (MRC) በመዘጋቱ ከፍልሰት ተመላሾች እና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተጎጂ ፍልሰተኞች ለተለያዩ ተደራራቢ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተጋላጭ ሆነዋል።

350. በሶማሊ ክልል በተደረገው የፍልሰተኞች ሰብአዊ መብቶች ክትትል ወቅት ለተጎጂዎች ጥበቃ እየሰጠ ያለው የዓለም አቀፍ የፍልሰተኞች ድርጅት (IOM) የፍልሰተኞች ምላሽ መስጫ ጣቢያ ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለመንግሥት ለማስረከብ መታቀዱን በክትትሉ ወቅት በተገኘ መረጃ የታወቀ ሲሆን፣ በመንግሥት አካላት በኩል ጣቢያውን ተረክቦ አገልግሎቱን ለማስቀጠል ምንም ዐይነት ዝግጅት እየተደረገ ባለመሆኑ የፍልሰተኞች ጥበቃ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊፈጥር የሚችል መሆኑ ተለይቷል።

351. የፍልሰተኞች መብቶች አያያዝን በተመለከተ ክትትል በተደረገባቸው አፋር እና ሶማሊ ክልሎች ላይ ምንም ዐይነት የተጎጂዎች ማቆያ ባለመኖሩ ተጎጂ ፍልሰተኞች ወደ መጡበት ስፍራ እስከሚመለሱ በፖሊስ ጣቢያዎች ላይ እንዲቆዩ ይደረጋል፣ ይህ ተግባር ደግሞ በሕግ የተከለከለ ነው። በተጨማሪም በሰዎች የመነገድ ወንጀል እና በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ድንበር የማሻገር ወንጀል ላይ ምስክር የሚሆኑ ፍልሰተኞች፣ በክሱ ሂደት ላይ ቆይተው ምስክርነታቸውን እንዲሰጡ የተዘጋጀ የፍልሰተኞች መቆያ ባለመኖሩ እና ምስክሮችን ማቆየት ባለመቻሉ የክስ መዝገቦች ማስረጃ በማጣት እንዲዘጉ ምክንያት ሆኗል።

352. ኢሰመኮ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት በመሥራት እየተከሰተ ያለውን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችሉ የውትወታና የምክረ-ሐሳቦች ማቅረቢያ መድረኮችን ያዘጋጀ ሲሆን፣ ጉዳዩ ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኝ የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት፣ የውትወታ ሥራዎችን ማከናወን እና ትስስሮችን ማጠናከሩን ይቀጥላል።

## ምክረ ሐሳቦች

### የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መብቶችን በተመለከተ

353. የካምፓላ ስምምነት ማስፈጸሚያ ብሔራዊ ረቂቅ አዋጅ በስምምነቱ ውስጥ ከተካተቱ የመንግሥት ግዴታዎች ጋር በተጣጣመ እና በቅድመ መፈናቀል፣ በመፈናቀል እንዲሁም በድኅረ-መፈናቀል ወቅት ለተፈናቃዮች ተገቢውን ጥበቃ እና ድጋፍ በአግባቡ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ በአጠቃላይ ከሰብአዊ መብቶች አንጻር የተቃኘ ይዘት እንዲኖረው በማድረግ በተፋጠነ ሁኔታ እንዲጸድቅና እንዲተገበር እንዲደረግ፤

354. በአዲስ አበባ ከተማ ለሚገኙ የከተማ ስደተኞች መንግሥት ተገቢውን ጥበቃ እና ድጋፍ የማድረግ እንዲሁም የስደተኞችን ከዘፈቀደ እስር የመጠበቅ እና ተገዶ ያለመመለስ መብቶች

እንዲከበሩ እንዲያደርግ፤ በተጨማሪም ምዝገባ ላልተደረገላቸው እና ዕውቅና ላላገኙ ስደተኞች መንግሥት ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በመተባበር ምላሽ እንዲሰጣቸው፤

355.መንግሥት ተገቢውን ክትትል በማድረግ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራዎችን እንዲሠራ እና ነዋሪዎችን ከሥጋት ነጻ የሆነ ቦታ ላይ እንዲያሰፍር እንዲሁም ለተፈናቃዮች ተገቢውን የሰብአዊ ድጋፍ እንዲያቀርብ፤

356.መንግሥት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች መርሖችን ታሳቢ ያደረገ እና በዕቅድ የተደገፈ የዘላቂ መፍትሔ መርኃ ግብር (ፕሮግራም) እንዲያመቻች፤ ተፈናቃዮች በዘላቂነት እስከሚቋቋሙ የሚመለከታቸውን መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን በማስተባበር ወቅቱን የጠበቀ፣ በቂ እና ተከታታይነት ያለው መሠረታዊ አገልግሎት እና ሰብአዊ ድጋፍ እንዲያቀርብ እንዲሁም መንግሥት ጉዳት የደረሰባቸውን መጠለያ ጣቢያዎች እንዲያድስ፤

357.ተፈናቃዮች ደኅንነታቸውን እና ክብራቸውን በጠበቀ መልኩ ወደ ቀያቸው የመመለስ፣ ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር ተዋሕዶ የመኖር፣ ወይም ወደ ሌላ ቦታ የመስፈር ያሉ አማራጮችን በነጻ ፈቃዳቸው መምረጥ እንዲችሉ ስላሏቸው አማራጮች መረጃ እንዲያገኙ እንዲደረግ፤

358.የማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የሚመለከተው የመንግሥት ተቋም ለተፈናቃዮች ተገቢውን ምዝገባ በማድረግ ለተፈናቃዮች ዕውቅና ሊሰጥ እና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ያካተተ በቂ ሰብአዊ ድጋፍ ሊያቀርብ እንዲሁም ደኅነታቸውን ሊጠብቅ ይገባል፤

359.ተፈናቃዮች በመፈናቀል ወቅት እና የዘላቂ መፍትሔ አግኝተው መደበኛ ኑሮዋቸውን እስኪጀምሩ ድረስ መሠረታዊ አገልግሎት እና የሰብአዊ ድጋፍ ማቅረብ የመንግሥት ግዴታ በመሆኑ አፈጻጸሙ የሰብአዊ መብቶች መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል። በተጨማሪም ተፈናቃዮች የሚገኙባቸው የከተማ፤ የዞን እና ክልል አስተዳደሮች የሰብአዊ መብቶችን መርሕ መሠረት ያደረገ የዘላቂ መፍትሔ አተገባበር ሂደቶችን ሊከተሉ ይገባል፤

360. የኦሮሚያ ክልል መንግሥት የሚመለከታቸውን መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን በማቀናጀት ከኦሮሚያ ክልል፣ ምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ ቦራ ወረዳ እና ዱግዳ ወረዳ ለተፈናቀሉ ሰዎች በቂ ምግብ፣ ውሃ፣ መጠለያ፣ የጤና፣ የንጽሕና፣ ትምህርት እና ሌሎች አስፈላጊ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ያካተተ አፋጣኝ ሰብአዊ ድጋፍ እንዲያቀርብ፤ ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔ ሳያገኙ በተራዘመ የመፈናቀል ሁኔታ ውስጥ መቆየታቸውን እና ሁኔታቸው አፋጣኝ እርምጃ የሚሻ መሆኑን በመገንዘብ የእርሻ መሬት ይዞታቸው እንዲመለስላቸው እና ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኙ እንዲደረግ፤

361.የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግሥት አካላት እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመተባበር በዳሰነች ወረዳ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን በቋሚነት እንዲያቋቁም፤ እንዲሁም በኦሞራቴ ከተማ እና በአካባቢው በሚገኙ የተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያዎች ላይ የተጋረጠውን የጎርፍ አደጋ አስቀድሞ ለመከላከል፣ በወረዳው መንግሥት እና በግብረሰናይ ድርጅቶች የተጀመሩ የመከላከል ሥራዎችን በመደገፍ ተጨማሪ መፈናቀል እንዳይከሰት አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ እንዲያደርግ፤

362.የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር እና የፌደራል መንግሥት ተመላሽ ተፈናቃዮች በዘላቂነት እስኪቋቋሙ ድረስ በቂ እና ወቅቱን የጠበቀ ሰብአዊ ድጋፍ የማቅረብ፣ የተመላሾችን ደኅንነት የመጠበቅ፣ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ተደራሽ የማድረግ ግዴታቸውን

እንዲወጡ፤ በተጨማሪም በክልሉ ለሚገኙ ተፈናቃዮች እየተመቻቸ ያለው ዘላቂ መፍትሔ የተሟላ እና የሰብአዊ መብቶች መርሖችን ያከበረ መሆኑን እንዲያረጋግጡ፤

## የስደተኞች መብቶችን በተመለከተ

363.በአዲስ አበባ ከተማ ለሚገኙ የከተማ ስደተኞች መንግሥት ተገቢውን ጥበቃ እና ድጋፍ የማድረግ እንዲሁም የስደተኞችን ከዘፈቀደ እስር የመጠበቅ እና ተገዶ ያለመመለስ መብቶች እንዲከበሩ እንዲያደርግ፤ በተጨማሪም ምዝገባ ላልተደረገላቸው እና ዕውቅና ላላገኙ ጥገኝነት ጠያቂዎች መንግሥት ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በመተባበር ምላሽ እንዲሰጣቸው፤

364. መንግሥት የስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የሰብአዊ መብቶች አያያዝ እንዲሻሻል ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር በመቀናጀት እንዲሠራ፤

## የፍልሰተኞች መብቶችን በተመለከተ

365.በአፋር ክልል በኩል ወደ ጂቡቲ በሚደረገው ኢ-መደበኛ ፍልሰት ላይ እንዲሁም ተጎጂ ፍልሰተኞች ጥበቃና ድጋፍ ማግኘት እንዲችሉ የፌዴራል እና የክልሉ መንግሥት እንዲሁም የዓለም አቀፍ ድርጅቶች በጋራ ትኩረት ሰጥተው እንዲሠሩ፤

366. መንግሥት በዓለም አቀፍ የፍልሰተኞች ድርጅት በኩል ለተጎጂ ወይም ተጋላጭ ፍልሰተኞች ይሰጥ የነበረው የጥበቃ (protection) አገልግሎት ሳይቋረጥ ለማስቀጠል የሚያስፈልጉ ዝግጅቶችን እንዲያደርግ፤

367.መንግሥት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተጎጂ እና ተጋላጭ ፍልሰተኞች እንዲሁም በወንጀል ክስ ጉዳይ ምስክር የሆኑ ፍልሰተኞች የሚቆዩባቸውን ቦታዎች (safe house) ኢ-መደበኛ ፍልሰት በሚበዛባቸው ዋና ዋና ስፍራዎች ላይ በጋራ በመሆን እንዲያዘጋጁ ኢሰመኮ ምክረ ሐሳቡን ያቀርባል።

# ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎች ከመወጣት አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ

ዝርዝር የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች

## ተ) ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎች ከመወጣት አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ

**368.** ሀገራት ሰብአዊ መብቶችን ለማስከበር ያላቸውን ቁርጠኝነት ከሚያሳዩበት መንገድ አንዱ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን መፈረምና ማጽደቅ ነው። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ በተለያየ ጊዜ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ፈርማ አጽድቃለች። ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች በአባል ሀገራት ላይ ግዴታዎችን ይጥላሉ፤ ከግዴታዎቹ መካከል የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ካጸደቁ በኋላ በስምምነቶቹ ውስጥ የሚገኙ መብቶችን በሀገራቸው ውስጥ ተፈጻሚነታቸውን የማረጋገጥ እንዲሁም ለስምምነቶቹ መፈጸም ያላቸውን ቁርጠኝነት ማሳየት ነው። አብዛኛዎቹ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች በአባል ሀገራት ላይ የአፈጻጸም ሪፖርት በስምምነቶቹ ለተቋቋሙ ኮሚቴዎች ወቅቱን በጠበቀ ሁኔታ የማቅረብ ግዴታዎችን ይጥላሉ።

### የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ከመፈረምና ከማጽደቅ አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ

**369.** በዚህ የሪፖርት ዓመት ኢትዮጵያ አዲስ የፈረመችውና ያጸደቀችው አህጉራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነት የለም። ይሁን እንጂ እስከ አሁን ኢትዮጵያ በርካታ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን የፈረመች ሲሆን እነዚህ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ በዝርዝር ተመላክተዋል።

## ሰንጠረዥ አንድ፡ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ከመፈረምና ከማጽደቅ አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ፡

| ተ.ቁ | ስምምነቶች | ሁኔታ | የተፈረመበት ወይም የጸደቀበት ቀን |
|---|---|---|---|
| | የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች[4] | | |
| 1. | የማሰቃየት እና ሌሎች የጭካኔ፣ ኢ-ሰብአዊ የሆነና ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ለማስቀረት የተደረገ ስምምነት (Convention Against Torture) | ጸድቋል | መጋቢት 5 ቀን 1986 |
| 2. | የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን (International Covenant on Civil and Political Rights) | ጸድቋል | ሰኔ 4 ቀን 1985 |
| 3. | በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውንም አድሏዊ ልዩነት ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት (Convention on Elimination of All Forms of Discrimination Against Women) | ጸድቋል | ጳጉሜ 5 ቀን 1973 |
| 4. | አድሏዊ የዘር ልዩነቶችን ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት (International Convention on the Elimination of Racial Discrimination) | ጸድቋል | ሰኔ 16 ቀን 1968 |
| 5. | የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ እና የባህል መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን (International Covenant on Economic, Social and Cultural Rights) | ጸድቋል | ሰኔ 4 ቀን 1985 |
| 6. | የሕፃናት መብቶች ስምምነት (Convention on the Rights of the Child) | ጸድቋል | ግንቦት 6 ቀን 1983 |
| 7. | ዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት (Convention on the Rights of Persons with Disabilities) | ጸድቋል | ሰኔ 30 ቀን 2002 |
| 8. | ሁሉንም ሰውዎች ከአስገዶ መሰወር ለመጠበቅ የተደረገ ስምምነት (Convention for the Protection of All Persons from Enforced Disappearance) | አልጸደቀም | - |

[4] https://tbinternet.ohchr.org/_layouts/15/TreatyBodyExternal/Treaty.aspx?CountryID=59&Lang=EN

| | | | |
|---|---|---|---|
| 9. | የስደተኛ ሠራተኞችን እና የቤተሰቦቻቸውን መብቶች ለመጠበቅ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት (International Convention on the Protection of the Rights of All Migrant Workers and Members of Their Families) | አልጸደቀም | - |
| **የተባበሩት መንግሥታት ስምምነቶች አማራጭ ፕሮቶኮሎች** | | | |
| 10. | የማሠቃየት ተግባርን ለማስቀረት የተደረገ ስምምነት አማራጭ ፕሮቶኮል (Optional Protocol to the Convention against Torture) | አልጸደቀም | - |
| 11. | የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን አማራጭ ፕሮቶኮል (Optional Protocol to the International Covenant on Civil and Political Rights (CCPR-OP1-IC)) | አልጸደቀም | - |
| 12. | የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን የሞት ቅጣትን ለማስቀረት ያለመ ሁለተኛ አማራጭ ፕሮቶኮል (Second Optional Protocol to the International Covenant on Civil and Political Rights aiming to the abolition of the death penalty) | አልጸደቀም | - |
| 13. | የሕፃናት መብቶች ስምምነት በግጭቶች ውስጥ የሕፃናት ተሳትፎ ላይ አማራጭ ፕሮቶኮል (Optional Protocol to the Convention on the Rights of the Child on the involvement of children in armed conflict) | ጸድቋል | ግንቦት 6 ቀን 2006 |
| 14. | የሕፃናት መብቶች ስምምነት በሕፃናት ሽያጭ፣ ሕፃናትን ለወሲብ ንግድ ማሰማራት እና የወሲብ ፊልም ማሰራትን ለማስወገድ የተደረገ አማራጭ ፕሮቶኮል (Optional Protocol to the Convention on the Rights of the Child on the sale of children, child prostitution and child pornography) | ጸድቋል | መጋቢት 16 ቀን 2006 |
| 15. | የሕፃናት መብቶች ስምምነት አማራጭ ፕሮቶኮል (Optional Protocol to the Convention on the Rights of the Child (CRC-OP-IC)) | አልጸደቀም | - |
| 16. | ዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኛ ሰዎች መብቶች ጥበቃ ስምምነት አማራጭ ፕሮቶኮል (Optional Protocol | አልጸደቀም | - |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | to the Convention on the Rights of Persons with Disabilities) | | |
| 17. | በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውንም አድሏዊ ልዩነት ላይ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት አማራጭ ፕሮቶኮል (Optional Protocol to the Convention on the Elimination of All forms of Discrimination against Women) | አልጸደቀም | - |
| 18. | የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ እና የባህል መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን አማራጭ ፕሮቶኮል (Optional Protocol to the International Covenant on Economic, Social and Cultural Rights) | አልጸደቀም | - |
| | **የአፍሪካ ኅብረት የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች**[5] | | |
| 19. | የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር (African Charter on Human and Peoples' Rights) | ጸድቋል | ሰኔ 8 ቀን 1990 |
| 20. | የአፍሪካ የሕፃናት መብቶች እና ደኅንነት ቻርተር (African Charter on the Rights and Welfare of the Child) | ጸድቋል | መስከረም 22 ቀን 1994 |
| 21. | የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል (Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Women in Africa (Maputo Protocol) | ጸድቋል | ሐምሌ11 ቀን 2010 |
| 22. | የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ፍርድ ቤት ማቋቋሚያ ፕሮቶኮል (Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Establishment of an African Court on Human and Peoples' Rights) | ተፈርሟል ግን አልጸደቀም | ሰኔ 2 ቀን 1990 |
| 23. | የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የአፍሪካ ስደተኞችን ችግሮች ለመቅረፍ የተደረገው ስምምነት (OAU Convention Governing the Specific Aspects of Refugee Problems in Africa) | ጸድቋል | ጥቅምት 5 ቀን 1966 |

[5] https://au.int/en/treaties

| | | | |
|---|---|---|---|
| 24. | የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የአረጋውያን መብቶች ፕሮቶኮል (Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Older Persons in Africa) | ጸድቋል | መጋቢት 4 ቀን 2012 |
| 25. | በአፍሪካ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጥበቃ እና ድጋፍን አስመልክቶ የተደረገው የአፍሪካ ኅብረት ስምምነት (ካምፓላ ስምምነት) (African Union Convention for the Protection and Assistance of Internally Displaced Persons in Africa (Kampala Convention) | ጸድቋል | መጋቢት 4 ቀን 2012 |
| 26. | የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የአካል ጉዳተኞች መብቶች ፕሮቶኮል (Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Persons with Disabilities in Africa) | አልጸደቀም | - |
| 27. | የአፍሪካውያን ዴሞክራሲ፣ ምርጫ እና አስተዳደር ቻርተር (African Charter on Democracy, Elections, and Governance) | ጸድቋል | ታኅሣሥ 28 ቀን 2001 |
| 28. | የአፍሪካ ወጣቶች ቻርተር (African Youth Charter) | ጸድቋል | ሚያዝያ 16 ቀን 2006 |
| 29. | ሙስናን ለመከላከል እና ለመዋጋት የተደረገ የአፍሪካ ኅብረት ስምምነት (African Union Convention on Preventing and Combating Corruption) | ጸድቋል | ጥቅምት 5 ቀን 2000 |
| 30. | ሽብርን ለመከላከል እና ለመዋጋት የተደረገ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ስምምነት (OAU Convention on the Prevention and Combating of Terrorism) | ጸድቋል | የካቲት 26 ቀን 1995 |
| 31. | የአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የዜግነት መብት እና በአፍሪካ ሀገር አልባነትን ማጥፋት ፕሮቶኮል (Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Specific Aspect of the Right to a Nationality and the Eradication of Statelessness in Africa) | አልጸደቀም | - |
| 32. | የአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች መብቶች የዜጎች ማኅበራዊ ጥበቃ እና ማኅበራዊ ደኅንነት ቻርተር ፕሮቶኮል (Protocol to the African Charter on | አልጸደቀም | - |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | Human and Peoples' Rights on the Rights of Citizens to Social Protection and Social Security) | | |
| 33. | በሴቶችና ልጅ አገረዶች ላይ የሚፈጸምን ጥቃት ለማስቅረት የተደረገ የአፍሪካ ሕብረት ስምምነት (The African Union Convention on Ending Violence Against Women and Girls) | አልጸደቀም | - |

## የሰብአዊ መብቶችን ሪፖርት ከማቅረብ አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ

370. ሀገራት ዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶችን ከፈረሙና ካጸደቁ በኋላ ከሚጠበቅባቸው ግዴታዎች አንዱ የስምምነቶቹን አፈጻጸም አስመልክቶ ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት የስምምነቶቹን አፈጻጸም ለመከታተልና ለመቆጣጠር በስምምነቶቹ ለተቋቋሙ ኮሚቴዎች እና ተቋማት በተቀመጠላቸው የጊዜ ወሰን ውስጥ ሪፖርቶችን መላክ እና ማቅረብ ነው። በዚህ የሪፖርት ዓመት ኢትዮጵያ አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶችን ስምምነቶችን በተመለከተ ለአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን (የአፍሪካ ኮሚሽን) (African Commission on Human and Peoples' Rights) የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር ((የአፍሪካ ቻርተር) (African Charter on Human and Peoples' Rights)) እንዲሁም የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል (ማፑቶ ፕሮቶኮል) (Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Women in Africa (Maputo Protocol)) አፈጻጸምን አስመልክቶ በጥቅምት ወር 2017 ዓ.ም. በተካሄደው የአፍሪካ ኮሚሽን 81ኛ መደበኛ ጉባኤ ወቅት ማቅረብ የነበረባትን ሪፖርት ሳታቀርብ አልፋለች። ይህን ተከትሎ በግንቦት ወር 2017 ዓ.ም. በተካሄደው የኮሚሽኑ 83ኛ መደበኛ ጉባኤ ላይ የስምምነቶቹን አፈጻጸም በተመለከተና በማፑቶ ፕሮቶኮል ላይ የመጀመሪያ ሪፖርት (initial report) ለኮሚሽኑ አቅርባለች። የአፍሪካ ኮሚሽን አሠራር በሚፈቅደው መሠረት ኢሰመኮ እንደ አንድ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ማሟያ ሪፖርት አቅርቧል።

371. ባለፉት ዓመታት ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሀገሪቱ ያለውን የሰብአዊ መብቶች አያያዝና ሁኔታዎችን አስመልክቶ ሪፖርቶችን ለተለያዩ የሰብአዊ መብት ኮሚቴዎች አቅርባለች። በዚህ የሪፖርት ዓመት ሪፖርቶችን ከማቅረብ አንጻር በዋነኝነት የሚጠቀሰው ከኅዳር 3 እስከ 6 ቀን 2017 ዓ.ም. በጄኔቫ ስዊዘርላንድ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት በተካሄደው የኢትዮጵያ 4ተኛ ዙር ሁሉን አቀፍ ወቅታዊ ግምገማ መድረክ ሲሆን፤ በዚህ መድረክ ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም በምክር ቤቱ በግንቦት 6 ቀን 2011 ዓ.ም. በሁሉን አቀፍ ወቅታዊ ግምገማ 3ተኛ ዙር በተገመገመችበት ወቅት የተቀበለቻቸው ምክረ ሐሳቦች ያሉበትን የአፈጻጸም ደረጃ አስመልክቶ ሀገራዊ ሪፖርት አቅርባለች። በሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት የሁሉን አቀፍ ወቅታዊ ግምገማ አሠራር በሚፈቅደው መሠረት ኢሰመኮ እንደ አንድ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም እና በርካታ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በጋራ እና በተናጠል ማሟያ ሪፖርቶቻቸውን አቅርበዋል። ይህንንም ተከትሎ በመድረኩ የተሳተፉ 114 የተ.መ.ድ. አባል ሀገራት በኢትዮጵያ ያለውን የሰብአዊ መብቶች

አያያዝ በተመለከት ባለፉት አምስት ዓመታት የታዩትን እመርታዎች እና አሳሳቢ ጉዳዮች በማንሳት በአጠቃላይ 316 ምክረ ሐሳቦችን ሰጥተዋል፡፡ ከተሰጡት ምክረ ሐሳቦች መካከልም 252 የሚሆኑት ተቀባይነት ሲያገኙ (supported) 12 ምክረሐሳቦች በከፊል ተቀባይነት ያገኙ (supported/ noted) ሲሆኑ 52 ምክረ ሐሳቦች ደግሞ ከግምት ውስጥ የገቡ (noted) ናቸው[6]፡፡

**372.** ባለፉት ጊዜያት ኢትዮጵያ በርካታ የአፈጻጸም ሪፖርቶችን ለተለያዩ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴዎች አቅርባለች፡፡ በኢትዮጵያ ከቀረቡ የመጨረሻዎቹ ሪፖርቶች መካከል የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር እና የማፑቶ ፕሮቶኮል አፈጻጸምን አስመልክቶ ለአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን የተላከው ሪፖርት፣ ለተ.መ.ድ የአካል ጉዳተኛ ሰዎች መብቶች ኮሚቴ የአካል ጉዳተኛ ሰዎች መብቶች ስምምነት (Convention on the Rights of Persons with Disabilities) አፈጻጸምን አስመልክቶ በ2015 ዓ.ም. የቀረበው ሪፖርት፣ ለተ.መ.ድ. የሕፃናት መብቶች ኮሚቴ (Committee on the Rights of the Child) የሕፃናት መብቶች ስምምነት (Convention on the Rights of the Child) አፈጻጸምን አስመልክቶ በየካቲት 18 ቀን 2013 ዓ.ም. የተላከው ሪፖርት፣ ለተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃልኪዳን አፈጻጸምን አስመልክቶ በጥቅምት 11 ቀን 2012 ዓ.ም. የተላከው ሪፖርትና ኢትዮጵያ ለተ.መ.ድ. ሰዎችን ከመሰቃየት ለመከላከል ለተቋቋመው ኮሚቴ (Committee Against Torture) በጥር ወር 2012 ዓ.ም. የተላኩ ሪፖርቶች ናቸው፡፡

**373.** ለተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴ (UN Human Rights Committee) የተላከውን ሪፖርት አስመልክቶ ኮሚቴው በሪፖርቱ ላይ ገንቢ የሆነ ውይይት (constructive dialogue) ከመስከረም 30 እስከ ጥቅምት 25 ቀን 2015 ዓ.ም. በተካሄደው የኮሚቴው ጉባኤ ላይ ካደረገ በኋላ በጥቅምት 21 ቀን 2015 ዓ.ም. ምክረ ሐሳቦችን የያዘ የመደምደሚያ ምልከታዎችን (concluding observations) ሰጥቷል፡፡ ሰዎችን ከመሰቃየት ለመከላከል ለተቋቋመው ኮሚቴ (Committee Against Torture) በቀረበው ሪፖርት ዙሪያ ኮሚቴው ገንቢ የሆነ ውይይት (constructive dialogue) በማድረግ በግንቦት 2 ቀን 2015 ዓ.ም. ምክረ ሐሳቦችን የያዘ የመደምደሚያ ምልከታዎችን (concluding observations) ሰጥቷል፡፡ ለሕፃናት መብቶች ኮሚቴ (Committee on the Rights of the Child) በተላከው ሪፖርት ዙሪያ ኮሚቴው ከነሐሴ 26 እስከ መስከረም 9 ቀን 2018 ዓ.ም. በሚያካሂደው 100ኛ ጉባኤ ላይ ኢትዮጵያ እንደምትገመገም ይጠበቃል፣ ለተ.መ.ድ የአካል ጉዳተኛ ሰዎች መብቶች ኮሚቴ የተላከው ሪፖርት የቅርብ ጊዜ ሪፖርት እንደ መሆኑ ወደፊት ኮሚቴው በሚወስነው ጊዜ እንደሚታይ ይጠበቃል፡፡ እስከ አሁን ኢትዮጵያ ለአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት ያቀረበቻቸው ሪፖርቶች ዝርዝር በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ተመልክቷል፡፡

[6] https://www.ohchr.org/sites/default/files/documents/hrbodies/upr/sessions/session47/eth/upr47-ethiopia-thematic-list-of-recommendatio.docx

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

## ሰንጠረዥ ሁለት፡ የሰብአዊ መብቶችን ሪፖርት ከማቅረብ አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ

| ተ.ቁ | ስምምነቶች | ሁኔታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| | **የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች** | | |
| 1. | የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን (International Covenant on Civil and Political Rights) | ኢትዮጵያ ሁለተኛውን ወቅታዊ ሪፖርት በ2007 ዓ.ም. ለኮሚቴው መላክ የነበረባት ቢሆንም ጥምር የ2ኛው እና 3ኛው ወቅታዊ ሪፖርት በ ጥቅምት 11 ቀን 2012 ዓ.ም. ተልኳል፡፡ ኮሚቴው በሪፖርቱ ላይ ገንቢ የሆነ ውይይት (constructive dialogue) ከመስከረም 30 እስከ ጥቅምት 25 ቀን 2015 ዓ.ም. በተካሄደው 136ኛ የኮሚቴው ጉባኤ ላይ ካደረገ በኋላ በጥቅምት 21 ቀን 2015 ዓ.ም. ምክረ ሐሳቦችን የያዘ የመደምደሚያ ምልከታዎችን (concluding observations) ሰጥቷል፡፡ [7] | ጊዜው ደርሶ ያልተላከ ሪፖርት የለም፡፡ |
| 2. | በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውም አድሏዊ ልዩነት ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት (Convention on the Elimination of All forms of Discrimination | ኢትዮጵያ በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውም አድሏዊ ልዩነትን ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት አፈጻጸምን አስመልክቶ 8ኛው ወቅታዊ ሪፖርትን ኅዳር 12 ቀን 2010 ዓ.ም. የላከች ሲሆን ሪፖርቱ መላክ የነበረበት በ2008 ዓ.ም. ነበር፡፡ ኮሚቴው በሪፖርቱ ላይ በመጋቢት 5 ቀን 2011 ዓ.ም. የመደምደሚያ ምልከታዎችን (concluding observations) ሰጥቷል፡፡[8] ኮሚቴው | ጊዜው ደርሶ ያልቀረበ አንድ ሪፖርት አለ፡፡[9] |

[7] ይህንን የመደምደሚያ ምልከታ የሚከተለውን ማስፈንጠሪያ በመጠቀም ማግኘት ይቻላል https://tbinternet.ohchr.org/_layouts/15/treatybodyexternal/SessionDetails1.aspx?SessionID=2575&Lang=en

[8] ይህንን የመደምደሚያ ምልከታ የሚከተለውን ማስፈንጠሪያ በመጠቀም ማግኘት ይቻላል https://tbinternet.ohchr.org/_layouts/15/treatybodyexternal/Download.aspx?symbolno=CEDAW/C/ETH/CO/8&Lang=En

[9] ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ይህንን ስምምነት አስመልክቶ ቀለል ያለ የሪፖርት ማቅረቢያ ሂደትን (simplified reporting procedure) ስለተቀበለች እና በዚህም ሂደት መሠረት ሀገራት ሪፖርት የሚያቀርቡት ኮሚቴው ሪፖርት ከመቅረቡ በፊት የጥያቄዎችን መዘርዝር (list of issues prior reporting/LOPR) ከላከ በኋላ ስለሆነ፣ ኮሚቴውም እስከዚህ የሪፖርት ዓመት ድረስ ለኢትዮጵያ ከላይ የተጠቀሰውን የጥያቄ መዘርዝር ስላልላከ ሪፖርቱ መቅረብ የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| | against Women) (CEDAW) | ኢትዮጵያ 9ኛውን ወቅታዊ ሪፖርት በመጋቢት 2015 ዓ.ም. እንድታቀርብ የጠየቀ ሲሆን ሪፖርቱ እስካሁን ባለው ጊዜ ውስጥ አልቀረበም፡፡ | |
| 3. | የሕፃናት መብቶች ስምምነት (Convention on the Rights of the Child (CRC)) | ኢትዮጵያ 4ኛውን እና 5ኛውን ጥምር ወቅታዊ ሪፖርት ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም. አቅርባለች፡፡ ኮሚቴው የመደምደሚያ ምልከታዎችን (concluding observations) ግንቦት 28 ቀን 2007 ዓ.ም. ሰጥቷል፡፡[10] ኢትዮጵያ 6ኛውንና 7ኛውን ጥምር ወቅታዊ ሪፖርቶች ሰኔ 5 ቀን 2012 ዓ.ም. እንድታቀርብ ጠይቋል፡፡ ኢትዮጵያም ይህን ሪፖርት የካቲት 18 ቀን 2013 ዓ.ም. አቅርባለች፣ በቀረበው ሪፖርት ላይ ኮሚቴው የጥያቄዎች መዘርዝር (list of issues) በጥቅምት 8 ቀን 2017 ዓ.ም. ያቀረበ ሲሆን በቀረቡት የጥያቄዎች መዘርዝር ላይ ኢትዮጵያ በነዚህ ጥያቄዎች ላይ በ6ኛው እና 7ኛው ጥምር ሪፖርት ላይ ከተጠቀሱት ውጪ ተጨማሪ እና ለውጦችን ያካተተ ሪፖርት የካቲት 8 ቀን 2017 ዓ.ም. እንድታቀርብ ጠይቋል፡፡ የሕፃናት መብቶች ኮሚቴ አሠራር በሚፈቅደው መሠረት ኢሰመኮ በሕፃናት መብቶች አፈጻጸም ላይ ማሚያ ሪፖርት አቅርቧል፡፡ | ሪፖርቱ የሚላክበት ጊዜ ሰኔ 5 ቀን 2012 ዓ.ም. ነበር ነገር ግን ሪፖርቱ የተላከው በየካቲት 18 ቀን 2013 ዓ.ም. ነው፡፡ |
| 4. | የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ እና የባህል መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን (International Covenant on | ኢትዮጵያ የመጀመሪያ፣ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ጥምር ወቅታዊ ሪፖርቶችን ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. ልካለች፡፡ ኮሚቴው የመደምደሚያ ምልከታዎችን (concluding observations) ግንቦት | ሪፖርቱ የሚቀርብበት ጊዜ ግንቦት 10 ቀን 2009 ዓ.ም. ነበር፡፡ |

[10] ይህንን የመደምደሚያ ምልከታ የሚከተለውን ማስፈንጠሪያ በመጠቀም ማግኘት ይቻላል https://digitallibrary.un.org/record/814391?ln=en&v=pdf

| | | | |
|---|---|---|---|
| | Economic, Social and Cultural Rights (ICESCR)) | 10 ቀን 2004 ዓ.ም. ሰጥቷል::[11] ኮሚቴው ሀገሪቱ 4ኛውን ወቅታዊ ሪፖርት ግንቦት 10 ቀን 2009 ዓ.ም. እንድታቀርብ የጠየቀ እና ሪፖርቱም በተቀመጠለት ጊዜ ያልተላከ ቢሆንም ሪፖርቱን ለማዘጋጀት አስፈላጊ ዝግጅቶች ተካሂደው ረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በ2017 በጀት ዓመት ከባለድርሻ አካላት ጋር የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረክ ተካሂዷል:: | ነገር ግን በተባለው ጊዜ አልተላከም::[12] |
| 5. | ሰዎችን ከመሠቃየት ለመከላከል የተቋቋመው ኮሚቴ (Committee against torture) | ኢትዮጵያ 2ኛው እና 3ኛው ጥምር ወቅታዊ ሪፖርቶችን ጥር ወር 2012 ዓ.ም. የላከች ቢሆንም መላክ የነበረበት ኅዳር ወር 2007 ዓ.ም. ነበር:: ኮሚቴው በሪፖርቱ ላይ ገንቢ የሆነ ውይይት (constructive dialogue) በማድረግ በግንቦት 2 ቀን 2015 ዓ.ም. የመደምደሚያ ምልከታዎችን (concluding observations) ሰጥቷል::[13] ኮሚቴው ኢትዮጵያ ቀጣዩን ወቅታዊ ሪፖርት በግንቦት 4 ቀን 2019 ዓ.ም. እንድትልክ ጠይቋል:: | ጊዜው ደርሶ ያልተላከ ሪፖርት የለም:: |
| 6. | አድሏዊ የዘር ልዩነቶች ለማስቀረት የተቋቋመ ኮሚቴ (Committee on the Elimination of Racial Discrimination (CERD)) | ኢትዮጵያ ከ7ኛው እስከ 16ኛው ያሉትን ጥምር ወቅታዊ ሪፖርቶች ከ1980/81 ዓ.ም. እስከ 2001/02 ዓ.ም. የሚሸፍን አንድ ሪፖርት በመስከረም 21 ቀን 2001 ዓ.ም. ለኮሚቴው ልካለች:: እነዚህ ሪፖርቶች መላክ የነበረባቸው ጊዜ 1981/82 ዓ.ም.፤ 1983/84 ዓ.ም.፤ 1985/86 ዓ.ም.፤ 1987/88 ዓ.ም.፤ 1989/90 ዓ.ም.፤ 1991/92 ዓ.ም.፤ | ሪፖርቱ የሚቀርብበት ጊዜ ሐምሌ 16 ቀን 2005 ዓ.ም. ነበር:: ነገር ግን በተባለው ጊዜ አልተላከም:: |

[11] ይህንን የመደምደሚያ ምልከታ የሚከተለውን ማስፈንጠሪያ በማስፈንጠር ማግኘት ይቻላል https://tbinternet.ohchr.org/_layouts/15/treatybodyexternal/Download.aspx?symbolno=E/C.12/ETH/CO/1-3&Lang=En

[12] ይህ ሪፖርት በተባለው ጊዜ ያልተላከ ቢሆንም ሪፖርቱን ለማቅረብ በሚመለከተው አካል ሥራዎች በመጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ።

[13] ይህንን የመደምደሚያ ምልከታ የሚከተለውን ማስፈንጠሪያ በማስፈንጠር ማግኘት ይቻላል https://tbinternet.ohchr.org/_layouts/15/treatybodyexternal/SessionDetails1.aspx?SessionID=2627&Lang=en

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | 1993/94 ዓ.ም.፤ 1995/96 ዓ.ም.፤ 1997/98 ዓ.ም. እና 1999/2000 ዓ.ም. ነበር። ኮሚቴው የመደምደሚያ ምልከታዎችን (concluding observations) ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. ሰጥቷል።[14] ኢትዮጵያ ከ17ኛው እስከ 19ኛው ያሉትን ወቅታዊ ሪፖርቶች ሐምሌ 16 ቀን 2005 ዓ.ም. በአንድ ሰነድ እንድትልክ ጠይቋል። | |
| 7. | ዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት (Convention on the Rights of Persons with Disabilities (CRPD)) | ኢትዮጵያ በዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት ላይ የመጀመሪያ ሪፖርት ታኅሣሥ 30 ቀን 2005 ዓ.ም. ያቀረበች ሲሆን ሪፖርቱ መቅረብ የነበረበት ጊዜ 2004 ዓ.ም. ነበር። ኮሚቴው የመደምደሚያ ምልከታዎችን (concluding observations) ነሐሴ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ሰጥቷል። ኮሚቴው ሀገሪቱ 2ኛውን እና 3ኛውን ጥምር ሪፖርቶች በነሐሴ 1 ቀን 2012 ዓ.ም. እንድታቀርብ ጠይቋል። ይህንንም ሪፖርት ኢትዮጵያ በጥር 11 ቀን 2015 ዓ.ም. አቅርባለች። | ሪፖርቱ እንዲቀርብ የተጠየቀው ነሐሴ 1 ቀን 2012 ዓ.ም. ነበር የቀረበው ጥር 11 ቀን 2015 ዓ.ም. ነው። |
| **የአፍሪካ ኅብረት የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች** | | | |
| 8. | የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር (African Charter on Human and Peoples' Rights) | ኢትዮጵያ 7ኛውን ወቅታዊ ሪፖርት በ2009 ዓ.ም. መላክ የነበረባት ቢሆንም ከ7ኛው እስከ 10ኛው (ከ2007 እስከ 2015) ዓ.ም. ያሉትን የሚያጠቃልል ጥምር ወቅታዊ ሪፖርት በ ጥር ወር 2016 ዓ.ም. ተልኳል። በግንቦት ወር 2017 ዓ.ም. ለአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን 83ተኛ መደበኛ ጉባኤ ላይ የልዑካን ቡድን በመላክ የተላከውን ሪፖርት አቅርባለች። | ሪፖርቱ መቅረብ የነበረበት በ2009 ዓ.ም. ቢሆንም የቀረበው በጥር ወር 2016 ዓ.ም. ነው። |

[14] ይህንን የመደምደሚያ ምልከታ የሚከተለውን ማስፈንጠሪያ በማስፈንጠር ማግኘት ይቻላል https://www.refworld.org/policy/polrec/cerd/2009/en/69552

| | | | |
|---|---|---|---|
| 9. | የአፍሪካ የሕፃናት መብቶች እና ደኅንነት ኮሚቴ (African Charter on the Rights and Welfare of the Child) | ኢትዮጵያ 4ኛውን እና 5ኛውን ከ 2006/07 ዓ.ም. እስከ 2011/12 ዓ.ም. ያሉትን የሚያጠቃልል ወቅታዊ ሪፖርት በሐምሌ ወር 2012 ዓ.ም. አቅርባለች። የአፍሪካ የሕፃናት መብቶች እና ደኅንነት ኮሚቴ የሪፖርቱን መደምደሚያ ምልከታዎች (concluding observations) በየካቲት ወር 2014 ዓ.ም. ሰጥቷል።[15] ኮሚቴውም ኢትዮጵያ ቀጣዩን ወቅታዊ ሪፖርት በየካቲት ወር 2017 ዓ.ም. እንድታቀርብ ጠይቋል። | ሪፖርቱ የሚቀርብበት ጊዜ በየካቲት 2017 ዓ.ም. ነበር። ነገር ግን በተባለው ጊዜ አልቀረበም። |
| 10. | የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል (ማፑቶ ፕሮቶኮል) (Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Women in Africa (Maputo Protocol)) | ኢትዮጵያ የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል (ማፑቶ ፕሮቶኮል) ላይ የመጀመሪያ ሪፖርት በጥር 2016 ዓ.ም. ልካለች። ይህም ሪፖርት ኢትዮጵያ የሰዎችንና ሕዝቦችን መብቶች ቻርተር አስመልክቶ በጥር 2016 ዓ.ም. ያቀረበችው ሪፖርት ክፍል "ለ" (part b of the Report on the African Charter on Human and Peoples Rights) ሆኖ የተላከ ነው። ኢትዮጵያ በ 83ኛው የኮሚሽኑ ጉባኤ ላይ የፕሮቶኮሉን አፈጻጸም አስመልክቶ መነሻ ወቅታዊ የአፈጻጸም ሪፖረት በግንቦት 2017 ዓ.ም. አቅርባል። | ጊዜው ደርሶ ያልቀረበ/ያልተላከ ሪፖርት የለም። |

## በሪፖርት ዘመኑ የታዩ ቁልፍ እመርታዎች

374. በመስከረም ወር መጨረሻ 2017 ዓ.ም. በተደረገው 79ኛው የተ.መ.ድ. ሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባዔ ወቅት ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. ከ2025 እስከ 2027 ያለውን ጊዜ ከ47 የምክር ቤቱ አባላት አንዷ ሆና እንድታገለግል መመረጧ፤

375. ግንቦት 10 ቀን 2009 ዓ.ም. መቅረብ የነበረበትን 4ኛውን የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ እና የባህል መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን (International Covenant on Economic, Social and

[15] ይህንን የመደምደሚያ ምልከታ የሚከተለውን ማስፈንጠሪያ በመጠቀም ማግኘት ይቻላል https://www.acerwc.africa/en/member-state/ratifications/66/ethiopia

Cultural Rights /ICESCR) ወቅታዊ ሪፖርት ለመላክ አስፈላጊ የዝግጅት ሥራዎች መጀመራቸው፤

376.በ4ኛው ሁሉን አቀፍ ወቅታዊ ግምገማ ወቅት ለኢትዮጵያ የተሰጡ ምክረ ሐሳቦችን ተግባራዊነት ለማስተባበር እና ለመከታተል ያለመ እና ኢሰመኮ እና ሲቪል ማኅበራት ድርጅቶችን ያሳተፈ የትግበራ ፍኖተ ካርታ ዝግጅት መጀመሩ፤

377.በረቂቅ ደረጃ ያለውን ሦስተኛውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች የድርጊት መርኃ-ግብር (2017-2022ዓ.ም.) የኢኮኖሚያዊ፤ ማኅበራዊ እና የባህል መብቶችን ባካተተ መልኩ የመከለስ እና ሰነዱን የማጎልበት ሥራዎች እየተካሄዱ መሆናቸው፤

378.የአፍሪካ ሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር እንዲሁም የማፑቶ ፕሮቶኮል አፈጻጸምን አስመልክቶ በ83ኛው የኮሚሽኑ ጉባዔ ላይ ወቅታዊ ሪፖርት መቅረቡ ይጠቀሳሉ።

## በሪፖርት ዘመኑ የታዩ መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮች

379.የሚቀርቡ ሪፖርቶች ወቅቱን ጠብቀው አለመላካቸው/አለመቅረባቸው፦ ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ እንደተመለከተው ኢትዮጵያ በጥቅምት 11 ቀን 2012 ዓ.ም. ለተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴ የላከችው ሪፖርት መላክ የነበረበት ሐምሌ 29 ቀን 2006 ዓ.ም. ነበር። በኅዳር 12 ቀን 2010 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ለተ.መ.ድ. ሴቶች ላይ የሚደርሰውን መድሎ ለማስወገድ ለተቋቋመው ኮሚቴ የላከችው 8ኛው ሪፖርት መቅረብ የነበረበት በሐምሌ ወር 2007 ዓ.ም. ነበር። በተመሳሳይ ሁኔታ በጥር ወር 2012 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ለተ.መ.ድ. ሰዎችን ከመሠቃየት ለመከላከል ለተቋቋመው ኮሚቴ (Committee Against Torture) የላከችው ሪፖርት የተላከው መላክ ከነበረበት ስድስት ዓመት ዘግይቶ ነው። እንዲሁም በነሐሴ 1 ቀን 2012 ዓ.ም. ለተ.መ.ድ የአካል ጉዳተኛ ሰዎች መብቶች ኮሚቴ መላክ የነበረበት ሪፖርት የቀረበው ከሁለት ዓመት በላይ ዘግይቶ ነው። በተጨማሪም በዚህ የሪፖርት ዓመት ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ኮሚሽን (ACHPR) ለአፍሪካ ቻርተር (African Charter on Human and Peoples' Rights)) እንዲሁም ማፑቶ ፕሮቶኮል (Maputo Protocol) አፈጻጸምን አስመልክቶ በጥቅምት ወር 2017 ዓ.ም. በተካሄደው የአፍሪካ ኮሚሽን 81ኛ መደበኛ ጉባኤ ወቅት ማቅረብ የነበረባትን ሪፖርት መቅረብ ከነበረበት ጊዜ በ 8 ወር ዘግይቶ በግንቦት ወር 2017 ዓ.ም. ነው የቀረበው። ይህ የሚያሳየው ኢትዮጵያ ለአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት የአፈጻጸም ሪፖርቶችን በጊዜው መላክ/ማቅረብ ላይ ክፍተት እንዳለ ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ ኢትዮጵያ ሪፖርት በማቅረብ/በመላክ የምታገኘውን ጠቃሚ ግብዓት የሚያሳጣና በጊዜ ሂደት የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል። ይህ ሁኔታ በተለይ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት አባል በመሆኗ ይሻሻላል ተብሎ ይጠበቃል።

380. በጊዜው ያልቀረቡ ሪፖርቶች መኖራቸው፦ ከላይ ካለው ሰንጠረዥ መገንዘብ እንደሚቻለው ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና ባህላዊ መብቶች ቃል ኪዳን (International Covenant on Economic, Social and Cultural Rights) አፈጻጸምን አስመልክቶ እና ዘርን መሠረት ያደረገ መድሎን ለማጥፋት የተደረገውን ስምምነት (Convention on the Elimination of Racial Discrimination (ICERD))[16] አፈጻጸም አስመልክቶ መላክ

[16] ICERD 60ኛ ዓመቱ እ.ኤ.አ. በ2025 ሲከበርም፤ ስምምነቱ አድሎአዊ የዘር ልዩነትን ለመከላከል፣ እኩልነትን ለማስፈን እንዲሁም በሰላም አብሮ ለመኖር ወሳኝ ነው። ኢትዮጵያ ስምምነቱን እ.ኤ.አ. ሰኔ 23 ቀን 1976 ያለተዐቅቦ በማጽደቅ ዘርን፣ ቀለምን፣ ትውልድን ወይም ብሔርን

የነበረባት ሪፖርቶች ሳይላኩ ጊዜያቸው አልፏል:: የእነዚህ ሪፖርቶች አለመቅረብና ዘርን መሠረት ያደረገ መድሎን ለማጥፋት የተደረገውን ስምምነት በተመለከተ ሪፖርቱን ለማቅረብ ግልጽ የሆነ ዕቅድ አለመኖሩ፣

381.ለሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም ሪፖርት በቂ ትኩረት አለመስጠት፦ የሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም ሪፖርት በባህሪው በአንድ ተቋም የሚዘጋጅ ሳይሆን የተለያዩ ተቋማትን ተሳትፎ የሚፈልግ ነው:: በተለይም ለሪፖርቱ ግብአት የሚሆኑ መረጃዎች የሚሰበሰቡት ከአስፈጻሚ አካላት ስለሆነ የእነዚህ አካላት የተቀናጀ ተሳትፎ ወሳኝ ነው:: ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ከዚህ አንጻር ብዙ ክፍተቶች ያሉ ሲሆን እነዚህም ክፍተቶች በአፈጻጸም ሪፖርት ዝግጅት ላይ ችግር እየፈጠሩ ይገኛሉ:: ግብዓት ለመሰብሰብ በሪፖርት አዘጋጅ ተቋም ለሚላኩ ጥያቄዎች አስፈጻሚ አካላት በቂ ጊዜ ሰጥቶ ምላሽ ከመላክ አንጻር እና ግብአቶችን በሚፈለገው ጥራትና ደረጃ አዘጋጅቶ ከመላክ አንጻር ያሉ ችግሮች የሪፖርት ዝግጅትን በማስተጓጎል ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት እንዳይቀርብ እንቅፋት ሆነዋል::

### ተግዳሮቶች

የሰብአዊ መብቶች ስምምነት አፈጻጸም ሪፖርቶችን ከማቅረብ አንጻር ዘርፈ ብዙ ችግሮች ያሉ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው:-

382.**የተቀናጀ መረጃ እጥረት፦** የሰብአዊ መብቶችን አፈጻጸም ሪፖርት ለማዘጋጀት የተቀናጀ መረጃ አስፈላጊ ነው:: የተቀናጀ መረጃ ከሌለ አንድ መብት የተፈጸመበትን ደረጃ ለመለካት፣ ለማወቅም ሆነ ለማስረዳት አስቸጋሪ ይሆናል:: የተቀናጀ መረጃ እንዲኖር ለማስቻል የፍትሕ ሚኒስቴር ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ምክረ ሐሳቦች መከታተያ የመረጃ ቋት ማደራጀቱ ከላይ የተጠቀሰውን ተግዳሮት ከማስወገድ አንጻር ትልቅ ሚና ቢኖረውም ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት መረጃዎችን በሚፈለገው ጥራትና ጊዜ ወደ ቋቱ በማስገባት ረገድ በቂ ትኩረት አለመሰጠቱ የመረጃ ቋቱን ውጤታማነት አዳጋች አድርጎታል::

383.**የአቅም ውስንነት፦** የአፈጻጸም ሪፖርት ዝግጅት ትልቅ የፋይናንስ አቅም የሚጠይቅ ነው:: ለሪፖርቱ ግብዓት ለመሰብሰብ፣ ሪፖርቱን ለማርቀቅ፣ በሪፖርቱ ዙሪያ የውይይት መድረኮችን ለማዘጋጀት እና ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን ለማከናወን በጀት ያስፈልጋል:: በኢትዮጵያ ይህንን በጀት በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ማግኘት አስቸጋሪ ነው:: ይህም የሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም ሪፖርቶችን ከማቅረብ አንጻር እንደ አንድ ተግዳሮት የሚቀመጥ ነው::

384. **ከሪፖርት ዝግጅት ባለሙያዎች ጋር የሚያያዝ ውስንነት፦** የአፈጻጸም ሪፖርት ዝግጅት በባሕርይው በዓለም አቀፍ ሪፖርት ዝግጅት ዙሪያ ልምድ እና እውቀት ያላቸውን ባለሙያዎች የሚፈልግ ነው:: የአፈጻጸም ሪፖርት አቅራቢ ተቋማት ከዚህ አንጻር ውስንነት እንዳለባቸው ኮሚሽኑ ተገንዝቧል::

### ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ውስጥ ያሉትን መብቶች በሕጎች ውስጥ ከማካተት (Domestication) አንጻር ያለችበት ሁኔታ:-

385.ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ውስጥ ያሉትን መብቶች በሀገር አቀፍ ሕጎች ውስጥ ከማካተት (domestication) አንጻር በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት ላይ

ወይም የዘር ሐረግን መሠረት ያደረገ አድልዎን ለማስወገድ ቃል ገብታለች። በተጨማሪም የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ 25 የስምምነቱን አድሎአዊ ልዩነት ያለማድረግ መርሕን የሚያንጸባርቅ ነው።

እነዚህ ስምምነቶች የሀገሪቷ የሕግ አካል እንደሚሆኑ በግልጽ ማስቀመጡ፣ በተጨማሪም በ2013 ዓ.ም. የወጣው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸውና ካጸደቀቻቸው የዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሚመነጩ ጉዳዮችን የማየት ሥልጣን እንዳላቸው በግልጽ መደንገጉ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች በፍርድ ቤቶች ሥራ ላይ እንዲውሉ ያስችላል። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸውን የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን እንደ ኢትዮጵያ ሕግ ቆጥሮ ከመፈጸም አንጻር ያሉትን ክፍተቶች፣ እንዲሁም ከእነዚህ ስምምነቶች ተደራሽነት አንጻር ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ ሰፊ ሥራዎች ወደፊት መሠራት ይኖርበታል።

### መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮች

386. ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ውስጥ ያሉትን መብቶች በሕጎች ውስጥ ከማካተት አንጻር ያለው ዋናውና አሳሳቢው ጉዳይ እነዚህን ስምምነቶች በሥራ ላይ ማዋል መተግበር/መተርጎም ላይ ክፍተት መኖሩ ነው። ለዚህ ማሳያው ፍርድ ቤቶች እና ሌሎች ውሳኔ ሰጪ አካላት በአንዳንድ አጋጣሚዎች የስምምነቶቹን አንቀጾች ከመጥቀስ በዘለለ እነዚህን ስምምነቶች በሚገባ ተርጉመው የሰዎችን መብቶች የሚያስከብሩበት አጋጣሚ የተወሰነ መሆኑ ነው።

387. ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች እንደ ኢትዮጵያ የሕግ አካል ያለመቀበል ችግር፦ ምንም እንኳን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች የኢትዮጵያ ሕግ አካል እንደሆኑ እንደሚቆጠሩ በግልጽ ቢደነግግም፣ ይህንን ሕገ መንግሥታዊ እውነታ ተቀብሎ መተግበር ላይ ክፍተት ይታያል። ይህም ክፍተት በዋናነት የሚገናኘው በነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1987 አንቀጽ 2(2 እና 4) ሥር ሁሉም የኢትዮጵያ ሕጎች በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች በነጋሪት ጋዜጣ ላይ መታተም አለባቸው ብሎ ስለሚደነግግ እና ከእነዚህ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ማጽደቂያ አዋጅ በቀር የስምምነቶቹ ሙሉ ይዘት በአማርኛም ሆነ በእንግሊዘኛ ቋንቋ በነጋሪት ጋዜጣ ላይ አለመታተማቸው ነው። ነገር ግን ይህ ሁኔታ ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች የኢትዮጵያ የሕግ አካል ከመሆን ሊያግዳቸው አይችልም። ምክንያቱም እነዚህ ስምምንነቶች የኢትዮጵያ ሕግ አካል እንደሚሆኑ የደነገገው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት በደረጃ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ስለሚበልጥ እና የሕገ መንግሥት ድንጋጌ በአዋጅ ድንጋጌ ሊሻር ስለማይችል ነው።

388. የሕግ ማሻሻያና ማርቀቅን በሚመለከት፡ በሀገሪቱ የሚወጡና የሚሻሻሉ ብሔራዊ ሕጎችና አተገባበራቸው ከሕገ መንግሥቱ ጋር መጣጣም እንዳለባቸው (አንቀጽ 9(1)) እና ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ የሕግ አካል እንደሆኑ በአንቀጽ 9(4) ላይ ተመላክቷል። ከዚህ በተጨማሪም በአንቀጽ 13(2) ላይ በሕገ- መንግሥቱ ውስጥ የተካተቱ የመብት ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ሕግጋት፣ ስምምነቶችና መርሖች ጋር በተጣጣመ መንገድ እንደሚተረጎሙ ተደንግጓል። እነዚህ የሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች ቢኖሩም፣ በሚያዝያ 2017 ዓ.ም. የመገናኛ ብዙኃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 ማሻሻያ ተደርጎበታል፣ በተካሄደው ማሻሻያ ላይ ኢሰመኮና የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ያሏቸውን ምክረ ሐሳቦች የገለጹ ቢሆንም ረቂቅ አዋጁ መሠረታዊ ለውጥ ሳይደረግበት ጸድቋል። ይህ ሪፖርት እስከወጣበት ጊዜ ድረስ፣ ኢሰመኮ የአዋጁን የመጨረሻ

ቅጂ ማግኘት እና ምልከታ ማድረግ አልተቻለም፡፡ ይህም በዘላቂነት ሊፈታ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

389. ለሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች አፈጻጸም በቂ የሆነ ትኩረት አለመስጠት፦ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ሲያጸድቅ በማጽደቂያ አዋጅ ውስጥ የስምምነቱን አፈጻጸም የትኛው ተቋም መከታተል እንዳለበት በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ በስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ውስጥ የስምምነቱን አፈጻጸም እንዲከታተሉ ኃላፊነት የሚሰጣቸው ተቋማት ብዙ ጊዜ በቂ ትኩረት ሰጥተው ክትትል በማድረግ ስምምነቱ እንዲፈጸም ሲሠሩ አይታይም፡፡ ይህም የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሯል፡፡ የሰብአዊ መብቶች ስምምነት አፈጻጸምን የሚከታተል አካል አለመኖር፣ ሦስተኛውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች የድርጊት መርኃ-ግብር (2017-2022) ጸድቆ ወደ ሥራ አለመግባቱ፣ በማጽደቂያ አዋጆች የስምምነቶቹን አፈጻጸም እንዲከታተሉ ኃላፊነት የተሰጣቸውን ተቋማት ሥራ የሚከታተለውና የሚቆጣጠረው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው ስምምነቶች አፈጻጸምን አስመልክቶ ጠንካራ የሆነ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ስለሌለው ተቋማቱ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዳይወጡ የራሱን ሚና ተጫውቷል፡፡

390. የተደራሽነት ችግር፦ ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምንነቶች በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ላይ አለመታተም የኢትዮጵያ ሕግ አካል ከመሆን ባያግዳቸውም የስምምነቶቹ ተደራሽነት ላይ ትልቅ እክል ፈጥሯል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በኢትዮጵያ ሲጸድቁ በነጋሪት ጋዜጣ ላይ የሚታተመው የማጽደቂያ አዋጁ ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የስምምነቶቹ ይዘት በሚገባ እንዳይታወቁ አድርጓል፡፡ እነዚህ ስምምነቶች በአማርኛ ወይም በሌላ የሀገር ውስጥ ቋንቋ ስለማይተረጎሙ እና እንደሌሎች ሕጎች በሕትመት ስለማይገኙ ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተደራሽ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ ይህም እነዚህ ስምምነቶች እንደ ኢትዮጵያ ሕጎች ተቆጥረውና ታውቀው በሚፈለገው መጠን በፍርድ ቤቶች ክርክር ቀርቦባቸውና የውሳኔ መሠረት ሆነው እንዳያገለግሉ አድርጓል፡፡

### ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ከመፈጸም አንጻር ያለችበት ሁኔታ

391. አንድ ሀገር የሰብአዊ መብቶችን ስምምነት ስትቀበልና ስታጸድቅ ስምምነቱን ለመፈጸም አስፈላጊ የሕግ (legislative)፣ የፍርድ (judicial)፣ የፖሊሲና ሌሎች እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታ ይኖርባታል፡፡ በተጨማሪም አባል ሀገራት በእነዚህ ስምምነቶች ውስጥ የተካተቱ መብቶችን አፈጻጸም ለመከታተልና ለመቆጣጠር የተቋቋሙ የሰብአዊ መብቶች ተቋማትን ምክረ ሐሳቦች የመቀበልና የመፈጸም ግዴታ አለባቸው፡፡ ሌላው የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎችን ከመቆጣጠርና ከመከታተል አንጻር የሚነሳው በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሁሉን-አቀፍ የግምገማ መድረክ (Universal Periodic Review) ሲሆን ይህም የተቋቋመው በመጋቢት ወር 1998 ዓ.ም. በተ.መ.ድ. የጠቅላላ ጉባኤ ነው፡፡ የተ.መ.ድ. ሁሉን-አቀፍ የግምገማ መድረክ አሳታፊና ፍላጎት/ትብብር ላይ ተመሥርቶ የተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት የሁሉንም የተ.መ.ድ. አባል ሀገራት የሰብአዊ መብቶች አተገባበር ሁኔታ ገምግሞ የሰብአዊ መብቶች አያያዝን ለማሻሻል ምክረ ሐሳብ የሚሰጥበት መድረክ ነው፡፡ እስከ አሁን ሁሉን-አቀፍ የግምገማ መድረክ በአራት ዙር የተከናወነ ሲሆን ኢትዮጵያ በአራቱም ዙሮች ተገምግማለች፡፡

392.ከላይ በተቀመጠው ሰንጠረዥ እንደ ተመለከተው ኢትዮጵያ ሰባቱን የተ.መ.ድ. ዋና ዋና የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ጨምሮ በርካታ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን አጽድቃለች። ኢትዮጵያ ከሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች የሚመነጩ ግዴታዎችን በዋናነት የምትፈጽመው በብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ድርጊት መርኃ ግብር አማካኝነት ሲሆን ይህንን የድርጊት መርኃ ግብር የፍትሕ ሚኒስቴር ከሌሎች አስፈጻሚ ተቋማት ጋር በመተባበር ያዘጋጀዋል። ኢትዮጵያ በባለፉት ዓመታት ሁለት የሰብአዊ መብቶች ድርጊት መርኃ ግብሮችን አውጥታ የተገበረች ሲሆን በ2013 ዓ.ም. ጸድቆ ሥራ ላይ መዋል የነበረበት 3ኛው የድርጊት መርኃ ግብር ይህ ሪፖርት እስከ ሚዘጋጅበት ጊዜ ድረስ በረቂቅ ደረጃ ላይ ይገኛል።

### ቁልፍ እመርታዎች

393.በረቂቅ ደረጃ ያለው ሦስተኛውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች የድርጊት መርኃ-ግብር (2017-2022) ከዚህ ቀደም እንደ ክፍተት ሲነሳ የነበረውን የኢኮኖሚ፤ የማኅበራዊ እና የባህል መብቶችን አለመካተት ለመቅረፍ ሰነዱን የመከለስ ሥራዎች እየተካሄዱ መሆናቸው መርኃ ግብሩ ቢጸድቅ ከኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና የባሕል መብቶች አንጻር የተሰጡ ምክረ ሐሳቦች አፈጻጸምን ለመከታተልና ለመቆጣጠር አስቻይ ሁኔታዎች እንዲኖሩ ለማድረግ ጥሩ እድል ይሰጣል። ይህም አካሄድ የሰብአዊ መብቶች አይነጣጠሉም፣ አንዳቸው በሌላቸው ላይ የተደገፉና የተያያዙ ናቸው የሚለውን የዓለም አቀፍ መርሕ ባከበረ መልኩ ሰነዱን ለመቅረጽ ይረዳል።

### መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮች

394. የሁለተኛው ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ድርጊት መርኃ ግብር በ2012 ዓ.ም. ከተጠናቀቀ በኋላ 3ኛው ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ድርጊት መርኃ ግብር በተገቢው ጊዜ ጸድቆ ሥራ ላይ ባለመዋሉ የሰብአዊ መብቶች አፈጻጸምን ከመከታተልና መቆጣጠር አንጻር አስቸጋሪ ሁኔታን ፈጥሯል።

### መደምደሚያ

395.አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ከመፈረምና ከማጽደቅ አንጻር በዚህ የሪፖርት ዓመት ኢትዮጵያ ፈርማ ያጸደቀችው የለም። ይሁን እንጂ አሁንም ኢትዮጵያ ያላጸደቀቻቸው በርካታ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ያሉ ሲሆን እነዚህ ስምምነቶች ቢጸድቁ በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶችን ከማረጋገጥ አንጻር ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል። በሌላ በኩል ምንም እንኳን በዚህ ዓመት እና ባለፉት ጊዜያት ኢትዮጵያ በርካታ የአፈጻጸም ሪፖርቶችን ለተለያዩ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴዎች አቅርባ የነበረ ቢሆንም እነዚህን ሪፖርቶች በተገቢው ጊዜ ከማቅረብ አንጻር ክፍተቶች ነበሩ። በርካታ የመቅረቢያ ጊዜያቸው የደረሰ ሪፖርቶች መኖራቸው አሳሳቢ ቢሆንም በዚህ ዓመት ኢትዮጵያ በ4ተኛው ዙር ሁሉን አቀፍ ግምገማና በአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች መብቶች ቻርተርና የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል (ማፑቶ ፕሮቶኮል) ላይ ሁለት የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ማቅረብ ችላለች።

396. ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ውስጥ ያሉትን መብቶች በሀገር አቀፍ ሕጎች ውስጥ ከማካተት (domestication) አንጻር የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት እነዚህ

ስምምነቶች የሀገሪቷ ሕግ አካል እንደሚሆኑ በግልጽ ማስቀመጡ፣ በተጨማሪም በ2013 ዓ.ም. የወጣው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸውና ካጸደቀቻቸው የዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሚመነጩ ጉዳዮችን የማየት ሥልጣን እንዳላቸው በግልጽ መደንገጉ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች በፍርድ ቤቶች ሥራ ላይ እንዲውሉ ያስችላል። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸውን የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን እንደ ኢትዮጵያ ሕግ ቆጥሮ ከመፈጸም አንጻር ያሉትን ክፍተቶች፣ እንዲሁም ከእነዚህ ስምምነቶች ተደራሽነት አንጻር ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ ሰፊ ሥራዎች ወደፊት መሠራት ይኖርበታል።

## ምክረ ሐሳቦች

397.አስፈጻሚ ተቋማት ለሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም ሪፖርት ተገቢውንና በቂ የሆነ ትኩረት እንዲሰጡ፣

398. ለሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም ሪፖርት ሥራ በቂ የፋይናንስና የሰው ኃይል መመደብ፣

399.መንግሥት የሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም ሪፖርቶችን በሚያዘጋጁ ተቋማት እነዚህን ሪፖርቶች የማዘጋጀት ሥራን በሚጠበቀው ጊዜ፣ ደረጃና ጥራት፣ እንዲሁም በጉዳዩ ላይ በቂ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ያካተተ ቋሚ ኮሚቴ እንዲያቋቁም፣

400. የሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈባቸውን የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብት ስልቶች/ተቋማት እንዲያቀርብ፣

401. ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን እንደ ኢትዮጵያ ሕግ አካል ከመቁጠር አንጻር ያለውን የግንዛቤ ችግር ለመቅረፍ ኢሰመኮና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን እንዲሠሩ፣

402. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸውን የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች እንደሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች በነጋሪት ጋዜጣ ላይ እንዲታተም በማድረግ ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፣

403. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሰብአዊ መብቶች ስምምነት ማጽደቂያ አዋጆች የስምምነቶቹን አፈጻጸም እንዲከታተሉ ኃላፊነት የተሰጣቸውን ተቋማት ሥራ ጠንካራ የሆነ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት በማበጀት እንዲከታተል፣

404. የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ሌሎች አስፈጻሚ ተቋማት የሰብአዊ መብቶች ምክረ ሐሳቦችን በሥራ ዕቅዳቸው ውስጥ በግልጽ በማካተት እንዲተገብሩና የሥራቸው ውጤታማነትም እነዚህን ምክረ ሐሳቦች ከመፈጸም አንጻር እንዲለካ፣

405. ሁሉም አስፈጻሚ ተቋማት በፍትሕ ሚኒስቴር ሥር የተደራጀው ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ምክረ ሐሳብ መከታተያ የመረጃ ቋት የሚፈለግበትን አገልግሎት እንዲሰጥ በወቅቱ እና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ መረጃ የማስገባቱን ሥራ እንዲያከናውኑ ቢደረግ፣

406. የሕግ አውጪ አካላት በሀገሪቱ የሚሻሻሉ እና አዲስ የሚወጡ ሕጎች ኢትዮጵያ ካጸደቀቻቸው አህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥና በሰብአዊ መብቶች ላይ ተጽዕኖ ያላቸው ረቂቅ ሕጎች ከመጽደቃቸው በፊት ኢሰመኮ ምልከታ እንዲያከናውንባቸው ክፍት ማድረግ፣

407. የሲቪል ማኅበራት የሰብአዊ መብቶች አፈጻጸምን በተለያየ መንገድ እንዲደግፉ ማበረታታት፣ ለምሳሌም ለኢትዮጵያ በተሰጡ ምክረ ሐሳቦች ዙሪያ የማንቃት (awareness

raising) ሥራዎችን በመሥራት፣ የተሰጡ ምክረ ሐሳቦች እንዲፈጸሙ ጉትጎታ በማድረግ እና ለአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት (human rights mechanisms) ሪፖርት በማቅረብና መረጃ በመስጠት እንዲሁም ሌሎች መሰል ተግባራትን በማከናወን መሳተፍ፣ የሚመለከታቸው አካላት በእነዚህ ሪፖርቶች ዝግጅትም ሆነ በሌሎች ሂደቶች ሲቪክ ማኅበራቱን ትርጉም ባለው መልኩ ማሳተፍ፣ መንግሥት ለአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ስልቶች (Human rights mechanisms) የሚቀርቡ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅና የሰብአዊ መብቶች ምክረ ሐሳቦች አፈጻጸምን አስመልክቶ ግምገማ ሲያደርግ የሲቪል ማኅበራትን ትርጉም ባለው መልኩ እንዲያሳትፍ ኢሰመኮ ያሳስባል፡፡

WWW.EHRC.ORG



# ክፍል ፬

# ክፍል አራት

# የሀገራዊ ምክክር እና የሽግግር ፍትሕ ሂደት

## የሀገራዊ ምክክር ሂደት

### አጠቃላይ ምልከታ

408. ብሔራዊ ፋይዳ ባላቸው ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የተፈጠሩ ችግሮች እና አለመግባባቶችን ለመፍታት በብዙ ዘርፎች ላይ የሚገኙ የተለያዩ ሀገራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ ባለድርሻ አካላት በጋራ ሀገራዊ ምክክር ያካሂዳሉ። ሀገራዊ ምክክሮች በሀገራት ባለቤትነት፤ በጥልቅ የፖለቲካ ቀውስ፣ በድኅረ ጦርነት ሁኔታዎች ወይም በዘላቂ ፖለቲካዊ ሽግግሮች ወቅት በሀገራቱ በርካታ ባለድርሻዎች መካከል የጋራ መግባባትን ለመፍጠር ያለሙ ናቸው። ግጭቶችን በመፍታት ለአንድ ሀገር የሰላም ግንባታ፣ ማኅበራዊ ግንኙነቶችን ለማደስ፣ ለኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መሻሻሎች እና እድገቶች አስተዋጽዖ ያደርጋል።

409. ዓለም አቀፍ ሕጎች ስለ ሀገራዊ ምክክር ምንነት በግልጽ ባያስቀምጡም ከሰብአዊ መብቶች፣ ከዲሞክራሲ እና ከሰላም ግንባታ ጋር የተያያዙ መርሖዎች ሀገራዊ ምክክር ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ። አካታችነት፣ ግልጽነት፣ አሳታፊነት፣ ምክክሩን ለሚመራው አካል ግልጽ የሆነ ሥልጣን መስጠት፣ ምክክሩን የሚያስተባብረው አካል ተዓማኒነት (ቅቡልነት)፣ ዋና ዋና የግጭት መንስኤዎችን ለይቶ በጉዳዮቹ ላይ ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲመካከሩበት ማድረግ እና ምክክሩ ያመላከታቸው ምክረ ሐሳቦች የሚፈጸሙበት አግባብ ላይ አስቀድሞ መግባባት ሀገራዊ ምክክር የተሳካ እንዲሆን የሚያደርጉ ቁልፍ መርሖዎች ናቸው።

410. የግጭት እና አለመግባባቶችን መንስኤ ለመለየት ይረዳ ዘንድ ሀገራዊ ምክክር ሴቶችን፣ ወጣቶችን፣ መገለል እየደረሰባቸው ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ የአንድ አካባቢ ቀደምት ነዋሪዎችን፣ ኅዳጣንን፣ የማኅበረሰብ መሪዎችን፣ የሃይማኖት መሪዎችን፣ ፖለቲከኞችን፣ ምሁራንን፣ የመንግሥት አካላትን፣ መንግሥትን የሚቃወሙ ታጣቂ ወይም ታጣቂ ያልሆኑ አካላትን፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን እና ንግድ ላይ የተሰማሩ አካላትን ጨምሮ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ማለትም ግጭቱ ወይም አለመግባባቱ የሚመለከታቸውን አካላት ያካተተ መሆን አለበት። ባለድርሻ አካላትን ያለአድልዎ በእኩልነት ማሳተፍ አንዱ አካል ስለሌላው ፍላጎት፣ ሥጋት እና ብሶት እንዲረዳ ያደርጋል። የሀገራዊ ምክክር ተሳታፊዎችን ለመምረጥ ከሚተገበሩ መስፈርቶች አንዱ አካታችነት መሆን ያለበት ሲሆን ሁሉም ባለድርሻ አካላት በውይይት ሂደቶች እና ውሳኔ በሚሰጥበት ምዕራፍ ላይ እንዲሁም የውሳኔዎቹ አፈጻጸም ላይ መካተት አለባቸው።

411. ሀገራዊ ምክክር አሳታፊ መሆን አለበት ሲባል ምክክሩን ተሳታፊዎች በሚረዱት ቀላል ቋንቋ ማካሄድን እና መስማት የተሳናቸውን ጨምሮ ምክክሩ እየተካሄደበት ያለውን ቋንቋ የማይረዱ ተሳታፊዎች ካሉ የትርጉም አገልግሎት በመስጠት ተሳታፊዎች ስለሂደቱ በቂ መረጃ እንዲኖራቸው እና ሐሳባቸውን በመግለጽ በእኩልነት እንዲሳተፉ ዕድል መስጠትን እንዲሁም ባለድርሻ አካላት በምክክር ሂደቱ ላይ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲያደርጉ በሚጠቅም ሁኔታ የሚሰጡትን ሐሳብ አስቀድመው እንዲያዘጋጁ ጊዜ መስጠትን ያካትታል።

በተጨማሪም ሕዝብ ከተመካከረ በኋላ የተስማማበትን ውሳኔ ማስፈጸም ይቻል ዘንድ ምክክር በሚካሄድበት ጉዳይ ላይ መንግሥት ምንም ዐይነት የማይገረሰስ ውሳኔ አስቀድሞ ማስተላለፍ የለበትም::

**412.** ሀገራዊ ምክክር መድልዎ እየደረሰባቸው ያሉ አካላትን ወይም ቡድኖችን እና ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑትን ለምሳሌ ሴቶችን፣ ኅዳጣንን፣ ቀደምት ነዋሪዎችን እና አካል ጉዳተኞችን በሂደቶቹ ላይ በዘላቂነት ማሳተፍ አለበት:: ለዚህም ከሚጠቅሙ ዘዴዎች መካከል ተሳታፊዎቹ በእያንዳንዱ የምክክር ምዕራፍ እንዲሳተፉ ለማድረግ ኮታ መስጠት እና ለአካል ጉዳተኛ ተሳታፊዎች ምቹ ከባቢያዊ ሁኔታን መፍጠር ይጠቀሳሉ::

**413.** ሀገራዊ ምክክርን የሚያስተባብረው አካል ስለሀገራዊ ምክክሩ ሂደቶች፣ መረጃ ስለሚሰበሰብባቸው፣ ስለሚተነተንባቸው ዘዴዎች እና ከሕዝብ የተሰበሰበው መረጃ መጨረሻ ላይ ለተወሰኑ ውሳኔዎች በምን መልክ ግብዓት እንደሆነ እንዲሁም በውሳኔዎች ላይ ያልተካተቱ ከሕዝብ የተገኙ መረጃዎች ካሉ ውሳኔዎች ላይ ስላልተካተቱበት ምክንያት የሕዝብ መገናኛ ብዙኃንን ጭምር በመጠቀም በግልጽ ለሕዝብ ማሳወቅ አለበት:: በተጨማሪም የምክክር ሂደቱ ማብቂያ ላይ የተደረሰባቸው ውሳኔዎች አፈጻጸምን በመከታተል የሚገኙ መረጃዎችን ለሕዝብ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው::

**414.** ሀገራዊ ምክክር ሕዳጣንን እና ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑትን ጨምሮ የተለያዩ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላትን እና የማኅበረሰብ ክፍሎችን በእኩልነት የሚያሳትፍ ሂደት በመሆኑ በሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ የመሳተፍ መብት፣ የእኩልነት እና ከአድልዎ ነጻ የመሆን መብት፣ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ እና መረጃ የማግኘት መብትን ጨምሮ የተለያዩ የሰብአዊ መብቶች እና መሰረታዊ ነጻነቶች የሚተገበሩበት ሂደት በመሆኑ ለሰብአዊ መብቶች ባህል መጎልበት አስተዋጽዖ ያደርጋል:: እንዲሁም ለግጭቶችና ቅራኔዎች መነሻ የሆኑ ጉዳዮች ላይ በውይይት ላይ የተመሠረተ መፍትሔ በመስጠት ለሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች መቀነስ አስተዋጽዖ ያደርጋል::

**415.** በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ የፖለቲካ እና የሐሳብ መሪዎች እንዲሁም የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ያሉትን ልዩነቶችና አለመግባባቶች በሕዝባዊ ውይይቶች፣ በጥናት እና ሌሎች መንገዶችን ተጠቅሞ በመለየት ምክክር እንዲደረግባቸው ለማመቻቸት በሕግ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሀገራዊ ምክክሩን እየመራና እያስተባበረ ይገኛል:: የምክክር ኮሚሽኑ ከግንቦት 2016 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሚያዝያ 2017 ዓ.ም. ባለው ጊዜ በ10 ክልሎች እና 2 ከተማ አስተዳደሮች ሕዝባዊ ውይይት በማድረግ አጀንዳ ያሰባሰበ ሲሆን ኢሰመኮም አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደቶቹ ላይ በመገኘት የሰብአዊ መብቶች ክትትል አከናውኖ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዋና ዋና አዎንታዊ ሁኔታዎች እና አሳሳቢ ጉዳዮችን ለይቶ ምክረ ሐሳብ ሰጥቷል::

### አዎንታዊ ጉዳዮች

**416.** ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ማለትም ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አረጋውያን፣ አርሶ አደሮች፣ የመንግሥት ሠራተኞች፣ የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች፣ ነጋዴዎች፣ መምህራን፣ የማኅበረሰብ መሪዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ የዕድሮች ተወካዮች፣ የመንግሥት ተቋማት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት እና ማኅበራት፣ ተጽዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች እና የተለያዩ ፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች አጀንዳ በማሰባሰብ ሂደቱ ላይ

መሳተፋቸው አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደቱ በሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ የመሳተፍ መብት የተተገበረበት ለመሆኑ ማሳያ መሆኑ፤

**417.** የቡድን ሰብሳቢዎች በውይይቶች ጊዜ ያለምንም አድሏዊ ልዩነት ለሁሉም ተሳታፊዎች አጀንዳ የሚሰጡበትን እኩል ዕድል መስጠታቸው፣ እና

**418.** ምንም እንኳን በቁጥር ደረጃ የሴቶች አጠቃላይ ተሳትፎ 50 በመቶ የማይሆን ቢሆንም የምክክር ኮሚሽኑ ለቡድኖች ውይይት ጸሐፊ እና ሰብሳቢ ሲመረጥ ሴቶችን መምረጥ ግዴታ በማድረግ፣ ሴቶች ለብቻ ተወያይተው የሴቶችን አጀንዳ እንዲያቀርቡ በማድረግ እና ለዋናው ምክክር የሚወከሉ ሰዎች ሲመረጡ ከየቡድኑ 30 በመቶ የግድ ሴቶች እንዲመረጡ ኮታ በመስጠት የሴቶችን ተሳትፎ የሚያበረታታ ሥራ መሥራቱ።

### አሳሳቢ ጉዳዮች

**419.** በአብዛኞቹ ክልሎች ተሳታፊዎች የግጭቶች እና አለመግባባቶችን ምክንያቶች እንዲሁም መፍትሔዎቻቸው ምን ምን እንደሆኑ በነጻነት ሲያብራሩ እና ሐሳባቸውን ሲገልጹ የነበረ ቢሆንም የተሳታፊዎችን ፈቃድ ሳይጠይቁ ሚዲያ የሚል ባጅ ያደረጉም ሆኑ ያላደረጉ ግለሰቦች አልፎ አልፎ ወደ ውይይቶች ቦታ እየመጡ አጀንዳ በተሰባሰበባቸው ሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ቪድዮ ሲቀርጹ እና ፎቶ ሲያነሱ የነበረ መሆኑ ታውቋል። በዚህም ምክንያት አንዳንድ የአማራ ክልል አጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት ተሳታፊዎች ክልሉ ውስጥ ያሉ ታጣቂ ኃይሎች ምክክሩ ላይ መሳተፋቸውን በመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት ካዩ ሊያጠቋቸው እንደሚችሉ ከመስጋታቸው የተነሳ ቀረጻዎቹ ሲካሄዱ ፊታቸውን ሲሸፍኑ እና ሐሳባቸውን ከመግለጽ ሲቆጠቡ የተስተዋሉ በመሆኑ ድርጊቱ የተሳታፊዎችን ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ላይ ተጽዕኖ አድርጓል፤ የተሳታፊዎች ምስሎች በምክክር ኮሚሽኑ ድረ ገጽ እና በአንዳንድ መገናኛ ብዙኃን መለጠፉ የተሳታፊዎችን ደኅንነት ስጋት ላይ ጥሏል።

**420.** አንዳንድ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች የምክክር ኮሚሽኑ ገለልተኝነት ላይ ጥያቄ ያላቸው በመሆኑ ራሳቸውን ከምክክር ሂደቱ ማግለላቸው እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል እና አማራ ክልል ውስጥ የትጥቅ ትግል ላይ ያሉ አካላትን እና በታጣቂዎቹ ቁጥጥር ስር ካሉ ወረዳዎች ሰዎችን የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደቱ ላይ ማሳተፍ አለመቻሉ ከአካታችነት አንጻር የታዩ ወስንነቶች ናቸው። ክልላዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች በዋናው ምክክር ላይ የማይሳተፉ መሆኑ አጀንዳዎቻቸው ትኩረት ላያገኝ የሚችልበትን ሥጋት መፍጠሩን ኢሰመኮ ተረድቷል።

**421.** በተጨማሪም አካል ጉዳተኛ ተሳታፊዎች ላሉባቸው ቡድኖች ምቹ የውይይት ቦታዎች አስቀድመው ባለመዘጋጀታቸው ምክንያት አካል ጉዳተኞች ደረጃዎችን ጭምር እየወጡ በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደቶች መሳተፋቸው፤ የአንዳንድ ክልሎች ተጽዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች ለምሳሌ የአማራ ክልል ተጽዕኖ ፈጣሪዎች በዋናው ምክክር የሚሳተፉ ሲሆን የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ደግሞ በዋናው ምክክር ላይ እንደማይሳተፉ ተነግሯቸው ነገር ግን ምክንያቱ ያልተነገራቸው መሆኑ የምክክር ሂደቱን ግልጽነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ መሆኑ፤ እና ከማኅበረሰብ ክፍሎች አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደት ላይ የኅዳጣን ብሔሮች ቁጥር ማነስ በተለይም በጅግጅጋ ከተማ ብዙ ሶማሊ ያልሆኑ የክልሉ ተወላጆች ቢኖሩም በከተማው በተከናወነው ከማኅበረሰብ ክፍሎች አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደት ግን የተሳተፉት የሶማሊ ብሔር ተወላጆች ብቻ መሆናቸው እና ከባለድርሻ አካላት አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደት ላይ የተለያዩ የሃይማኖት ተቋማትን ወክለው አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደቱ ላይ የተሳተፉ ከሶማሊ ብሔር ውጪ የሆኑ ሰዎች በሶማሊ ብሔር ተወላጆች ክልሉን

አይወክሉም ተብለው አጀንዳቸውን ቆመው እንዳያቀርቡ መከልከላቸው ሌሎች ኢሰመኮ በክትትሉ የለያቸው አሳሳቢ ጉዳዮች ናቸው፡፡

### ምክረ ሐሳቦች

ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ምክክሩ የበለጠ አካታች እና አሳታፊ እንዲሆን የሚከተሉትን ዋና ዋና እርምጃዎች መውሰድ ይጠበቅበታል፦

422. በየትኛውም የምክክሩ ሂደት ላይ በማንኛውም አካል ፎቶ ለማንሳት እና ቪድዮ ለመቅረጽ የተሳታፊዎችን ፈቃድ ጠይቆ ፈቃደኛ የሆኑትን ብቻ መቅረጽ፤

423. የምክክር ሂደቶች ከመጀመራቸው አስቀድሞ በሚከናወን የተሳታፊ ልየታ ላይ የአካል ጉዳተኛ ተሳታፊዎችን ቁጥር እና ቡድኖቻቸውን በመለየት አካል ጉዳታቸውን ባገናዘበ ሁኔታ ምቹ የሆነ ቦታ ላይ እንዲወያዩ ቦታ መርጦ ማዘጋጀት እና መጠነኛ ማመቻቸት ማድረግ፤

424. አጀንዳቸውን ያልሰጡ በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ ኅዳጣን ብሔሮችን፣ ታጣቂ ኃይሎች እና ራሳቸውን ከምክክሩ ያገለሉ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎችን ለየብቻ በማወያየት አጀንዳዎቻቸውን መውሰድ እና በቀጣይ ሂደቶችም እንዲሳተፉ ማድረግ፣ እና

425. ዋናው ምክክር ላይ የሚሳተፉ አካላት የተመረጡበትን እና እየተመረጡበት ያለበትን መስፈርት ከነምክንያቱ ለሕዝብ በግልጽ ማሳወቅ፡፡

## የሽግግር ፍትሕ ሂደት

426. የሽግግር ፍትሕ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ፣ ፍትሕን ለማስፈን እና ዕርቅን ለማምጣት በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ በደሎቹ ላስከተሉት ቀውሶች መፍትሔ ለማምጣት ከሚደረገው ጥረት ጋር የተያያዙ ሙሉ ሂደቶች እና ዘዴዎችን ያጠቃልላል፡፡ አጠቃላይ የሽግግር ፍትሕ ሂደት ዓላማ ለደረሱ ጉዳቶች እና ለተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ዘላቂ እልባት እና ፍትሕ ማስገኘትን ያካትታል፡፡ ከግቦቹ መካከል በአጭር ጊዜ ሊሳኩ የሚታሰቡ ግቦች ለተጎጂዎች እውቅና መስጠት እና ማኅበረሰባዊ መተማመንን ማጎልበትን ሲጨምር በረዥም ጊዜ የሚሳኩ ግቦች ማኅበረሰባዊ እርቅን ማምጣት እና የሕግ የበላይነትን ማጠናከርን ይጨምራል፡፡

427. በኢትዮጵያም የሽግግር ፍትሕ ሂደትን የሚመራ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ በሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጸድቋል፡፡ በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው ላይ በዝግጅት ላይ ባሉ ረቂቅ ሰነዶች ይዘት እና አጠቃላይ የሰነዶች ዝግጅትና መጽደቅ ሂደትን ጨምሮ በሁሉም የሽግግር ፍትሕ ሂደቶች ተፈጻሚ የሚሆኑ የሰብአዊ መብቶች መርሖችና ድንጋጌዎች እና ዓለም አቀፍ መስፈርቶች ተመላክተዋል፡፡ በፖሊሲው ከተቀመጡ መርሖችና ድንጋጌዎች መካከል ሀገራዊ ባለቤትነት፣ የሰብአዊ መብቶች ተኮር የትግበራ ሂደት፣ አካታችነትና አሳታፊነት፣ ሥርዓተ-ጾታ ተኮር አተገባበር፣ እና ልዩ ትኩረት የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎ ይገኙበታል፡፡

428. በአፍሪካ ኅብረት የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ መሠረት መንግሥታት የሽግግር ፍትሕ ሂደቶችን ተደራሽ፣ ፍትሐዊ እና አሳታፊ በሆነ አግባብ የመንደፍና የመተግበር ግዴታ አለባቸው፡፡ ይህም ሁሉም ተጎጂዎች እና የተጎዱ ማኅበረሰቦች በተለይም አካል ጉዳተኞች፣ በግጭት የተጎዱ ሕፃናት፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞች እና ጾታዊና ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ተጎጂዎችን ጨምሮ ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ለሽግግር

ፍትሕ ስልቶች አቀራረጽ እና አተገባበር እውነተኛ አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ በማድረግ ማኅበራዊ ማካተትን እና ባለቤትነትን ለማጎልበት እንዲሁም ዕርቅን ለማስፈን ይረዳል። የተሳትፎ መርሕ መንግሥታት ትርጉም ያለው የሕዝብ ተሳትፎን፣ በሕግ ማውጣት ሂደቶች ውስጥ ጭምር እንዲያመቻቹ ያለባቸውን ግዴታ ያካትታል። ይህንን እውን ለማድረግም የሚመለከታቸው አካላት የሕግ ማርቀቅ ሂደቶችን አካታች እና አሳታፊ ከማድረግ አልፈው ትርጉም ያላቸው እና አካታች የሕዝብ ምክክሮችን የማዘጋጀትም ኃላፊነት ይኖርባቸዋል። ይህ የተሳትፎ መርሕ የፍትሕ ሂደቶች ቅቡልነት እንዲያገኙ ከማድረግ ባለፈ የሚወጡ ሕጎች የተጎጂዎችንና የተጎዱ ማኅበረሰቦችን ፍላጎቶችና ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮች የሚመልሱ እንዲሆኑ በማድረግ ለዐውድ ተኮር እና እውነተኛ የፍትሕ ሂደት መነሻ ይሆናል።

**429.** የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ የሽግግር ፍትሕን በሰብአዊ መብቶች ላይ በተመሠረተ አቀራረብ መተግበርን እንደ አንድ መርሕ ያስቀምጣል። ይህም ሁሉም ተግባራት ከዓለም አቀፍ፣ ከአህጉራዊ፣ እና ከብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች መርሖዎችና መስፈርቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይጠይቃል። ፖሊሲው የሽግግር ፍትሕ ሰፊ እና ከአድልዎ የጸዳ ተሳትፎን በሚያበረታታ መልኩ እንዲከናወን አቅጣጫ ያስቀምጣል። ይህም ሂደቱ ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍሎች፣ በተለይም ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ሌሎችም ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ትርጉም ባለው መልኩ መሳተፍ እንዳለባቸው ያሳያል።

**430.** በተጨማሪም ሀገራዊ ባለቤትነት፣ ከሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ መርሖዎች አንዱ ሲሆን ይህ መርሕ የፍትሕ ሂደቱ የኢትዮጵያውያንን በተለይም የተጎጂዎችን እና የተጎዱ ማኅበረሰቦችን ልዩ ሁኔታዎች፣ ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮች እና ምኞቶች የሚያንፀባርቅ መሆን እንዳለበት ያሳያል። በተለይም ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተሳትፎ የሕግ ማዕቀፉ የኢትዮጵያን ሕዝብ የፍትሕ ፍላጎቶች የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ ወሳኝ በመሆኑ ትኩረት የሚሰጠው ነው። ከዚህም አንጻር በኢትዮጵያ በ2017 በጀት ዓመት የተከናወኑ ዋና ተግባራት በተለይም የተቋማት መመስረቻ የሕግ ሰነዶች ዝግጅት ሂደት እና ሌሎች በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ የትግበራ ፍኖተ ካርታው ላይ የተቀመጡ ተግባራት አፈጻጸም ከእነዚህ መርሖች አንጻር ሲታዩ የሚከተሉት አዎንታዊ ሁኔታዎች እና አሳሳቢ ጉዳዮች ሊለዩ ችለዋል።

### አዎንታዊ ሁኔታዎች

**431.** ያለፉ ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ለመፍታት እና ዳግም እንዳይከሰቱ ዋስትና ለመስጠት የሽግግር ፍትሕን ለመተግበር ግልጽ የሆነ መነቃቃት መኖሩ፣ ለዚህም የፖሊሲ ትግበራ ፍኖተ ካርታው ላይ በተቀመጠው መሠረት የተቋማት ማቋቋሚያ ሕጎች የመጀመሪያ ረቂቅ መጠናቀቁ የሚያበረታታ ነው።

**432.** የዓለም አቀፍ ሕግን በመጣስ የሚፈጸሙ መሠረታውያን ወንጀሎች ረቂቅ አዋጅ መዘጋጀቱ በሀገሪቱ የወንጀል ሕግ ውስጥ ያልተካተቱ ዓለም አቀፍ ወንጀሎችን ከዓለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ ለመተግበር የሚያስችል፤ ያለውን የሕግ ክፍተት በአግባቡ የሚሞላ የተሟላ እና ከሽግግር ፍትሕ ማዕቀፍ ውጪ ዘላቂ ሕግ እንዲሆን ተደርጎ መቀረጹ የሚበረታታ ነው።

433.የተጎጂዎችንና ልዩ ትኩረት የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎችን መካተትና ተሳትፎ ላይ የሚያተኩር ረቂቅ ስትራቴጂ እንደሚዘጋጅ በፍኖተ ካርታው ላይ ተቀምጧል፡፡ እስከ ጥር ወር 2017 ዓ.ም. በሁለት ዙር በተካሄዱ የቴክኒክ ቡድኑ የረቂቅ ሰነድ ዝግጅት ስብሰባና በጽሑፍ በተከናወኑ ሥራዎች አማካኝነት ይህ ስትራቴጂ ለውይይትና ለግብዓት ማሰባሰብ ሊቀርብ በሚችል መልኩ በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ የተዘጋጀ በረቂቅ ደረጃ የሚገኝ ሰነድ መኖሩ አበረታች ነው፡፡ በረቂቁም ላይ በኢሰመኮ ድጋፍ አንድ የግብአት ማሰባሰብ ሂደት መከናወኑ የሚበረታታ ነው፡፡

### አሳሳቢ ጉዳዮች

434. በሽግግር ፍትሕ ትግበራ ፍኖተ ካርታ ላይ ከተቀመጡ በ2017 በጀት ዓመት ሊተገበሩ ከታቀዱ ተግባራት መካከል የሰነዶች ዝግጅት እና የሽግግር ፍትሕ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ማቋቋም፣ በሽግግር ፍትሕ ሥራዎች መካከል ውድድር ለማስቀረት/ተመጋጋቢነት ለማረጋገጥ የትግበራ ቅደም-ተከተል ጥቅል እቅድ ማውጣት እና በትግበራ ዋና ዋና ምዕራፎች የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን፣ የሕዝብን ተሳትፎና የባለድርሻ አካላት ድጋፍና የባለቤትነት ስሜት የሚያጠናክሩ ሥራዎችን (ሕዝባዊ ውይይቶች ስልጠናዎች ወዘተ) ማከናወን በዋነኝነት የሚጠቀሱ ሲሆኑ ተግባራቱም በዋነኝነት በፍትሕ ሚኒስቴር ዋና አስተባባሪነት እንደሚተገበሩ ተገልጿል፡፡ በዚህ ረገድ ከሕግ ረቂቅ ሰነዶች ውጪ ሌሎች ተግባራት በታቀደላቸው ጊዜ አለመከናወናቸው አሳሳቢ ነው፡፡ የተዘጋጁት ረቂቅ ሕጎችም ለሕዝብ ውይይት እስከ አሁን አልቀረቡም፣ እንዲሁም በሂደቱ ዋና አስተባባሪ የፍትሕ ሚኒስቴር እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች አጠቃላይ ሂደቱ እየተመራ ያለበት አግባብ ለሕዝብ ግልጽ አልተደረገም፡፡

435.የሽግግር ፍትሕን የመተግበር የፖለቲካ ቁርጠኝነት በሀገሪቱ ያሉ ግጭቶችን የማስቆም ጥረቶችን ሊያካትት ይገባል፡፡ በበርካታ የሀገሪቱ አካባቢዎች ግጭቶች እና የጸጥታ ችግሮች መኖራቸው ለእነዚህም ምላሽ ለመስጠት እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች ውጤታማ አለመሆን የሽግግር ፍትሕ ትግበራ አሳሳቢ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

436. በአጠቃላይ የሽግግር ፍትሕ መተግበሪያ ረቂቅ ሕጎች ለሕዝብ ውይይት ይፋ አለመደረጋቸው፣ በሽግግር ፍትሕ ፍኖተ ካርታ የተመላከቱ ተግባራት እየተከናወኑ አለመሆኑ ሂደቱን አስመልክቶ የንቃትና የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎች እየተሠሩ አለመሆኑ የሽግግር ፍትሕ ሂደቱ ወደ ትግበራ ምዕራፍ ከተሸጋገረ በኋላ የመቀዛቀዝ አዝማሚያ እያሰየ መሆኑ አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡

### ምክረ ሐሳቦች

437. እየተከሰቱ ያሉ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ በውይይት በመፍታት፣ በመላ ሀገሪቱ ሰላምና ጸጥታን በማስጠበቅ እና የሕግ የበላይነትን በማስከበር፣ አካታች፣ ተጎጂዎችን ያማከለ እና ሰብአዊ መብትን የሚያከብር የሽግግር ፍትሕ ሂደት ለመተግበር ምቹ ሁኔታን መፍጠር በዋነኝነት ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊሠራ ይገባል፤

438. መንግሥት ከሽግግር ፍትሕ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለሕብረተሰቡ በሂደቱ በሙሉ ግልጽ፣ ወቅታዊና ክፍት በሆነ መንገድ ተደራሽ ማድረግ አለበት፤

439. የተጎጂዎችን እና ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተሳትፎ ስትራቴጂ ጨምሮ የሽግግር ፍትሕ ማስተግበሪያ ረቂቅ ሕጎች አካታችና አሳታፊ የሆነ ሕዝባዊ ምክክር

ተደርጎባቸው በሚሰጡ ግብዓት ዳብረው ቅድሚያ እና ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊጸድቁ ይገባል፤

440. ተሳትፎንና አካታችነትን በተመለከተ ሂደቱ ሥርዓተ ጾታ ተኮር አተገባበር መርሕን የተከተለ እንዲሆን ማድረግ ማለት ሴቶችን በተጎጂነትና በተጠቂነት ብቻ መመልከትና በተለያዩ የትግበራ ክንውኖች በቁጥር/በብዛት እንዲገኙ ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ በባለሞያነት፣ በሽግግር ፍትሕ ተቋማቱ መሪነትና ሌሎች የሥራ ዘርፎች በበቂ ሁኔታ መካተት፣ በክልልም ሆነ በፌዴራል ደረጃ በሚካሄዱ መድረኮች በቂ እና ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማስቻልና የመሳሰሉት ተያያዥ እርምጃዎችን በየደረጃው እና በየጊዜው መውሰድ ይገባል፤

441. በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ በሽግግር ፍትሕ ሂደት የዋና አስተባባሪነት ሚና የተሰጠው የፍትሕ ሚኒስቴርን ጨምሮ መንግሥታዊና ባለድርሻ አካላት በፖሊሲው የተሰጣቸውን ኃላፊነትና ተግባር ግልጽ አሳታፊና አካታች በሆነ አግባብ በመተግበር የሽግግር ፍትሕ እውን እንዲሆን የበኩላቸውን ሚና መወጣት አለባቸው፡፡

WWW.EHRC.ORG



# ክፍል ፫

# ክፍል አምስት

# ምክረ ሐሳቦች እና ቀጣይ አቅጣጫዎች

በ2017 በጀት ዓመት የታዩ አሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮችን በሚመለከት በየዘርፉ የቀረቡ ምክረ ሐሳቦች ተፈጻሚ ሊደረጉ የሚገባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ለጠቅላላ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታው መሻሻል የሚከተሉት የመፍትሔ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ኢሰመኮ ያሳስባል።

### በትጥቅ ግጭት ዐውድ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕጎችን ማክበርን በተመለከተ

**442.** በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች በትጥቅ ግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ሁሉም አካላት በማናቸውም የግጭት ሂደት ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕጎች ድንጋጌዎችን እንዲያከብሩ፤ በሲቪል ሰዎች ሕይወት፣ አካል እና ንብረት ላይ ጥቃት ከማድረስ እንዲሁም ሌሎች ጥሰቶችን ከመፈጸም እንዲቆጠቡ፣ የሚፈጸሙ ጥሰቶችን በይፋ እንዲያወግዙ እና ተጠያቂነትን እንዲያረጋግጡ፤

### ለግጭቶች ሰላማዊ መፍትሔዎችን ማፈላለግን በተመለከተ

**443.** ኢሰመኮ ከዚህ ቀደም ባወጣቸው ሪፖርቶችና መግለጫዎች በተደጋጋሚ እንዳሳሰበው በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች የሚካሄዱ የትጥቅ ግጭቶች እንዲሁም የጸጥታ መደፍረስ ሁኔታዎች ዋነኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ምክንያቶች ናቸው። ስለሆነም መንግሥትን ጨምሮ ሁሉም በትጥቅ ግጭት ውስጥ የሚሳተፉ ተፋላሚ ኃይሎች ፖለቲካዊ አለመግባባቶችን በውይይት ለመፍታት በቁርጠኝነት እንዲሠሩ በአጽንዖት ያሳስባል። በተለይም በጅምር ላይ የሚገኙት የብሔራዊ ምክክር እና የሽግግር ፍትሕ ሂደቶች ዘላቂ፣ ሰላማዊ እና ሰፊ ተቀባይነት ያላቸው ውጤቶችን ለማስገኘት በሚችሉበት አግባብ ተግባራዊ እንዲደረጉ መንግሥት እና አማራና ኦሮሚያ ክልሎችን ጨምሮ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ኃይሎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተኩስ አቁም በማድረግ ወደ ውይይት እንዲገቡ ኢሰመኮ ጥሪውን ያቀርባል።

### ከዚህ ቀደም የተፈረሙ የሰላም ስምምነቶችን ተፈጻሚነት ማጠናከርን በተመለከተ

**444.** በፕሪቶሪያ የተፈረመውን የዘላቂ ተኩስ አቁምና የሰላም ስምምነት ተከትሎ በትግራይ ክልል አንጻራዊ ሰላምና መረጋጋት መስፈኑ የክልሉን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ለማሻሻል ዕድል መስጠቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በ2017 በጀት ዓመት በስምምነቱ የተሟላ ተፈጻሚነት ላይ ተግዳሮት የሚፈጥሩ እና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች አደጋዎችንና ሥጋቶችን የፈጠሩ ክስተቶች መታየታቸውን ከግንዛቤ በማስገባት፤ ኢሰመኮ የስምምነቱ ፈራሚዎች ከአሉታዊ መግለጫዎችና ተግባራት በመቆጠብ የክልሉን ሰላምና የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በሚያረጋግጥ አኳኋን እንዲንቀሳቀሱ ጥሪ ያቀርባል።

## ለመልሶ ግንባታ እና መልሶ ማቋቋም ሥራዎች ተገቢውን ትኩረት መስጠትን በተመለከተ

445. በትጥቅ ግጭት ውስጥ ባለፉ የሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ጠንካራ የመልሶ ግንባታና ማቋቋም ሥራ አለመከናወኑ የትምህርት እና የጤና አገልግሎቶችን ጨምሮ፣ በበርካታ የሰብአዊ መብቶች ዘርፎች ያሉ ችግሮችን ማባባሱን ከግምት ውስጥ በማስገባት እንዲንቀሳቀሱ ኢሰመኮ የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት እንዲሁም መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ያሳስባል። የመልሶ ግንባታ እና ማቋቋም ሥራዎች ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እንዲሁም ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ፍላጎቶች ከግምት ያስገቡ ሊሆኑ ይገባል።

## ሰው ሠራሽ እና የተፈጥሮ አደጋዎችን መከላከልና ምላሽ መስጠትን እና የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦትን በተመለከተ

446. በኢትዮጵያ ሰው ሠራሽ እና በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት በሰዎች ላይ የሚደርሰው ዘርፈ ብዙ ጉዳት እየተስፋፋ መምጣቱን ባገናዘበ ሁኔታ የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻዎች ተገቢ የቅደመ ጥንቃቄ እርምጃዎችን ሊወስዱ እና በአደጋ ወቅት ፈጣን እና ውጤታማ ምላሽ የመስጫ አሠራሮችን ሊዘረጉ ይገባል።

447. በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በሰው ሠራሽ እና የተፈጥሮ አደጋዎች ሳቢያ ጉዳት የደረሰባቸው እንዲሁም ከቀያቸው የተፈናቀሉ ሰዎች ወቅቱን የጠበቀ፣ በቂ፣ ያልተቆራረጠ እንዲሁም ልዩ ፍላጎቶች ያሏቸውን ሰዎች ሁኔታ መሠረት ያደረገ የሰብአዊ ድጋፍ እና ማኅበራዊ አገልግሎቶች ሊቀርቡላቸው፤ ውጤታማ የዘላቂ መፍትሔ አማራጮችም ሊፈለጉላቸው ይገባል።

## ለሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች በር የሚከፍቱ የሕግና መዋቅር ክፍተቶችን መፍትሔ መስጠትን በተመለከተ

448. መንግሥት ረቂቁን የአካል ጉዳተኞች ሕግ አጸድቆ ወደ ሥራ ለማስገባት እንዲቻል የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በጅምር ላይ ያለውን የአካል ጉዳተኞች ፖሊሲ በፍጥነት እንዲያጠናቅቅ እና ፍትሕ ሚኒስቴርም ረቂቅ ሕጉ ጸድቆ ወደ ሥራ ለመግባት የሚችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር ሁኔታዎችን እንዲያመቻች፤

449. ሠራተኞች ፍትሐዊ፣ አመቺና ጤናማ የሥራ ሁኔታ በማግኘት ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን በበቂ ሁኔታ ለማኖር የሚያስችል ክፍያ የማግኘት መብትን ከማስከበር አንጻር ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል ሥርዓትን የሚዘረጋ ሕግ እና የደመወዝ ቦርድ ማቋቋሚያ ደንብ እንዲወጣ፤

450. የካምፓላ ስምምነት ማስፈጸሚያ ብሔራዊ ረቂቅ አዋጅ በስምምነቱ ውስጥ ከተካተቱ የመንግሥት ግዴታዎች ጋር በተጣጣመ እና በቅድመ መፈናቀል፣ በመፈናቀል እንዲሁም በድኅረ-መፈናቀል ወቅት ለተፈናቃዮች ተገቢውን ጥበቃ እና ድጋፍ በአግባቡ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ በአጠቃላይ ከሰብአዊ መብቶች አንጻር የተቃኘ ይዘት እንዲኖረው አድርጎ በመቅረጽ በተፋጠነ ሁኔታ ማጽደቅና ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

## የብሔራዊ ምክክር ሂደትን በተመለከተ

451.የሀገራዊ ምክክር ሂደት ለሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች መነሻ የሚሆኑ ቅራኔዎችና ግጭቶችን በዘላቂነት ለመፍታት ያለውን አስተዋጽዖ ከግንዛቤ በማስገባት የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ የምክክር ሂደቱ የበለጠ አካታች እና አሳታፊ እንዲሆን ለማድረግ እርምጃዎችን እንዲወስድ፤ በተለይም የምክክር ሂደቶች ከመጀመራቸው አስቀድሞ በሚከናወን የተሳታፊ ልየታ ላይ ሴቶች እና አካል ጉዳተኛ ተሳታፊዎችን ጨምሮ ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተሳትፎ የሚያሳድጉ ስልቶችን ተግባራዊ እንዲያደርግ፤ አጀንዳቸውን ያልሰጡ ታጣቂ ኃይሎች እና ራሳቸውን ከምክክሩ ያገለሉ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎችን ለየብቻ በማወያየት አጀንዳዎቻቸውን መውሰድ እና በቀጣይ ሂደቶችም እንዲሳተፉ ማድረግን ጨምሮ የሂደቱን ቅቡልነት የሚያሳድጉ እርምጃዎችን በመውሰድ ለሀገራዊ ምክክሩ የተሻለ ውጤታማነት እንዲሠራ ኢሰመኮ ምክረ ሐሳቡን ያቀርባል።

## የሽግግር ፍትሕን በተመለከተ

452. የሽግግር ፍትሕ ለሰብአዊ መብቶች መከበር፣ ለሕግ የበላይነት መረጋገጥ፣ ለሀገረ መንግሥት ግንባታ ቁልፍ አበርክቶ ያለው ሂደት እንደመሆኑ እየተከሰቱ ያሉ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ በውይይት በመፍታት፣ በመላ ሀገሪቱ ሰላምና ጸጥታን በማስጠበቅ፣ አካታች፣ ተጎጂዎችን ያማከለ እና ሰብአዊ መብቶችን የሚያከብር የሽግግር ፍትሕ ሂደት ለመተግበር ምቹ ሁኔታን መፍጠር እንዲሁም ትግበራውን ሊያደናቅፉ ከሚችሉ እርምጃዎች መቆጠብ ይገባል፣

453.የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ትግበራ በሽግግር ፍትሕ ፍኖተ ካርታ በተቀመጠበት አግባብ በመምራት የታቀዱ ተግባራትን በመፈጸም እና በረቂቅ ደረጃ ያሉ የተጎጂዎችን እና ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ተሳትፎ ስትራተጂ ጨምሮ የሽግግር ፍትሕ ማስተግበሪያ ረቂቅ ሕጎች የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ማስፈጸሚያ ሕጎች አካታችና አሳታፊ የሆነ ሕዝባዊ ምክክር ተደርጎባቸው በሚሰጡ ግብዓት ዳብረው ቅደሚያ እና ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲጸድቁ ኢሰመኮ ምክረ ሐሳቡን ያቀርባል።

## የሕግና ፖሊሲ ማሻሻያዎችና ለውጦችን በተመለከተ

454. መንግሥት በሚያደርጋቸው የሕግና ፖሊሲ ማሻሻያዎች ላይ የተሻለ ግልጽነትና አሳታፊነትን እንዲያረጋግጥ፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን በስፋት በማከናወን የሰዎችን በሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ ተሳትፎ የማድረግ መብት እንዲያከብር፤ ለዚህም የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ የሲቪክ ማኅበራት፣ እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በቂ ትኩረት እና ጊዜ ተሰጥቷቸው ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲያደርጉ እና የሚያቀርቧቸው አስተያየቶችና ግብዓቶችም ግልጽና ምክንያታዊ በሆነ ደረጃ ረቂቅ ሕጎችና ፖሊሲዎችን ለማዳበር ጥቅም ላይ እንዲውሉ፣ እንዲሁም የሰብአዊ መብቶችን መስፈርቶች ያከበሩ እንዲሆኑ እንዲያደርግ ኢሰመኮ ያሳስባል።

## 7ኛውን ዙር ጠቅላላ ምርጫ በተመለከተ

455. በቀጣዩ የ2018 በጀት ዓመት 7ኛው ዙር ጠቅላላ ምርጫ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንደሚካሄድ ይጠበቃል። ኢሰመኮ በተሻሻለው መቋቋሚያ አዋጁ አንቀጽ 6 (11) የተሰጠውን በምርጫ

ወቅት የሰብአዊ መብቶች ክትትል የማድረግ ሥልጣን እና ኃላፊነት መሠረት በማድረግ በ6ኛው ዙር ጠቅላላ ምርጫ እንዳደረገው ሁሉ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሠራ እየገለጸ፤ ሁሉም ባለድርሻዎች በየዘርፋቸው ተገቢ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን እንዲያከናውኑ ጥሪ ያቀርባል። በተለይም መንግሥት የሰብአዊ መብቶች መርሖችና ድንጋጌዎችን ያከበረ፣ ለመራጮችም ሆነ ለተወዳዳሪዎች ምቹ እና የጸጥታ ሁኔታው እና ደኅንነቱ የተጠበቀ አሳታፊ የምርጫ ዐውድ ለመፍጠር አስፈላጊ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን እንዲያከናውን፤ መንግሥት፣ ምርጫ ቦርድ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲሁም የሲቪክ ማኅበራት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ሴቶችና አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ሁሉም የማኅበረሰብ ክፍሎች በምርጫው ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉበት ሁኔታ መፈጠሩን ለማረጋገጥ የየበኩላቸውን አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ፤ ከምርጫ ጋር በተገናኙ መርኃ ግብሮቻቸው የሰብአዊ መብቶች መርሖችንና ድንጋጌዎችን አካትተው እንዲንቀሳቀሱ ኢሰመኮ ምክረ ሐሳብ ያቀርባል።

## ስለ ኢሰመኮ

**የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በፌዴራል ሕገ መንግሥቱ መሠረት ነጻ ፌዴራላዊ መንግሥት አካል ሆኖ የተቋቋመና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆነ ለሰብአዊ መብቶች መስፋፋት፣ መከበር እና ጥበቃ የሚሠራ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ነው። *(የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/14 እና አዋጅ ቁጥር 210/1992 በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው)***